@BOOKALEM

የመጻሕፍት አለም


ፍኖተ፡አእምሮ፡
የዕውቀት ፡ ጐዳና ።
ከልዑል ፡ ራስ ፡ ካሳ ፡ ኃይሉ ።

# ፍኖተ፡ አእምሮ፡

## የዕውቀት ፡ ጎዳና ።

ከልዑል ፡ ራስ ፡ ካሳ ፡ ኃይሉ ።

በግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡
ዘኢትዮጵያ ፡ በሠላሳ ፡ አንደኛው ፡ ዘመን ፡ መንግሥት ፤

አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፤

በአርቲስቲክ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ፤ ቍ ፡ 1521

ያለፈቃድ ፡ ማሳተም ፡ ክልክል ፡ ነው ።
COPYRIGHT

ዋጋው ፤ ፪ ፡ ብር ።



ልዑል ፡ ራስ ፡ ካሳ ፡ ኃይሉ ።

## ማውጫ ።


አርእስት ፡ — ገጽ ፡

መግለጫ ፡ ........ ፯

መቅድም ፡ ........ ፲፫

ምዕራፍ ፡ ፩

ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ ልክ ፡ ........ ፲፩

ምዕራፍ ፡ ፪ ፡

ስለ ፡ ምግባር ፡ ምክር ፡ ........ ፲፯

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

ስለ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ መመልከቻ ፡ ........ ፴

ምዕራፍ ፡ ፬ ።

ስለ ፡ ጸሎት ፡ ምርምር ፡ ........ ፵

ምዕራፍ ፡ ፭ ።

ምኞት ፡ እንዳይለወጥ ፡ ሰው ፡ ባሳቡ ፡ እንዲጉዳ ፡ ባሳ
ቡም ፡ እንዲጠቀም ፡ ማወቂያ ፡ ........ ፵፯

ምዕራፍ ፡ ፮ ።

ስላሳብ፡እንዳይባክን፡ምኞት፡እንዳይለዋወጥ፡መሰብሰቢያ ........ ፶

ምዕራፍ ፡ ፯ ።

ስለ ፡ ምጽዋት ፡ ........ ፶፩

ምዕራፍ ፡ ፰ ።

ስለ ፡ ገንዘብ ፡ ወዳጅ ፡ ምክር ፡ ........ ፷

ማውጫ ።


እርእስት ፤ ገጽ ፤

ምዕራፍ ፤ ፱ ።

ስለ ፤ ገንዘብ ፤ አቀባበል ፤ ______ ፸፰

ምዕራፍ ፤ ፲ ።

ሴላውን ፤ መምከር ፤ ለሚያውቅ ፤ ያመካከሩ ፤ ዘዴ ፤ እየ ጠፋው ፤ ራሱ ፤ እንዳይጐዳ ፤ ስለ ፤ ሰው ፤ የምክር ፤ ምጽ ዋት ፤ የሚገባና ፤ የማይገባውን ፤ መለያ ፤ ______ ፹፩

ምዕራፍ ፤ ፲፩ ።

የሰው፤ ገንዘብ፤ ከሚወድና፤ የራሱን፤ ገንዘብ ፤ ከሚወድ ፤ የማናቸው ፤ ኀጢአት ፤ ለመብለጡ ፤ ማወቂያ ፤ ______ ፺፬

ምዕራፍ ፤ ፲፪ ።

ስለ ፤ ጌትነት ፤ አለመጥቀም ፤ ______ ፺፮

ምዕራፍ ፤ ፲፫ ።

ስለ ፤ ምስጢረ ፤ ሥላሴ ፤ የማየት ፤ ምርምር ፤ ______ ፻፬

ምዕራፍ ፤ ፲፬ ።

ሰው፤ያናዎሩን፤ እሳብ፤ለፈጣሪው፤የሚሰጥበት ፤ መንገድ፤ ፻፲

ምዕራፍ ፤ ፲፭ ።

ስለ ፤ ሥራ ፤ ሰዓት ፤ አከፋፈል ፤ ______ ፻፲፫

ምዕራፍ ፤ ፲፮ ።

ስለ ፤ አእምሮ ፤ አሠራር ፤ ምክር ፤ ______ ፻፲፱

ምዕራፍ ፤ ፲፯ ።

ስለ ፤ ሰው ፤ ማዕርግ ፤ ______ ፻፳፩

ማውጫ ።

እርእስት ፤ ገጽ ፤

ምዕራፍ ፤ ፲፰ ።

ጠላትን ፤ ላለመጥላት ፤ ለወዳጅ ፤ ላለማድላት ፤ ______ ፻፵፩

ምዕራፍ ፤ ፲፱ ።

በወዳጅ ፤ እጠቀማለሁ ፤ ለሚል ፤ የሚጐዳበትንና ፤ የሚ ጠቀምበትን ፤ የፍቅርን ፤ ዐይነት ፤ ማወቂያ ፤ ______ ፻፵፱

ምዕራፍ ፤ ፳ ።

የዳኛን ፤ ኀጢአትና ፤ ጽድቅ ፤ ማወቂያ ፤ ______ ፻፶

ምዕራፍ ፤ ፳፩ ።

ስለ ፤ ምግብ ፤ ______ ፻፶፩

ምዕራፍ ፤ ፳፪ ።

ስለ ፤ እግዚአብሔር ፤ ፍቅር ፤ ______ ፻፷፪

ምዕራፍ ፤ ፳፫ ።

የስንፍናን ፤ የቍጣን ፤ የዝንጋታን ፤ መነሻ ፤ ማወቂያ ፤ ፻፸፩

ምዕራፍ ፤ ፳፬ ።

እልመክር ፤ ስለሚል ፤ ልጅ ፤ ምርምር ፤ ______ ፻፸፱

ምዕራፍ ፤ ፳፭ ።

ስለ ፤ ዓለም ፤ እድፍነት ፤ ስለ ፤ ፈረንጆች ፤ አለመብለጥ ፤ ፻፹፩

ምዕራፍ ፤ ፳፮ ።

ለሃይማኖት ፤ ዕንቅፋት ፤ ለሚሆኑ ፤ ሥራዎች ፤ ምርምር ፤ ፻፺

ምዕራፍ ፤ ፳፯ ።

ስላነጋገር ፤ ምክር ፤ ______ ፻፺፩

ማውጫ ።

አርእርት ፣ ገጽ ፡

ምዕራፍ ፡ ፳፰ ።

ልዩራ ፡ ለሚል ፡ ሰው ፡ ለሰውነቱም ፡ ከንቱ ፡ ማስረጃ ፡ ፪፻፳፱

ምዕራፍ ፡ ፳፱ ።

ስለ ፡ መድኀኒት ፡ ማዳንና ፡ እለማዳን ፡ ማወቂያ ፡ ........ ፪፻፴፪

ምዕራፍ ፡ ፴ ።

ስለ ፡ ቅዳሜ ፡ እክባበር ፡ ምርምር ፡ ........ ፪፻፴፭

ምዕራፍ ፡ ፴፩ ።

ላስተማሪና ፡ ተማሪ ፡ ጥቅም ፡ የትምርት ፡ ምርምር ፡ ፪፻፴፯

ምዕራፍ ፡ ፴፪ ።

ስለ ፡ ጠንቋይ ፡ ወይም ፡ መነኮሲ ፡ ቃል ፡ ........ ፪፻፵፫

ምዕራፍ ፡ ፴፫ ።

በዚህ ፡ ዓለም ፡ ስለምናየው ፡ ሁሉ ፡ ውሸትነት ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የምናየውም ፡ የምንሰማውም ፡ የምንሠራውም ፡ መምሰል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ መሆን ፡ የለውም ፡ ........ ፪፻፶፯

ምዕራፍ ፡ ፴፬ ።

እሳቤን ፡ ጽፈ ፡ እጨርሳለሁ ፡ ስለሚመስለው ፡ ስላለማወቁ ፡ ማስረጃ ፡ ........ ፪፻፷፩

ምዕራፍ ፡ ፴፭ ።

ስለ ፡ ውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ ........ ፪፻፷፯

ምዕራፍ ፡ ፴፮ ።

ሰው ፡ የሚገባውን ፡ ንጽሕና ፡ እንዳያውቅ ፡ ንጽሕና ፡ ስለሚባለው ፡ ማስረጃ ፡ ........ ፪፻፸፬


## መግስፍዓ ።

ይህን ፡ ፍኖተ ፡ እእምሮ ፡ (የዕውቀት ፡ ጐዳና) ፡ የተባለውን ፡ መጽሐፍ ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ ካሳ ፡ ኃይሉ ፡ ባ፲፱፻፲፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ለመጻፍ ፡ ዠምረው ፡ ባ፲፱፻፳፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ፈጽመውት ፡ በዘመኑ ፡ በነበረው ፡ በደኅና ፡ ቁም ፡ ጽሕፈት ፡ አስገልብጠውት ፡ ባ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በትግሬ ፡ ጦር ፡ ግንባር ፡ ጠቅላይ ፡ አዝ ማች ፡ ሆነው ፡ ሲሄዱ ፡ ይህን ፡ መጽሐፋቸውንም ፡ ይዘውት ፡ ሄደው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ከብዙ ፡ የግል ፡ ጽሑፎቻቸው ፡ ጋራ ፡ ላስታ ፡ ላይ ፡ ትተውት ፡ ከዚያ ፡ ቈይቶ ፡ የጠላት ፡ ኃይል ፡ እየገፋ ፡ በሄደበት ፡ ጊዜያት ፡ በእደራ ፡ ይህንኑ ፡ መጽሐፍና ፡ ጽሑፎች ፡ ተረክቦ ፡ የነበረው ፡ እሽከራቸው ፡ ከላስታ ፡ አምጥቶ፡ ልዑልነታቸው ፡ በስደት ፡ ከሄዱ ፡ በኋላ ፡ በአርበኘ ነት ፡ ሥራ ፡ ሲከላከሉ ፡ ለነበሩት ፡ ለሁለቱ ፡ ልጆ ቻቸው ፡ ለክቡራን ፡ ደጃዝማች ፡ አበራ ፡ ካሳና ፡ ደጃዝማች ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፡ ካሳ ፡ በዚሁ ፡ ዓመት ፡ ምሕረት ፡ መጨረሻ ፡ ፍቼ ፡ ላይ ፡ አስረከበ ፡ እነሱም፡ ይህን ፡ አባታቸው ፡ የደከሙበትን ፡ መጽሐፍ ፡ ከጠ ላት ፡ ወረራ ፡ ለማዳን ፡ ብለው ፡ አባታቸው ፡ ባሠ ሩት ፡ በቀራንዮ ፡ መድኀኔ ፡ ዓለም ፡ ገዳም ፡ እንዲ ቀመጥ ፡ አደረጉ ። ባ፲፱፻፳፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሁለቱን ፡ ወንድማማቾች ፡ ጠላት ፡ ሰላሌን ፡ በጦር ፡ ኃይል ፡ ወሮ ፡ ከገደላቸው ፡ በኋላ ፡ የልዑልነታቸው ፡ የሆ

ነውን ፡ ንብረትና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እያደነ ፡ ሲበዘብዝ ፡ ይህም ፡ መጽሐፍ ፡ በጠላት ፡ ወታደሮች ፡ እጅ ፡ ተዘርፎ ፡ ወታደሮቹ ፡ ውስጡን ፡ ሳይመረምሩ ፡ ከሌላው ፡ ከዘረፉት ፡ ንዋየ ፡ ቅድሳት ፡ ጋራ ፡ በየ መንደሩ ፡ ገበያ ፡ አውጥተው ፡ ሲሸጡት ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ የደከሙበት ፡ መሆኑን ፡ የሚያውቀው ፡ አሽከራቸው ፡ በቀለ ፡ እንትባልከ ፡ ገዝቶ ፡ ደብቆ ፡ አስቀምጦ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በድል ፡ አድራጊነት ፡ ባ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሲመለሱ ፡ ለልዑ ልነታቸው ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ አምጥቶ ፡ አስረከበ ፡ ልዑልነታቸው ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በስደት ፡ በሎን ዶንና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በነበሩባቸው ፡ ጊዜያቶችና ፡ ከስደትም ፡ መልስ ፡ እስካረፉበት ፡ ዘመን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ድረስ ፡

፩ኛ ፡ ስለ ፡ አባት ፡ እናት ፡
፪ኛ ፡ ምርጥ ፡ ቃላት ፡
፫ኛ ፡ ጊዜ ፡ ጥበባት ፡
፬ኛ ፡ ጣዕመ ፡ ጸሎት ፡
፭ኛ ፡ አበራ ፡ ወንጌል ፡
፮ኛ ፡ ጣፋጭ ፡ ጥበብ ፡
፯ኛ ፡ ሕብረ ፡ ጥበባት ፡
፰ኛ ፡ አጭር ፡ ጸሎት ፡ ከሁሉ ፡ ዐይነት ፡
፱ኛ ፡ በእንግሊዝና ፡ በፈረንሳይ ፡ በዐረብኛና ፡ ባማርኛ ፡ ባራት ፡ ቋንቋ ፡ የተጻፈ ፡ የንግግር ፡ መለ ማመጃ ፡ በድምሩ ፡ ፱ ፡ መጻሕፍት ፡ ጽፈዋል ።



እንዚሁን ፡ በየጊዜው ፡ ለማሳተም ፡ ሲቻል ፡ በሕ ይወተ ፡ ዘመናቸው ፡ እንዲሆን ፡ ባለመፈለጋቸው ፡ ምክንያት ፡ ቈየ ።

ወደ ፡ ፊት ፡ ታትመው ፡ በሚወጡት ፡ መጽሐፎቻ ቸው ፡ ላይ ፡ ተገልጾ ፡ እንደሚገኘው ፡ ከሕይወታቸው ፡ በኋላ ፡ እንኳን ፡ እንዲታተሙላቸው ፡ አደራውን ፡ ለኋላ ፡ ቀሪ ፡ ሳይተዉ ፡ በፈቀደበት ፡ ጊዜና ፡ በፈቀ ደው ፡ አሠሪነት ፡ እንዲያስፈጽምላቸው ፡ ለአምላካ ቸው ፡ ትተዋል ።

መጽሐፎቻቸው ፡ ታትመው ፡ ለሚያነቧቸው ፡ ሁሉ ፡ የኀምሳ ፡ ዘመን ፡ የፖለቲካዊ ፡ የወታደራዊና ፡ ያስተዳዳሪ ፡ መሪነት ፡ ከስጣቸው ፡ ዕውቀት ፡ ያገኙትን ፡ የዓለማዊ ፡ ኑሮ ፡ ርዳታ ፡ ሆኖ ፡ እንዲገ ኝላቸው ፡ እንዲሁም ፡ በሙሉ ፡ በ፸፮ ፡ ዓመታቸው ፡ የተከተሉትና ፡ ያመኑበት ፡ የመንፈሳዊ ፡ እምነታ ቸው ፡ ያስገኘላቸውን ፡ ለመግለጥና ፡ ለማካፈል ፡ የልዑልነታቸው ፡ መሠረታዊ ፡ ምኞትና ፡ ሐሳብ ፡ በመሆኑ ፡ እንዚህን ፡ መጽሐፎቻቸውን ፡ ሁሉም ፡ እንዲያገኛቸው ፡ ያለትርፍ ፡ በታተሙበት ፡ ዋጋ ፡ ብቻ ፡ እንዲሸጡ ፡ ሆኗል ።

ልዑል ፡ ራስ ፡ ካሳ ፡ ከሕፃንነታቸው ፡ ወራት ፡ ገምሮ ፡ ጊዜያቸው ፡ ሁሉ ፡ በሥራ ፡ እንዲያዝ ፡ በማሰብ ፡ በየዘመናቱ ፡ የነበራቸው ፡ ታላላቅ ፡ የኀላፊነትና ፡ የመሪነት ፡ ሥራቸው ፡ ዕረፍት ፡ ሊሰ ጣቸው ፡ በቻለ ፡ ጊዜ ፡ ዕረፍታቸውን ፡ ለሌላ ፡

ሳያውሉ ፡ እንዚህን ፡ ለመሳሰሉ ፡ ጽሑፎች ፡ ማስ
ናጃ ፡ ጊዜ ፡ በማድረጋቸው ፡ ለሀገራቸውና ፡ ለንጉሠ ፡
ነገሥታቸው ፡ በጦር ፡ ሜዳና ፡ በፖለቲካ ፡ ባስተ
ዳደርም ፡ ከፈጸሙቸው ፡ ከፍተኛ ፡ ግልጋሎቶችም ፡
በላይ ፡ ለትውልዳቸውና ፡ ለመጪውም ፡ ይህን ፡
የማይረሳ ፡ ቅርስ ፡ ትተው ፡ ሄደዋል ። በእምላክ
ቸውም ፡ ዘንድ ፡ “በስጠኸኝ ፡ ዘመናቶች ፡ ሁሉ ፡
ሠርቼባቸው ፡ እንዲሄድ ፡ ስላደረግከኝ ፡ ዘመናቶቼ
ንም ፡ በከንቱ ፡ ስላላሳለፍክብኝ ፡ አመሰግንሃለሁ ፡
የመደብክልኝን ፡ ሥራ ፡ ፈጽሚያለሁ ፡ ለማለት ፡
ችለዋል” ።

ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ የእእምሮ ፡ መንገድ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡

ስሙ ፡ ፍኖተ ፡ እእምሮ ፡ ይባላል ።

ከውስጡ ፡ ያሉትን ፡ የእእምሮ ፡ መንገድ ፡ ሁሉ ፡
የሰበሰብኳቸው ፡ እስከሚቻለኝ ፡ ልክ ፡ ራሴ ፡
እየፈተንኩ ፡ እያየሁ ፡ የዐይን ፡ ምስክር ፡ ሆኜ ፡
ባየሁትና ፡ ባመዛዘንኩት ፡ የጻፍኩት ፡ ነው ፡
እንጂ ፡ እንዳንዳንዶቹ ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡
ወሬ ፡ ብቻ ፡ እየሰበሰብኩ ፡ የጻፍኩትና ፡ ምስ
ጋና ፡ የፈለግኩ ፡ እንደ ፡ ነጋዴም ፡ ከሰው ፡ ላይ ፡
የሚገኝ ፡ ዋጋ ፡ ያማረው ፡ አይደለሁምና ፡ የም
ስክርነት ፡ ምክሬን ፡ እስተውላችሁ ፡ መርም
ራችሁ ፡ በቀናው ፡ መንገድ ፡ እንድትሄዱልኝ ፡
እማልዳችኋለሁ ።

ልዑል ፡ ራስ ፡ ካሳ ፡ ኃይሉ ።

## መቅድም ።

ሰው ፡ በተሰጠው ፡ አእምሮ ፡ ነዋሪ ፡ ሥራ ፡ ሊሠራ
በት ፡ ይገባልና ፤ ጀግና ፡ መሣሪያ ፡ ተቀብሎ ፡ ሳይ
ዋጋ ፡ ቢቀር ፡ እንዲቀጣ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሰጠው ፡
አእምሮ ፡ ለሰው ፡ ጥቅም ፡ የሚረዳ ፡ ሆኖለት ፡ በአእ
ምሮው ፡ ሥራ ፡ ሳይሠራበት ፡ ቢቀር ፡ በወንጌል ፡ የተ
ነገረው ፡ የጌታውን ፡ ወርቅ ፡ በቀበረው ፡ ላይ ፡ የተ
ፈረደው ፡ እንዳይደርስብን ፡ በሚቻለኝ ፡ ዕውቀት ፡
የተፈጥሮ ፡ ወንድሞቼን ፡ በምክር ፡ ማዳን ፡ የሚያ
ስፈልግ ፡ ቢመስለኝ ፡ ለኔም ፡ ማስታወሻ ፡ ለወንድ
ሞቼም ፡ መምከሪያ ፡ እንዲሆን ፡ እግዚአብሔር ፡ የገ
ለጸልኝን ፡ ለመጻፍ ፡ ገምሬያለሁ ፡ ስለዚህ ፡ አንባ
ቢዎችን ፡ እማልዳለሁ ፡ ከናንተ ፡ የምፈልገው ፡ ነገር ፡
ሳይኖር ፡ የቅንነት ፡ ሥራ ፡ ቢመስለኝ ፡ ነውና ፡ የገ
መርኩት ፡ የሚታረም ፡ ቃል ፡ ባገኛችሁ ፡ ጊዜ ፡ ከኔ ፡
በሚሻለው ፡ አእምሯችሁ ፡ ንባብ ፡ አራሚ ፡ ሳትሆኑ ፡
ምስጢሩን ፡ መርምሩት ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ክፉ ፡ እንዳ
ትተረጉሙብኝ ፡ አፍቅር ፡ ቢጸከ ፡ ከመ ፡ ነፍስከ ፡
ባለው ፡ አምላክ ፡ አማፅኜ ፡ እለምናችኋለሁ ። ይህ
ንም ፡ መጽሐፍ ፡ ፍኖተ ፡ አእምሮ ፡ ያልኩበት ፡ የሚ
መራው ፡ መንገድ ፡ የውስጥን ፡ አሳብ ፡ እየመረመረ ፡
ላዋቂዋ ፡ ነፍስ ፡ የሚያሳይ ፡ ነውና ። መገምሪያ ፡
ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ ካጠናህ ፡ በኋላ ፡ ይህን ፡ መጽ
ሐፍ ፡ በዐይነ ፡ ነፍስህ ፡ መርምረው ፡ እንጂ ፡ ቅዱ

ሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ በፊት ፡ ሳታይ ፡ ሳታጠና ፡
ይህንን ፡ መግመሪያ ፡ አታድርገው ፤ ባይን ፡ ሥጋ
ህም ፡ ብቻ ፡ አትየው ። ይህንም ፡ ያልኩበት ፡ ምክን
ያት ፡ ይህም ፡ መጽሐፍ ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡
እንደ ፡ ዐረቂ ፡ እየተጨመቀ ፡ የወጣ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡
በደራሲ ፡ ዕውቀት ፡ የተሠራ ፡ ጉሽ ፡ ነገር ፡ አይደለ
ምና ፤ የሚያጸናውን ፡ እኽል ፡ ውሃ ፡ ሳይቀምስ ፡
ዐረቂ ፡ አስቀድሞ ፡ የሚጠጣ ፡ ሰው ፡ ያስክረዋል ፡
እንጂ ፡ እንደማይጠቅመው ፡ የሚያጸናውን ፡ መጽ
ሐፍ ፡ ቅዱስንም ፡ ሳይመለከት ፡ ይህን ፡ የሚያይ ፡
እንደዚያ ፡ እንዳይሆን ፡ ነው ።

# ፍኖተ ፡ እእምሮ ፡ (የዕውቀት ፡ ጐዳና) ።

## ምዕራፍ ፡ ፩ ።

## ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ ልክ ።

፩ ፤ ሃይማኖትስ ፡ መሠረት ፡ ይእቲ ፡ እንደ ፡ ተባለ ፡
ለቤት ፡ መሠረቱን ፡ ለነገር ፡ ጥንቱን ፡ ማጥናት ፡
እንዲገባ ፤ የፈጣሪውን ፡ ጥበቡን ፡ ጌትነቱን ፡
ፍትሩን ፡ ሁሉን ፡ ቻይነቱን ፡ ዐውቆ ፡ ከሚሠራው፡
ከግብሩ ፡ አስቀድሞ ፡ የሚገበርለትን ፡ ጌታ ፡
ማወቅ ፡ ይቀድማልና ፡ ስለዚህ ፡ ያባቶቻችን ፡
እእምሮ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እየመራው ፡ የደረስ
በትን ፡ ያኽል ፡ ሰው ፡ ፈጣሪውን ፡ እንዲያውቅ
በት ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ መግመሪያ ፡ እንዲሆን ፡
ጸሎተ ፡ ሃይማኖትን ፡ ማወቅ ፡ ይገባል ።

፪ ፤ ቅዱሳን ፡ አባቶቻችን ፡ የሰው ፡ አሳብ ፡ በዚህ ፡
እንዲቆም ፡ ወስነውታልና ፤ ዐራፊ ፡ ልቡና ፡ ላ
ለው ፡ ክርስቲያን ፡ አምኖ ፡ ለመገዛት ፡ ጸሎተ ፡
ሃይማኖት ፡ ይበቃዋል ፡ (ጣዕመ ፡ ጸሎት ፡ ም ፡ ፳) ።

፫ ፤ ልቡናህ ፡ ግን ፡ አላርፍልህ ፡ ብሎ ፡ ብዙ ፡ መመ
ርመር ፡ ቢፈልግህ ፡ ዳርቻውን ፡ አታገኘውም ፡
እንጂ ፡ ክርክርና ፡ ድካም ፡ ቢሻህ ፡ አባቶቻችን ፡
የደከሙበትን ፡ ያኽል ፡ እንድታውቀው ፡ ሃይማ
ኖት ፡ አበው ፡ ተመልከት ።

፬ ፡ እንደኛ ፡ ምክር ፡ ግን ፡ ስንኳን ፡ ፈጣሪ ፡ ፍጡ
ርም ፡ ጌታ ፡ ቢሆን ፡ ሱሪህን ፡ ፈትቼ ፡ ልብስህን ፡
ገልጬ ፡ የውስጥ ፡ አካልህን ፡ አይቼ ፡ ልገዛልህ ፡
ቢሉት ፡ ከድፍረትና ፡ ከንቀት ፡ ቈጥሮ ፡ ይጣላ
ዋል ፡ እንጂ ፡ መርምሮ ፡ ሊወደኝ ፡ ነው ፡ አይል
ምና ፡ እንደዚሁም ፡ ሁሉ ፡ የራሱን ፡ ተፈጥሮ ፡ ማ
ወቅ ፡ የማይችል ፡ ሰው ፡ የፈጣሪውን ፡ ምስጢር ፡
ፀውቃለሁ ፡ ማለት ፡ የድፍረት ፡ ወገን ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡
ያለምርምር ፡ አምነን ፡ ያለጥርጥር ፡ ወደን ፡ ያለ
ድፍረት ፡ አክብረን ፡ ከተገዛነው ፡ በዓለሙ ፡ ያለ ፡
የክርስቲያን ፡ ወገን ፡ ሁሉ ፡ የተቀበለው ፡ እውነ
ተኛ ፡ የሃይማኖት ፡ ፀዋጅ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እምኖ ፡
ለመዳን ፡ ይህ ፡ ጸሎተ ፡ ሃይማኖት ፡ ይበቃናል ።

ጥያቄ ።

፭ ፡ በሃይማኖት ፡ አሳብ ፡ የተለያዩ ፡ ያም ፡ የኔ ፡ ይህም ፡
የኔ ፡ ነው ፡ እውነቱ ፡ እያሉ ፡ በወሬና ፡ በጥቅስ ፡
ብዛት ፡ ልቤን ፡ ሲያስቸግሩብኝ ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡
ይሻለኛል ።

መልስ ።

፮ ፡ ሰዎች ፡ የጌታቸውን ፡ መልክ ፡ በሩቅ ፡ ሆነው ፡ ሲ
መለከቱ ፡ አንዱ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ሁለተኛው ፡
እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ባንድ ፡ ሰው ፡ መል
ክ ፡ ላይ ፡ ቢከራከሩ ፡ ጌትነቱን ፡ አምነው ፡ ሥልጣ
ኑን ፡ ፈርተው ፡ ከተገዙለት ፡ ጌትየው ፡ ከነሱ ፡ ላይ ፡



የሚፈልግባቸው ፡ የጌትነቱን ፡ መጠንና ፡ የትእዛዙ
ን ፡ መፈጸም ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በመልኩ ፡ ቅር
ጽ ፡ ላይ ፡ የሚከራከሩት ፡ ግን ፡ ርቀው ፡ በሚመለከ
ቱበት ፡ በየዐይናቸው ፡ ብርሃን ፡ መጠን ፡ በሚያዩት ፡
የመሰላቸውን ፡ ብቻ ፡ የሚያወሩ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ አላ
ዋቆች ፡ ሕፃናት ፡ እንደሚጫወቱበት ፡ ቃል ፡ እያደ
ረገ ፡ ንግግራቸውን ፡ እየናቀ ፡ ያልፈዋል ፡ እንጂ ፡
የሚከራከሩበት ፡ ምክንያት ፡ ለቅናት ፡ ለኩራት ፡
ካልሆነ ፡ በውነት ፡ ለልባቸው ፡ ለእግዚአብሔር ፡
ክብር ፡ የሚሆን ፡ እየመሰላቸው ፡ የሚነጋገሩበትን ፡
ማየት ፡ የማይችሉትን ፡ መልኩን ፡ ማወቅ ፡ የማይ
ችሉትን ፡ ጠባዩን ፡ ካላወቁ ፡ ብሎ ፡ አይፈርድባቸ
ውም ። ይህንም ፡ ልትረዳ ፡ ብትሻ ፡ ሀልዎቱን ፡ የሚ
ያምኑ ፡ ክርስቲያናች ፡ ሁሉ ፡ ምንም ፡ እርስ ፡ በርሳ
ቸው ፡ መናፍቅ ፡ እየተባባሉ ፡ ቢነቃቀፉ ፡ ሁሉም ፡
በየያዙት ፡ ሃይማኖት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ እየ
ጸለዩ ፡ ተአምራትን ፡ ለመሥራት ፡ የሚችሉ ፡ መ
ሆናቸውን ፡ አስተውል ፡ (ጣ ፡ ጺ ፡ ም ፡ ፮) ።

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ምግባር ፡ ምክር ።

፯ ፡ ሰይጣን ፡ እማኒውን ፡ ብርቱውን ፡ የእግዚአብ
ሔር ፡ ፍቅር ፡ ያለበትን ፡ ሰው ፡ የሚያስትበት ፡

ከዚህ ፡ የሚከተለውን ፡ ጥበብ ፡ አሳስቦ ፡ ነው ።
በትሩፋት ፡ ሥራዬ ፡ እጠቀማለሁ ፡ ማለት ፡ ትም
ክሕት ፡ ነውና ፡ በቸርነቱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የትሩ
ፋት ፡ ሥራው ፡ ለመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ዋጋዋ ፡
አይደለምና ፡ ለሰው ፡ የሚጠቅመው ፡ በቸርነቱ ፡
መታመን ፡ ነው ፡ እንጂ ። በጕልበቱ ፡ ጥቅሙን ፡
እንደሚገዛ ፡ ባለኪራይ ፡ በጕልበትህ ፡ ከተገዛህ ፡
የእግዚአብሔርን ፡ ቸርነት ፡ መንቀፍህ ፡ ነውና ፡
አትረባም ፡ አትጠቅምም ፡ ብሎ ፡ ያሳስብሃል ።

ይህንን ፡ ማሳሰቡ ፡ የመንፈሳዊ ፡ ልብ ፡ የሚረታ
ለት ፡ በመንፈሳዊ ፡ አሳብ ፡ ነውና ፡ ስለዚህ ፡
ነው ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ ቃሉ ፡ እውነት ፡ ቢሆን ፡
ጥበቡ ፡ በሃይማኖት ፡ አመካኝቶ ፡ በጎ ፡ ሥራውን ፡
አስጥሎ ፡ ክፉ ፡ ለማሠራት ፡ ነው ። ይህን ፡ የሚያ
ስተምሩ ፡ ሰዎች ፡ የስንፍና ፡ ዐዋጅ ፡ ነጋሪዎች ፡
ናቸውና ፡ ምንም ፡ ማመሳሰያ ፡ እየፈጠሩ ፡ ቢነ
ግሩህ ፡ አትቀበላቸው ።

ሰው ፡ ለአምላኩ ፡ የሚያቀርብለት ፡ ግብሩ ፡ የሚ
ገዛበት ፡ ዐይነቱ ፡ መታወቂያው ፡ ፍትወቱንና ፡
ጕልበቱን ፡ በሚሰጥበት ፡ ምግባር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡
የጕልበት ፡ ድካም ፡ የሌለበትን ፡ ያፍና ፡ የልብ ፡
ሃይማኖት ፡ ብቻ ፡ ይዞ ፡ ምግባር ፡ የማይሠራ ፡
በፈጠረው ፡ የሚቀልድ ፡ ሥጋውን ፡ የሚወድ ፡
ብልጥ ፡ እምናለሁ ፡ አልገብርም ፡ የሚል ፡ በመ



ፀኛ ፡ መሆኑን ፡ ዕወቅ ፡ እንጂ ፡ ይህን ፡ ዐይነት ፡
እንጋገር ፡ አትስማው ።

የሚጸድቀው ፡ ግን ፡ እውነት ፡ ነው ፡ በሰውየው ፡
ሃይማኖት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ነው ፡
እንጂ ፡ በሞትና ፡ በድካም ፡ የሚወሰን ፡ ሥራና ፡
ትሩፋት ፡ ወሰን ፡ ለሌለው ፡ ለመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡
ዋጋ ፡ አይሆነውም ።

፰ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ምግባራችን ፡ ለመንግሥተ፡
ሰማይ ፡ ዋጋንት ፡ ባይበቃ ፡ ዋጋው ፡ ብዙ ፡ የሆ
ነን ፡ ርስት ፡ ከቸር ፡ ተካይ ፡ ላይ ፡ ደጅ ፡ ቢጠኑት ፡
ነው ፡ እንጂ ፡ የሚገኘው ፡ እቤቱ ፡ እንደ ፡ ተቀ
መጠ ፡ እንዲያው ፡ ባፌ ፡ እወድሃለሁና ፡ ርስት
ህን ፡ ስጠኝ ፡ ቢለው ፡ በመናቁ ፡ ይጣላዋል ፡
እንጂ ፡ እንኳን ፡ ርስቱን ፡ ትንሹንም ፡ ገንዘቡን ፡
አይሰጠውምና ፡ ስለዚህ ፡ ሰው ፡ ወሰን ፡ ያላት ፡
ትንሽ ፡ ርስቱን ፡ ሽጦ ፡ ለውጦ ፡ ለደጅ ፡ መጥኛ ፡
የሚሆነውን ፡ ፈረስና ፡ በቅሎ ፡ ገዝቶ ፡ ሰውነቱን ፡
በልብስና ፡ በመሣሪያ ፡ አጊጦ ፡ ለንጉሥ ፡ ገብቶ፡
ሌት ፡ ከዘብ ፡ ቀን ፡ ካጀብ ፡ ሳይለይ ፡ የጌታውን ፡
ባሕርይ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝበትን ፡ እየመረመረ ፡
የሚወደውን ፡ እየሠራ ፡ ደስ ፡ ቢያሰኘው ፡ ሳገ
ልግሎቱ ፡ ዋጋው ፡ እንዳይራብ ፡ ማብላት ፡ እንዳ
ይታረዝ ፡ ማልበስ ፡ እንዳይዋረድ ፡ ማክበር ፡ ብቻ ፡
ሲሆን ፡ ያለሥራው ፡ ዋጋ ፡ በንጉሡ ፡ ቸርነት ፡

ከሱ ፡ ተርፎ ፡ ለሰው ፡ የሚጠቅምበት ፡ ብዙ ፡ ሀብት ፡ ሰፊ ፡ ግዛት ፡ ሰጥቶ ፡ ያኖረዋል ።

ልብሱ ፡ ጉርሡ ፡ ዋጋው ፡ ግዛቱና ፡ ሀብቱ ፡ ከቸር ነቱ ፡ መሆኑን ፡ የሚያስረዳው ፡ ልብሱና ፡ ጉርሡ ፡ ሲቀርበት ፡ ተካሶና ፡ አቤት ፡ ብሎ ፡ ይቀበለዋል ።

ሹመቱን ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ዕውቀቱ ፡ መዝኖ ፡ እንደ ፡ ቸርነቱ ፡ ለግሶ ፡ ገኘው ፡ እንደ ፡ ዕውቀቱ ፡ ይሰ ጠዋል ፡ እንጂ ፡ ሹመቱን ፡ ከሺሚው ፡ ተሻግቶ ፡ ሊያገኝ ፡ አለመቻሉን ፡ አስተውል ።

፱ ፡ እንደዚህም ፡ ሁሉ ፡ ለሥጋዊ ፡ ትሩፋታችን ፡ ዋጋው ፡ ለመናኒው ፡ ረድ ፡ ሰጥቶ ፡ አራዊቱን ፡ አስገዝቶ ፡ ዕፀዋትን ፡ አስፈርቶ ፡ መመገቡ ፡ ለሰብእ ፡ ዓለም ፡ በፀሓይ ፡ አብስሎ ፡ በዝናም ፡ አብቅሎ ፡ ማብላቱ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ዋጋው ፡ በብልየት ፡ በኀልፈት ፡ የሚጠፋው ፡ ገንዘብ ፡ በድካምና ፡ በሞት ፡ የሚወሰነው ፡ ትሩፋተ ፡ ሥጋ ፡ ወሰንና ፡ ብልየት ፡ ለሌላት ፡ ለመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ዋጋ ፡ ለመሆን ፡ የማይበቃ ፡ መሆኑ ፡ ስንኳን ፡ መጻሕፍት ፡ ተጨምረው ፡ ልቡናም ፡ ብቻ ፡ የሚፈርደው ፡ ርግጥ ፡ ነው ።

፲ ፡ ይህ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ ለንጉሥ ፡ አዳር ፡ የሄደ ፡ ሎሌ ፡ የንጉሡን ፡ ፀዋጅና ፡ ደንብ ፡ መጠበቅ ፡ ግዴታው ፡ ነውና ፡ ቢያፈርስ ፡ ይቀጣበታል ፡ እንጂ ፡ ንጉሥነቱን ፡ ብቻ ፡ ቢያውቅና ፡ ቢያምን ፡



ከቅጣት ፡ አያድነውምና ። እንደዚህም ፡ ሁሉ ፡ ፈጣሪው ፡ የነገረውን ፡ ፀዋጅና ፡ ደንብ ፡ እያፈረሰ ፡ አመልካለሁ ፡ በቸርነቱ ፡ አምናለሁ ፡ የሚል ፡ የተራቀቅሁ ፡ እየመሰለው ፡ በፈጣሪው ፡ ይዘብ ታል ።

፲፩ ፡ ሰው ፡ ወይ ፡ ክፉ ፡ ወይ ፡ በጎ ፡ ግብር ፡ ሳይሠራ ፡ በተስፋና ፡ በሃይማኖት ፡ ብቻ ፡ ለመኖር ፡ የማይ ችል ፡ መሆኑ ፡ ርግጥ ፡ ነውና ፡ ሰይጣን ፡ ልቡና ህን ፡ በተስፋና ፡ በሃይማኖት ፡ አመካኝቶ ፡ በሃይ ማኖት ፡ በጎ ፡ ሥራህን ፡ ባስተወህ ፡ ጊዜ ፡ ፈቃ ዱን ፡ ለማሠራት ፡ የሰይጣን ፡ ምርኮኛ ፡ መሆን ክን ፡ ዕወቀውና ፡ ሊጋንንት ፡ እንኳን ፡ የማይጸድ ቁበት ፡ ሃይማኖት ፡ እንዳላቸው ፡ አስተውል ፡ እንጂ ፡ ሃይማኖትና ፡ ተስፋህን ፡ አገኛለሁ ፡ አይም ሰልህ ።

፲፪ ፡ ሰይጣን ፡ ግብርህን ፡ ጨርሰህ ፡ እስክትተው ለት ፡ ድረስ ፡ ሃይማኖትህንና ፡ ተስፋህን ፡ ያቆ ይልሃል ፡ ግብርህን ፡ አፍርሰህ ፡ ሳትጨርስለት ፡ ግን ፡ ሃይማኖትና ፡ ተስፋህን ፡ አስጥሎ ፡ ለዘለ ዓለም ፡ ወደ ፡ ሰይጣን ፡ ባርነት ፡ መሄድክን ፡ ዕወቀው ።

፲፫ ፡ በምግባሬም ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ አገኛ ለሁ ፡ ሳይመስልህ ፡ በጎ ፡ ሥራህንም ፡ ሳትተው ፡ በጎ ፡ ግብር ፡ ከአዳም ፡ ለወረስነው ፡ ለክፉ ፡ ምኞት ፡

ማገጃ ፡ አጥር ፡ ለሰይጣን ፡ መከልከያ ፡ ቅጥር ፡ መሆኑን ፡ ዕወቅ ።

፲፬ ፡ የምትጸድቀው ፡ በሃይማኖት ፡ የምታገኘው ፡ በቸርነት ፡ መሆኑን ፡ አምነህ ፡ አሳብህን ፡ በዚህ ፡ አቁመህ ፡ ተስፋህን ፡ ከቸርነቱ ፡ ላይ ፡ አጽና ።

፲፭ ፡ እንደ ፡ ሰነፎቹ ፡ በተስፋዩና ፡ በሃይማኖቴ ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ትምክሕተኞች ፡ በምግባሬና ፡ በትሩፋቴ ፡ ብቻ ፡ እድናለሁ ፡ አትበል ። (ጣዕመ ፡ ጸሎት ፡ ም ፡ ፲) ።

፲፮ ፡ አሳብና ፡ ሥራህ ፡ ድንበር ፡ እንዲያገኝ ፡ ሃይማኖትህን ፡ በጸሎተ ፡ ሃይማኖት ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ ቃል ፡ ምግባርህን ፡ ከአሪት ፡ ባ፲ ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ አካሄድ ፡ አድርገህ ፡ ትሩፋትህንም ፡ ለማጥፋት ፡ አብነታቸውን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ያሳየንን ፡ ከወንጌል ፡ እያነበብክ ፡ ብታምንና ፡ ብትሠራ ፡ የዘላለም ፡ ደኅንነትና ፡ ሕይወትህን ፡ ታገኛለህ ፡ (ጣዕመ ፡ ጸሎት ፡ ም ፡ ፱) ።

፲፯ ፡ የምግባርን ፡ ለምለምነት ፡ የትሩፋትን ፡ አበባነትና ፡ የሃይማኖትን ፡ ፍሬነትም ፡ ልትረዳ ፡ ብትሻ ፡ ከሚከተለው ፡ ምሳሌ ፡ አስተውለው ።

ድንች ፡ ወይም ፡ እንደሱ ፡ ያሉ ፡ አታክልቶች ፡ ሁሉ ፡ የሚጠቅሙት ፡ በማይታየው ፡ ፍሬያቸው ፡ ሲሆን ፡ በጸደቁ ፡ ጊዜ ፡ በግድ ፡ አበባቸውንና ፡ ቅጠላቸውን ፡ አውጥተው ፡ ያሳያሉ ።



ካልጠፉ ፡ በቀር ፡ አበባቸውን ፡ ለማስቀረት ፡ እንዳይችሉ ፡ ከልቡ ፡ ውስጥ ፡ ሃይማኖት ፡ የተዘራበት ፡ ሰውም ፡ ካልጠፋበት ፡ በቀር ፡ ቅጠል ፡ ምግባሩ ፡ አበባ ፡ ትሩፋቱ ፡ በግድ ፡ ይታያል ።

ለባለቤቱ ፡ ግን ፡ ለምልሞ ፡ በማበቡ ፡ የፍሬውን ፡ አለመጥፋት ፡ ብቻ ፡ ያውቅበታል ፡ እንጂ ፡ አበባውም ፡ ቅጠሉም ፡ ከዋጋው ፡ እንዳይገባለት ፡ ለሰውም ፡ በቅጠል ፡ ምግባሩ ፡ ባበባ ፡ ትሩፋቱ ፡ የሃይማኖቱን ፡ ማጽደቅ ፡ ያውቅበታል ፡ እንጂ ።

ምግባሩን ፡ እንደ ፡ ዋጋ ፡ አድርጎ ፡ ሰማያዊ ፡ ርስት ፡ አይገባበትምና ።

እንደዚህም ፡ ሁሉ ፡ ምግባር ፡ ትሩፋት ፡ ከሃይማኖት ፡ ፍሬ ፡ ላይ ፡ የሚበቅል ፡ መሆኑን ፡ ይወቅ ፡ እንጂ ፡ ሃይማኖት ፡ አለኝ ፡ ብሎ ፡ ምግባር ፡ ትሩፋት ፡ የማይሠራ ፡ የፍሬው ፡ መጥፋት ፡ ባለመለምለሙና ፡ ባለማበቡ ፡ እንዲታወቅ ፡ የሃይማኖቱንም ፡ መጥፋት ፡ ምግባር ፡ ትሩፋት ፡ ባለመሥራቱ ፡ ይወቅ ።

ጥያቄ ።

፲፰ ፡ ሰው ፡ ምግባር ፡ ትሩፋትን ፡ ያጸድቀኛል ፡ ይጠቅመኛል ፡ ብሎ ፡ ካልደከመበት ፡ በነ ፡ ሥራውን ፡ ምን ፡ እያሰበ ፡ ቢሠራው ፡ ይገባል ።

ምላሽ ።

፲፱ ፡ አንተ ፡ ለሠራኸው ፡ ሥራ ፡ ያጸድቀኛል ፡ ይጠቅመኛል ፡ ያልከ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንደ ፡ ጣዖት ፡ ሠሪዎች ፡ የገዛ ፡ ሥራህን ፡ ስጨና ፡ ነሺ ፡ አድርገህ ፡ ማምለክ ፡ እንዳይሆንብህ ፡ ሥራዬ ፡ ብቻ ፡ ያጸድቀኛል ፡ አትበል ።

፳ ፡ ሰማያዊ ፡ መንግሥትም ፡ ተሸጭ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ሸያጭ ፡ አይደለምና ፤ በጎ ፡ ሥራዬን ፡ እንደ ፡ ዋጋ ፡ ገምቼ ፡ እንደ ፡ በረከት ፡ ሰጥቼ ፡ ሥራዬ ፡ ብቻ ፡ ጽድቅ ፡ ማግኛ ፡ ይሆነኛል ፡ አትበል ።

፳፩ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ፈርቶ ፡ እንደሚለማመጥ ፡ ገዥ ፡ አድርገህ ፡ እኔ ፡ እያመንኩት ፡ ልቀመጥ ፡ እሱ ፡ ብቻ ፡ ይስጠኝ ፡ እያልክ ፡ ያለሥራ ፡ በሃይማኖትህም ፡ አትዘባነን ።

፳፪ ፡ በጎ ፡ ግብርህን ፡ ስትሠራ ፡ ልቡናህን ፡ የምታሳስብበት ፡ ዐይነቱ ፡ የምትሠራበት ፡ ምክንያቱ ፡ ስለ ፡ ሦስት ፡ ነገር ፡ መሆኑን ፡ እሳውቀህ ፡ ሥራው ።

፳፫ኛ ፡ ስለ ፡ ፈጠረህ ፡ ስለ ፡ መገበህ ፡ ለጌትነቱ ፡ ለመገዛት ፡ ሊቃሉ ፡ በመታዘዝ ፡ እምላካዊ ፡ ባሕርይን ፡ ለማስደሰት ።

፳፬ኛ ፡ በደሙ ፡ ገዝቶ ፡ በጥምቀት ፡ ወልዶ ፡ በቸርነቱ ፡ የሰጠህን ፡ ባባትነቱ ፡ የተከለህን ፡ ሰማያዊ ፡ ርስትህን ፡ እንዳትነቀል ፡ ለመገበር ።



፳፭ኛ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አልገዛም ፡ አልገብርም ፡ እያለ ፡ ለገዛ ፡ ባሕርዩ ፡ የሚገዛ ፡ ባሕርየ ፡ ሥጋን ፡ ከክፉ ፡ ምኞት ፡ እስኪመለስ ፡ በትሩፋት ፡ ለመቅጣት ።

፳፮ኛ ፡ ጌታችን ፡ ስለኛ ፡ ኀጢአት ፡ ስለ ፡ ተሠዋልን ፡ በሌላ ፡ ስጦታ ፡ የማይመለስ ፡ ትልቅ ፡ ወሮታ ፡ እለብንና ፡ ፍቅሩን ፡ ለመኻት ፡ በሱ ፡ ፍቅር ፡ ነደን ፡ የትሩፋት ፡ ሥራችንን ፡ ለመሠዋት ፡ ነውና ።

እንደ ፡ ጾምና ፡ ጸሎት ፡ እንደ ፡ ሰጊድና ፡ ምጽዋት ፡ ያለውን ፡ በጎ ፡ ሥራችንን ፡ ሁሉ ፡ ስንሠራ ፡ ይህን ፡ ፬ቱን ፡ ምክንያት ፡ እያሰብን ፡ ስንሠራው ፡ የገዛ ፡ ሥራችንንም ፡ ባለማወቅ ።

ካለማምለክ ፡ የሃይማኖታችንንም ፡ ፍሬ ፡ ሳናውቅ ፡ በስንፍና ፡ ከመበደል ።

ርስታችንንም ፡ በንቢታ ፡ ከመነቀል ፡ ድነን ፡ በትሩፋትም ፡ ባለፃልነትን ፡ አትርፈን ፡ በቸርነቱ ፡ የዘላለምን ፡ ጥቅም ፡ እንድናገኝ ፡ እንመን ።

ለበጎ ፡ ሥራችን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ያሳባችንን ፡ አካሄድ ፡ በዚህ ፡ እናቁመው ።

፳፯ ፡ ምግባር ፡ ማለትም ፡ ሥራ ፡ ማለት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሥራ ፡ እንጂ ፡ መሣሪያ ፡ አይደለም ።

እካልም ፡ መሣሪያ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሠሪም ፡ አሠሪም ፡ አይደለምና ፡ በጎ ፡ ምግባርን ፡ ሁሉ ፡ ባለጤና ፡

በአካልም ፡ ሠራሁበት ፡ ሊል ፡ አይገባውምና ፡ በሃይማኖትህም ፡ በጎ ፡ ግብር ፡ ሠሪ ፡ ብትሆን ፡ አትመካ ፡ (ስለ ፡ አባት ፡ እናት ፡ ም ፡ ፳፩ ፡ ፳፯) ።

## ጥያቄ ።

፳፬ ፤ አካልም ፡ ካልሠራው ፡ ጠባይም ፡ ካልሠራው ፡ በጎ ፡ ግብር ፡ ሠሪም ፡ አሠሪም ፡ ማጣቱ ፡ አይደለምን ፡ እንግዲህ ፡ ሠሪው ፡ ማን ፡ ሊሆን ፡ ነው ።

## ምላሽ ።

፳፭ ፤ ሠሪዋ ፡ ነፍስ ፤ አሠሪው ፡ ሃይማኖት ፡ ነው ። ምሳሌውም ፡ አካልም ፡ እንደ ፡ በሬ ፡ ያለ ፡ መሣሪያ ፤ ጠባይ ፡ እንደ ፡ መሣሪያ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፤ ነፍስ ፡ እንደ ፡ ገበሬውም ፡ የሆነች ፡ ሠሪ ፤ ሃይማኖት ፡ እንደ ባለቤቱ ፡ የሆነ ፡ አሠሪ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ የታረሰበትም ፡ በሬው ፡ የታረሰው ፡ ምድሩ ፡ የእገሌ ፡ በሬ ፡ የእገሌ ፡ እርሻ ፡ ተብለው ፡ እንደሚጠሩት ፡ ለበጎ ፡ ምግባር ፡ አሠሪው ፡ ሃይማኖት ፡ ሠሪው ፡ ነፍስ ፡ ሆኖ ፡ ከሃይማኖት ፡ ተዋሕዳ ፡ የሥጋ ፡ በሕርይ ፡ ከሚወደው ፡ ጠባይ ፡ ተለይታ ፡ የምትሠራው ፡ ነውና ።

ስለዚህ ፡ በቋንቋችን ፡ በጎ ፡ ምግባር ፡ የምንለው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ትርጓሜው ፡ የሃይማኖታችን ፡ ሥራ ፡ የነፍሳችን ፡ መሥሪያ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነውና ።



ስለዚህ ፡ በሃይማኖት ፡ ለሚወደደው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ተብሎ ፡ የሚሠራ ፡ በልማድ ፡ ብቻ ፡ የሚሠራ ፡ ምግባር ፡ ሁሉ ፡ እንኳን ፡ የሚያጸድቅበት ፡ የሚጠራበትም ፡ ስም ፡ የሌለው ፡ ከንቱ ፡ ሥራ ፡ መሆኑን ፡ ልናውቅ ፡ ይገባል ።

፳፮ ፤ ይህንም ፡ ልትረዳ ፡ ብትሻ ፡ ስለ ፡ በጎ ፡ ሥራችን ፡ አኳኋን ፡ ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ መሆኑን ፡ በምሳሌ ፡ እንወቅ ።

ሰው ፡ በብርጭቆ ፡ ወተትም ፡ ቅቤም ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ጤናው ፡ ወይን ፡ ቢጠጣ ፡ የጠጣው ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ የገባው ፡ የማይጨበጠው ፡ ረቂቁ ፡ ቅቤ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሚጠቀመው ፡ የጠጣበት ፡ ብርጭቆ ፡ አይጠቀመውም ፤ ከከንፈር ፡ ውስጥ ፡ ስለ ገባ ፡ ብርጭቆ ፡ ተጠጣ ፡ አይባልም ፤ የሚበላም ፡ ምግብ ፡ ሁሉ ፡ ከገባ ፡ በኋላ ፡ ከሰውነታችን ፡ ውስጥ ፡ ነጥሮ ፡ ተለይቶ ፡ የሚቀረው ፡ ረቂቁ ፡ ቅባት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሚጠቀመው ፡ ሲበላ ፡ ተላምጦ ፡ ገብቶ ፡ ተመልሶ ፡ የሚወጣው ፡ ግዙፉ ፡ አሠር ፡ ለሚነጥረው ፡ ቅባት ፡ የመግቢያ ፡ ዕቃ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ያ ፡ ግዙፉ ፡ እንዲያው ፡ ሲገባና ፡ ሲወጣ ፡ ከማድከም ፡ በቀር ፡ የሚጠቅመው ፡ ነገር ፡ እንደሌለ ።

እንደዚሁም ፡ ሁሉ ፡ ለነፍስ ፡ የሚጠቅመው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘው ፡ ከልቡና ፡ ውስ

ጥ ፡ የሚገባውን ፡ የማይጨብጠውን ፡ ረቂቅ ፡ ፍት
ረ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሃይማኖት ፡ ጽዋ ፡ ቀድቶ ፡
በምግባር ፡ እጅ ፡ ጨብጦ ፡ ሲጠጡት ፡ ነውና ፡
የሚጠቅመው ፡ ሰው ፡ እግዚአብሔርን ፡ በውነት ፡
ወዶ ፡ የሚሠራውን ፡ ሁሉ ፡ ለሱ ፡ ፍቅር ፡ ሲል ፡
ካልሠራው ፡ በልማድ ፡ ብቻ ፡ በጎ ፡ ነገር ፡ ቢሠራ ፡
አሠር ፡ እንደ ፡ ማላመጥ ፡ ባዶ ፡ ብርጭቆ ፡ እንደ ፡
መጨበጥ ፡ ይሆንበታል ፡ እንጂ ፡ አይጠቅመውም ።

፳፯ ፡ ይህ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ ግዙፉ ፡ ብርጭቆና ፡ የእ
ኽል ፡ አሠር ፡ ነጥሮ ፡ ለሚጠቅመው ፡ ቅባት ፡ መግ
ቢያ ፡ እንዲሆን ።

በጎም ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ የሚወደደውን ፡ ረቂቁን ፡
የአምላክን ፡ ፍቅር ፡ ጨብጦ ፡ ወደ ፡ ነፍሳችን ፡
ውስጥ ፡ ለማግባት ፡ መሣሪያ ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡
መጥቀሚያውም ፡ በረቂቅ ፡ ፍቅሩ ፡ ጥቅም ፡ ተቀ
ባይዋም ፡ ረቂቋ ፡ ነፍሳችን ፡ ጥቅም ፡ ሰጪውም ፡
ረቂቁ ፡ አምላካችን ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሰው ፡ መጠቀሚ
ያው ፡ በረቂቅ ፡ አሳቡ ፡ በሚያደርገው ፡ በመንፈ
ሳዊ ፡ ቅንነት ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ በሚሠ
ራው ፡ ትጋት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በግዙፉ ፡ ሥጋው ፡
ለሥጋው ፡ ፈቃድና ፡ ልማድ ፡ ብቻ ፡ ሲል ፡ በሠ
ራው ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ ግን ፡ ለሥጋው ፡ ፍትወት ፡
መፈጸሚያ ፡ የሚሆነውን ፡ ከንቱ ፡ ሀብት ፡
ብቻ ፡ ያገኝበታል ፡ እንጂ ፡ ለነፍስ ፡ የሚጠቅመ
ውን ፡ ሰማያዊ ፡ ርስት ፡ ለማግኘት ፡ አይሆንለትም ።



ጥያቄ ።

፳፰ ፡ ረቂቋ ፡ ነፍሳችን ፡ ሳትጨመርበት ፡ ሥጋችን ፡
ብቻ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ በጎ ፡ ለመሥራት ፡ ይቻለዋል ።
ሥጋስ ፡ በጎ ፡ ነገር ፡ ሲሠራ ፡ ነፍሳችን ፡ የት ፡
ተለይታ ፡ ቀርታ ፡ የሷ ፡ ጥቅም ፡ ይቀርባታል ።

ምላሽ ።

፳፱ ፡ ሥጋ ፡ ለሥጋው ፡ ግዙፍ ፡ በጎነትን ፡ ሲሠራ ፡
ነፍስም ፡ ለሥጋ ፡ አሳቢ ፡ ሁና ፡ ለራሷ ፡ ጥቅም ፡
ልትሠራ ፡ ይገባት ፡ የነበረውን ፡ በጎ ፡ አሳብ ፡
ዕውቀቷን ፡ ለሥጋዋ ፡ ፈቃድ ፡ መሣሪያ ፡ እድርጋ ፡
ትሰጥና ፡ ሠሪ ፡ ሳትሆን ፡ የሥጋዋ ፡ መሣሪያ ፡ ሆና ፡
ስለ ፡ ኖረች ፡ ለሷም ፡ የሚሆን ፡ የሰማያዊ ፡ ርስቷ
ንም ፡ ትነቀላለች ።

ጥያቄ ።

፴ ፡ የሷን ፡ ሥራ ፡ ትታ ፡ ለሥጋዋ ፡ መሣሪያ ፡
ሁና ፡ የምትጐዳበት ፡ ለምን ፡ ሥራ ፡ መሣሪያ ፡
ስትሆን ፡ ነው ።

ምላሽ ።

፴፩ ፡ ነፍስ ፡ ራሷ ፡ ሠራተኛ ፡ ሁና ፡ ሥጋዋን ፡
መሣሪያ ፡ እድርጋ ፡ የምትጠቀምበት ፡ ጾምና ፡ ጸ
ሎት ፡ ስግደትን ፡ ለትእዛዙ ፡ መገዛትን ፡ ፍቅረ ፡
ቢጽና ፡ ቅንነትን ፡ ትዕግሥትና ፡ ምጽዋትን ፡ ትሕ

ትናና ፡ እውነትን ፡ ይህን ፡ ፀሥሩን ፡ መጠቀሚ
ያ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብላ ፡ ስትሠራው ፡ ነበር ፤
ለሥጋ ፡ ፈቃድ ፡ ተሸንፋ ፡ ግዙፍ ፡ በኀኑት ፡
ሠረ ፡ ሁና ፡ ለሥጋዋ ፡ መዛሪያ ፡ ስትሆን ፡ ግን ፡
ጾምና ፡ ጸሎትን ፡ ስጊድና ፡ መገዛትንም ፡ ለእግዚ
አብሔር ፡ ፍቅር ፡ ሳትል ፡ ለሥጋዋ ፡ ዕድሜ ፡ መለ
መኛ ፡ ለንብረቷ ፡ ደጅ ፡ መጥኛ ፡ ታደርግና ፡
ፍቅረ ፡ ቢጽንም ፡ ወዶ ፡ ለመወደድ ፡ ከዋጋ ፡ ቢት ፡
ታገባና ፡ ትዕግሥቷን ፡ ችላ ፡ ለመብለጥ ፡ ምጽዋ
ቷንም ፡ ስጥታ ፡ ለመመስገን ፡ ትሕትናዋንም ፡
አታላ ፡ ለመወደድ ፡ እውነቷንም ፡ ታማኝ ፡ ተብላ ፡
ራሷን ፡ ለማስከበር ፡ በጎ ፡ ሥራዋን ፡ ሁሉ ፡ ለእ
ንዲህ ፡ ያለ ፡ ለብልጠት ፡ መሥራት ፡ ለዓለም ፡ መ
ኘት ፡ ስትል ፡ ብትሠራው ፡ በጎውን ፡ ሥራ ፡ መሥራ
ቷም ፡ ሳይቀር ፡ ስለ ፡ አሳቧ ፡ ሥጋዊነት ፡ ከዕድሜዋ ፡
የሚተርፈውንም ፡ የምድር ፡ ረድኤት ፡ ለመኖሪያዋ ፡
የሚሆነውን ፡ ሰማያዊ ፡ ርስት ፡ አጥታ ፡ ትጐዳለች ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ መመልከቻ ።

፲፱ ፡ ባለህ ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍ
ትን ፡ ለመመልከት ፡ አጥብቀህ ፡ ትጉህ ፡ ሁን ።
ወዘሕን ፡ ያንብብ ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ፡ ወይከ



ውን ፡ ከመ ፡ ዕፅ ፡ እንተ ፡ ትከልት ፡ ኀበ ፡ ሙሐዘ ፡
ማይ ፡ የተባለውንም ፡ አትርሳ ።

፳ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ የመመልከት ፡ ብዛ
ት ፡ መጠን ፡ አጥተህ ፡ መንገድ ፡ በዝቶብህ ፡ እን
ዳትጐዳ ።

መንገዱም ፡ ሁሉ ፡ እንዲያምርህ ፡ እግዚአብሔር ፡
በከፈለው ፡ መንገድ ፡ እንዲያጸናህ ፡ መጻሕፍትን ፡
እንደየመንገዳቸው ፡ በዐይነት ፡ ተመልከት ።

ጥያቄ ።

፳፩ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ የሚያሳዩን ፡ መንገድ ፡
አንድ ፡ አይደለም ፡ በምን ፡ ይለያል ።

ምላሽ ።

፳፪ ፡ ሁሉም ፡ ተስማምተው ፡ ልንሄድበት ፡ የሚ
ገባን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መሆኑን ፡ ይነግሩ
ናል ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔርስ ፡ የሚያስኬ
ዱን ፡ መንገዶች ፡ ፬ ፡ ናቸው ። ከእነሱም ፡ ከ፪ቱ ፡
መንገዶች ፡ ባንዳቸው ፡ ከሄድን ፡ ወደ ፡ ሰማያዊ ፡
አገራችን ፡ ወደ ፡ ዘላለም ፡ ሕይወታችን ፡ የሚያደ
ርሱን ፡ መንገድ ፡ ሁነዋልና ፡ በመንገድ ፡ መም
ረጥ ፡ ጊዜው ፡ እንዳያልቅብን ፡ ባንዳቸው ፡ መን
ገድ ፡ መሄድ ፡ ይገባናል ።

፳፫ ፡ መንገድ ፡ ከሆነ ፡ ብለን ፡ ባራት ፡ መንገድ ፡
እንሂድ ፡ ያልን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በመመላለስ ፡ ቀኑ ፡

እንዳይመሽብን ፡ ልንሠራበት ፡ የተቀበልነውን ፡ ሰዓት ፡ በዙረት ፡ ጨረስን ፡ ወደ ፡ ቅጣት ፡ እንዳና ልፍ ፡ ላሳባችን ፡ ካራቱ ፡ አንዱን ፡ አስመርጦ ፡ ማሲያዝ ፡ ነው ።

፴፯ ፡ ፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አላስኬድህ ፡ ብሎ ፡ በግድ ፡ ካልከለከለህ ፡ በቀር ፡ ባንተ ፡ ፈቃድ ፡ የገመርከውን ፡ መንገድ ፡ ሳትለቅ ፡ ስትመለስ ፡ ከፍጻሜው ፡ ክብር ፡ እስክትደርስ ፡ ድረስ ፡ የገመርከውን ፡ መንገድ ፡ መሄድ ፡ ነው ።

፴፰ ፡ አንተ ፡ የገመርከውን ፡ መንገድ ፡ መልቀቁ ፡ ፈቃድህ ፡ ሳይሆን ፡ እንደ ፡ ሊቀ ፡ ሀገር ፡ በመጠራት ፡ እንደ ፡ ዘርዐ ፡ ያዕቆብ ፡ በመቀባት ፡ እንደ ፡ ወቅረስ ፡ በመግዛት ፡ እንደ ፡ ድሚጥሮስ ፡ በተአምራት ፡ በግድ ፡ ስትታዘዝ ፡ ግን ፡ ከገመርከው ፡ መንገድ ፡ ተመልሰህ ፡ በታዘዝከው ፡ መንገድ ፡ ሂደህ ፡ እስከ ፡ ፍጻሜው ፡ መድረስ ፡ ነው ።

፴፱ ፡ ባንተም ፡ ፈቃድ ፡ ብቻ ፡ የገመርከውን ፡ በመጣል ፡ ያየኸውን ፡ መንገድ ፡ ሁሉ ፡ በመከተል ፡ ሥራህን ፡ እንደ ፡ ትቢያ ፡ አትበትነው ፡ አሳብህንም ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ አታዋለው ፡ የመረጥካቸውን ፡ ሥራ ። የሚመረጡት ፡ አራቱ ፡ ጐዳናዎች ፡ የተባሉትም ፡ ከዚህ ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ።

አንዱ ፡ በየኑሯቸው ፡ ዐይነት ፡ ሠርተውና ፡ ለሰው ፡ ተገዝተው ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ለሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ የሚያሻቸውን ፡ የየሕይወታቸውን ፡ መንገድ ፡ ለማሳየት ፡ የተጻፈባቸውን ፡ ቃል ፡ ያሳያቸዋል ።



## ፮ኛው ፡ መንገድ ።

ተገዝቶ ፡ መኖርም ፡ ባለትልቅ ፡ ዋጋ ፡ መሆኑን ፡ አውሎጊስን ፡ ከመግዛት ፡ ወደ ፡ መገዛት ፡ በመመለሱ ፡ እስተውልና ፡ ከዚህ ፡ የሚከተሉትን ፡ ፵፮ ቱን ፡ መጻሕፍት ፡ ተመልከታቸው ።

ኩብሉያት ።
ዘፍጥረት ።
ዘፀአት ።
ኩፋሌ ።
ሩት ።
ዮዲት ።
ዕዝራ ፡ ፪ኛ ።
ነሐምያ ።
አስቴር ።
ኢዮብ ።
ምሳሌ ።
ጦቢት ።
ሢራክ ።
መቃብያን ።
ከሐዲሳት ።
የማርቆስ ፡ ወንጌል ።
፲፬ ፡ የጳውሎስ ፡ መልክት ።

፪ቱ ፡ የጴጥሮስ ፡ መልክት ።
፫ቱ ፡ የዮሐንስ ፡ መልክት ።
፩ ፡ የይሁዳ ፡ መልክት ።
የአፈ ፡ ወርቅ ፡ ተግሣጽ ።
ከአዋልድ ።
ፈላስፋ ።
ድምር ፡ ፹፩ ፡ ነውና ፤ ይህን ፡ ተመልከት ።

ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ጋራ ፡ የሚስማማውን ፡ ምዕዳን ፡ ምእላድ ፡ ተመልከት ፡ ግን ፡ የክፍልህ ፡ ኑሮ ፡ በተግባረ ፡ እድ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሥራህን ፡ እንዳ ያስፈታህ፡ በተለይ፡ ቀን፡ በተወሰነ፡ ሰዓት ፡ ተመል ከት ፡ እንጂ ፡ ማብዛት ፡ ከመሰልቸት ፡ መሰልቸት ፡ ከመተው ፡ መተው ፡ ከመንቀፍ ፡ መንቀፍ ፡ ከመ ኰነን ፡ ማድረሱን ፡ እስተውለህ ፡ ከሥራህ ፡ ጋራ ፡ እያቀላቀልክ ፡ በመጠን ፡ ተመልከተው ።

## ፪ኛው ፡ መንገድ ።

፲ ፤ ሰውን ፡ ለሚያሳድሩ ፡ ለሰብእ ፡ ዓለም ፡ ለነገሥታትና ፡ ለመኳንንት ፡ ለጭቃና ፡ ለአለቃም ፡ ቢሆን ፡ ገዢቶ ፡ ዳኙቶ ፡ መኖርም ፡ ባለትልቅ ፡ ዋጋ፡ መሆኑን ፡ ዘርዐ ፡ ያዕቆብን ፡ ከገዳም ፡ ትሩፋት ፡ ወደ ፡ መንግሥት ፡ ትሩፋት ፡ በመመለሱ ፡ አስተውልና ፡ ፲፰ቱን ፡ መጻሕፍት ፡ ተመልከት ።

አሪት ፡ ዘዳግምን ።
ኢያሱን ።



መሳፍንትን ።
፬ቱን ፡ ነገሥት ።
ዳዊት ።
ከሐዲሳት ፡ ሉቃስ ፡ ወንጌል ።
ከሊቃውንት ።
ፍትሐ ፡ ሥጋዊ ።
ከአዋልድ ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ።

ታሪክ ፡ ሀገር ፡ ተመልከተህ ፡ ይህን ፡ አዋልድ ፡ ስትመለከት ፡ ግን ፡ የዓለም ፡ ታሪክ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ከፍሬው ፡ ጋራ ፡ ብዙ ፡ ገለባ ፡ አለበትና ፡ ገለባ ው ፡ ጭምር ፡ እየገባ ፡ የፍሬውን ፡ መያገ ፡ አእ ምሮህን ፡ እንዳይሞላብህ ፡ ፍሬ ፡ ፍሬውን ፡ በም ልክት ፡ እየመረጥህ ፡ ተመልከት ።

ከገድል ፡ በረለአምና ፡ ገድለ ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስን ፡ ተመልከት ።

፲፩ ፤ ዓለምን ፡ ለናቁ ፡
ፈቃደ ፡ ሥጋን ፡ ላጠቁ ፡
ፈቃደ ፡ ነፍስን ፡ ላወቁ ፡
በምንኵስና ፡ ለሚጸድቁ ፡
መንና ፡ መሄድም ፡ ባለትልቅ ፡ ዋጋ ፡ መሆኑንም ፡ ሊቀ ፡ ሀገርን ፡ ከዓለም ፡ ትሩፋት ፡ ወደ ፡ ምናኔ ፡ ትሩፋት ፡ ጠርቶ ፡ መውሰዱን ፡ አስተውልና ፡ በሥ ሩን ፡ መጻሕፍት ፡ ከጸሎትህ ፡ እየደባለቅህ ፡ ተመ ልከት ።

ከብሉያት ፡ መክብብን ። ከሐዲሳት ፡ ፬ቱን ፡ ወን
ጌል ፡ ይልቁንም ፡ የዮሐንስን ፡ ወንጌል ። ግን ፡ ም
ንም ፡ የግብረ ፡ ምንኵስና ፡ ዐዋጅ ፡ ቢበዛበት ፡
ዐዋጅ ፡ ነውና ፡ መነኮሳት ፡ አብዝተው ፡ ካህናት ፡
ምእመናን ፡ ወስነው ፡ ሁሉም ፡ ሊመለከቱት ፡ ይ
ገባል ።

ከዮሐንስ ፡ መልክት ፡ መገመሪያውን ።
አንዱን ፡ የያዕቆብ ፡ መልክት ።
ከሊቃውንት ።
፲፰ቱን ፡ መጽሐፈ ፡ መነኮሳት ።
ማለት ፡
አረጋዊ ፡ መንፈሳዊ ፡
ማር ፡ ይሥሐቅ ፡
ፊልክስዩስ ፡
መጽሐፈ ፡ ገነት ፡
ይመልከቱ ።

ከአዋልድ ፡ ገድለ ፡ ቅዱሳን ፡ ስንክሳርን ።
ዜና ፡ አበውን ፡ ተመልከት ። አዋልድ ፡ ስትመለ
ከት ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ቅዱሳን ፡ ቢሆኑ ፡ ሰው ፡
ናቸው ፡ በማለት ፡ ከወሰን ፡ ያለፈ ፡ ለልብ ፡ የማይ
ረዳ ፡ ነገር ፡ ስታገኝ ፡ ሳትነቅፍም ፡ ሳትከራከርም ፡
ለእግዚአብሔር ፡ ተውለትና ፡ እለፈው ።

እስመ ፡ እልበ ፡ ነገር ፡ ዘይስአኖ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
የተባለውንም ፡ አትርሳው ።



፵፪ ፤ ለካህናት ፡ ተሹሞ ፡ አስተምሮ ፡ መኖርም ፡
ባለትልቅ ፡ ዋጋ ፡ ለመሆኑ ፡ ድሚጥሮስ ፡ ከምእመ
ናን ፡ የስውር ፡ ትሩፋት ፡ ወደ ፡ ግልጥ ፡ የትምህ
ርት ፡ ትሩፋት ፡ በመጠራቱ ፡ አስተውልና ፡
ዘጉልቊ ።
ሔኖክ ።
ሱቱኤል ፡ ዕዝራ ።
መሓልይ ።
፲፪ ፡ ነቢያት ።

ከሐዲሳት ፡ የማቴዎስ ፡ ወንጌል ።
ግብረ ፡ ሐዋርያ ።
ቀለምሲስ ።
፫ ፡ ሲኖዶስ ፡ ዲድስቅልያ ፡
ከሊቃውንት ።
፲፩ቱ ፡ ቅዳሴ ።
ሃይማኖተ ፡ አበው ።
ቄርሎስ ።
ፍትሕ ፡ መንፈሳዊ ።
ያፌ ፡ ወርቅ ፡ ድርሳን ።
ከአዋልድ ፡ ስንክሳር ።
ትርጓሜ ፡ መጻሕፍት ።
ዮሐንስ ፡ መደብር ።
ሐዊ ።
ረድእ ፡ ወመምህር ።
ሥርዐተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።

ርቱዐ ፡ ሃይማኖትና ፡ ሳዊሮስ ።
የያሬድ ፡ የዜማ ፡ ድርሰት ፡ ለምስጋና ።
የአባ ፡ ጊዮርጊስን ፡ የምስጋና ፡ ድርሰት ።
ፈውስ ፡ መንፈሳዊ ፡ አጥና ። ማጥናትህ ፡ ግን ፡ ሥር ተህ ፡ ለማሠራት ፡ እንጂ ፡ ለዦራት ፡ አይሁን ። የሚያጠናበትም ፡ እኒህን ፡ ለራሱ ፡ ምስጢር ፡ መማሪያ ፡ ያጥናና ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ለሌላው ፡ ማስተማሪያ ፡ በሚቻለው ፡ ልክ ፡ ያጥና ።

የጉባኤ ፡ መጻሕፍት ፡ እሊህ ፡ ፹፩ዱና ፡ አባት ፡ መጻሕፍት ፡ ናቸው ።

፺፩ ፡ ሊቃውንትና ፡ ፫ ፡ የመነኮሳት ፡ መጽሐፍ ፡ የ፹፩ዱ ፡ መጻሕፍት ፡ ትርጓሜ ፡ ናቸው ።

እኒህ ፡ ፹፩ ፡ የጉባኤ ፡ መጻሕፍት ፡ ይባላሉ ። ከሊህ ፡ ሌላ ፡ ግን ፡ እኒህን ፡ መሠረት ፡ እያደረጉ ፡ በየጊዜው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንደ ፡ መራቸው ፡ እየተከተሉ ፡ የተደረሱ ፡ የኒህ ፡ ልጆች ፡ የሚባሉ ፡ መልተዋልና ፡ ባገኘሃቸው ፡ ጊዜ ፡ የሊህን ፡ መሠረት ፡ እለመልቀ ቃቸውን ፡ ከውስጣቸው ፡ እየመረጥክ ፡ እያስተዋ ልክ ፡ ለያዝከው ፡ ግብር ፡ የሚረዱህን ፡ ተመልከ ታቸው ፡ ከኒህ ፡ ከተከፈሉት ፡ መጻሕፍት ፡ ውስ ጥ ፡ እንዱ ፡ ካንዱ ፡ ክፍል ፡ የሌለ ፡ ሁኖ ፡ አይደ ለም ፤ መሠረቱ ፡ አንድ ፡ ነውና ፡ ሰዓት ፡ ተርፎህ ፡ ለምትሄድበት ፡ መንገድ ፡ የሚረዳህን ፡ እየመረ ጥህ ፡ ብትመለከት ፡ ካንዱ ፡ ያለው ፡ ካንዱ ፡ ይገኛል ።



ግን ፡ እንዲሠራ ፡ እንጂ ፡ እንዳይበዛ ፡ ተብሎ ፡ እን ደየሥራው ፡ በዐይነት ፡ ነውና ፡ የተከፈለው ፡ የተከ ፈለልህን ፡ በውቀህ ፡ ሳታጠና ፡ ወደ ፡ አልተከፈ ለልህ ፡ አትለፍ ።

እንደዚህ ፡ ከፍለህ ፡ ከሠራህ ፡ የሚመስለውን ፡ ነገ ር ፡ ስታጠና ፡ ሁሉን ፡ ላንበው ፡ ብትል ፡ ግን ፡ ለገዓር ፡ ዘአልቦ ፡ ምጣኔ ፡ ይተልዎ ፡ ገንጋኔ ።

ባማርኛም ፡ ብዙ ፡ ቢያወጉ ፡ ይዘንጉ ፡ የተባለው ፡ ይደርስብሃና ፡ ለፍላፊ ፡ ንቃፊ ፡ ብቻ ፡ ሆነህ ፡ የዐ ዋቂ ፡ በዳይ ፡ ለነፍስህ ፡ ገዳይ ፡ ትሆናለህ ፡ ማብ ዛትህ ፡ አይጠቅምህም ፤ መመጠንህ ፡ አያጐድል ህምና ፡ መጠነኛ ፡ ዕውቀት ፡ መርጠህ ፡ ያወቅኸ ውን ፡ ለመሥራት ፡ ፍጠን ።

፺፫ ፡ ለሰው ፡ ማስተማር ፡ የተመረጡ ፡ መምህ ራን ፡ ግን ፡ ሁሉ ፡ ያረቀቀውን ፡ ለሚጠይቃቸው ፡ የሁሉ ፡ መንገድ ፡ አሳይዎች ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ የሚች ሉትን ፡ ያኽል ፡ ከሁሉም ፡ ላይ ፡ ሊያጠኑ ፡ ሊመለ ከቱ ፡ ይገባል ።

፺፬ ፡ ከያይነቱ ፡ ኑሮ ፡ መርጠህ ፡ ባንዳቸው ፡ ሀያጅ ፡ ስትሆን ፡ በፊት ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ላይ ፡ የተከፈለልህን ፡ በውል ፡ መላልሰህ ፡ ካጠ ናህ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ አዋልዱ ፡ አልፈህ ፡ በጥቂቱ ፡ ተመልከተው ።

መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ አሳንሰህ ፡ የአዋልድ ፡ መመል ከትን ፡ አታብዛ ፡ አዋልድም ፡ የሰው ፡ ድርሰት ፡ የተለዋዋጩ ፡ የፍጡር ፡ ፍልስፍናና ፡ የቃል ፡ እውቀት ፡ የተቀላቀለበት ፡ መሆኑን ፡ አትርሳው ።

ምዕራፍ ፡ ፬ ።

## ስለ ፡ ጸሎት ፡ ምርምር ።

፺፬ ፡ የተጻፉት ፡ ጸሎቶች ፡ ሁሉ ፡ የጸሎት ፡ ማስታወሻዎች ፡ ናቸው ። ጸሎት ፡ የሚሆኑት ፡ አንባቢው ፡ በልቡ ፡ እያስተዋለ ፡ ሲጸልያቸው ፡ ነው ። ማስታወሻውን ፡ እያየ ፡ ካልሠራበት ፡ ቢያነበው ፡ ቢጽፈውም ፡ እንደማይጠቀም ፤ ሰውም ፡ የተጻፉትን ፡ ጸሎቶች ፡ ቢያያቸው ፡ ቢያነባቸው ፡ በልቡ ፡ ካልሠራቸው ፡ አይጠቅሙትም ። ይህንንም ፡ ለመረዳት ፡ ጸሎትን ፡ በልብ ፡ እያሰቡ ፡ ባንደበት ፡ ካልጸለዩት ፡ የማይጠቅም ፡ መሆኑን ፡ መጻሕፍት ፡ እንደ ፡ ነገሩን ፡ ርግጥ ፡ መሆኑን ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለው ፡ ምሳሌና ፡ ትርጓሜ ፡ ያስረዳሃል ።

ባፍ ፡ ብቻ ፡ መናገር ፡ የሚጠቅም ፡ አለመሆኑም ፡ ፎኖግራፍ ፡ ሬዲዮ ፡ ዋሻና ፡ ስልክ ፡ ሰው ፡ የተናገረውን ፡ መልሰው ፡ ቢናገሩም ፡ ጥቅምና ፡ ዋጋ ፡ እንዳያገኙ ።

፺፭ ፡ ቅዱሳን ፡ በፍጹም ፡ አሳባቸው ፡ እያሰቡና ፡ እያራቀቁ ፡ እንባና ፡ ጸጸት ፡ እየጨመሩ ፡ የደረሱ



ትን ፡ እኛ ፡ በልባችን ፡ ሌላ ፡ እያሰብን ፡ ባፋችን ፡ ብቻ ፡ እንደነሱ ፡ ብንናገር ፡ እንደ ፡ ገደል ፡ እንደ ፡ ዋሻ ፡ ሆነን ፡ በእግዚአብሔር ፡ መቀለድ ፡ ይሆናል ፡ እንጂ ፡ ጸሎት ፡ አይሆንልንም ።

፺፮ ፡ እንደኛስ ፡ አሳብ ፡ ጸሎትስ ፡ ተናግሮተ ፡ ሰብእ ፡ ምስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተባለ ፡ ነውና ።

ባፉ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በልቡ ፡ ከዓለም ፡ በመነጋገሩ ፡ ከንጉሥ ፡ ፊት ፡ ቁሞ ፡ ሲነጋገር ፡ ዞሮ ፡ ከሌላ ፡ ቢጫወት ፡ ቅጣት ፡ እንደሚገባው ፡ እንደዚሁም ፡ ልቡን ፡ ሳይጠቀልል ፡ የሚጸልይ ፡ ሰው ፡ አምላኩን ፡ የሚንቅና ፡ የሚያቃልል ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ቅጣቱ ፡ እጅግ ፡ ያስፈራል ።

፺፯ ፡ ስለዚህ ፡ የሚጸልይ ፡ ሰው ፡ በየንባባቸው ፡ ሲደርስ ፡ ከዚህ ፡ የሚከተሉትን ፡ በልቡናው ፡ ማሰብ ፡ ይገባዋል ።

በጸሎት ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ቃሎች ፡ የቅዳሴ ፡ የምስጋና ፡ የልመና ፡ ቃል ፡ ማቅረቢያ ፡ የምግባርና ፡ የሃይማኖት ፡ ማስቢያ ፡ ናቸውና ። ፩ኛ ፡ ከቅዳሴው ፡ ንባብ ፡ ስትደርስ ፡ ቅዳሴ ፡ ማለት ፡ ማክበር ፡ ነውና ፡ ከአክብሮው ፡ አነጋገር ፡ ስትደርስ ፡ ፈጣሪ ፡ መንግ ሥቱን ፡ ፈርዶ ፡ መግደሉን ፡ መስጠት ፡ መንግሥቱን ፡ እያሰብክ ፡ ልብህ ፡ ያከብረው ። ፪ኛ ፡ በሥራው ፡ ንባብ ፡ ስትደርስ ፡ ከሚመሰገንበት ፡ ከምስጋናው ፡ ጥበቡን ፡ የአምላክነቱን ፡ ሥራና ፡ ተአምራቱን ፡ ጥበቡን ፡

በእንክሮ ፡ አሳብ ። ፫ኛ ፡ በሰውነቱ ፡ ከሠራው ፡ ስትደርስ ፡ ትሕትናውን ፡ ለቤዛነቱ ፡ ፍቅሩን ፡ እያሰብክ ፡ አመስግነው ።

ከልመናው ፡ ንባብ ፡ ስትደርስ ፡ የምትለምነውን ፡ ለማድረግ ፡ ከሃሊነቱን ፡ ከሰጭዎች ፡ የሚበልጥ ፡ ቸር ፡ ካባት ፡ የሚበልጥ ፡ አሳቢ ፡ መሆኑን ፡ እያ መንክ ፡ እያሰብክ ፡ ለምን ።

፯ኛ ፡ ከፉ ፡ ሥራ ፡ አትሥራ ፡ ከሚለው ፡ ከምግባር ፡ ትእዛዝ ፡ ስትደርስ ፡ በሠራኸው ፡ በጎ ፡ ግብር ፡ ስለ ፡ ረዳህ ፡ አምላክህን ፡ አመስግንበት ፡ ባጠፋ ኸው ፡ በጎ ፡ ግብር ፡ ተጸጽተህ ፡ ረድኤት ፡ ፈልግ በት ።

፰ኛ ፡ ከሃይማኖት ፡ ንባብ ፡ ስትደርስ ፡ በዚች ፡ ማመንህንና ፡ አለማመንህን ፡ ልቡናህን ፡ መርም ረው ። እንስ ፡ ዐቀብኩ ፡ ፍናወ ፡ ዕጼባተ ፡ እንደሚ ለው ፡ ያለውን ፡ በምታነብበት ፡ ጊዜ ፡ ባሕርየ ፡ ሥጋ ህን ፡ ባሕርይ ፡ አድርጎ ፡ ቤዛህ ፡ ኢየሱስ ፡ ስላንተ ፡ የሠራልህን ፡ በሃይማኖት ፡ የሱን ፡ ሥራ ፡ ገንዘብ ፡ ማድረግህን ፡ ዕወቅበት ።

፵፱ ፡ ሌሎቹንም ፡ ከጸሎትህ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ ቃሎች ፡ ሁሉ ፡ አፍህ ፡ ሲያነብ ፡ በልቡናህ ፡ እየ ተረጐምህ ፡ ካልጸለይክ ፡ ጸሎትህ ፡ ከንቱ ፡ ይሆ ናል ። እስበህ ፡ ግን ፡ ብትጸልይ ፡ ጥቅም ፡ ይሆናል ።



ጥያቄ ።

፶ ፡ ልቡናውን ፡ ሰብስቦ ፡ ለመጸለይ ፡ አልችለው ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ያፍ ፡ ጸሎቱን ፡ እንዲህ ፡ ከሆን ፡ ቢተ ወው ፡ ይሻላልን ፡ ወይስ ፡ ባይተወው ፡ ይሻላል ።

ምላሽ ።

፶፩ ፡ ይህንኑ ፡ ጥያቄ ፡ ለጠየቀው ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ አረጋዊው ፡ ሲመልስለት ፡ ዕውር ፡ ሰው ፡ በዘንጉ ፡ ምድር ፡ እየመታ ፡ ሲሄድ ፡ ከመንገድ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ እባብ ፡ ለጊዜው ፡ ድምፁን ፡ ሰምቶ ፡ ይመታኛል ፡ መስሎት ፡ እንደሚሸሽለት ፡ ሁሉ ፡ እንደዚህም ፡ ሁሉ ፡ አስተውሎ ፡ የማይጸልይ ፡ ሰው ፡ በአፉ ፡ ውስጥ ፡ የቃለ ፡ እግዚአብሔርን ፡ መንኲኳት ፡ እየሰሙ ፡ አጋንንት ፡ መሸሻቸው ፡ አይቀርምና ፡ ምንም ፡ ከቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ባይደርስ ፡ አጋንንትንም ፡ ማባረር ፡ ጥቅም ፡ ነውና ፡ ብዙ ፡ ከምትጸልየው ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ልብህ ፡ የሚወድቅ ባት ፡ ቃል ፡ ተጠሪቅማ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንድትደርስልህ ፡ ምንም ፡ ዝርወ ፡ ልብ ፡ ብት ሆን ፡ አፍህም ፡ ፍጥረቱ ፡ ነውና ፡ አንተው ፡ በዳይ ፡ አንተው ፡ አኩራፊ ፡ እንዳትሆን ፡ ባፍህም ፡ ብቻ ፡ ቢሆን ፡ መነጋገሩን ፡ አትተወው ።

፶፪ ፡ የምትጸልየውም ፡ ጸሎት ፡ አስቀድመህ ፡ በሕግ ፡ የታዘዘውን ፡ ጸሎት ፡ ሳታደርስ ፡ ወደ ፡ ትሩፋት ፡ ጸሎት ፡ አትለፍ ።

ዐይነቱም ፡ ይህ ፡ ነው ። ጌታ ፡ ያስተማረውን ፡ አጭሩን ፡ የአቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ ጸሎት ፡ የሚጸልይ ፡ ሰው ።

ወፍድፋዴ ፡ ጸሎትክሙስ ፡ ይኩን ፡ እመዝሙረ ፡ ዳዊት ፡ ተብሏልና ፡ ብሎ ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያትን ፡ ትቶ ፡ ዳዊትን ፡ ብቻ ፡ ቢደግም ፡ አሳብ ፡ የመለወጥ ፡ ጸሎት ፡ የማበላለጥ ፡ በመልካም ፡ አሳብ ፡ ኀጢአት ፡ ይሠራል ። በአቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ ላይ ፡ ዳዊትን ፡ ቢጨምር ፡ ግን ፡ ምግባር ፡ ትሩፋት ፡ ሁኖ ፡ ዋጋ ፡ ይሰጠዋል ።

እንደዚሁም ፡ ሁሉ ፡ ዳዊትና ፡ ሌሎችም ፡ የጸሎት ፡ መጻሕፍት ።

ድርሳነ ፡ ማሕየዊ ፡ የደገመ ፡ እንደ ፡ ዮሐንስ ፡ ይሆናል ።

ውዳሴ ፡ ማርያም ፡ የደገመ ፡ ራሱንና ፡ ሌላውንም ፡ ያድናል ። ቅዳሴ ፡ ማርያም ፡ የደገመ ፡ እንደ ፡ አባ ፡ ሳሙኤል ፡ ይሆናል ። ውዳሴ ፡ አምላክና ፡ ዕቀበኒን ፡ የደገመ ፡ ለንስሓ ፡ ሞት ፡ ይበቃል ። አርጋኖ ፡ የደገመ ፡ እንደ ፡ ጴጥሮስ ፡ እንደ ፡ ዮሐንስ ፡ ይሆናል ፡ የተባለውን ፡ ሰምቶ ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያትንና ፡ ዳዊቱን ፡ ትቶ ፡ እነዚህን ፡ ብቻ ፡ ቢጸልይ ፡ ባሳቡ ፡ ሕጉንና ፡ የሕጉን ፡ ጸሎት ፡ ትቶ ፡ እሊህን ፡ ጸሎታት ፡ እንደ ፡ መድኀኒት ፡ አድርጎ ፡ በምግባርና ፡ በሃይማኖት ፡ ሳይደክም ፡ በጥቂት ፡



ብልኀት ፡ ለመዳን ፡ መተንኰሉ ፡ ነውና ፡ ከሐናንያና ፡ ከሳፊራ ፡ ተንኰል ፡ ጋራ ፡ ይመሳሰልበታል ፡ እንጂ ፤ በጎ ፡ አሳብ ፡ አይሆንለትም ።

ስለዚህ ፡ የታዘዙትን ፡ ከአቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ ከዳዊት ፡ ላይ ፡ እየጨመረ ፡ ቢያደርሳቸው ፡ የተነገረውን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ያገኛል ፡ እንጂ ፡ ዳዊቱንና ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያትን ፡ ትቶ ፡ እነዚህን ፡ ብቻ ፡ አብዝቶ ፡ ጸሎት ፡ ቢያደርግ ፡ በዚህ ፡ አሳቡ ፡ በጽድቁ ፡ መግረፊያ ፡ ኀጢአት ፡ መሥራት ፡ ይሆንበታል ።

ይልቁንም ፡ ለነፍሱ ፡ ጥቅም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ፍቅር ፡ ሳይሆን ፡ ለዕድሜዬ ፡ መርዘሚያ ፡ ለንብረቱ ፡ መጥቀሚያ ፡ ለግዛቴ ፡ ማቅኛ ፡ ለጠላቴ ፡ መጉጃ ፡ እንዲሆነኝ ፡ ብሎ ፡ ማንኛውንም ፡ ጸሎት ፡ ቢሆን ፡ ለዚህ ፡ አሳብ ፡ ሲል ፡ ቢጸልየው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ምስጋና ፡ የኀጢአት ፡ መግረፊያ ፡ በማድረጉ ፡ ታላቅ ፡ ኀጢአት ፡ ሁኖ ፡ ያጠፋዋልና ፤ በምትጸልይበት ፡ ጊዜ ፡ ኀሡ ፡ መንግሥቶ ፡ ወጽድቆ ፡ የተባለውን ፡ የጌታን ፡ ቃል ፡ አትርሳው ። ባላጋራም ፡ ቢነሣብህ ፡ ከጁ ፡ ከተንኰሉ ፡ አድነኝ ፡ እያልክ ፡ ለምነው ፡ እንጂ ፡ አጥፋልኝ ፡ እያልክ ፡ ለፈጣሪህ ፡ ፍርድ ፡ አስተማሪ ፡ ቅጣት ፡ ሰንዛሪ ፡ አትሁን ።

፶፫ ፤ የጸሎት ፡ ማድረሻውን ፡ ሰዓት ፡ ከሰዓቱ ፡ ክፍል ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ እያደረግህ ፡ አድርሰው ፡

ለምትጸልየውም ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ጊዜ ፡ ማግኘ ትህ ፡ አብዛው ፡ አሳንሰው ፡ እንጂ ፡ የነግሁን ፡ የሠርኩን ፡ የሌሊቱን ፡ ጸሎት ፡ ግን ፡ ለሰው ፡ ከእግ ዚአብሔር ፡ መናገር ፡ የሚበልጥ ፡ ነገር ፡ ከነፍስ ፡ የሚበልጥ ፡ ጉዳይ ፡ የለበትምና ፡ ምንም ፡ ቢቸ ግርኽ ፡ አታስታጉለው ።

፶፬ ፣ የልቡናንም ፡ ጸሎት ፡ ያፍንም ፡ ጸሎት ፡ ቢሆን ፡ በምትጸልይበት ፡ ጊዜ ፡ ሰውነትህን ፡ ሁሉ ፡ በእ ንቀጸ ፡ ጸሎት ፡ ሠለስቱ ፡ ምእት ፡ እንዳዘዙት ፡ ዐይንህን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ በማንሣት ፡ እጅህን ፡ በመዘርጋት ፡ ጕልበትህን ፡ በማስተብረክ ፡ በማስ ገድ ፡ እግርህን ፡ በቁመት ፡ ወገብህን ፡ በመታ ጠቅ ፡ የጸሎትህንም ፡ ቦታ ፡ በመሰወር ፡ አድርገህ ፡ ጸልይ ፡ እንጂ ፡ ይህን ፡ የምትሠራበት ፡ ምግባል ፡ ቦታ ፡ ካልቸገረህ ፡ በቀር ፡ የአፍአውን ፡ ሰውነ ትህን ፡ አቦዝነህ ፡ በልብህና ፡ ባፍህ ፡ ብቻ ፡ አመስጋኝ ፡ አትሁን ፤ ሰውነትንም ፡ አቦዝኖ ፡ መጸለይ ፡ ቀላል ፡ ኀጢአት ፡ እንዳይመስልህ ፡ ካባቶቻችን ፡ በፍትሐ ፡ ነገ ፡ አን ፡ ፲ ፡ የእግዚአብ ሔርን ፡ ሥራ ፡ በቸልታ ፡ የሚሠራ ፡ ርጉም ፡ ይሁን ፡ የተባለውን ፡ አስተውልና ፡ ሌላውም ፡ ግብረ ፡ ጸሎት ፡ እንኳ ፡ ቢቸግርህ ፡ ካልታመምክ ፡ ወይም ፡ የማያስቆም ፡ የግድ ፡ ችግር ፡ ካላገኘህ ፡ በቀር ፡ እንደ ፡ ተሚዋች ፡ ተቀምጨ ፡ እግዚአብ ሔርን ፡ ልለምነው ፡ ብለህ ፡ አትዳፈረው ።



ሌላውም ፡ ጸሎት ፡ ቢቸግርህ ፡ በየሰዓቱ ፡ አንዳንድ ፡ አቡን ፡ ዘበሰማያትን ፡ አትንፈገው ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

ምኞት ፡ እንዳይለወጥ ፡ ሰው ፡ ባሳቡ ፡ እንዲ ጐዳ ፡ ባሳቡም ፡ እንዲጠቀም ፡ ማወቂያ ።

፶፭ ፣ የሰው ፡ መጠቀሚያውና ፡ የመጐጃው ፡ መሠ ረት ፡ አሳቡ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በሥራው ፡ አለመሆ ኑን ፡ ብዙ ፡ የሚያስረዳ ፡ ነገር ፡ አለልህና ፡ አስ ተውል ።

ሰው ፡ በጽድቁ ፡ መሠረት ፡ ኀጢአትን ፡ ይሠራል ። እንዲሁን ፡ ሥራ ፡ የሥራውን ፡ ዐይነት ፡ ሳይለውጥ ፡ ባሳቡ ፡ መለወጥ ፡ ብቻ ፡ ጽድቅና ፡ ኀጢአት ፡ የሚ ሆኑትንም ፡ አስተውል ።

፩ኛ ፣ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ የታዘዘውን ፡ ጸሎት ፡ ሰው ፡ በውቆለት ፡ እንዲያበላውና ፡ እንዲያ ከብረው ፡ ቢያደርግ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚገባ ውን ፡ ገንዘብ ፡ ለሱ ፡ ጥቅም ፡ ሸጦለታልና ፡ ኀጢ አት ፡ ይሆንበታል ።

ለሱ ፡ ጥቅም ፡ ባይሸጠው ፡ ግን ፡ ጽድቅ ፡ ይሆን ለታል ።

ሥራው ፡ ሳይለወጥ ፡ ባሳቡ ፡ መለወጥ ፡ ብቻ ፡ ይጐዳልና ፡ በዚህ ፡ አስተውል ።

፺፮ ፡ ምጽዋትንም ፡ መስጠቱ ፡ አንድ ፡ ሆኖ ፡ ሲሰጥ ፡ ምስጋና ፡ መሻትን ፡ አስቦ ፡ ሲሆን ፡ ከንቱ ፡ ይሆን በታል ፤ መመስገንን ፡ ሸሽቶ ፡ ሲሰጥ ፡ ለጽድቅ ፡ ይሆንለታል ።

፺፯ ፡ አለባበስም ፡ እንደዚሁ ፡ ሁሉ ፡ ሥራው ፡ አንድ ፡ ሆኖ ፡ ባሳብ ፡ ብቻ ፡ መለወጥ ፡ ያስፈርዳል ። አለባ በስም ፡ ኢታስተኀፍሮሙ ፡ ለነዳያን ፡ በበይነ ፡ ትፍሥሕትከ ፡ ያለውን ፡ አስቦ ፡ እንደሱ ፡ ባለመ ልበሳቸው ፡ የሚያዝኑ ፡ ሰዎች ፡ ኑረው ፡ እነሱን ፡ ላለማሳፈር ፡ ራሱንም ፡ በልብሱ ፡ ላለማኩራት ፡ ፍትወቱን ፡ በማንበቡ ፡ ደስ ፡ ለማሰኘት ፡ ሲል ፡ ዝቅተኛ ፡ ቢለብስ ፡ የሚያምር ፡ ምግብ ፡ መተው ፡ ጾም ፡ ሆኖ ፡ እንደሚጠቅም ፡ የሚያምረውንም ፡ ልብስ ፡ ስለዚህ ፡ አሳብ ፡ ሲል ፡ ቢተው ፡ ባለባ በሱ ፡ ጽድቅ ፡ ይሠራል ፤ ንቆ ፡ ኰርቶ ፡ ቀንቶ ፡ አኰርፎ ፡ እያለው ፡ ወራዳ ፡ ቢለብስ ፡ ኀጢአት ፡ ይሠራል ፤ ከቤቱ ፡ ያለውን ፡ የሱን ፡ ልብስ ፡ የለ በሱትን ፡ ሁሉ ፡ መናቁ ፡ ነውና ፡ ሳይቸግረው ፡ ኀጢአት ፡ ይሠራል ።

፺፰ ፤ አነጋገርም ፡ ቃሉም ፡ ሳይለወጥ ፡ በድምፅ ፡ ስልት ፡ ብቻ ፡ እየጐተተ ፡ ሲናገረው ፡ የንቀት ፡ እያጠበቀ ፡ ሲናገረው ፡ የድፍረት ፡ እየጮኸ ፡ ሲናገረው ፡ የብደት ፡ ሆኖ ፡ ሰው ፡ የሚያስቀይም ፡ ኀጢአት ፡ ይሆናል ፤ እየከፈለ ፡ ሲያወጣው ፡ እየመጠነ ፡ ሲናገረው ፡ የዕውቀትና ፡ ለሰው ፡



የሚጠቅም ፡ አጽዳቂ ፡ ቃል ፡ ይሆናል ። ራሱም ፡ እምቃልከ ፡ ትጸድቅ ፡ የተባለውን ፡ ያገኛል ። እያሳዘነ ፡ በቀስታ ፡ በፍራት ፡ ሲናገረው ፡ ሰውን ፡ እያሳዘነው ፡ ራሱን ፡ የሚጠቅምበትን ፡ ያገኛል ። የፈደሉ ፡ ስም ፡ ያንደበቱ ፡ አነጋገር ፡ ሳይለወጥ ፡ መጉጃውና ፡ መጠቀሚያው ፡ በድምፁ ፡ ስልት ፡ ብቻ ፡ መሆኑን ፡ አስተውል ።

ዐይነቱም ፡ ደኅናም ፡ አይደለህ ፡ ማለት ፡ ሲነግ ፡ ስድብ ፡ ሲለዝብ ፡ ጥያቄ ፡ በመሆኑ ፡ አስተውል ።

፺፱ ፤ አስተያየትም ፡ የቅንድቡ ፡ አገላለጥ ፡ አንድ ፡ ሲሆን ፡ ሲያጨነቅረው ፡ የሰው ፡ ንቀት ፡ ሲያስ ፈጥጠው ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ ሲያገላብጠው ፡ የቍጣ ፡ የብደት ፡ ሆኖበት ፡ ይጐዳበታል ።

መጥና ፡ ረግቶ ፡ ሲገልጠው ፡ የዕውቀትና ፡ የፍ ቅር ፡ ሆኖ ፡ ይጠቀምበታል ።

፻ ፤ ስለዚህ ፡ ሥራ ፡ ያሳብ ፡ ታዛዥ ፡ ነውና ፡ ሰው ፡ የሚጐዳበትም ፡ የሚጠቀምበትም ፡ እንደ ፡ አሳቡ ፡ ዐይነት ፡ መሆኑን ፡ ዕወቅና ፡ የምትሠራው ፡ ሁሉ ፡ ምክንያቱን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሆኑን ፡ ወይም ፡ ለስምና ፡ ለሰውም ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ ለነፍስህም ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ሥጋህ ፡ ምኞት ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ ከሥራህ ፡ በፊት ፡ የምትሠራበትን ፡ ምክንያት ፡ ልቡናህን ፡ መርምረህ ፡ የምትሠራለ ትን ፡ ባለቤቱን ፡ የምትሠራበትን ፡ ምክንያቱን ፡

እያወቅኸው ፡ ሥራ ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ እንስሳ ፡ በልማድህ ፡ ብቻ ፡ አትሥራ ።

ይህንም ፡ ለማስረዳት ፡ በአውሮፓ ፡ ክርስቶሳውያን ፡ የሚባሉ ፡ የሊቃውንት ፡ ማኅበር ፡ ሥራን ፡ ምኞቱ ፡ ይቀድሰዋል ፡ በማለት ፡ ተስማምተውበት ፡ ለማስረጃ ፡ መጽሐፍ ፡ ጽፈውለታል ፡ ይባላል ።

## ምዕራፍ ፡ ፯ ።

### ስላሳብ ፡ እንዳይባክን ፡ ምኞት ፡ እንዳይለዋወጥ ፡

# መሰብሰቢያ ።

፳፩ ፤ አሳብህ ፡ ብዙ ፡ የሚመኝ ፡ አንዱን ፡ ይዞ ፡ የማይሠራ ፡ ሲሆንብህ ፡ ሰይጣን ፡ በጎም ፡ ሥራ ፡ እንዳትሠራ ፡ ባለመሥራትህም ፡ እንዳትደነግጥበት ፡ መልካምን ፡ በማሳሰብ ፡ እየከለከለ ፡ በጥበብ ፡ ሰንሰለቱ ፡ እንዳሰረህ ፡ ዕወቅ ።

ስለዚህ ፡ አንተ ፡ አንድ ፡ ሁንህ ፡ አሳብህን ፡ ብዙ ፡ አታድርግ ።

የምትኖርበትን ፡ የማትለቀው ፡ አንድ ፡ ሥራ ፡ ያዝ ፡ እንጂ ፡ ምኞትህን ፡ በየቀኑ ፡ አትለዋውጠው ።

አንዱን ፡ መያዝ ፡ አንዱን ፡ መልቀቅ ፡ የብደትና ፡ የዝሙት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ ደግ ፡ አሳብ ፡ ቢሆን ፡ የዕውቀት ፡ ጠባይ ፡ አይደለም ፤ ስለዚህ ፡



ቀድሞ ፡ የጀመርከውን ፡ ትንሹን ፡ የበጎ ፡ ምኞትህን ፡ ሳትሠራው ፡ ደግሞ ፡ ሌላ ፡ ትልቅ ፡ አትመኝ ።

### ጥያቄ ።

፳፪ ፤ ምነው ፡ መልካምን ፡ አሳብ ፡ ቢመኙት ፡ ከመሥራት ፡ ይደርሳል ፡ እንጂ ፡ ለምን ፡ ይጐዳል ።

### ምላሽ ።

፳፫ ፤ ለሰብአ ፡ ዓለም ፡ የታዘዘውን ፡ ሳይሠራ ፡ የመናኒውን ፡ ሥራ ፡ ቢመኝ ፤ የቅርቡን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መሄድ ፡ ሳይሆንለት ፡ መልካም ፡ አሳብ ፡ ከሆነ ፡ ብሎ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መሄድ ፡ ቢመኝ ፤ እሱንም ፡ ሐሰተኛ ፡ ሐሳቡንም ፡ ሴሰኛ ፡ ያሰኝዋል ፡ እንጂ ፡ መልካም ፡ አሳብ ፡ ተብሎ ፡ ዋጋ ፡ አያሰጠውም ። የሚቻለውን ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ ቸል ፡ እያለ ፡ የማይሠራውን ፡ ማሰብ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ማላገጥ ፡ ነው ።

### ጥያቄ ።

፳፬ ፤ እዛዲያ ፡ ሰው ፡ ሳያስብ ፡ ሳይመኝ ፡ ለመኖር ፡ አይቻለው ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ያለ ፡ አሳብና ፡ ምኞት ፡ ነው ፡ የሚገባው ።

### ምላሽ ።

፳፭ ፤ ሰው ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሳለ ፡ ለሰብአ ፡ ዓለም ፡ የታዘዘውን ፡ ዠምሮ ፡ ጨርሶ ፡ እንዲሠራ ፡ እየተ

መኖ ፡ የሚጨርስበትን ፡ ቢያስብ ፡ የገፀመረውን ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ ሳይለቅ ፡ በዚያው ፡ ላይ ፡ የጐልበቱን ፡ ያኸል ፡ እየጨመረ ፡ ቢሄድ ፡ እገባቡ ፡ ነውና ፤ እግዚአብሔርም ፡ ይረዳዋል ፤ ሥራውንም ፡ ይጨርሰዋል ።

ጥያቄ ።

፳፯ ፤ ምነው ፡ እነሙሴ ፡ ጸሊም ፡ እነአትናስያ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ጥቂት ፡ እንኳ ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ ሳይገፀምሩ ፡ ትልቁን ፡ ሥራ ፡ ተመኝተው ፡ ወደ ፡ ምናኔ ፡ አልሄዱምን ፤ ትልቅ ፡ አሳብ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ይከለከላል ።

ምላሽ ።

፳፯ ፤ እነዚህንና ፡ እነዚህን ፡ የመሰሉን ፡ ሰዎች ፡ በእንዲህ ፡ ያለ ፡ ምኞት ፡ ማንቀሳቀሱና ፡ ማስጨረሱ ፡ ኀጢአተኞች ፡ የንስሓን ፡ ጥቅም ፡ እንዲያውቁ ። ጻድቃን ፡ በሥራ ፡ ብቻ ፡ እንጸድቃለን ፡ በማለት ፡ እንዳይመኩ ። ለእንዲህ ፡ ላለው ፡ ለሁለቱ ፡ አብነትና ፡ ትእምርት ፡ እንዲሆን ። እግዚአብሔር ፡ የቸርነቱን ፡ ታምራት ፡ ለማሳየት ፡ ሠራው ፡ እንጂ ፤ ጥቂትን ፡ ሥራ ፡ ሳይገፀምሩ ፡ ትልቅ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ አብነት ፡ አላደረጋቸውም ፤ እነሱም ፡ ቢሆኑ ፡ በዚያው ፡ በገፀመሩት ፡ በትልቁ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እየጨመሩ ፡ ስለ ፡ ጨረሱ ፡ ለትልቅ ፡ ንስሓ ፡ አብነት ፡ ሆኑ ፡ እንጂ ፡ የገፀመረውን ፡ ባልገፀመረው ፡ እየለወጠ ፡ ለሚሠራ ፡ አብነት ፡ አልሆኑም ።



የገፀመረውንስ ፡ በመተው ፡ በማለዋወጥ ፡ እንኳን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለባልንጀራም ፡ ቢሆን ፡ እንካ ፡ ብላ ፡ ብሎ ፡ አሳይቶ ፡ ለመቀበል ፡ እጁን ፡ ለመብላት ፡ አፉን ፡ ሲከፍት ፡ ቈይ ፡ ሌላ ፡ ትልቅ ፡ እሰጥሃለሁ ፡ ብሎ ፡ አሳይቶና ፡ አንጐቶ ፡ ስላሳፈረው ፡ አጣልቶ ፡ ይለያየዋል ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ አላዋቂ ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ ትንሹን ፡ ሲነሣው ፡ ትልቅ ፡ ይሰጠኛል ፡ ብሎ ፡ የሚጠብቅ ፡ ሰው ፡ አይገኝምና ።

ስለዚህ ፡ ትንሹን ፡ በጎ ፡ ሥራህን ፡ ሳትለቅ ፡ በዚያው ፡ ላይ ፡ ለመጨመር ፡ ትጋ ፡ እንጂ ፡ የያዝከውን ፡ ለመልቀቅ ፡ ያለዐቅምህ ፡ ለመመኘት ፡ ምክንያትና ፡ ጥቅስ ፡ አትፈልግ ።

ጥያቄ ።

፳፰ ፤ ያሳብ ፡ መለዋወጥ ፡ ከምን ፡ ይነሣል ።

ምላሽ ።

፳፰ ፤ አሳብ ፡ ካንድ ፡ ቦታ ፡ አልቆምም ፡ የሚለው ፡ የእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ በመለየቱ ፡ ምክንያት ፡ ነው ። ረድኤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ባልተለየ ፡ ጊዜ ፡ ከልብህ ፡ ውስጥ ፡ የሚቀመጠው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የንፍስን ፡ የልጓም ፡ ዛብ ፡ ይዞ ፡ ባንድ ፡ መንገድ ፡ ያስኬዳታል ።

ረድኤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ በተለየ ፡ ጊዜ ፡ ዛቡን ፡ ይዞ ፡ ስትፈራ ፡ እያዳፈረና ፡ እያተጋ ፡ እሚያስ ኬዳት ፡ ባለቤት ፡ ታጣና ፡ በዚህ ፡ ብሄድ ፡ እውሬ ፡ ያገኘኛል ፡ በዚህ ፡ ብሄድ ፡ ጠላት ፡ ያገኘኛል ፡ እንዲህ ፡ ብናገር ፡ እንዲህ ፡ ይመስልብኛል ፡ እን ዲህ ፡ ብሠራ ፡ እንዲህ ፡ ይጠፋብኛል ፡ እያለ ፡ አሳቦቹ ፡ ሁሉ ፡ የተተካከሉ ፡ ጌቶቼ ፡ ሁነው ፡ ሁሉም ፡ አዛዦቼ ፡ ይሆኑብትና ፡ ዙሪያው ፡ ገደል ፡ ሆኖበት ፡ የሚፈራ ፡ አንድም ፡ የማይሠራ ፡ ይሆናል ።

ዘክልኤ ፡ ልቡ ፡ ህጉእ ፡ ውእቱ ፡ የተባለው ፡ ይደርስበታል ፤ በገበታ ፡ ላይ ፡ ተይዞ ፡ እንደሚወ ዛወዝ ፡ ውሃ ፡ አሳቡም ፡ በየቦታው ፡ ሁሉ ፡ ፈሶ ፡ እሱም ፡ ተዋርዶና ፡ ረክሶ ፡ ይቀራል ።

ጥያቄ ።

፹ ፤ እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ ሰው ፡ አሳቡም ፡ አንድ ፡ እንዲ ሆን ፡ በዚያው ፡ እንዲጸና ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ ይሻለዋል ።

ምላሽ ።

፹፩ ፤ መጀመሪያ ፡ ያሰበውን ፡ እሚያዘልቀው ፡ ሲ ሆን ፡ ቶሎ ፡ ሳይለውጥ ፡ ጠንክሮ ፡ ካሳቡ ፡ ጋራ ፡ ይከራከር ፡ በግድ ፡ ሊለወጥ ፡ የሚገባ ፡ የተለወ ጠውም ፡ አሳብ ፡ የሚሻልና ፡ የሚበልጥ ፡ ሲሆን ፡ የፊቱ ፡ የሰይጣን ፡ የኋላው ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ምልክት ፡ መሆኑ ፡ ነውና ፡ በመሻሉ ፡ ለው



ጠው ። የሁለቱም ፡ ጥቅምና ፡ ጉዳት ፡ ተካክሎ ፡ ሲታይ ፡ እግዚአብሔር ፡ በማትያስ ፡ መመረጥ ፡ ጊዜ ፡ በሐዋርያት ፡ ጎሊና ፡ እንዳደረገው ፡ መም ረጥን ፡ ለሱ ፡ እንድትሰጠው ፡ ሲሻብህ ፡ ነውና ፡ በጸሎትህ ፡ ለምነህ ፡ በዕጣ ፡ ቍረጠው ።

ብዙም ፡ ሐሳብ ፡ ተንሥቶ ፡ ሲያስቸግርህ ፡ በብዙ ፡ ዕጣ ፡ ቍረጠውና ፡ በቈረጥኸው ፡ ሐሳብ ፡ ክፉም ፡ ቢያገኝህ ፡ እግዚአብሔር ፡ የፈረደብህ ፡ መሆኑን ፡ ዐውቀህ ፡ በትዕግሥት ፡ ተቀበለው ፤ በጎም ፡ ቢያ ገኝህ ፡ እሱን ፡ አመስግነህ ፡ ተቀበለው ።

ይህን ፡ ካላደረግህ ፡ ግን ፡ ከሁለቱ ፡ ዐይነት ፡ አሳብ ፡ በላይ ፡ ያለው ፡ አሳብ ፡ ለማስጨነቅና ፡ ተስፋ ፡ ለማስቈረጥ ፡ ከሰይጣን ፡ የሚመጣብህ ፡ ጾር ፡ ነውና ።

ዘወትር ፡ ጸሎትህ ፡ ምርሐኒ ፡ እግዚኦ ፡ ፍኖተ ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ እሖውር ፡ እያልክ ፡ ቈራጥ ፡ ልቡ ናን ፡ ከፈጣሪ ፡ ለምን ።

ጥያቄ ።

፹፪ ፤ ሥራን ፡ ማለዋወጥ ፡ ምኞት ፡ ማብዛት ፡ ማለት ፡ እንዴት ፡ ነው ።

ምላሽ ።

፹፪ ፤ ሰው ፡ የሚመኘውም ፡ የሚለዋውጠውም ፡ ከቍጥር ፡ የበዛ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ለመቍጠር ፡ አይቻ

ልም ፡ በጥቂቱ ፡ ዐይነቱን ፡ ለማወቅ ፡ ግን ፡ በዓለም ፡ የሚሠራውን ፡ በፍትወቱ ፡ የሚታገሠውን ፡ የንጽሕ ፡ ሥጋን ፡ ሥራ ፡ ሳይሠራ ፡ ባንደበት ፡ በሚናገረው ፡ የእርምምን ፡ ማጽናት ፡ ሳይገዛ ፡ በጕልበቱ ፡ የሚሠራውን ፡ ቁመቱን ፡ ስግደቱን ፡ ትግሀ ፡ ጸሎቱን ፡ ይህን ፡ የእፍአውን ፡ ጕልሑን ፡ ትእዛዝ ፡ ሳይሠራ ፡ ውሳጣዊውን ፡ ረቂቁን ፡ ሥራ ፡ የንጽሕ ፡ ነፍስን ፡ ሥራ ፡ ልሥራ ፡ የሚልና ፡ የሚያስብ ፡ ባሳብ ፡ ሲሰን ፡ ሰይጣን ፡ ያሸንፈው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሁሉንም ፡ የሚሠራ ፡ አለመሆኑ ፡ ይታወቃል ። በሥጋው ፡ አዳር ፡ ቢሆን ፡ እንዱን ፡ ዐይነት ፡ ዠምሮ ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ የሚዞር ፡ ባካና ፡ ይሆንና ፡ ማናቸውም ፡ ንብረት ፡ ሳይሞላለት ፡ የምኞት ፡ ብዛት ፡ እባክና ፡ እንትቶ ፡ እስከ ፡ ጥፋት ፡ ያደርሰዋል ።

ጥያቄ ።

፸፱ ፤ ሐሳብ ፡ እንደ ፡ እንደበት ፡ በከንፈር ፡ እንደ ፡ ዐይን ፡ በቅንድብ ፡ እንደ ፡ ዠሮ ፡ በጣት ፡ አይዘጋ ፤ መንፈሳዊውንም ፡ በብዙ ፡ እየመረመረ ፡ ሥጋዊውንም ፡ በብዙ ፡ እየፈለሰፈ ፡ ሲያስቸግር ፡ በምን ፡ መወሰን ፡ ይሻላል ።

ምላሽ ።

፸፱ ፤ አሳብ ፡ ረቂቅ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የነፍሳችን ፡ እንጂ ፡ የሥጋችን ፡ ሥራ ፡ አይደለምና ፤ በግዙፍ ፡ ሥጋ



ችን ፡ ልንዘጋው ፡ የማንችል ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ መግዘሪያው ፡ ሁሉ ፡ ወደሚቻለው ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚቻለውን ፡ የምሠራውን ፡ አሳስበኝ ፡ የተበተነውን ፡ የሚባክነውን ፡ ሐሳብ ፡ ወስንልኝ ፡ ብለህ ፡ ለምነው ።

ሁለተኛ ፡ አሳብህን ፡ ሥራህ ፡ እንደሚወስንልህ ፡ እጅህን ፡ የሥራ ፡ ትጋት ፡ ሳንደበትህ ፡ የጸሎት ፡ ወይም ፡ የዜማ ፡ ወይም ፡ የፍርድ ፡ ጣዕም ፡ አስለምደው ፡ ይህ ፡ ሁለቱ ፡ የሐሳብህን ፡ መባክን ፡ ይወስንልሃል ።

ሥራውንም ፡ ጸሎቱንም ፡ እየከለከለ ፡ ሐሳብ ፡ ብቻ ፡ ሲበዛብህ ፡ ግን ፡ የአጋንንት ፡ ጾር ፡ መሆኑ ፡ ነውና ፡ አማትብባቸውና ፡ ርኩሳን ፡ ወውዱቃን ፡ አጋንንት ፡ ረሐቁ ፡ እምኔየ ፡ በኀይለ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አምላኪየ ፡ ብለህ ፡ በስሙ ፡ አብርራቸው ፤ ስለ ፡ ክፉ ፡ ሐሳብም ፡ አጋንንትን ፡ ረግሞ ፡ ማማተብ ፡ የሚገባ ፡ መሆኑን ፡ ፊልክስዩስ ፡ አስተውል ።

ጥያቄ ።

፹ ፤ አጋንንት ፡ በሐሳብ ፡ ብዛት ፡ የሚዋጉን ፡ በማንኛው ፡ ኀጢአት ፡ እንድንጕዳላቸው ፡ ነው ።

ምላሽ ።

፹ ፤ ሐሳብ ፡ ሲበዛ ፡ በናላ ፡ ላይ ፡ ትንሽ ፡ ትልቁ ፡ ተንባብሮ ፡ ይሰፍርበትና ፡ ናላችን ፡ እንደ ፡ ቤት ፡

እንደ ፡ ወረቀት ፡ ነፍሳችን ፡ እንደ ፡ ጸሓፊ ፡ እንደ ፡ ባለቤት ፡ ስለ ፡ ሆነች ፡ ነፍስ ፡ ከወረቀት ፡ ናላዋ ፡ ላይ ፡ የጸፈችውን ፡ የውጭ ፡ አካሏን ፡ እያዘዘች ፡ በሥራ ፡ ስታወጣው ፡ አንባብራ ፡ ያስቀመጠችው ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ ነፍስ ፡ የራሷን ፡ ዕውቀት ፡ ትጋት ፡ የምትሥልበት ፡ ስሌዳ ፡ ዕውቀቷን ፡ የምታስቀምጥበት ፡ ቦታ ፡ ታጣና ፡ ዝንጉ ፡ ሰነፍ ፡ አላዋቂ ፡ ሁና ፡ መጐዳቷን ፡ ይህን ፡ የባሕርያችንን ፡ ጥበብ ፡ አጋንንት ፡ በሞት ፡ ሳይጐድሉ ፡ በእርጅና ፡ ሳይዘነጉ ፡ ከአዳም ፡ እስካሁን ፡ ጠባያችንን ፡ የሚያውቁ ፡ አብረውን ፡ የሚኖሩ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ የሐሳብ ፡ ብዛት ፡ አስንፎ ፡ አጅሎ ፡ አጥብቆ ፡ እንዲጐዳን ፡ ያውቃሉና ፡ ክብረት ፡ ልጨምር ፡ ገንዘብ ፡ ላጠራቅም ፡ ቤት ፡ ላሳምር ፡ የሚል ፡ ብልጥን ፡ ሰው ፡ አሳብ ፡ በማብዛት ፡ በሥራ ፡ ማዋተት ፡ ድል ፡ ነሥተው ፡ ይጐዱታል ።

ሰው ፡ ሳስተምር ፡ መጽሐፍ ፡ ልመርምር ፡ የሚልን ፡ ብልኅን ፡ ሰው ፡ ወሰን ፡ አሳልፈው ፡ ምስጢር ፡ አስመርምረው ፡ ይጐዱታል ።

ንግግር ፡ አሳምሬ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ አሳድሬ ፡ እኔ ፡ ከብሬ ፡ ልኑር ፡ ለሚል ፡ ጕጉን ፡ ሰው ፡ ነገር ፡ በማስላት ፡ ጭንቀት ፡ በማብዛት ፡ ይጐዱታልና ፡ ስለ ፡ ዚህ ፡ ሰይጣን ፡ ብርቱን ፡ ሰው ፡ ድል ፡ የሚነሣበት ፡ የያዘውን ፡ ነገር ፡ አለልክ ፡ እያሠራ ፡ ነውና ፡ ስለ ዚህ ፡ ጌታ ፡ በወንጌል ፡ በሚያስጨንቅ ፡ አሳብ ፡



አትዋለሉ ፡ ያለውን ፡ ከልቡ ፡ አጠፍተው ፡ እንዱን ፡ ሳይሠሬ ፡ በብዙ ፡ አባክነው ፡ በሁለቱም ፡ ዓለም ፡ የማይጠቀም ፡ አድርገው ፡ በነፍሱና ፡ በሥጋው ፡ ይጐዱታል ።

ይህንንም ፡ ልትረዳ ፡ ብትሻ ፡ በሐሳብ ፡ ብዛት ፡ የተጐዱትን ፡ አስተውል ።

ምርምር ፡ ማሳበዱን ፡ በነአርዮስ ፡ በንስጥሮስ ፡ ታሪክ ፡ ብልጠት ፡ ማሳበዱን ፡ በነዊልሶን ፡ በነዘርቡደኬ ፡ ታሪክ ፡ ግዛት ፡ ማሳበዱን ፡ የየነገሥታቱን ፡ ሁሉ ፡ የመጨረሻቸውን ፡ ታሪክ ፡ አስተውል ።

ስለዚህ ፡ የሰውን ፡ ባሕርይ ፡ የሚያውቀው ፡ ጌታም ፡ በወንጌል ፡ በሚያስጨንቅ ፡ ሐሳብ ፡ አትዋለሉ ፡ ብሎናልና ፡ ሐሳብ ፡ አናብዛ ።

ጥያቄ ።

፫፰ ፡ መላና ፡ ምርምር ፡ አሳብ ፡ ምክር ፡ የሚያበዛ ፡ ሰው ፡ ጠንቃቃ ፡ ሁኖ ፡ ንብረቱንና ፡ ሕይወቱን ፡ ይጠብቃል ፡ ብልኅም ፡ ተብሎ ፡ ይከበራል ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ጉዳት ፡ ይደርስበታል ።

ምላሽ ።

፫፰ ፡ የሕይወትና ፡ የንብረት ፡ ጥቅም ፡ ባንዱ ፡ ቁርጦ ፡ ቢሠራበት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አንዱን ፡ ሳይሠራ ፡ ብዙ ፡ የሚያስብስ ፡ ሃይማኖት ፡ የሌለው ፡ ጅል ፡

ይባላል ፡ እንጂ ፡ እንኳን ፡ ብልኅ ፡ ብልጥም ፡ የዋ
ህም ፡ መባል ፡ አይገባውም ።

ጥያቄ ።

፹ ፡ ያለፈውን ፡ እየመረመረ ፡ እየመላለሰ ፡ የሚመ
ጣውን ፡ እያማረጠ ፡ መላ ፡ እየጣለ ፡ ማመዛዘኑ ፡
አላዳርሰው ፡ ብሎት ፡ ባይሠራስ ፡ እንዴት ፡ ጅል ፡
ይባላል ።

ምላሽ ።

፹፩ ፡ ጅል ፡ ስላለማወቁ ፡ ክፉም ፡ በጎም ፡ የማይ
ሠራ ፡ ስም ፡ ነው ። ብልጥ ፡ የሚያየውን ፡ ዓለመ ፡
ምድር ፡ ከሚሰማው ፡ ዓለመ ፡ ሰማይ ፡ አብልጦ ፡
እያከበረ ፡ ነፍሱን ፡ ለሥጋው ፡ እያስገዛ ፡ ለሥጋ
ውም ፡ ብቻ ፡ የሚሠራ ፡ ነው ።

ብልኅ ፡ የሚባልም ፡ አይቶ ፡ በማስተዋሉ ፡ የዓለ
ምን ፡ ከንቱነት ፡ የመረመረ ፡ የሚያየውን ፡ ምድ
ራዊ ፡ ዓለምን ፡ ንቆ ፡ የሚሰማውን ፡ ሰማያዊ ፡ ዓለ
ምን ፡ አክብሮ ፡ መልካም ፡ የሚሠራ ፡ ነው ።

ብዙ ፡ የሚያውቅና ፡ ብዙ ፡ የሚያስብ ፡ ግን ፡ እንዲ
ረዳው ፡ ባምላኩ ፡ አምኖ ፡ ባንዱ ፡ ቈርጦ ፡ የማይ
ሠራ ፡ እንዲህ ፡ ባደርግ ፡ እንዲህ ፡ ይመስልብኛል ፡
እያለ ፡ ላሰበው ፡ ሚዛን ፡ የሚሆን ፡ ደግሞ ፡ ሌላ ፡
ሐሳብ ፡ እያመጣ ፡ እንደ ፡ ልጆች ፡ ካብ ፡ ሐሳቡን ፡
በሐሳቡ ፡ እያፈረሰ ፡ በገዛ ፡ ራሱ ፡ ጕዳይ ፡ የሚጫ



ወትስ ፡ ሌላ ፡ እምጠራበት ፡ ስም ፡ ባጣ ፡ ባለመሥራት ፡
ከጅሉ ፡ ስለ ፡ ተመሳሰለ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ጅል ፡ ይባላል ፡
ያልኩህ ፡ እያወቀ ፡ ሐሳቡን ፡ እያባከነ ፡ ልቡን ፡
እያዋለለ ፡ አንድ ፡ ሥራ ፡ ሳይዝ ፡ በሐሳብ ፡ ብቻ ፡
የሚኖር ፡ ሰው ፡ ያዋቂ ፡ በዳይ ፡ ነውና ፡ እንዲያ
ውም ፡ ከጅል ፡ ይብሳል ፡ (ስላባት ፡ እናት ፡ ፴፩ ፡
፶፫ ፡ ምዕ ። ጣፋጭ ፡ ጥበብ ፡ ገጽ ፡ ፶) ፡ እይ ።

ምዕራፍ ፡ ፯ ።

## ስለ ፡ ምጽዋት ።

፹፪ ፡ ምጽዋት ፡ አስጣጥህ ፡ ለዚህ ፡ ዓለም ፡ ኑሮ ፡
የተቈረጠ ፡ የልክ ፡ ደንብ ፡ ካላበጀህለት ፡ ለመመ
ጽወት ፡ ሰይጣን ፡ በልቡናህ ፡ ያድርና ፡ መንፈሳ
ዊ ፡ ሐሳብ ፡ አስመስሎ ፡ ቅድመ ፡ አሠኒ ፡ ለሰብእ ፡
ቤትከ ፡ እያለ ፡ እነሱን ፡ ምክንያት ፡ እያደረገ ፡
ከመመጽወት ፡ አግዶ ፡ ከገሃነም ፡ አውርዶ ፡ እን
ዳይጐዳህ ፡ ለዚህ ፡ ዓለም ፡ ኑሮህ ፡ አንተ ፡ ሳት
ሻው ፡ እግዚአብሔር ፡ የሰው ፡ ምሪት ፡ ቢመራ
ብህ ፡ ልጅና ፡ ዘመድም ፡ አሽከርና ፡ ገረድም ፡
ቢሆን ፡ በሱ ፡ ፈቃድ ፡ የተመሩብህ ፡ መሆና
ቸው ፡ ነውና ፡ እግዚአብሔር ፡ ምድርንም ፡ ሰው
ንም ፡ እያዘዘ ፡ አስጣጡን ፡ ባመት ፡ ባመት ፡
ማድረጉ ፡ ካመት ፡ ወዲያ ፡ ያለን ፡ የትዳር ፡ ሐ

ሳብ ፡ ሲከለክለን ፡ ነውና ፡ ባመት ፡ ባመት ፡ የሚሰጥህን ፡ ገንዘብ ፡ ተርበው ፡ እንዳያዝኑ ፡ ጠግበው ፡ እንዳይበድሉ ፡ አድርገህ ፡ በልካቸው ፡ መዝነህ ፡ ሳመት ፡ የሚያስፈልጋቸውን ፡ አስልተህ ፡ አስቀርተህ ፡ ካመት ፡ የሚተርፈውን ፡ ቶሎ ፡ ስጠው ፡ መጽውተው ፡ እንጂ ፡ እነሱን ፡ ምክንያት ፡ አድርገህ ፡ ደግሞ ፡ በሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ እታቈየው ።

ጥያቄ ።

፹፫ ፡ ምነው ፡ ለመጋቢነት ፡ የተመረጠው ፡ ዮሴፍ ፡ የሰባት ፡ ዓመቱን ፡ እኽል ፡ አጠራቅሞ ፡ ለሰባት ፡ ዘመኑ ፡ ረኃብ ፡ በማድረጉ ፡ አስመስግኖት ፡ የለም ፡ ለሰው ፡ ብሎ ፡ ማጠራቀምማ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ኀጢአት ፡ ይሆናል ።

ምላሽ ።

፹፬ ፡ ይህ ፡ የተሠራው ፡ እንኳን ፡ እኽልን ፡ ጣዖት ፡ ለሚያመልኩ ፡ አሕዛብ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መጋቢነት ፡ ለሚያምኑ ፡ ክርስቲያን ፡ አለመሆኑን ፡ ልብ ፡ አድርግ ።

ክርስቲያን ፡ እንዲህ ፡ ቢያደርግ ፡ ያስቀመጥኩት ፡ ገንዘብ ፡ ከችግር ፡ ያድነኛል ፡ በማለቱ ፡ ጣዖት ፡ ማምለኩ ፡ ነው ።

ያውም ፡ ዮሴፍ ፡ ቢሆን ፡ ከሕዝብ ፡ ሰብስቦ ፡ ለሕዝብ ፡ መልሶ ፡ ሰጠ ፡ እንጂ ፡ እንኳን ፡ ሊያመል



ከው ፡ ለራሱ ፡ ገንዘብ ፡ አለማድረጉን ፡ ሰባቱን ፡ ጥጋብ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ሰባቱን ፡ ረኃብ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ አድርጎ ፡ መዝኖ ፡ በተገለጸለት ፡ የሰባቱን ፡ ዘመን ፡ ለሰባቱ ፡ ዘመን ፡ አካፈለ ፡ እንጂ ፡ አስቀመጠው ፡ አመለከው ፡ አይባልም ። አንተ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ዮሴፍ ፡ የሚመጣው ፡ ዘመን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ሳይገለጥልህ ፡ ከንጉሥ ፡ ሳትታዘዝ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰብል ፡ አጥፍቶ ፡ እንተንም ፡ የምትሰጣቸው ፡ አሳጥቶ ፡ ሊቀጣቸው ፡ ከፈለገ ፡ አንተ ፡ አስቀምጠህ ፡ የኔን ፡ ቅጣት ፡ ካልከለከልህ ፡ ብሎ ፡ አይፈርድብህምና ፡ ካመት ፡ ወዲያ ፡ ለሚሆን ፡ ነገር ፡ አታስብላቸው ፡ እንዲህ ፡ ያደረግህ ፡ እንደሆነ ፡ ለእመ ፡ ተርፈከ ፡ እመፍቅደ ፡ ዕለት ፡ ሀቦ ፡ ለነዳይ ፡ ወነዐ ፡ በሞገስ ።

በአሪት ፡ ለኅድገተ ፡ ዓመት ፡ የተሰጠው ፡ ተስፋ ፡ ይፈጸምልሃል ፡ የተባለውን ፡ ክብር ፡ ታገኛለህ ።

ጥያቄ ።

፹፭ ፡ በያመቱ ፡ የሚገኘውንስ ፡ የሰብሉን ፡ ችሮታ ፡ እንደዚሁ ፡ ቢያደርጉት ፡ ይቻላል ፡ ነግዶ ፡ ሠርቶ ፡ ወይም ፡ ለቀረጥ ፡ ለግብር ፡ አጠራቅሞ ፡ በብዙ ፡ ቀን ፡ የሚጠራቀመውን ፡ ገንዘብስ ፡ እስከ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ አቈይቼ ፡ በምን ፡ ጊዜ ፡ ልጨርሰው ፡ ይገባል ።

### ምላሽ ።

፹፮ ፡ ኑሮህ ፡ ብፁዓን ፡ ነዳያን ፡ እንደ ፡ ተባሉት ፡ ሁኖ ልህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለልብስህ ፡ መግግ ፡ የሚበቃ ፡ ገንዘብ ፡ እስከታገኝ ፡ ሠርተህ ፡ ነግደህ ፡ አጠራቅ መህ ፡ ለሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ የሚሆንህን ፡ ግዛና ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ያለውን ፡ ስጠው ፡ መጽውተው ። ኑሮህ ፡ ብፁዓን ፡ መሐርያን ፡ ከተባሉት ፡ ሁኖ ፡ ከሰው ፡ አሳዳሪዎችና ፡ ከሀብታሞች ፡ ወገን ፡ ሲሆ ንብህ ፡ ክብረትና ፡ መስጠትን ፡ እንድ ፡ ላይ ፡ ለማ ኖር ፡ እጅግ ፡ ብርቱ ፡ ጦር ፡ አለበትና ፡ ጠንክረህ ፡ ተዋግተህ ፡ ብልጠትን ፡ አሸንፈህ ፡ ለብልኀት ፡ ተሸንፈህ ፡ በገንዘብህ ፡ ላይ ፡ የዋህ ፡ ቸር ፡ ብልኀ ፡ መሐሪ ፡ ሁንና ፡ በሰው ፡ እያመካኘህ ፡ ለራስህ ፡ ሳታደላ ፡ ላንተም ፡ ለቤተ ፡ ሰብህም ፡ ወይም ፡ ባሳብህ ፡ ለምታሳድረው ፡ ሰው ፡ የሚበቃህን ፡ ያኽል ፡ እስከምታገኝበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ያንኑ ፡ የሚበቃህን ፡ ሰብስበህ ፡ ያገኘኸውን ፡ ገንዘብ ፡ የምትሰጠውም ፡ ሰው ፡ ተበላልጦ ፡ በሚሰበሰበ ውም ፡ ገንዘብ ፡ ማነስ ፡ ለከንቱ ፡ ሥራ ፡ ወጪ ፡ በማብዛት ፡ ሰው ፡ እንዳይጐዳብህ ፡ በጥንቃቄ ፡ እያሰ ብህ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ከሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ ተርፎ ፡ የመጣውን ፡ ገንዘብ ፡ እንደ ፡ ትርፍ ፡ ገንዘብ ፡ ቈጥ ረህ ፡ ገንዘቡ ፡ የሰው ፡ ማሳደሪያ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ አማ ካሪ ፡ አብጅተህ ፡ በቃል ፡ ብዛት ፡ አስጣጥና ፡ አስ ባሰቡን ፡ ቍረጠውና ፡ የተወሰነውን ፡ ስጠው ፡ መ



ጽውተው ። ከባንክና ፡ ከትርፍ ፡ የጋራም ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ የሚሠራበትን ፡ ገንዘብህን ፡ ዋናውን ፡ እን ደ ፡ ምድር ፡ ወለዱን ፡ እንደ ፡ ሰብል ፡ አድርገህ ፡ እንደ ፡ ፹፮ ፡ ቍ ፡ እያደረግህ ፡ ስጠው ።

### ጥያቄ ።

፹፯ ፤ ይህ ፡ ደመ ፡ ነፍስ ፡ ለሌለበት ፡ የብር ፡ የወርቅ ፡ የዕቃ ፡ ገንዘብ ፡ ሲሆን ፡ ነው ፡ ደመ ፡ ነፍስ ፡ ያለበ ትንስ ፡ የእንስሳትን ፡ ችሮታ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ላድር ገው ።

### ምላሽ ።

፹፯ ፤ አራሽ ፡ ባላገር ፡ ስትሆን ፡ ከእንስሳት ፡ ወገን ፡ በ ያይነቱ ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡ ካገኘህ ፡ ከዚያ ፡ በላይ ፡ ያለውን ፡ እንደ ፡ ትርፍ ፡ ቈጥረህ ፡ ስጠው ፤ ነጋዴም ፡ ስትሆን ፡ የምትነግድበትን ፡ ገንዘብና ፡ ከብት ፡ ዋናውን ፡ ሳታጠፋ ፡ ትርፉ ፡ ላመት ፡ ልብስና ፡ ቀ ለብ ፡ ከነቤተ ፡ ሰቦችህ ፡ የሚበቃህን ፡ ካገኘህ ፡ በ ኋላ ፡ ከዚያ ፡ በላይ ፡ ያለውን ፡ ከብቱንም ፡ ለከብቱ ፡ ማፈራረቂያ ፡ ላንድ ፡ ጭንት ፡ በጥፍ ፡ አስበህ ፡ ከዚያ ፡ በላይ ፡ ያለውን ፡ እንደ ፡ ትርፍ ፡ ቈጥረህ ፡ ስጠው ።

ሰው ፡ አሳዳሪም ፡ ጌታ ፡ ስትሆን ፡ ለምታሳድረው ፡ ሰው ፡ የሚሜኑትንም ፡ የሚበሉትንም ፡ እንስሶች ፡ ከየመሰላቸው ፡ ሲጐድሉ ፡ እንዲተካኩ ፡ በሚበቃህ ፡

ልክ ፡ ዕጥፍ ፡ አድርገህ ፡ ገምተህ ፡ አስቀርተህ ፡ የቀረውን ፡ ስጠው ፡ መጽውተው ። መፍቅደ ፡ ዕለትንም ፡ መናንያን ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ሰብአ ፡ ዓለም ፡ ባመት ፡ ባመት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የሚቀበሉት ፡ ትራፊያቸውን ፡ ይስጡ ፡ ማለት ፡ ነውና ፡ የምጽዋት ፡ ወጣኒ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ሰው ፡ ገንዘቡን ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ይመጽውት ።

ጥያቄ ።

፹፱ ፡ መነኰሴ ፡ ከዕለት ፡ ምእመን ፡ ካመት ፡ ምግባቸው ፡ የተረፋቸውን ፡ ከሰጡ ፡ ለምን ፡ ወጣኒ ፡ ይባላሉ ፡ ፍጹማን ፡ አይባሉምን ።

ምላሽ ።

፺ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ እየጠበቁ ፡ የተረፋቸውን ፡ የሰጡ ፡ ብንሰጥ ፡ ይሰጠናል ፡ ብለው ፡ በቸርነቱ ፡ ያመኑ ፡ ናቸውና ፤ ያሰጣጥን ፡ ዘዴና ፡ የሚጠቅማቸውን ፡ ትርፍ ፡ ዐዋቂዎች ፡ ይባላሉ ፡ እንጂ ፡ የሚሰጡት ፡ ከአፍኣ ፡ ያገኙትን ፡ ጸጋ ፡ ገንዘባቸውን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የባሕርይ ፡ ገንዘብ ፡ የሆነ ፡ አካላቸውን ፡ አልሰጡምና ፡ ፍጹማን ፡ አይባሉም ።

ጥያቄ ።

፺፩ ፡ የሰው ፡ ምጽዋት ፡ ፍጹም ፡ የሚሆንለት ፡ ምን ፡ ሲሰጥ ፡ ነው ።



ምላሽ ።

፺፪ ፡ ለሰው ፡ የባሕርይ ፡ ገንዘቡ ፡ አካሉ ፡ ነውና ፡ ፍጹም ፡ የሚያሰኘው ፡ ሰው ፡ አካሉን ፡ ሲመጸውት ፡ ነው ።

ጥያቄ ።

፺፫ ፡ ሰው ፡ አካሉን ፡ እየቈረጠ ፡ አይሰጥ ፡ የአካል ፡ ስጦታ ፡ ማለት ፡ ደግሞ ፡ ምድነው ።

ምላሽ ።

፺፬ ፡ ለሚያደርግለት ፡ ሰው ፡ ባደርግለት ፡ ያደርግልኛል ፡ ብሎ ፡ ሳይታመንበት ፡ ጕልበት ፡ ያለው ፡ ወዙ ፡ እስኪፈስ ፡ ወንድሙን ፡ ለመርዳት ፡ ቢደክም ።

ሁለተኛ ፡ አእምሮ ፡ ያለው ፡ ወንድሙ ፡ ዐውቆ ፡ እንደሱ ፡ እስኪሆን ፡ ድረስ ፡ ለመምከር ፡ ለማስተማር ፡ ቢደክም ፡ ፈጣሪው ፡ አዋሕዶ ፡ የሰጠውን ፡ የባሕርይ ፡ ገንዘቡን ፡ ከአካሉ ፡ እየቈረጠ ፡ መስጠቱ ፡ ነውና ፤ ፍጹም ፡ ቸር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ምጽዋቱም ፡ ፍጹም ፡ የሚባለው ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው ፡

ጥያቄ ።

፺፭ ፡ ሰው ፡ አገልግሎ ፡ ለፍቶ ፡ ወዙን ፡ አፍሶ ፡ ሠርቶ ፡ ያገኘውን ፡ ገንዘብ ፡ ቢመጸውት ፡ የባሕርይ ፡ ገንዘቡን ፡ መስጠት ፡ አይደለምን ።

እንዲህ ፡ ያለውን ፡ የደከመበትን ፡ ገንዘብ ፡ ቢሰጥ ፡ የደከመው ፡ አካሉ ፡ አይደለምን ፤ ፍጹም ፡ የማያ ሰኘው ፡ ስለ ፡ ምንድነው ።

ምላሽ ።

፺፯ ፤ በዓለም ፡ ከሚኖሩ ፡ መጽዋቾች ፡ የራሳቸው ፡ አካል ፡ የደከመበትን ፡ ለመመጽወት ፡ የሚችሉት ፡ ሠርተው ፡ የሚያድሩ ፡ ድኾች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፤ የድኾችን ፡ ድካም ፡ እየተቀበሉ ፡ ለሚመጸውቱት ፡ ሀብታሞች ፡ ግን ፡ የባሕርይ ፡ ገንዘባቸውን ፡ ዕውቀትን ፡ እንደ ፡ ቻለልን ፡ እንደራጃለን ፡ በማለት ፡ ከድኾች ፡ ድካም ፡ ለሚገኘው ፡ ገንዘብ ፡ ሽጡት ፡ እንጂ ፡ አልመጸወቱትምና ፤ ያንኑ ፡ ዕውቀታቸውን ፡ ሽጠው ፡ የሚያመጡትን ፡ ገንዘብ ፡ ለደካሞች፡ ቢሰጡ ፡ ብልኅ ፡ አስተንታኝ ፡ ያሰኛቸዋል ፡ እንጂ ፡ ገንዘቡ ፡ የባለድካሙ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እነሱን ፡ ፍጹም ፡ ቸር ፡ አያሰኛቸውም ።

ጥያቄ ።

፺፰ ፤ ወታደር ፡ ከጌታው ፡ መኳንንት ፡ ከበላዩ ፡ ወዙንና ፡ ደሙን ፡ እፍሶ ፡ አሳቡንና ፡ ምክሩን ፡ ለግሶ ፡ ለጌታው ፡ እየሰጠ ፡ ከሚያመጣው ፡ ሀብትና ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ ቢመጸውት ፡ የባሕርይ ፡ ገንዘቡን ፡ ከመመጽወት ፡ አይቈጠርለትምን ።



ምላሽ ።

፺፰ ፤ የወታደሮችም ፡ የመኳንንቶችም ፡ ደምና ፡ ወዝ ፡ የሚፈስበትን ፡ የበላያቸው ፡ ለማስተንተን ፡ የተቀበለውን ፡ ሀብት ፡ ተካፍለን ፡ እኛም ፡ እንደሱ ፡ ዕውቀታችንን ፡ እየሸጥን ፡ የድኾችን ፡ ገንዘብ ፡ እናምጣ ፡ በማለት ፡ የፈሰሰ ፡ ወዝ ፡ ነውና ፡ ምጽዋት ፡ ቢሆን ፡ የወታደሮች ፡ ከጌቶች ፡ ይሻላል ፡ እንጂ ፤ ፍጹም ፡ ምጽዋት ፡ አይባልም ።

ጥያቄ ።

፺፱ ፤ የገንዘብ ፡ ምጽዋት ፡ ስልቱ ፡ እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ አካላቸውን ፡ የማይመጸውቱ ፡ ሀብታሞች ፡ ሁሉ ፡ ገንዘባቸውን ፡ በብዙ ፡ ለመመጽወት ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ይደክማሉ ።

ምላሽ ።

፻ ፤ ይህስ ፡ ያልገደለ ፡ ዘማች ፡ ከቤቱ ፡ አይገባምን ፡ እንደሚባለው ፡ ነው ። ፍጹም ፡ ያልሆነ ፡ ሰው ፡ መጽውቶ ፡ አይጸድቅምን ፡ ማለት ፡ እንዳይሆንብህ ፡ አካሌን ፡ ካልመጸወትኩ ፡ ፍጹም ፡ አልሆንምና ፡ ገንዘቤን ፡ በከንቱ ፡ አልጨርስ ፡ ሳትል ፡ ያንኑም ፡ የሀብቱን ፡ ብትመጸውት ፡ ከማይመጸውት ፡ ትሻላለህ ፡ በማስቀመጥም ፡ ከሚመጣብህ ፡ ፍዳ ፡ ትድናለህ ።

ስለ ፡ ቸርነትህም ፡ በቸርነቱ ፡ ምሕረት ፡ ትጸድቃለህና ፡ የገንዘብ ፡ ምጽዋትህን ፡ አትተው ።

ይልቁንም ፡ የዐመፅ ፡ ገንዘብ ፡ በገባብህ ፡ ጊዜስ ፡ እሳት ፡ ነውና ፡ ቤትህን ፡ እንዳያቃጥልብህ ፡ በመ ስጠት ፡ ውሃ ፡ ቶሎ ፡ ከቤትህ ፡ አጥፋው ።

ተችሎህ ፡ ግን ፡ አካልህን ፡ ለመመጽወት ፡ ስት በቃ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ባለሟልነት ፡ የታደልህ ፡ ወንድምህንም ፡ በውነት ፡ የወደድህ ፡ ለዘለዓለም ፡ ክብር ፡ የተመረጥህ ፡ መሆንህን ፡ በውቀህ ፡ ከባ ሕርይ ፡ ምጽዋት ፡ ለግስህ ፡ ጨምርበት ፡ (ጣ ዕመ ፡ ጸሎት ፡ ም ፡ ፫፮) ።

ምዕራፍ ፡ ፳ ።

## ስለ ፡ ገንዘብ ፡ ወዳጅ ፡ ምክር ።

፻፩ ፡ አጥቶ ፡ ከሚቀማ ፡ ድኻ ፡ ሊሰጥ ፡ ከጌታው ፡ የተ ቀበለውን ፡ ገንዘብ ፡ አልሰጥ ፡ ብሎ ፡ የሚያስቀ ምጥ ፡ ከሆነ ፡ ከድኻው ፡ ቀሚ ፡ ጋራ ፡ ጌታው ፡ በቅ ሚያው ፡ ይተካከልና ፡ በፍትሐ ፡ እምላክ ፡ አጥቶ ፡ ከሚቀማ ፡ ድኻ ፡ ጋራ ፡ አብረው ፡ ይቀጣሉ ፡ እን ጂ ፡ ቀማኛው ፡ ጌታ ፡ በድኻው ፡ ቀማኛ ፡ ላይ ፡ ዳኛ ፡ ሊሆን ፡ አይገባውም ።

ጥያቄ ።

፻፪ ፡ ደጅ ፡ ጠንቶ ፡ በጕልበቱ ፡ አጋር ፡ ገዝቶ ፡ ከሀ ብቱ ፡ ያገኘውን ፡ ገንዘብ ፡ ቢያኖር ፡ ንፉግ ፡ ይባ



ላል ፡ እንጂ ፡ የሰው ፡ የቀማ ፡ ይመስል ፡ እንዴት ፡ ቀማኛ ፡ ይሆናል ።

ምላሽ ።

፻፫ ፡ እግዚአብሔር ፡ በቸርነቱ ፡ ጌታ ፡ በያይነቱ ፡ በበታቹ ፡ ላሉት ፡ እያካፈለ ፡ እንዲሰጥ ፡ የሰውትን ፡ አገር ፡ ሲሆን ፡ ማድ ፡ ቤት ፡ አብዝቶ ፡ ገንዘብ ፡ ሲሆ ን ፡ ምክንያት ፡ አስናድቶ ፡ ለሰራዊቱ ፡ ሊሰጥ ፡ ከተቀበለው ፡ ላይ ፡ እየከፈለ ፡ ለሰራዊቱ ፡ ጥቅም ፡ የተቀበለውን ፡ ለራሱ ፡ ብቻ ፡ ጥቅም ፡ እያደረገ ፡ እያስተረፈ ፡ ገንዘብ ፡ ሲያስቀምጥ ፡ ምንም ፡ ሰሱ ፡ ባይታወቀው ፡ በባለሟልነቱ ፡ ዘንግቶ ፡ በጌትነቱ ፡ አስፈርቶ ፡ ለወታደር ፡ የተሰጠውን ፡ ማሳደሪያማ ፡ ለራሱ ፡ ማካበት ፡ ሲል ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚያው ቀው ፡ ዋና ፡ ቀማኝነት ፡ ነውና ፡ ስለዚህ ፡ በባላገር ና ፡ በወታደር ፡ ዳኛ ፡ ሁኖ ፡ በወታደር ፡ ስም ፡ የሚ ቀበለውን ፡ ገንዘብ ፡ እየከፈለ ፡ ወደ ፡ ተቀማጭ ፡ ጥሪቱ ፡ ካደረገው ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ጌታ ፡ እንዳይ ታይበት ፡ በጌትነቱ ፡ ውድማ ፡ እየሸፈነ ፡ የሌሎቹ ን ፡ ገንዘብ ፡ ይቀማልና ፡ ስለዚህ ፡ እሱ ፡ ሳያጣ ፡ የ ሰውን ፡ ማሳደሪያ ፡ ለጥሪቱ ፡ ሲል ፡ እየቀማ ፡ በማ ጣት ፡ በሚቀማው ፡ ሌባ ፡ ላይ ፡ ዳኛ ፡ ሆኖ ፡ ሊፈ ርድ ፡ አይገባውም ፡ ያልኩህ ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።

ጥያቄ ።

፻፬ ፡ ባገራችን ፡ ያሉ ፡ ጌቶች ፡ ሁሉ ፡ ይህን ፡ የማያደርጉ ፡ የሉ ፡ እንግዲህ ፡ ማን ፡ ይዳኘልን ፡ ማለትህ ፡ ነው ።

ምላሽ ።

፻፩ ፡ ሥጋ ፡ ወደሙን ፡ የቢቀም ፡ ያልበቃም ፡ ቄስ ፡ ቢይዘው ፡ እግዚአብሔር ፡ ለድውይ ፡ የሚያደርግ ለትን ፡ ቸርነት ፡ የቄሱ ፡ ኀጢአት ፡ ሊያስቀርበት ፡ እንደማይችል ፡ ለተሰረቀውም ፡ ሰው ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፈል ፡ ያንኑ ፡ ቀማኛውን ፡ ዳኛ ፡ በባልንጀ ራው ፡ በቀማኛው ፡ ላይ ፡ አስፈርዶ ፡ ያስከፍለዋል ፡ እንጂ ፡ የዳኛው ፡ ኀጢአት ፡ ፍትሐ ፡ እግዚአብ ሔርን ፡ ሊያስቀረው ፡ አይችልምና ፡ ፍርዱንም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጥበብ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ዳንኤል ፡ ከተቀማጩ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ያንኑ ፡ ዳኛውን ፡ አናግሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለድኻው ፡ ጕዳት ፡ ሲል ፡ አዞለት ፡ ያስፈርደዋል ።

ጥያቄ ።

፻፪ ፡ ቀማኝነት ፡ የሌለበት ፡ ገንዘብ ፡ ወዳጅነት ፡ ብቻ ፡ የሚባለው ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ያለው ፡ ንፍገት ፡ ነው ። ያን ፡ ጊዜ ፡ የነፈግኸውን ፡ በሌላ ፡ ሲያስቀ ማህ ፡ ሲያስርቅህ ፡ እንደ ፡ አድብኖ ፡ እንደ ፡ አባ ፡ ኢዮብ ፡ ያመሰገንክ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ ቀኖና ፡ ሆኖ ፡ ይ ጠቅምሃልን ።

ምላሽ ።

፻፪ ፡ ጌታው ፡ ቤት ፡ ሥራበት ፡ ጌጥ ፡ ግባበት ፡ ብሎ ፡ የሚሰጠውን ፡ ገንዘብ ፡ ገብርበት ፡ ብሎ ፡ የሚተክ



ለውን ፡ ምድር ፡ ውርቶ ፡ ያጠራቀመውን ፡ ተቀ ውሎ ፡ የሚቀበለውን ፡ ካባቱ ፡ ለራሱ ፡ በረጃት ፡ የደረሰውን ፡ ክብትና ፡ ርስት ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ለባለቤቱ ፡ ለራሱ ፡ የተሰጠ ፡ ገንዘቡ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ቢሰጠው ፡ ቸር ፡ ቢያስቀምጠው ፡ ንፉግ ፡ ብቻ ፡ ያሰኘዋል ፡ እንጂ ፡ ቀማኛ ፡ አያሰኘውም ።

ሲያረጅ ፡ እንዲጦርበት ፡ የሚያካብት ፡ ተቀማ ጩን ፡ ሲያበዛው ፡ ንፉግ ፡ እንደ ፡ ዘኬዎስ ፡ እኩሉ ን ፡ እያወጣ ፡ እኩሉን ፡ ቢያስቀምጥ ፡ ግን ፡ ብልጥ ፡ እንጂ ፡ ንፉግ ፡ አያሰኘውም ።

ጥያቄ ።

፻፫ ፡ ነጋዴስ ፡ ደክሞ ፡ የሚያመጣው ፡ ወረት ፡ ቀማ ኝነት ፡ የሌለበት ፡ እውነተኛ ፡ ገንዘብ ፡ አይደለምን።

ምላሽ ።

፻፫ ፡ ነጋዴም ፡ ቢሆን ፡ ምንም ፡ የመንገድ ፡ ድካም ፡ ቢኖርበት ፡ ወይ ፡ ሲገዛ ፡ ወይ ፡ ሲሸጥ ፡ ማታለል ፡ የግድ ፡ ሥራው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ከሚያታልለው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የማይገባውን ፡ ሳይወስድ ፡ አይቀርምና ፡ ከንግድ ፡ ገንዘብ ፡ ውስጥ ፡ እንደቅሚያ ፡ ያለ ፡ ገንዘብ ፡ በግድ ፡ መቀላቀሉ ፡ የማይቀር ፡ ነው ።

ጥያቄ ።

፻፬ ፡ የንግድ ፡ ገንዘብ ፡ ቅሚያ ፡ ያልተቀላቀለበት ፡ ጥሩ ፡ እንዲሆን ፡ ምን ፡ መሥራት ፡ ይሻላል ።

ምላሽ ።

፻፲፩ ፡ ከንግዱ ፡ ጐዳና ፡ አስቀድሞ ፡ የመንፈሳዊነትና ፡ የውነተኛነትን ፡ ጐዳና ፡ ይዞ ፡ የደከመውን ፡ ጕል በቱን ፡ በቅን ፡ በሚገዛ ፡ ባለምንዳ ፡ ልክ ፡ እያሰላ ፡ ዐርፎ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ያደረገባቸውን ፡ ቀኖች ፡ እ የተወ ፡ ለመግዣና ፡ ለመንገዱ ፡ ያወጣውን ፡ ገንዘ ቡን ፡ ዋና ፡ አድርጎ ፡ በጕልበቱ ፡ ልክ ፡ ትርፍን ፡ እየገመተ ፡ የሚሸጥ ፡ በጕልበቱ ፡ ዋጋ ፡ ላይ ፡ ያልዋሸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሌብነት ፡ ያልተቀላቀለበት ፡ ገንዘብ ፡ ይሆንለታልና ፤ ቢያስቀምጠው ፡ ንፉግ ፡ ብቻ ፡ ያሰኘዋል ፡ እንጂ ፡ ቀሚ ፡ አያሰኘውም ።

ጥያቄ ።

፻፲፪ ፤ በርኛ ፡ በእጅ ፡ ሥራ ፡ የሚኖር ፡ ምንደኛና ፡ አራሹሳ ፡ ቀማኛ ፡ የሚያሰኛቸው ፡ ገንዘብ ፡ ይኖር ባቸው ፡ ይሆን ።

ምላሽ ።

፻፲፫ ፡ አራሽና ፡ ምንደኛ ፡ ብላዕ ፡ በሀፈ ፡ ገጽከ ፡ የተባሉ ፡ ወዛቸውን ፡ አፍሰው ፡ ድካማቸውን ፡ ሸጠው ፡ የሚያገኙት ፡ ገንዘብ ፡ ከሆነ ፡ ዋጋቸውም ፡ የአካላቸው ፡ ዋጋ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሚቀበሉት ፡ የእፍኣ ፡ ገንዘባቸውን ፡ የሚሰጡ ፡ የሚያስቀምጡ ፡ አይደሉምና ፡ ቢያጠራቅሙም ፡ ባይሰጡም ፡ ንፉግ ፡ እንጂ ፡ ቀማኛ ፡ አያሰኛቸውም ።



ቢሰጡም ፡ ካንዱ ፡ ወስደው ፡ ላንዱ ፡ ከሚሰጡት ፡ ጌቶች ፡ ከብዙው ፡ ስጦታ ፡ የድኾች ፡ ጥቂቱ ፡ ስጦታ ፡ እጅግ ፡ የበለጠ ፡ ሁኖ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ብዙ ፡ ዋጋ ፡ ያሰጣቸዋል ። ይህን ፡ ለመረዳት ፡ ጌታ ፡ ስለ ፡ ጸሪቀ ፡ መበለት ፡ የተናገረውን ፡ አስተውል ። ያንኑ ፡ የደከሙበትን ፡ ስብል ፡ እየሸጡ ፡ ገንዘብ ፡ ለማድረግ ፡ እንደ ፡ ነጋዴው ፡ ከዋናው ፡ በቀር ፡ ከት ርፉ ፡ ላይ ፡ እንደዚያው ፡ ማድረግ ፡ ያስፈልጋል ፡ (ስለ ፡ አባት ፡ እናት ፡ ም ፡ ፺፪) ።

ጥያቄ ።

፻፲፬ ፤ ገንዘብ ፡ የሚባለው ፡ ሊጠላ ፡ የሚገባው ፡ ወር ቅና ፡ ብር ፡ አይደለምን ፤ ሌሎችም ፡ የቤት ፡ ዕቃ ዎች ፡ ሁሉ ፡ ከገንዘብ ፡ ተቈጥረው ፡ መወደዳቸው ፡ ይጐዳል ፡ ይሆን ።

ምላሽ ።

፻፲፭ ፤ እንዲያውም ፡ የቤትና ፡ የጌጥ ፡ ዕቃዎችን ፡ አጥ ብቆ ፡ የሚወድ ፡ ሰው ፡ የጅልነትና ፡ የዕቃ ፡ ሌሰን ፡ በመጨመሩ ፡ የበለጠ ፡ ገንዘብ ፡ ወዳጅ ፡ ሆኖ ፡ ይጐዳል ።

ጥያቄ ።

፻፲፮ ፤ ከየሠረዎች ፡ እየገዛ ፡ ራሱ ፡ ባጌጠ ፡ ቤቱን ፡ ባስ ጌጠ ፡ ከገንዘብ ፡ ወዳጅ ፡ ፍዳ ፡ በላይ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ የጅልነትና ፡ የሌሰኝነት ፡ ፍዳ ፡ ይጨመርበታል ።

### ምላሽ ።

፻፲፯ ፡ ጅል ፡ የሚያሰኘው ፡ ወይ ፡ ገንዘቡን ፡ ለድኾች ፡ ሳይሰጥ ፡ ወይ ፡ ገንዘቡን ፡ ወዶ ፡ ከገንዘቡም ፡ ሳይሆን ፡ ቢለብሰው ፡ የማይሞቀውን ፡ ቢያየው ፡ ለዐይኑ ፡ የሚያንጸባርቀውን ፡ የሐር ፡ ጨርቁን ፡ በቀለም ፡ የተዝጐረጐረ ፡ የቤት ፡ ዕቃውን ፡ በእጅ ፡ ሥራ ፡ የተማበረበሩ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የቤት ፡ ዕቃዎች ፡ እየገዛ ፡ በመልካቸው ፡ እየተደሰተ ፡ ለማየቱ ፡ እየማማ ፡ ወድቀው ፡ በተሰበሩ ፡ በተቀደዱ ፡ ተጐሳቍለው ፡ በጠቈሩ ፡ በተበላሹ ፡ ቍጥር ፡ አሳቡን ፡ በብስጭት ፡ ከየዕቃዎቹ ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ እየቀደደና ፡ እየሰበረ ፡ በማደፍና ፡ በመሰበር ፡ የሚያስጨንቀውን ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ባስጨናቂ ፡ ለሕይወቱ ፡ በማይጠቅመው ፡ አሳቡን ፡ ለማይረባው ፡ ዕቃ ፡ አገልጋይ ፡ አድርጎ ፡ በመድከሙ ፡ ጅል ፡ ገንዘብ ፡ ወዳጅ ፡ አሰኝቶ ፡ የዕቃና ፡ የቤት ፡ የልብስን ፡ ሽልም ፡ እየፈለገ ፡ በመማማቱ ፡ እየሻ ፡ በማከማቸቱ ፡ በገንዘብ ፡ ወዳጅነቱ ፡ ላይ ፡ የዕቃ ፡ ዘማዊነትን ፡ በመጨመሩ ፡ አሳቡን ፡ የዕቃ ፡ ዘማዊ ፡ አድርጎ ፡ በማየት ፡ በመደሰቱ ፡ በመያዝ ፡ በመውደድ ፡ ያለፈውን ፡ ዝሙት ፡ ሁሉ ፡ የሚፈጽምበት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ዘመወ ፡ ማለት ፡ ወደደ ፡ ነውና ፡ የዕቃ ፡ ዝሙት ፡ እየተጨመረበት ፡ ፍዳ ፡ ያበዛበታልና ፡ ስለዚህም ፡ ምንም ፡ ሁለቱ ፡ ትልቅ ፡ ኀጢአት ፡ ቢሆን ፡ ገንዘቡን ፡ እውጥቶ ፡ የሚገዛ



በት ፡ ለዕቃው ፡ መውደድና ፡ ለመማማት ፡ ሲል ፡ ከሆነ ፡ ከገንዘብ ፡ ወዳጅ ፡ የዕቃ ፡ ወዳጅ ፡ አሳቡን ፡ የሚገዙትን ፡ ዕቃዎች ፡ ለመሰብሰብ ፡ በመጣሩ ፡ ፍዳው ፡ ይጠናል ።

### ጥያቄ ።

፻፲፰ ፡ ገንዘብ ፡ ወዳጅ ፡ ብሩና ፡ ወርቁን ፡ ቈልፎ ፡ ወይም ፡ ቀብሮ ፡ ሠራተኞቹም ፡ ሳያገኙት ፡ እሱም ፡ ሳያጌጥበት ፡ በከንቱ ፡ ያስቀረዋል ፤ ዕቃና ፡ ጌጥ ፡ ወዳጅ ፡ ግን ፡ ገንዘቡን ፡ ለዕቃ ፡ መግዣ ፡ ሲያወጣው ፡ እሱም ፡ የፈለገውን ፡ አግኝቶ ፡ ለጌጥ ፡ ዕቃ ፡ ሠሪ ፡ ለድኾችና ፡ ለነጋዴዎች ፡ ግን ፡ የጕልበት ፡ ዋጋቸውን ፡ በማግኘታቸው ፡ የሚጠቅማቸው ፡ ሲሆን ፡ የዕቃ ፡ ወዳጅ ፡ ከገንዘብ ፡ ወዳጅ ፡ ይሻላል ፡ እንጂ ፡ ገንዘቡን ፡ ከሰው ፡ ተካፍሎ ፡ ባጌጠ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ፍዳው ፡ ይጠናበታል ።

### ምላሽ ።

፻፲፰ ፡ ፍትሐ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚወድቅበት ፡ ፍርድ ፡ ኅሊና ፡ የሚሠራውን ፡ ነገር ፡ እየተከተለ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በወርቅና ፡ በጨርቅ ፡ መልኮች ፡ ላይ ፡ አይደለምና ፡ የሚፈርደው ፡ መውደዱ ፡ ከተካከለ ፡ ወርቁም ፡ ጨርቁም ፡ እኩል ፡ ገንዘብ ፡ ወዳጅ ፡ እድርገው ፡ እኩል ፡ ገንዘብ ፡ ወዳጅ ፡ ያሰኙታል ፤ ዋጋውንም ፡ ያወጣው ፡ ዕቃውን ፡ ወዶ ፡ እንጂ ፡ ሠራተኞቹን ፡ ወዶና ፡ አዝኖ ፡ አለመሆኑን ፡

ያው ፡ ፈሪጁ ፡ አምላክ ፡ የሚያውቀው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በገንዘብ ፡ መውደዱ ፡ ላይ ፡ የዕቃ ፡ ዘማዊ ፡ ፍርድ ፡ ጨምሮ ፡ ይፈርድበታል ። የገዛውን ፡ ዕቃ ፡ ግን ፡ ከገዛው ፡ በኋላ ፡ ቢንቀውና ፡ ለሰው ፡ ቢሰጠው ፡ ለዕቃው ፡ አገልጋይ ፡ ሆኖ ፡ ማክበሩና ፡ መጨነቁን ፡ ቢተወው ፡ ግን ፡ ለሠራተኞቹም ፡ የጕልበት ፡ ዋጋ ፡ በመክፈሉም ፡ ዕቃውንም ፡ ለየፈላጊዎቹ ፡ በመስጠቱ ፡ ባለዋጋ ፡ ይሆናል ፡ እንጂ ፡ ባለዕዳ ፡ (ባለፍዳ) ፡ አይሆንም ።

## ምዕራፍ ፡ ፱ ።

# ስለ ፡ ገንዘብ ፡ አቀባበል ።

### ጥያቄ ።

፪፻ ፡ ኀጢአት ፡ ሳይሆን ፡ የሚሠራ ፡ ኀጢአት ፡ ሁኖ ፡ የሚሠራ ፡ የገንዘብ ፡ አገባብስ ፡ ስንት ፡ ነው ።

### ምላሽ ።

፪፻፩ ፡ ጌታ ፡ ሆኖ ፡ ስለ ፡ መተያያ ፡ ብሎ ፡ የሰው ፡ ገንዘብ ፡ ሲያመጣለት ፡ ደግሞ ፡ እንዲጨምርለት ፡ ያየውም ፡ ሌላውም ፡ እንዲያመጣለት ፡ በጥርሱ ፡ እየፈገገ ፡ በቃሉ ፡ እያመሰጋገነ ፡ መቀበል ፡ ገንዘብ ፡ መውደድ ፡ የፈጠረው ፡ የኀጢአት ፡ ተንኰል ፡ ነው ።



፪፻፪ ፡ ዘጋህ ፡ የሆነ ፡ ዕወቀኝ ፡ ሲል ፡

ሎሌህ ፡ የሆነ ፡ ልመደኝ ፡ ሲል ፡

ዘመድ ፡ የሆነ ፡ ውደደኝ ፡ ሲል ፡ የሚያመጣልህን ፡ ገንዘብ ፡ ካቀባበሉ ፡ ላይ ፡ ሳትከፋም ፡ ሳትደሰትም ፡ በጸጥታ ፡ ማንባር ፡ ተቀብለህ ፡ እንዳይረሳበት ፡ አጽፈህ ፡ እንዳይቀርበት ፡ አስታውሰህ ፡ የገንዘቡን ፡ ወሮታ ፡ ለመመለስ ፡ የሚቻል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብትቀበል ፡ የማይቻልህ ፡ ሲሆን ፡ ብትመልስ ፡ የጽድቅ ፡ ሥራ ፡ ነው ።

፪፻፫ ፡ ገንዘብ ፡ የሚያመጣለት ፡ ሰው ፡ ባላጋራ ፡ ከሆነ ፡ ገንዘቡን ፡ ተቀብሎ ፡ እውነቱንም ፡ ሲበይን ፡ በት ፡ ገንዘቡን ፡ ያለዋጋ ፡ ያለወረታ ፡ መውሰዱ ፡ ነውና ፤ ከወንበዴ ፡ ይቈጠራል ።

፪፻፬ ፡ ገንዘቡንም ፡ ተቀብሎ ፡ ሲበይንለት ፡ ፍትሐ ፡ እግዚአብሔር ፡ መሸጡ ፡ ነውና ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሻጭ ፡ ከይሁዳ ፡ ይቈጠራል ።

ስለዚህ ፡ በዳኝነቱ ፡ ገንዘብ ፡ ተቀብሎ ፡ ቢያዳላም ፡ ባያዳላም ፡ ገንዘብ ፡ መቀበሉ ፡ ብቻ ፡ ትልቅ ፡ ኀጢአት ፡ ነው ።

፪፻፭ ፡ ርስት ፡ ትክለኝ ፡ ዕዳ ፡ ማረኝ ፡ ገንዘብ ፡ የሚያመጣውን ፡ ገንዘብ ፡ ተቀብለህ ፡ ስጠኝ ፡ ሲል ፡ የሚያመጣውን ፡ ገንዘብ ፡ ተቀብለህ ፡ በትንሽ ፡ በረከት ፡ ምክንያት ፡ የፈለገውን ፡ የሚበ ልጠውን ፡ ጥቅም ፡ ስጦታ ፡ ብታደርግለት ፡ ግን ፡ ትሩፋትና ፡ ጽድቅ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ይጠቅማል ።

፻፳፮ ፡ መቀጫ ፡ ዳኝነት ፡ ብለህ ፡ በምታገባውም ፡
ገንዘብ ፡ ምክንያት ፡ ትንሿን ፡ በደል ፡ ያለመጠኗ ፡
አግነህ ፡ ተናግረህና ፡ ተቈጥተህ ፡ ሰውም ፡ እንዲ
ፈርድበት ፡ ባንተ ፡ አነጋገር ፡ አመሳስለህ ፡ ያለ
በደሉ ፡ ዐቅም ፡ ከትንሽ ፡ በደል ፡ የተነሣ ፡ በብዙ ፡
ገንዘብ ፡ ብትቀጣው ፡ ወይም ፡ ስቈጣውና ፡ ሳስፈ
ራራው ፡ ደንግጦ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲያመጣ
ልኝ ፡ ብለህ ፡ ብትጠበብ ፡ ተንኰል ፡ ትሠራለህና ፡
ኀጢአት ፡ ነው ።

፻፳፯ ፡ በመቀጫ ፡ ለሚገባው ፡ ገንዘብ ፡ ለጥቅሙ ፡
ሳትጓጓ ፡ ሠለስቱ ፡ ምእት ፡ እንደ ፡ ጻፉልህ ፡ ከዚ
ያም ፡ የሌለው ፡ ንጉሥ ፡ እንደ ፡ ሠራልህ ፡ አዲስ ፡
ለመጣው ፡ እስመከረህ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡
ገለጸልህ ፡ ከነሱ ፡ ቃል ፡ ላይ ፡ መርጠህ ፡ ቈርጠህ ፡
ብትቀጣ ፡ የሚገባ ፡ ነውና ፡ ጽድቅ ፡ ነው ።

፻፳፰ ፡ በሰርግ ፡ በተዝካር ፡ በንጉሥ ፡ እመካኝቶ ፡
ገንዘቡን ፡ በደቦ ፡ በልመና ፡ እመካኝቶ ፡ ጕልበ
ቱን ፡ ከታዘዘው ፡ ካዋጁ ፡ ሥራ ፡ ከተደነባው ፡
ከምድሩ ፡ ግብር ፡ አልፈህ ፡ በጥበብ ፡ አመካኝተህ ፡
ገንዘቡንም ፡ ጕልበቱንም ፡ ብትወስድበት ፡ ኀጢ
አት ፡ ነው ።

፻፳፱ ፡ ከገባሪም ፡ የምትቀበለውንም ፡ ግብር ፡ ያንኑ ፡
የተወሰነውን ፡ ግብር ፡ እንዳይረሳ ፡ እያጻፍክ ፡
እንዳይበላለጥ ፡ እያስተካከልክ ፡ እንዳይቀር ፡ እየተ
ቋጠርክ ፡ ብትቀበል ፡ ዋጋህ ፡ ነውና ፡ ጽድቅ ፡ ነው ።



## ምዕራፍ ፡ ፲ ።

ሌላውን ፡ መምከር ፡ ለሚያውቅ ፡ ያመካከሩ ፡
ዘዴ ፡ እየጠፋው ፡ ራሱ ፡ እንዳይጐዳ ፡ ስለ ፡ ሰው ፡
የምክር ፡ ምጽዋት ፡ የሚገባና ፡ የማይገባውን ፡

## መሪያ ።

### ጥያቄ ።

፻፴ ፡ ሰው ፡ ለተፈጥሮ ፡ ወንድሙ ፡ ለችግሩ ፡ ርዳታ ፡
ገንዘብ ፡ ከሚሰጥና ፡ ላለማወቁ ፡ ርዳታ ፡ ምክር ፡
ከሚሰጥ ፡ ሰው ፡ የማንኛው ፡ ክብር ፡ ይበልጣል ።

### ምላሽ ።

፻፴፩ ፡ ሁለቱም ፡ የሚገባ ፡ ርኅራኄ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ መን
ግሥት ፡ ሰማያትን ፡ የሚያሰጥ ፡ ነው ፡ ለመብለጡ
ግን ፡ ገንዘብ ፡ የሚሰጥ ፡ ከእፍእ ፡ በጸጋ ፡ ያገኘ
ውን ፡ ትርፍ ፡ ገንዘቡን ፡ የሚሰጥ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡
ምክር ፡ የሚሰጥ ፡ ከራሱ ፡ የሚገኘውን ፡ ያለውን ፡
የባሕርይ ፡ ገንዘቡን ፡ የሚሰጥ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ምክ
ሩን ፡ የሚሰጥ ፡ ቅን ፡ መካር ፡ ዋጋው ፡ እጅግ ፡
ብዙ ፡ ይሆናልና ፡ የምክር ፡ የትምርት ፡ ቸር ፡
የሚበልጥ ፡ መሆኑን ፡ ስላወቁ ፡ ጌታችንም ፡
በሰውነቱ ፡ ሐዋርያትም ፡ ሁሉ ፡ በየስብከታቸው ፡
የሥራት ፡ ቸርነት ፡ የምክር ፡ ምጽዋት ፡ መሆኑን ፡
አስተውል ።

ጥያቄ ።

፻፴፪ ፡ ገንዘብ ፡ እያለው ፡ ባይመጸውት ፡ ፍዳም ፡ ኀጢአትም ፡ ሁኖ ፡ ይጐዳበታል ። መካር ፡ ዝም ፡ ቢል ፡ ግን ፡ ከእርምሞ ፡ ነው ፡ የሚቈጠርለት ፡ ያልመከረና ፡ ያልመጸወተ ፡ ኀጢአቱ ፡ እኩል ፡ ይሆናልን ፤ ወይስ ፡ ይበላለጣል ።

ምላሽ ።

፻፴፫ ፡ ተመካሪው ፡ ሰውዬ ፡ ምክሩን ፡ የሚቀበለው ፡ ሲሆን ፡ ኵርቶ ፡ ፈርቶ ፡ ቀንቶ ፡ ለግሞ ፡ እማይመክር ፡ ካለመመጽወት ፡ የበለጠ ፡ ኀጢአት ፡ ይሆንበታል ። ይህንም ፡ በኢሳይያስ ፡ ባለመምከሩ ፡ በአዝያን ፡ የተፈረደበት ፡ ለምጽ ፡ በሱም ፡ እንደ ፡ ደረሰበት ፡ አስተውል ።

፻፴፬ ፡ ምክሩን ፡ ለማይቀበለው ፡ እሱን ፡ ለማይፈልገው ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ከመምከር ፡ ዝም ፡ ቢል ፡ ከእርምሞ ፡ ከትዕግሥት ፡ ተቈጥሮ ፡ ዋጋ ፡ ያሰጠዋል ፡ እንጂ ፡ ፍዳ ፡ ኀጢአት ፡ አይሆንበትም ፤ ይህንም ፡ ልትረዳ ፡ ብትሻ ፡ ዕንቍህን ፡ በሪያ ፡ ፊት ፡ አታድርግ ፡ ባለው ፡ አስተውል ።

፻፴፭ ፡ ገንዘብ ፡ ወዳጅ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፍርድ ፡ መቀጣቱም ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ገንዘብ ፡ የሚሰበሰብበት ፡ ሰው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዕቃ ፡ ቤትነት ፡ መሾሙ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እሱ ፡ ባለገንዘብ ፡ አይደለም።



ይህንም ፡ ልትረዳ ፡ ብትሻ ፡ የሥጋም ፡ ዕውቀት ፡ አብሮ ፡ ሲቀበር ፡ የነፍስ ፡ ዕውቀት ፡ አብሮ ፡ ሲያርግ ፡ ይህ ፡ ገንዘብ ፡ ካንዳቸው ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ ለመሄድ ፡ የማይቻለው ፡ ቀሪ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የገንዘቡ ፡ ባለቤት ፡ ፈጣሪው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ስለዚህ ፡ ገንዘብ ፡ ወዳጅ ፡ የሚቀጣበት ፡ ምክንያት፡ በዕቃ፡ ቤት ፡ እንጂር ፡ ነው ። ዕቃ ፡ ቤት ፡ የሱ ፡ ያይደለውን ፡ የጌታውን ፡ ገንዘብ ፡ ለታዘዘለት ፡ እላካፍል ፡ እያለ ፡ እንደሚጠም ፡ እግዚአብሔር ፡ ስጥ ፡ ብሎ ፡ ላዘዘላቸው ፡ ችግረኞች ፡ አልሰጥም ፡ እያለ ፡ አለገንዘቡ ፡ እየከለከለ ፡ ስለ ፡ ለገመ ፡ በእንቢታው፡ ነው ፡ የሚቀጣው ።

፻፴፮ ፡ የባሕርዩ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲሆነው ፡ ከአምላኩ ፡ የተቀበለውን ፡ ምክር ፡ የማይሰጥ ፡ የራሱን ፡ ገንዘብ ፡ ስለ፡ ከለከለ፡ ክፉ፡ ንፉግ ፡ መባልና ፡ በዕቃ ፡ ቤትነቱ ፡ ከዓለም ፡ ላይ ፡ የሚቀበለውን ፡ ገንዘብ ፡ ስለ ፡ ከለከለ ፡ ግን ፡ ጅል ፡ ጠማማ ፡ መባል ፡ ነው ፡ የሚገባው ።

ጥያቄ ።

፻፴፯ ፡ ተመካሪው ፡ ለዓለማዊ ፡ ፍትወቱ ፡ አገልጋይ ፡ ሆኖ ፡ በማድላት ፡ ወዳጁን ፡ የሚጠቅምበትን ፡ በመጥላት ፡ ጠላቱን ፡ የሚጐዳበትን ፡ ምክር ፡ የሚሻብኝ ፡ ለወዳጅህም ፡ አታድላ ፡ ጠላትህንም ፡ አትጕዳ ፡ ማለትን ፡ የማይወድልኝ ፡ ሲሆንላ ፡ ለዚ

ያው ፡ ለሚወደው ፡ ለጠላት ፡ ማጥቃቱንና ፡ ማድ
ላቱን ፡ ልምከረውን ፡ አልምከረው ።

ምላሽ ።

፻፴፰ ፡ ይህንማ ፡ ከመከርክ ፡ የኀጢአት ፡ መሪና ፡ አስ
ታዋሽ ፡ መሆንህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ መቼ ፡ መካር ፡ ትባላለህ ።
እንዲያውም ፡ ጴጥሮስ ፡ ጌታን ፡ በሥጋዊ ፡ ቃል ፡
ቢመክረው ፡ ሰይጣን ፡ እንዳለው ፤ ሰይጣን ፡ ያሰኛ
ልና ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ፍትወቱ ፡ አይሉብት ፡
ግብረ ፡ ዓለሙ ፡ ተብትቦት ፡ በግዱ ፡ ወይም ፡
በውዱ ፡ ለኀጢአት ፡ ተገዥ ፡ ለሆነ ፡ ሰውስ ፡
እዘንለት ፡ እንጂ ፡ እየረሳውና ፡ እያቃተው ፡ የማድ
ላትና ፡ የጠላት ፡ መጉዳት ፡ ፍዳ ፡ እንዳይቀልለት ፡
መካርና ፡ አቃኝ ፡ አስታዋሽና ፡ አፋጣኝ ፡ አትሁን ።

ጥያቄ ።

፻፴፱ ፡ ምክሬን ፡ የሚፈልግ ፡ ሰው ፡ የበላዩ ፡ ገዥዬ ፡
ሆኖ ፡ እሱ ፡ የወደደውን ፡ የማድላት ፡ ሥራውን ፡
እንዳቃናለት ፡ የሚሻብኝ ፡ ሲሆን ፡ ብሸሽውና ፡
ባልመከረው ፡ የሚጣላኝ ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ ለገሌ ፡
ልስጠው ፡ ልሹመው ፡ ወይ ፡ እገሌን ፡ ልንሣው ፡
ልሻረው ፡ እያለ ፡ በሚጠይቀኝ ፡ ጊዜ ፡ ዝም ፡
ብል ፡ ንቀት ፤ በመሰል ፡ ብናገር ፡ የሰውየውን ፡
ባሕሪ ፡ ጠርሼ ፡ ሳላውቀው ፡ በመሰል ፡ ብቻ ፡
በሰው ፡ በመመስከሬ ፡ ሐሰተኛ ፡ ያየሁትንና ፡
ያወቅሁትን ፡ ክፉ ፡ ባሕርዩን ፡ ስናገር ፡ ሰብቀኛ ፤



በክፋቱም ፡ ብናገር ፡ ምቀኛ ፡ በመሆኔ ፡ ክፉ ፡
ባሕርዩንም ፡ ደግ ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ ስናገር ፡ አምኖ ፡
ጌታዬ ፡ ሲጠይቀኝ ፡ ሰውሬ ፡ በመናገሬ ፡ አታላይ ፡
ልግመኛ ፡ መሆኔ ፡ ነው ። ለጌታ ፡ መካር ፡ በምሆ
ንበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉም ፡ የመጉጃ ፡ መንገድ ፡ አሰበ
ትና ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ ይሻለኛል ።

ምላሽ ።

፻፵ ፡ ከዚህ ፡ ለመዳን ፡ በሹም ፡ ሽርና ፡ ለስጦታ ፡
አማካሪ ፡ ለመሆን ፡ አትትጋ ፤ ቢመጣብህም ፡ የሚቻ
ልህን ፡ ያኽል ፡ ሽሸው ፤ ዕቃ ፡ ጠባቂ ፡ ጌታው ፡
እንዳዘዘው ፡ ይሰጣል ፡ እንጂ ፡ ታዞ ፡ ለሚሰጥ ፡
ለግምጃ ፡ ቤቱ ፡ አማካሪ ፡ መሆን ፡ እንደማይገባ ፡
ስጪውም ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡
ነውና ፡ ልቡን ፡ እምላኩ ፡ እንደሚያዘው ፡ እያደ
ረገ ፡ ይሥራ ፡ እንጂ ፡ አንተ ፡ ለግምጃ ፡ ቤትነቱ ፡
መካር ፡ መሆን ፡ አይመርህ ፤ በግድ ፡ በጌትነቱ ፡
እያዘዘም ፡ ሲጠይቅህ ፡ ሳታብልም ፡ በጠየቀህም ፡
ጊዜ ፡ ዝምም ፡ ሳትል ፡ እሱ ፡ የሚወደውን ፡ ሳትሻ ፡
እግዚአብሔር ፡ የሚወደውን ፡ እውነት ፡ ብቻ ፡
ንገረው ።

፻፵፩ ፡ የሰው ፡ ስም ፡ እየጠራ ፡ ከገሌና ፡ ከገሌ ፡ ማን ፡
ይሻላል ፡ የገሌስ ፡ ባሕርዩ ፡ ምንድነው ፡ ሲልህ ፡
የሰውን ፡ ባሕርይ ፡ የፈጠረው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡
እንደሱ ፡ የተፈጠረ ፡ ሰው ፡ ሊያውቀው ፡ የሚች

ለው ፡ ስላልሆን ፡ ምላሽህ ፡ አላውቅም ፡ ወይ ፡ ማለትህ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ከሰው ፡ በሰማኸው ፡ ወሬና ፡ በመምሰል ፡ ብቻ ፡ እንዳት መስክርበት ፡ ተጠንቀቀህ ፡ ተጠበቅ ፤ አትፍረዱ ፡ እንዳይፈረድባችሁ ፡ ያለውንም ፡ አትርሳ ።

የሰውን ፡ ባሕሪ ፡ ያየኸውንም ፡ ቢሆን ፡ ጌትዮው ፡ ሳይጠይቅህ ፡ አትናገርበት ፤ ስሙን ፡ ጠርቶ ፡ ነገሩን ፡ ለይቶ ፡ የሚገዛህ ፡ ጌታህ ፡ ከጠየቀህ ፡ ግን ፡ ምስክርነት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አሳባቂነት ፡ አይደለምና ፤ ለዚያው ፡ ለጠየቀህ ፡ ቃል ፡ የሰማ ኸውን ፡ ባየኸው ፡ ላይ ፡ ሳትጨምርበት ፡ ያየኸ ውን ፡ ብቻ ፡ መስክረህ ፡ ንገረው ።

፻፺፪ ፤ የሰማህበትን ፡ የሰውየውን ፡ ጠባይ ፡ ባይን ህም ፡ ባታይ ፡ ንገረኝ ፡ ብሎ ፡ ሲያስገድድህ ፡ ግን ፡ እኔ ፡ የማልመሰክርበትን ፡ ከሰው ፡ ላይ ፡ ወሬ ፡ የሰማሁት ፡ አለና ፡ ያንኑ ፡ የነገረኝን ፡ በማየ ትህ ፡ እንተው ፡ ቀርበህ ፡ ትመሰክራለህ ፡ ወይ ፡ ብዬ ፡ ልጠይቅና ፡ አዎን ፡ ሲል ፡ ያየው ፡ ይመስ ክርበት ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ ያላየሁትን ፡ ነገር ፡ ተናግሬ ፡ ከዳኛ ፡ ልብ ፡ ላይ ፡ ያልተረገጠ ፡ የወሬ ፡ ቃል ፡ ጽፌ ፡ አስቀምጬ ፡ የተወራብቱን ፡ ሰው ፡ እክል ፡ አጋጥሞት ፡ ከወሬው ፡ ጋራ ፡ የሚመሳሰል ፡ ጥፋት ፡ በሚሠራበት ፡ ጊዜ ፡ የኔ ፡ ወሬ ፡ መጨመሪያ ፡ ሁኖ ፡ ሰው ፡ በመጐዳቱ ፡ በፈጣሪዬ ፡ ፍርድ ፡ እጐዳለሁ ፡ ስል ፡ እፈራለሁ ፡ ብለህ ፡ ግልጠህ ፡



ፍርሀትህን ፡ አስታውቀው ፡ እንጂ ፡ በሰማኸው ፡ ወሬ ፡ በሰው ፡ ጠባይ ፡ ላይ ፡ አትመስክርበት ።

፻፺፫ ፤ ሳይጠይቅህ ፡ ግን ፡ ለጌታህ ፡ የሰብቅ ፡ አገል ጋይ ፡ ለመሆን ፡ ስትል ፡ እንኳን ፡ የሰማኸውን ፡ ያየ ኸውን ፡ ቢሆን ፡ አትናገርበት ።

እሱም ፡ ጌታህ ፡ ቢሆን ሰብቅ ፡ የምትነግርበ ትም ፡ ወንድምህ ፡ መሆኑን ፡ አትርሳው ።

፻፺፬ ፤ ጌታህን ፡ ሊጐዳ ፡ የተነሣውን ፡ ሰው ፡ ለጌ ታህ ፡ ባለመንገርህ ፡ ጌታህ ፡ እንዳይጐዳ ፡ አንተ ፡ እስከሚቻልህ ፡ ጠብቀው ።

ከጠላቱም ፡ እንዲያድነው ፡ ከአምላክህ ፡ ለምን ለት ፤ ሰው ፡ ሰውን ፡ ያለእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ሊጐዳው ፡ አይችልምና ።

ሰውየው ፡ ያሰበውን ፡ ክፋትና ፡ ክዳት ፡ ወይ ፡ እንደ ፡ ጴጥሮስ ፡ ተጠጥቶ ፡ ወይ ፡ እንደ ፡ ጳው ሎስ ፡ አቅቶት ፡ አልቻለው ፡ ብሎ ፡ ጌታውንም ፡ ሳይጐዳው ፡ ተመልሶ ፡ ወዳጅ ፡ የሚሆነው ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ አታውቅምና ፡ ወይ ፡ ሎሌው ፡ ወይ ፡ ዘበኛው ፡ ሳትሆን ፡ አስቀድመህ ፡ ኀጢአቱን ፡ ለጌታው ፡ ነግረህ ፡ በማጣላትህ ፡ ወንድምህን ፡ አትጐዳው ።

አንተ ፡ በሰውየው ፡ አሳብቀህበት ፡ ጌትየው ፡ በት ዕግሥት ፡ ቢምረውም ፡ ባንተ ፡ አሳብ ፡ በኩል ፡

ጉድተኸዋልና ፡ ከፍዳው ፡ የማትድን ፡ መሆንክን ፡ በውቀህ ፡ ተጠንቀቅበት ።

፻፵፭ ፡ ጌታህንም ፡ ለመምከር ፡ የምትበቃ ፡ ቀራቢ ፡ በሆንክበትም ፡ ጊዜ ፡ ሳይጠይቅህ ፡ የምትነግረው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለሚሠራለት ፡ መንፈሳዊ ፡ ሥራ ፡ እስታዋሽነት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሳይጐዳ ፡ ላንዱ ፡ በሚሠራለት ፡ ለምሕረት ፡ አማላጅነት ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ እናዋር ፡ የተካከለ ፡ የጤና ፡ እና ዋር ፡ በሚሠራበት ፡ ጊዜ ፡ ለሰው ፡ ለጤናው ፡ እኗኗር ፡ ለሚሆን ፡ ደንብ ፡ ሥራ ፡ በመካርነት ፡ ብትረዳው ፡ አእምሮህን ፡ ለጌታህ ፡ በመስጠትህ ፡ ቸር ፡ ወንድምህን ፡ በመጥቀም ፡ ቅን ፡ ሆነህ ፡ የፈጣሪህ ፡ ባለዋጋ ፡ ትሆናለህ ።

፻፵፮ ፡ የሹም ፡ ሽርና ፡ የስጦታ ፡ አማካሪ ፡ የሆንክ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ የሚመከረው ፡ ጌትየው ፡ የሚመክ ርበት ፡ የተጐጅው ፡ የሚመክርለት ፡ የተቀባዩ ፡ ሦስት ፡ ዐይነት ፡ ጉዳይ ፡ ስላለበት ፡ ወይ ፡ ከኣህ ፡ ከሦስቱ ፡ ካንዳቸው ፡ ወይ ፡ ከፈጣሪው ፡ ሳያጣላ ፡ የማይቀር ፡ ነውና ፡ መንፈሳዊ ፡ ልብ ፡ ላለው ፡ ማድላት ፡ ለማይወድ ፡ ሰው ፡ ብዙ ፡ የሚያስቸግሩ ፡ የኀጢአት ፡ ጾሮች ፡ ስለ ፡ መሉበት ፡ አማካሪነትህ ፡ በግድ ፡ ካልመጣብህ ፡ ለጌታህ ፡ መካር ፡ ከመሆን ፡ ያገልጋይነትህ ፡ ኑሮ ፡ የሚሻልህ ፡ መሆኑን ፡ ዐውቀህ ፡ ለወንድምህ ፡ እንጂ ፡ ለጌታ ፡ መካር፡ መሆንክን ፡ ተወው ።



መጻሕፍትም ፡ ተቀንዩ ፡ ለአጋዕዝተኪሙ ፡ ሲሉ ፡ መሀርምሙ ፡ ለአጋዕዝተኪሙ ፡ አለማለታቸው ፡ ም ክር ፡ የትእዛዝ ፡ ወገን ፡ ስለ ፡ ሆን ፡ ከሚያዘው ፡ ከሚ በልጠው ፡ ከጌታው ፡ እኔ ፡ እበልጣለሁ ፡ በውቃ ለሁ ፡ ብሎ ፡ ጌትየው ፡ ያልወደደውን ፡ እውነት ፡ አጥብቆ ፡ ሲናገር ፡ ከጌታው ፡ የሚያጣላው ፡ እንዳ ይሆን ፡ ጌታው ፡ ከሚወደውም ፡ ከማድላቱ ፡ ቃል ፡ ጋሬ ፡ መስሎ ፡ ቢናገር ፡ ከፈጣሪው ፡ የሚ ያጣላው ፡ እንዳይሆን ፡ ጠንቅቀው ፡ ማዘዛቸውን ፡ እስተውለህ ፡ ዕወቀውና ፡ ለጌታህ ፡ አገልጋይ ፡ እንጂ ፡ መካር ፡ መሆንክን ፡ አትፈልገው ።

፻፵፯ ፡ መካርነቱ ፡ በግድ ፡ ቢመጣብህ ፡ ለማዳላ ቱም ፡ አንተ ፡ ለኔ ፡ ፈቃድ ፡ ረዳት ፡ ሁነህ ፡ ሳታ ደንቅ ፡ ከቀረህ ፡ እያለ ፡ ቢጣላህ ፡ ቢጐዳህ ፡ አን ተም ፡ እውነቱን ፡ ለመናገር ፡ ሳትመለስ ፡ ስለ ፡ ጸናህ ፡ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ የሚያገኝህ ፡ ጉዳት ፡ ሁሉ ፡ የሰማዕትነት ፡ ዋጋ ፡ የሚያስጥህ ፡ መሆ ኑን ፡ እመነው ።

፻፵፰ ፡ መካርነትም ፡ በጥቅሉ ፡ ዐይነቱ ፡ ሦስት ፡ ነውና ፡ ዐውቀህ ፡ ለይተህ ፡ ሥራው ፡ ስሙ ፡ አንድ ፡ ከሆን ፡ ብለህ ፡ ሁሉንም ፡ ልሥራው ፡ እንዳትል ፡ በሚከተለው ፡ አስተውለህ ፡ ሁሉቱን ፡ ዐይነት ፡ እንድትሠራው ፡ አንዱን ፡ ዐይነት ፡ እንድታስ በው ፡ ሁን ።

አንዱ ፡ ዐይነት ፡ መንፈሳዊ ፡ ምክር ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ቃል ፡ ሳትጨምርበት ፡ ላንተ ፡ ጥቅም ፡ ይሁንኝ ፡ ሳትል ፡ ለነፍሱ ፡ ማዳን ፡ የምትመከረው ፡ የሚገባ ፡ ምክር ፡ ነው ።

ሁለተኛው ፡ የእውነት ፡ ለመመዘን ፡ ለዳኛ ፡ የሚመከረው ፡ ቃል ፡ ነው ፤ በሶስና ፡ ፍርድ ፡ ጊዜ ፡ ዳንኤል ፡ እንዳደረገው ፡ የሚመከርበት ፡ ሰውዬ ፡ ራሱ ፡ ሲናገር ፡ በተሰማው ፡ ወይም ፡ ሲሠራው ፡ በታየው ፡ ሊደረግበት ፡ በሚያስፈልገው ፡ ነገር ፡ ኀጢአቱንና ፡ ቅጣቱን ፡ አመዛዝኖ ፡ ሰው ፡ አላግባብ ፡ እንዳይጐዳ ፡ ለቀጪው ፡ መምከር ፡ የሚገባ ፡ ምክር ፡ ነው ።

ሦስተኛው ፡ ሥጋዊ ፡ ምክር ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ለሚሠራ ፡ ነገር ፡ እንዲህ ፡ ብታደርግ ፡ እንዲህ ፡ ይሆንልሃል ፡ እያሉ ፡ እንደ ፡ ጠንቋይ ፡ መላ ፡ እየጣሉ ፡ እንደ ፡ ሰባኪ ፡ ካለፈው ፡ ጋራ ፡ እያመሳሰሉ ፡ ገና ፡ በሚሆነው ፡ ላይ ፡ ይሆናል ፡ ብለው ፡ የሚመክሩ ፡ የመሆኑን ፡ ርግጥነት ፡ ሳያውቁ ፡ በመናገራቸው ፡ ሐሰተኞች ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚሠራውንም ፡ ሳያውቁ ፡ እንደ ፡ ዐዋቂ ፡ ሁነው ፡ በመናገራቸው ፡ ደፋሮች ፡ ይሆናሉ ። ያሉትም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ጋራ ፡ ተጋጥሞላቸው ፡ ቢሆንም ፡ መለኞችና ፡ ጠንቋዮች ፡ ያሰኛቸዋል ፡ ይሆናል ፡ ያለው ፡ ሳይሆን ፡ ቀርቶ ፡ ተመካሪው ፡ ሳይጐዳ ፡ በከሌ ፡ ምክር ፡ ነው ፡ እን



ዲህ ፡ የሆነው ፡ እየተባለ ፡ እንኳን ፡ ከተመካሪው ፡ ከወገኑ ፡ ሁሉ ፡ ያጣላዋል ፤ ያልተጐዳውም ፡ ሁሉ ፡ ይፈርድበታል ፤ በወንጌልም ፡ ከዚህ ፡ ከታናሾች ፡ አንዱን ፡ በምክሩ ፡ ያሳተ ፡ የወፍጮ ፡ ድንጊያ ፡ አስሮ ፡ ከባሕር ፡ ቢሰጥም ፡ ይሻለዋል ፡ የተባለው ፡ ይደርስበታል ።

ስለዚህ ፡ እንዲህ ፡ ብታደርግ ፡ እንዲህ ፡ ይሆናል ፡ የሚሉት ፡ እውነተኛ ፡ መካሮች ፡ አይባሉምና ፡ ባላየኸው ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ የመላ ፡ መካር ፡ ከመሆን ፡ አጥብቀህ ፡ ሽሽ ፡ እንጂ ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ለሚመጣ ፡ ነገር ፡ ሳይጠይቅህ ፡ መካሩ ፡ ልሁን ፡ አትበል ።

፻፵፱ ፤ ተመካሪው ፡ እየተከተለ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ለሚሠራው ፡ ሥጋዊ ፡ አናወሩ ፡ ምክርህን ፡ የሚሻ ብህ ፡ ሲሆን ፡ ገበሬ ፡ ዘሩን ፡ እግዚአብሔር ፡ ያበቅልልኛል ፡ ብሎ ፡ እንደሚዘራው ፡ ሁሉ ፡ አንተም ፡ እግዚአብሔር ፡ ይሠራልኛል ፡ ብለህ ፡ ታምነህ ፡ እንደ ፡ ዐዋቂ ፡ አድርገህ ፡ አንገና ፡ ምክሬን ፡ አላፊና ፡ ዐዋቂ ፡ ሳታደርገን ፡ ሃይማኖትህን ፡ አላፊ ፡ ፈጣሪህን ፡ ሠሪ ፡ የምታደርግ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ እንዲህ ፡ ብታደርግ ፡ ይሻል ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ አንተው ፡ አመዛዝነህ ፡ እንደ ፡ ማመንህ ፡ ልክ ፡ ሥራው ፡ እያልክ ፡ አላፊነቱን ፡ ከሱ ፡ ላይ ፡ እየጣልክ ፡ አነጋገሩንም ፡ ክፉ ፡ እሚያመጣ ፡ የመስለ ልክ ፡ አንጋገሩንም ፡ ይመስለኛል ፡ እንዲህ ፡ ይሆን ፡ አ ሆን ፡ እንዲህ ፡ ይመስለኛል ፡ እንዲህ ፡ ይሆን ፡ እ

ንደሆን ፡ በለው ። መልካም ፡ የመሰለህንም ፡ እንዲህ ፡ ቢሆን ፡ ይሻል ፡ ይመስለኛል ፡ እያልክ ፡ ንገረው ፤ ምከረው ። እሚሆነውም ፡ እንደሱ ፡ ማመን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንዳንተ ፡ ማወቅ ፡ አይሆንምና ፤ ገና ፡ በሚሆነው ፡ በሥጋዊ ፡ ነገር ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ደፍረህ ፡ ነው ፡ ይሆናል ፡ እያልክ ፡ አትከራከረው ፤ ፈልገህም ፡ ይሆንብሃል ፡ ሊሆንብህ ፡ ነው ፡ እያልክ ፡ አታስፈራው ። ጣፋጭ ፡ ጥበብ ፡ እይ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፩ ።

የሰው ፡ ገንዘብ ፡ ከሚወድና ፡ የራሱን ፡ ገንዘብ ፡ ከሚወድ ፡ የማናቸው ፡ ኀጢአት ፡ ለመብለጡ ፡

## ማወቂያ ።

፻፵ ፡ ገንዘብ ፡ አወዳድ ፡ ራሱ ፡ የያዘውንም ፡ ቢወድ ፡ ከሰውም ፡ ላይ ፡ እንዲመጣለት ፡ ቢወድ ፡ ሁለቱም ፡ ዐይነት ፡ ኀጢአት ፡ ነው ።

ከሁለቱ ፡ ግን ፡ እንዴ ፡ የሚበልጥ ፡ ኀጢአት ፡ ይሆናል ።

የራሱን ፡ ገንዘብ ፡ የሚወድ ፡ ቄይቶ ፡ ለልጄ ፡ እስካለሁም ፡ ለኔ ፡ ጠባቂ ፡ ይሁነኝ ፡ በማለቱ ፡ ኢታምልክን ፡ ያፈርሳል ።

የሱ ፡ ካመት ፡ ልብስ ፡ ከለት ፡ ጉርሥ ፡ ተርፎ ፡ ለማያውቀው ፡ ዘመን ፡ እያስቀመጠ ፡ የተፈጥሮ ፡



ወንድሞቹ ፡ እየተቸገሩ ፡ ዝም ፡ በማለት ፡ እፍቅር ፡ ቢጸከን ፡ ያፈርሳል ፤ በዚህ ፡ በ፪ቱ ፡ ዐይነት ፡ ኀጢአት ፡ ይሠራል ።

ሁለተኛው ፡ የሰው ፡ ገንዘብ ፡ የሚወድ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ፪ቱን ፡ ኀጢአት ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ ከዚህ ፡ የሚከፋ ፡ ዕጥፍ ፡ ኀጢአት ፡ ይሠራል ።

የሰው ፡ ገንዘብ ፡ የሚገኘው ፡

አንደኛ ፡ እታሎ ፡ በተንኰል ።

ሁለተኛ ፡ ተጋፍቶ ፡ በመበደል ።

ሦስተኛ ፡ ተበላልጦ ፡ ተለማምጦ ፡ በማባበል ።

አራተኛ ፡ የሚጠቅመውን ፡ መንፈሳዊ ፡ አሳብ ፡ ሁሉ ፡ ትቶ ፡ አሳቡንም ፡ ጕልበቱንም ፡ ለገንዘብ ፡ ተገዥነት ፡ ለውጦ ፡ ተግቶ ፡ በማገልገል ፡ እሊህን ፡ አራቱን ፡ ኀጣውእ ፡ ሳይሠራ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ የሰውን ፡ ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ አይቻለውምና ፤ እምጥቶ ፡ ለመውደድም ፡ ሲል ፡ ለመስጠትም ፡ ቢያደርገው ፡ የራሱን ፡ ገንዘብ ፡ ከሚወድ ፡ ሰው ፡ የሰውን ፡ ገንዘብ ፡ የሚወድ ፡ ኀጢአቱ ፡ እጅግ ፡ ይበልጣል ።

ጥያቄ ።

፻፵፩ ፡ ካንዱ ፡ እምጥቶ ፡ ላንዱ ፡ ቢሰጠውማ ፡ ካላስቀመጠው ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ኀጢአት ፡ ይሆንበታል ።

ምላሽ ።

፻፵፯ ፡ ጥንቱን ፡ ሥጋዊ ፡ ፈቃድ ፡ ያሸነፈው ፡ ካል ሆነ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ፈቃደኛ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ የሰውን ፡ ገንዘብ ፡ አይሻምና ፡ የሚፈልግበት ፡ በሥጋዊ ፡ ፈቃዱ ፡ ነውና ፡ የሚሰጠውም ፡ ሥጋዊ ፡ ጥቅም ፡ ለመሻት ፡ ነው ።

ያሰጣጡም ፡ ዐይነት ፡ ካራቱ ፡ ኀጣውእ ፡ አንዱን ፡ ሠርቶ ፡ ካንዱ ፡ አምጥቶ ፡ ላንዱ ፡ ሲሰጥ ፡ ወይ ፡ ሰው ፡ ወዶ ፡ ይጠቅመኛልን ፡ ወይ ፡ አመስግኖ ፡ ያወራልኛልን ፡ ወይ ፡ አጊጦ ፡ ያከብረኛልን ፡ ይህ ን ፡ ምስቱን ፡ የውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ ጓዝ ፡ ሳያስከትል ፡ ለመስጠት ፡ አይቻለውምና ፡ ያሰጣጡ ፡ እምነት ፡ ለኀጢአት ፡ ይሆንበታል ።

ጥያቄ ።

፻፵፰ ፡ የሰውንም ፡ ገንዘብ ፡ የራሱንም ፡ ገንዘብ ፡ መውደድ ፡ ምንም ፡ የኀጢአትነቱ ፡ መጠን ፡ አንዱ ፡ በልጦ ፡ አንዱ ፡ ቢያንስ ፡ ሁለቱም ፡ ኀጢ አት ፡ ከሆነ ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ ይሻላል ።

ምላሽ ።

፻፵፱ ፡ የሰውን ፡ ገንዘብ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ጥበብና ፡ በመጠንኛ ፡ ትጋትህ ፡ ካልመጣ ፡ በቀር ፡ በራስህ ፡ ብልጠት ፡ አለመሻት ፡ የራስህንም ፡ ገንዘብ ፡ ላን ተና ፡ ለቤት ፡ ሰብህ ፡ ካመት ፡ ልብስህና ፡ ቀለብ ፡



የሚተርፈውን ፡ ስጦታው ፡ በዝቶም ፡ እንዳያስመስ ግንህ ፡ አቈራረሱን ፡ አሳንስህ ፡ እንዳያዳርስ ፡ አ ክፍለህ ፡ ተርፎም ፡ ተቀማጭ ፡ እንዳይሆንብህ ፡ ለግሰህ ፡ በስጦታህም ፡ ምክንያት ፡ ከሰው ፡ ላይ ፡ የምትሻው ፡ ሳይኖር ፡ ገንዘብህን ፡ ያለምስጋና ፡ አውጥተህ ፡ ብትሰጠው ፡ ስጦታህም ፡ ሰው ፡ የሚ ጠላው ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚወደው ፡ ይሆናል ። አንተንም ፡ ወደ ፡ ፍጹም ፡ መንፈሳዊነት ፡ ያደርስ ሃልና ፡ እግዚአብሔር ፡ ገንዘብ ፡ በሰጠህ ፡ ጊዜ ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ብትሠራ ፡ ትድናለህ ።

ጥያቄ ።

፻፶ ፡ ያላደጉ ፡ ሕፃናት ፡ የደከሙ ፡ ወላጆች ፡ ስላ ሉት ፡ ሽማግሎች ፡ ዐርፈው ፡ ዐፈር ፡ እስኪለብሱ ፡ ሕፃናቱ ፡ አድገው ፡ ለሥራ ፡ እስኪደርሱ ፡ መጦ ርና ፡ ማሳደግ ፡ የታዘዘ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ለከብት ፡ ድር ቆሽ ፡ ዐጭዶ ፡ እንደ ፡ ማስቀመጥ ፡ ያለ ፡ ነውና ፡ ስለ ነሱ ፡ የሚያሻውን ፡ ማኖር ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ኀጢአት ፡ ይሆናል ።

ምላሽ ።

፻፶፩ ፡ ሲሆን ፡ ለኒህም ፡ አሳቢያቸው ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በነሱ ፡ አመካኝተህ ፡ ገንዘብ ፡ ባታኖር ፡ ይሻላል ። ወይም ፡ የማስቀመጥህ ፡ ምክ ንያት ፡ እነሱ ፡ ከሆን ፡ ለራስህ ፡ ሳታደርግ ፡ ስለ ፡ እነሱ ፡ መሻት ፡ አድርገውና ፡ ዐቅሙ ፡ አዳም ፡

ሳያደርሱ ፡ ቢሞቱም ፡ ለነሱ ፡ ፈንታ ፡ ያስቀመ ጥከውን ፡ ለነዳያን ፡ ስጥላቸው ፡ ሲያድጉና ፡ በቅ ሙ ፡ አዳም ፡ ሲያደርሱም ፡ ለነሱ ፡ ባልከው ፡ ገን ዘብ ፡ አንተ ፡ እንዳትከሎንንበት ፡ ለነሱ ፡ ስጣቸውና፡ እንዳወቁ ፡ ያድርጉት ።

(ታሪክ) ፡ መልአከ ፡ ብርሃን ፡ ሰላማ ፡ የጐንደር ፡ ሊቅ ፡ እጅግ ፡ ቸር ፡ ነበሩና ፡ ወዳጃቸው ፡ ምነው ፡ ገንዘብን ፡ እንዲህ ፡ አድርገው ፡ ይጠሉታል ፡ ቢላ ቸው ፡ እኔም ፡ ልጆቼም ፡ ወደምንሄድበት ፡ አስ ቀድሜ ፡ ብሰደው ፡ መውደዴ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ መች፡ ጠላሁት ፡ አሉ ፡ ይባላል ፡ እንሆ ፡ ይኸን ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ ልብ ፡ አድርገው ።

ምዕራፍ ፡ ፲፪ ።

## ስለ ፡ ጌትነት ፡ አለመጥቀም ።

ጥያቄ ።

፻፶፮ ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ጌትነት ፡ ጥቅሙ፡ ምንድነው ።

ምላሽ ።

፻፶፯ ፡ ምንም ፡ ጥቅም ፡ ትርፍም ፡ የለው ፡ ይልቁንም ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ጌትነት ፡ በሥጋው ፡ መጠላትን ፡ በነፍሱም ፡ መጐዳትን ፡ ያገኛል ፡ እንጂ ፡ ለሱ ፡ አንድም ፡ የሚጠቅም ፡ ነገር ፡ አያገኝበትም ።



ከንጉሡ ፡ በታች ፡ ከድኾች ፡ በላይ ፡ ያለው ፡ ጌት ነትማ ፡ እንደ ፡ ዕውቀቱ ፡ አዞና ፡ ሠርቶ ፡ እንዳይ ጸድቅ ፡ በላይ ፡ አዛዥ ፡ ያለበት ፡ ታዞ ፡ እንዳይጸ ድቅ ፡ በበታቹ ፡ ታዛዥ ፡ ያለበት ፡ ዐጉል ፡ አስኰ ናኝ ፡ ኑሮ ፡ ሆኖበት ፡ ይጐዳል ።

ጥያቄ ።

፻፵፱ ፡ በልቶ ፡ መጥገቡ ፡ ለብሶ ፡ ማጌጡ ፡ ሥቶ ፡ መ ጫወቱ ፡ ታጅቦ ፡ በመከበሩ ፡ ገንዘብ ፡ ሰጥቶ ፡ በ መወደዱ ፡ ጠላቱን ፡ በማጥቃቱ ፡ በሞቱ ፡ እስኪ ጠራ ፡ ድረስ ፡ የሚያገኘው ፡ ደስታ ፡ ሁሉ ፡ ትር ፉና ፡ ጥቅሙ ፡ አይሆንምን ።

ምላሽ ።

፻፶ ፡ ይህ ፡ የቈጠርከው ፡ ሁሉ ፡ አላዋቂ ፡ ባሕርይ ፡ ያሸነፈውን ፡ ሰው ፡ እጋንንት ፡ ጨርሰው ፡ የሚያ ደነቁሩበት ፡ ለሕፃናትና ፡ ለእንስሳት ፡ ጥላና ፡ ም ስል ፡ የቁም ፡ ነገር ፡ እየመሰለ ፡ እንደሚያታልላ ቸው ፡ ዕውቀትም ፡ ላጠራቸው ፡ ሰዎች ፡ እንስሳዊ፡ ባሕርያቸው ፡ እየተሸነፈ ፡ የሚጠቅም ፡ ይመስላ ቸዋል ፡ እንጂ ፡ ባዋቂዋ ፡ ነፍሳችን ፡ ጠባይ ፡ ከመ ረመርነው ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ጌትነት ፡ እንኳን ፡ ለነ ፍስ ፡ ለሥጋም ፡ ቢሆን ፡ ይጐዳል ፡ እንጂ ፡ አይጠ ቅምም ።

፻፶፩ ፡ የመብሉም ፡ ደስታ ፡ በራበው ፡ ጊዜ ፡ ካገ ኘው ፡ የድኻውም ፡ ጥና ፡ ውሃሬ ፡ የጌታውም ፡ የጣ

መና ፡ የላመው ፡ ምግብ ፡ ቢመገቡት ፡ ሁሉ ፡ ደስ
ታቸው ፡ እኩል ፡ ነው ።

፻፳፪ ፤ ከቶውንም ፡ የጌታው ፡ መብል ፡ የለመለመ ፡ በ
መሆኑ ፡ ቶሎ ፡ ይጠፋና ፡ በየጊዜው ፡ በመሻት ፡
ያባክነዋል ።

ያንኑም ፡ አለጠ ፡ ሖረጠ ፡ እያለ ፡ ለገዛ ፡ ምላሱ ፡ አገ
ልጋይ ፡ አድርጎ ፡ ያበሳጨዋል ።

የድኻው ፡ ጥሬ ፡ በመሆኑ ፡ ያቈያል ፤ ያጠናል ፤
ብዙውንም ፡ ጣርና ፡ ጕጕት ፡ ያስቀርለታል ።

የድኻው ፡ ምግብ ፡ ደረቅ ፡ ነውና ፡ ጥቂት ፡ ጥቂት ፡
መጠጥ ፡ በቅቶት ፡ በጤና ፡ ይውላል ።

ጌታው ፡ ግን ፡ ቅመምና ፡ ጨውን ፡ ሁሉ ፡ ሰብስቦ ፡
በመብላቱ ፡ መጠጥ ፡ ጥሙን ፡ አላቀምለት ፡ እያለ፡
ከመጠጡ ፡ ላይ ፡ በያይነቱ ፡ መርዝ ፡ ወይም ፡ ጌሾ
ን ፡ እየቀላቀለ ፡ እየጠጣ ፡ ልቡን ፡ እያፈረሰ ፡ በደ
ዌ ፡ በሞት ፡ ከድኻው ፡ ይቀድማል ።

ከምግቡ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ሥጋውን ፡ አለስልሶ ፡
የቁም ፡ እስረኛ ፡ የባለጤና ፡ ሕመምተኛ ፡ ያደር
ገዋል ።

ይህም ፡ ባይሆን ፡ ጥጋቡ ፡ ሰው ፡ ያስንቀዋል ፤
ሰካሩም ፡ ከእግዚአብሔርና ፡ ከሰውም ፡ ሁሉ ፡ ያጣ
ላዋል ።



፻፳፫ ፤ ይህነኑም ፡ የሆድ ፡ ደስታ ፡ የምትሻው ፡ ከሆን ፡
ያለጌትነት ፡ በርሻ ፡ ትጋትም ፡ ብቻ ፡ የሚገኝ ፡
ነውና ፤ ሆድ ፡ ጌትነት ፡ የሚያሻው ፡ አለመሆኑን ፡
እስተውል ።

ስለ ፡ ልብሱም ፡ ከሱ ፡ አብልጦ ፡ ያጌጠ ፡ ሲያይ ፡
አሳቡን ፡ ቀናተኛ ፡ ተረማማጅ ፡ አድርጎ ፡ ገንዘ
ቡን ፡ ያስበትነዋል ።

እንደሱ ፡ አድርጎ ፡ ለማጌጥ ፡ ያልቻሉትንም ፡
አብሮም ፡ ለመብላት ፡ አብሮም ፡ ለመሄድ ፡ ባጠ
ገባቸውም ፡ ለመቀመጥ ፡ ያሳፍረዋል ፤ እነሱንም ፡
ያስንቀዋል ።

ይህን ፡ የመልበሱ ፡ ደስታ ፡ ጥቅም ፡ መስሎህ ፡ እ
ለማወቅም ፡ ቢያሸንፍህ ፡ ያለጌትነት ፡ ባዝማሪነ
ትና ፡ በካህንነት ፡ ብቻ ፡ የሚገኝ ፡ ለማጌጥ ፡ ጌት
ነት ፡ ብቻ ፡ የሚያሻው ፡ አለመሆኑን ፡ አስተውል ።

፻፳፬ ፤ ስለ ፡ ሣቂና ፡ ስለ ፡ ደስታውም ፡ ጥቅም ፡ እንዳይ
ሆንው ፡ የደስታ ፡ ደንብ ፡ ግብሩ ፡ ቶሎ ፡ በሐዘን ፡
የሚለወጥ ፡ ነውና ፡ የሚመጣበትም ፡ ሐዘን ፡ ይፈ
ጥንበታል ፡ እንጂ ፡ ላቡን ፡ እያንቈረቈረ ፡ ከንፈ
ሩን ፡ በሣቅ ፡ እያንፈራፈረ ፡ በማይረባ ፡ ደስታ ፡
ከመድከም ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ አይረባም ።

ይኸውም ፡ ልጆችም ፡ ቧልተኞችም ፡ ሁሉ ፡ የሚ
ያደርጉት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ጌትነት ፡ የሚያሻው ፡
አይደለም ።

፻፳፭ ፡ ሲታጀብም ፡ ለሱ ፡ ክብር ፡ የሚመስለው ፡ አጃቢው ፡ ለራሱ ፡ ጉዳይ ፡ የተሰበሰበ ፡ መሆኑን ፡ እየረሳው ፡ ነው ።

ለገዛ ፡ ጉዳዩ ፡ መጥቶ ፡ በገዛ ፡ እግሩ ፡ የሚሄድን ፡ ሰው ፡ ለኔ ፡ ክብር ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መኵራት ፡ ባለ ማወቁ ፡ መሰለው ፡ እንጂ ፡ የሱ ፡ ጥቅም ፡ የለበ ትም ።

ከኋላ ፡ በመታጀቡ ፡ የከበርኩ ፡ እንዳይመስለው ፡ እሱ ፡ ከፊቱ ፡ ላሉት ፡ ተከታይ ፡ ነው ።

እፊቱ ፡ ከቀደሙት ፡ እኋላ ፡ በመሆኑ ፡ የከበርኩ ፡ እንዳይመስለው ፡ እሱም ፡ ከኋላው ፡ ላሉት ፡ ቀዳ ሚ ፡ ነው ።

ከመካከል ፡ በመሄዱ ፡ የከበርኩ ፡ እንዳይመስለው፡ ከቀደመና ፡ እኋላ ፡ ከቀረው ፡ መካከል ፡ የሚሄዱ ፡ ብዙ ፡ ናቸው ።

እንግዲህ ፡ ጌታ ፡ ነኝ ፡ የሚለው ፡ ሰው ፡ ከሚያጅ ቡት ፡ የሚበልጥበት ፡ ጥቅም ፡ በውሸት ፡ መም ሰል ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ በውነትስ ፡ ትርፍም ፡ ጥቅ ምም ፡ የለውም ።

ይኸም ፡ ጭቃ ፡ ሹሞች ፡ በያመቱ ፡ ነጋድራሶች ፡ በየሳምንቱ ፡ ሹመታቸው ፡ ለየጉዳዩ ፡ በመጣው ፡ ሰው ፡ ያለጌትነት ፡ ሊታጀቡ ፡ መቻላቸውን ፡ አስ ተውል ።



፻፳፮ ፡ ገንዘብ ፡ በመሰብሰቡም ፡ ያንኑም ፡ ሲተሰበሰ በው ፡ ሰው ፡ እያካፈለ ፡ በመስጠቱም ፡ ጌታና ፡ ባለ ገንዘብ ፡ ነኝ ፡ ቢመስለው ፡ ይህንም ፡ ባለማወቅ ፡ ያስባል ።

አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ሌባም ፡ ወንበዴም ፡ እሳ ትም ፡ በመዓት ፡ እየታዘዘ ፡ የበላይም ፡ ዳኛ ፡ እያ ዳላም ፡ እየተቈጣም ፡ በጠፉ ፡ ቍጥር ፡ ሲያሳዝ ነው ፡ ይኖራል ።

ከዚህም ፡ ሁሉ ፡ ጥፋት ፡ ተርፎ ፡ ለሰውም ፡ የሚ ሰጥ ፡ ሀብታም ፡ ቢሆን ፡ ምስለኔ ፡ በሚሰበስበው ፡ አሳላፊ ፡ በሚያካፍለው ፡ ዕቃ ፡ ቤት ፡ በሚጠብ ቀው ፡ ጌታም ፡ ነን ፡ ባለገንዘብም ፡ ነን ፡ ለማለት ፡ እንደማይገባቸው ፡ ጌታ ፡ በሆነ ፡ ሰውም ፡ እጅ ፡ ያለ ፡ ገንዘብ ፡ ፈጣሪው ፡ እግዚአብሔር ፡ ደክሞ ም ፡ የሰበሰበው ፡ ባለቤቱ ፡ ባላገርና ፡ ነጋዴ ፡ ነው ና ፡ ከነሱ ፡ እየወሰደ ፡ ለወታደሩ ፡ ቢያካፍለው ፡ እ ያስቀመጠም ፡ ቢያየው ፡ ጌታውና ፡ ባለገንዘቡ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ሲልም ፡ ይዋሻል ።

፻፳፯ ፡ ይልቁንም ፡ እንደ ፡ ባለገንዘቡ ፡ ሁኖ ፡ ሲሰ ጥም ፡ ባሰጣጥ ፡ በማድላቱ ፡ ሳይሰጥም ፡ በማካ በቱ ፡ ከሚቀበለው ፡ ከባላገሩ ፡ በማታለሉና ፡ በመ ቀማቱ ፡ በሥጋው ፡ ርግማንን ፡ ለነፍሱ ፡ የዘለ ዓለም ፡ ሞትን ፡ ያተርፋል ።

ገንዘቡንም ፡ ይረባኛል ፡ መስሎህ ፡ ፈላጊው ፡ ከሆንክ ፤ ያለጌትነት ፡ በብልጠት ፡ ብቻ ፡ ነግዶና ፡ አታሎ ፡ ያገኛል ።

፻፳፰ ፤ ስለ ፡ ጌትነቱም ፡ ጠላትን ፡ በመጕዳቱ ፡ ደስ፡ የሚለው ፡ በሬና ፡ በሬ ፡ ተዋግቶ ፡ በሬውን ፡ በሬ ፡ ሲያሸንፈው ፡ ደስ ፡ እንደሚለው ፡ እንስሳ ፤ እንደሱ ፡ ያለውን ፡ ወንድሙን ፡ በጕዳ ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ የሚለው ፡ በእንስሳዊ ፡ ጠባዩ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ለዐዋቂዋ ፡ ነፍሱ ፡ ደስታዋ ፡ አይደለም ።

እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ቂመኛነቱና ፡ ስለ ፡ ጠላት ፡ አለመውደዱ ፡ ይጠላዋል ።

በሥጋው ፡ ከጠላቱ ፡ ወገን ፡ ጋራ ፡ በቍርጥ ፡ ተለያይቶ ፡ ደሙን ፡ ለልጁ ፡ አትርፎ ፡ ለሱና ፡ ለዘሩም፡ የደምና ፡ የጠብ ፡ ቅርስ ፡ ሁኖ ፡ ይጐዳዋል ።

ስለዚህ ፡ ጌትነት ፡ ባለመመርመሩ ፡ የገዛ ፡ ራሱን በማታለሉ ፡ ጥቅም ፡ ይመስለዋል ፡ እንጂ ፤ በውነት ፡ ስትመዝነው ፡ በውቀት ፡ ስትመረምረው ፡ ምንም ፡ ጥቅም ፡ የሌለው ፡ ጕዳት ፡ ብቻ ፡ የሆን ፡ የውሸት ፡ ሥራ ፡ መሆኑን ፡ በነዚህ ፡ ተመራምረህ ፡ አስተውለው ።

ይኸውም ፡ ሰው ፡ አጥቅቶ ፡ መጕዳትን ፡ ከቻኸው ፡ ሌባ ፡ ወንበዴም ፡ ተንኰለኛም ፡ ሆኖ ፡ ያለጌትነት ፡ ሊሠራ ፡ መቻሉን ፡ እስተውል ።

ፍኖተ ፡ አእምሮ ፡ (የዕውቀት ፡ ጎዳና) ። 

(ጥያቄ) ።  በጠቅላላው ፡ በየስማቸው ፡ ዐዋጅ ፡ ሲጠሩ ፡ ሹመት ፡ ሺ ፡ ሞት ፡ ማጣት ፡ ድኅነት ፡ በመባሉ ፡ ጌትነት ፡ በሞት ፡ ስም ፡ ማጣት ፡ በሕይወት፡ ስም ፡ መጠራታቸው ፡ ያስረዳሃልና ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ጌትነት ፡ ሺ ፡ ሞት ፡ ተባለ ።
(ምላሽ) ።  የተሾመ ፡ ሰው ፡ የተሾመባቸውን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ መጠበቁ ፡ በነሱ ፡ ኀጢአት ፡ እሱ ፡ እሚቀጣበት ። ስለ ፡ ገንዘቡም ፡ ሲመቻቸው ፡ ሌቦች ፡ የሚያታልሉት ፡ ወንበዶች ፡ የሚያደበድቡት ፡ ምቀኞች ፡ የመከሰሻ ፡ ዳኞች ፡ የመውረሻ ፡ ምክንያት ፡ እየፈለጉ ፡ እኒህ ፡ ሁሉ ፡ ዙሪያውን ፡ ከበው ፡ እያስጨነቁ፡ በተነሶላ ፡ መኻል ፡ እንዳለ ፡ በግ ፡ አድርገው ፡ በብዙ ፡ ጦር ፡ እየወጉ ፡ በብስጭት ፡ የሚገድሉት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ጥያቄ ።

፻፳፱ ፤ ድኻንስ ፡ ማጣት ፡ ይገድለው ፡ የለምን ፡ ስለ፡ ምን ፡ ደኅንነት ፡ ተባለ ።

ምላሽ ።

፻፴ ፤ ድኻን ፡ የሚገድለው ፡ አንድ ፡ የችጋር ፡ ጸር ፡ ነው ፤ ለዚያውም ፡ ሰውም ፡ እግዚአብሔርም ፡ እያዘንለት ፡ ነው ፡ በድኽነቱ ፡ ላይ ፡ ቅሌት ፡ ጨምሮ ፡ ጕጉ ፡ ካልሆነም ፡ የፈጣሪም ፡ ሰው ፡ እምላክ ፡ ነዳያን ፡ ነው ፤ ስለ ፡ ድኽነቱ ፡ እምላኩ ፡ በሁሉም ፡ እየረዳው ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ አውጥቶ ፡ መንግሥት ፡ ሰማይ ፡ የሚያገባው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

## ስለ ፡ ምስጢረ ፡ ሥላሴ ፡ የማየት ፡ ምርምር ።

፻፸፩ ፡ ያካላቸውን ፡ ሦስትነት ፡ የባሕርያቸውን ፡ አንድነት ፡ የሚነግሩህን ፡ መጻሕፍት ፡ ስታነብ ፡ አካላቸውን ፡ ካላየሁ ፡ ባሕርያቸውን ፡ ካልመዘንኩ ፡ እንዴት ፡ አድርጌ ፡ እጸናለሁ ፡ እንዳትል ፡ እየታዩ ፡ የሚያጸኑህ ፡ የሚያስረዱ ፡ ስድስት ፡ ነገሮች ፡ አሉ ፡ ልሀና ፡ በነሱ ፡ ተመራምረህ ፡ ዕወቅ ።

አንደኛ ፡ የልቡናቸውን ፡ ኃይል ፡ ለማወቅ ፡ ስትሻ ፡ ሁሉን ፡ በመፍጠራቸው ፡ እንድታይ ፡ ሰውና ፡ እንስሳ ፡ አዝርዕትና ፡ አትክልት ፡ አንድ ፡ ከብዙ ፡ እየተከፈለ ፡ ሲረባ ፡ ታያለህ ፤ ፀሓይና ፡ ጨረቃ ፡ ብርሃንና ፡ ጨለማ ፡ ነፋስና ፡ ሙቀት ፡ በጋና ፡ ክረ ምት ፡ ማፈራረቃቸውን ፡ ያሳይሃልና ፡ እነዚህም ፡ ሥራ ፡ ናቸውና ፡ ያለሠሪ ፡ እንዳይሠሩ ፡ በዚህ ፡ አስተውል ።

ሁለተኛ ፤ የቃላቸውን ፡ ኃይል ፡ ለማወቅ ፡ ስትሻ ፡ በሁሉ ፡ በመፍረዳቸው ፡ እንድታይ ፡ በገፊና ፡ በተገፊ ፡ ላይ ፡ ብድር ፡ ሲያመላልሱ ፡ በደካማው ፡ እጅ ፡ ኃይለኛውን ፡ ሲቀጡ ፡ ዘወትር ፡ ታያለህና ፡ በዚህ ፡ አስተውል ።

ሦስተኛ ፤ የእስትንፋሳቸውን ፡ ኃይል ፡ ለማወቅ ፡ ስትሻ ፡ ለሁሉ ፡ በመስጠታቸው ፡ እንድታይ ፡



የሌለውን ፡ ድኻ ፡ ሲያበለጽጉ ፡ ጌታ ፡ ሲያደርጉ ፡ ጌታ ፡ ባለጸጋ ፡ የነበረውን ፡ አዋርደው ፡ አደኸይ ተው ፡ ድኻ ፡ ለነበረው ፡ ሲያስገዙ ፡ ዕውቀት ፡ ያ ልነበረውን ፡ ሕፃን ፡ እያሳደጉ ፡ ዕውቀት ፡ ሲሰጡ ፡ ዕውቀት ፡ ከነበረው ፡ ሽማግሌ ፡ ላይ ፡ እየወሰዱ ፡ አላዋቂ ፡ ሲያደርጉ ፡ ዘወትር ፡ ታያለህና ፤ በዚህ ፡ አስተውል ።

፻፸፪ ፡ አንድ ፡ የሚያደርጋቸው ፡ የአምላክነታቸው ፡ የሚታየን ፡ ሥራቸው ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለው ፡ ነው ። የሥራ ፡ ሁሉ ፡ መደቡ ፡ ዕውቀት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ላን ድነት ፡ ባሕርዩም ፡ መሠረቱ ፡ ሁሉን ፡ ማወቅ ፡ ነው ።

ይህን ፡ አንዱን ፡ ዕውቀቱን ፡ ሦስት ፡ በይነት ፡ ሥራው ፡ ያስረዳናል ።

አንደኛ ፡ ወንድ ፡ በሴት ፡ ማሕፀን ፡ ዘሩን ፡ ሲዘ ራ ፡ እንኳን ፡ ሌላው ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ ያላየውን ፡ ዘር ፡ እሱን ፡ ዐውቆ ፡ መልክ ፡ ቀርጾ ፡ ከተሰወረበት ፡ ማሕፀን ፡ አውጥቶ ፡ የዘራውን ፡ አስመስሎ ፡ ያሳየ ናል ፡ ይህ ፡ ዐውቆ ፡ መሥራቱን ፡ ያሳውቀናል ።

ሁለተኛም ፡ በየጊዜው ፡ ሁሉ ፡ ሰው ፡ ተሰውሮ ፡ የሚሠራውን ፡ ጽድቅና ፡ ኀጢአት ፡ ሠርቶ ፡ አል ሠራሁም ፡ ብሎ ፡ እንኳን ፡ በስሙ ፡ በባሮቹም ፡ ስም ፡ ቢሆን ፡ በማለ ፡ ጊዜ ፡ ባየው ፡ መስክሮ ፡ ቅጣት ፡ በመፍረዱ ፡ ሁሉን ፡ ማየቱን ፡ ያስረዳናል ።

ሦስተኛ ፡ የሚገባንን ፡ ስንለምን ፡ የሻነውን ፡ በመ

ስጠቱ ፡ ስንበድልም ፡ የተበዳዩንም ፡ ጩኸት ፡ ሰምቶ ፡ በዳዩን ፡ ቀጥቶ ፡ በማሳየቱ ፡ ሁሉን ፡ መስ ማቱን ፡ ያሳምነናል ።

፻፳፫ ፡ እሊህም ፡ ሁሉ ፡ በልማድ ፡ የሚሠሩ ፡ እንዳይ መስለን ፡ ለፍጥረቶችም ፡ ቅርጻቸው ፡ የሥራዎችም ፡ ዐይነታቸው ፡ የሚለዋወጡ ፡ ሥራዎች ፡ ናቸው ። ተለዋዋጭ ፡ ሥራም ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ሠሪ ፡ ያስፈል ጋቸዋል ።

ሠሪም ፡ እንዲያስፈልጋቸው ፡ ስናውቅ ፡ ሥራ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ሠሪ ፡ እንዳለው ፡ በግልጥ ፡ እያስረዳ ፡ ያሳምነናል ።

ስለዚህ ፡ ፍጡር ፡ ፈጣሪውን ፡ በሥራው ፡ ብቻ ፡ ሊያምነው ፡ ሊረዳው ፡ ሊያውቀው ፡ ይችላል ።

ይህም ፡ የተቈጠረው ፡ ስድስቱ ፡ ዐይናችን ፡ የማ ያየው ፡ ያለሠሪ ፡ የማይሠራ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ከአብርሃም ፡ ዠምረው ፡ አባቶቻችን ፡ ሁሉ ፡ በሥራው ፡ ተመራ ምረው ፡ ሠሪውን ፡ አምላክ ፡ እንዳወቁት ፡ እኛም ፡ ባስተዋይ ፡ ልቡና ፡ ከመረመርነው ፡ በሥራው ፡ ብቻ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ልናምነውና ፡ ልናውቀው ፡ እንችላለንና ፡ ሃይማኖትህ ፡ የመስማት ፡ ብቻ ፡ የ ሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እፍኢዊና ፡ ግብዝ ፡ ሃይማኖት ፡ እንዳይሆንብህ ፡ በመስማትህ ፡ ላይ ፡ የፈጣሪህን ፡ ሁሉን ፡ ቻይነቱን ፡ በሥራው ፡ እየመረመርኽ ፡ ማ ወቅን ፡ ጨምርበት ።



ጥያቄ ።

፻፳፬ ፡ ስንምል ፡ ስንለምን ፡ ስናምንለ ፡ የምንጠራብ ት ፡ ስመ ፡ አምላክ ፡ ስንት ፡ ነው ።

ምላሽ ።

፻፳፭ ፡ ዐይነቱ ፡ ስምንት ፡ ነው ፤ ከዚሁ ፡ አራቱ ፡ ዐይ ነት ፡ የሚቈጠሩ ፡ አራቱ ፡ ዐይነት ፡ በቍጥር ፡ ያ ልተወሰኑ ፡ ናቸው ።

ጥያቄ ።

፻፳፮ ፡ የሚቈጠሩት ፡ ስሞች ፡ ማን ፡ ማን ፡ ይባላሉ ።

ምላሽ ።

፻፳፯ ፡ አንደኛ ፡ ስመ ፡ ተጸውዖ ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሥላሴ ፡ ኢየሱስ ፡ ዐማኑኤል ፡ መድኀኔ ፡ ዓለም ። እሊህ ፡ ፰ቱ ፡ ስሞች ፡ እንዲሰገድባቸው ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ የታነጸባቸው ፡ እንዲከበሩ ፡ የበ ዓል ፡ ቀን ፡ የተለየባቸው ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ የመጠሪያ ፡ ስም ፡ ይባላሉ ።

ትርጕሙ ፡ ይኸው ፡ ሁኖ ፡ በዕብራይስጥም ፡ ስም ፡ ሁነው ፡ የተቈጠሩ ፡ አሉ ፡፡ በግእዛችንም ፡ ስም ፡ ጠርተን ፡ ብንሰግድ ፡ በዕብራይስጥም ፡ ስሙን ፡ ጠርተን ፡ ብንሰግድ ፡ ሁሉም ፡ አንድ ፡ ነው ።

እኒሁም ፡ አልፋ ፡ ወዖ ፡ ቤጣ ፡ የውጣ ፡ ትስቡጣ ፡ አብኖዲ ፡ ታእስ ፡ አልሻዳይ ፡ ናቸው ፡ ስመ ፡ ተከ ፃቶ ፡ ናቸው ።

ይኸው ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ ባንድነቱ ፡ ወልደ ፡ አብ ፡ በተወላዲነቱ ፡ ጰራቅሊጦስ ፡ በሠራጺነቱ ፤ ቃለ ፡ አብ ፡ በነባቢነቱ ፤ መለኮት ፡ በገዢነቱ ፤ ክርስቶስ ፡ በቅቡዕነቱ ፤ ወልደ ፡ ማርያም ፡ በልጅነቱ ። እሊህ ፡ ጊቱ ፡ ስሞች ፡ ቅዱሳን ፡ ስለ ፡ ተረጐሟቸው ፡ ምስጢር ፡ የተገለጸባቸው ፡ ስሞች ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ የመታወቂያ ፡ ስም ፡ ይባላሉ ።

ስመ ፡ ግብር ። ፈጣሪ ፡ በመሥራቱ ፤ ጠቢብ ፡ በመጠበቡ ፡ ኄር ፡ በመስጠቱ ፤ መሐሪ ፡ በመማሩ ፤ ከሃሊ ፡ በሁሉ ፡ ቻይነቱ ፤ ፈታሒ ፡ በመፍረዱ ፤ ኖላዊ ፡ በመጠበቁ ፤ ሠዋዒ ፡ በመሠዋቱ ። እሊህ ፡ ጊቱ ፡ ስሞች ፡ ሥራ ፡ የታየባቸው ፡ ግብር ፡ የተገለጸባቸው ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ የግብር ፡ ስም ፡ ይባላሉ ።

ስመ ፡ እንክር ። መንክር ፡ በድንቅነቱ ፤ ሕያው ፡ በነዋሪነቱ ፤ ቅዱስ ፡ በልዩነቱ ፤ ዐቢይ ፡ በትልቅነቱ፤ ጸባኦት ፡ ላሸናፊ ፡ ጌትነቱ ፤ ምሉእ ፡ በምሉእነቱ ፤ ፍጹም ፡ በውነተኝነቱ ፤ ኀያል ፡ ለኃይለኝነቱ ። እሊህ ፡ ጊቱ ፡ ስሞች ፡ ምስጢሩን ፡ ከሚያዩቱ ፡ ወዳጆቹ ፡ የድንቅነቱ ፡ ስሞች ፡ ስለ ፡ ተባሉ ፡ የመደነቅ ፡ ስም ፡ ይባላሉ ።



ጥያቄ ።

፻፸፯ ፤ በቍጥር ፡ የማይወሰኑት ፡ ስሞችስ ፡ ማን ፡ ማን ፡ ይባላሉ ።

ምላሽ ።

፻፸፯ ፤ አንደኛ ፤ እንደ ፡ አሌፋት ፡ እንደ ፡ ኢልመክኑን ፡ ያለው ፡ በየዓለሙ ፡ ቋንቋ ፡ ሁሉ ፡ የሚጠራበት ፡ ትርጓሜው ፡ የታወቀም ፤ ያልታወቀም ፡ ኅቡእ ፡ ስም ፡ የሚባለው ፡ ነው ።

ሁለተኛ ፤ እንደ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ እንደ ፡ እግዚእ ፡ አጋዕዝት ፡ እንደ ፡ ልዑል ፡ እምልዑላን ፡ ያለው ፡ የእንጻር ፡ ስም ፡ የሚባለው ፡ ነው ።

ሦስተኛ ፤ እንደ ፡ ፀሐየ ፡ ጽድቅ ፡ እንደ ፡ ብርሃን ፡ ዘበእማን ፡ ያለው ፡ የምሳሌ ፡ ስም ፡ የሚባለው ፡ ነው ።

አራተኛ ፤ እንደ ፡ አምላኪየ ፡ እንደ ፡ ጸወንየ ፡ ያለ ፡ የተጋንዮ ፡ ስም ፡ የሚባለው ፡ ነው ።

እሊህ ፡ አራቱ ፡ ወሰን ፡ ለሌለው ፡ ፍቅሩ ፡ ብዙዎች ፡ ወዳጆቹ ፡ እንዳደረጉላቸው ፡ ክብር ፡ እንደየሚወዱት ፡ ፍቅር ፡ የሰየሙት ፡ የሚሰይሙት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የተወሰነ ፡ ቍጥር ፡ የለውም ።

ጥያቄ ።

፻፸፰ ፤ እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ ከመ ፡ ለስሙ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ይስግድ ፡ ኵሉ ፡ ብርክ ፡ በተባለው ፡ ትእዛዝ ፡ ለማናቸው ፡ ስሙ ፡ መስገድ ፡ ይገባናል ።

## ምላሽ ።

፫፻፮ ፡ ስም ፡ ማለት ፡ መጠሪያ ፡ ነው ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ታንጾበት ፡ በዓል ፡ ተለይቶበት ፡ መጠሪያ ፡ ለሆነው ፡ ለጽላቱ ፡ ስም ፡ መስገድ ፡ ይገባል ። ከተቻለህ ፡ ግን ፡ ለሁሉም ፡ ዐይነት ፡ ብትሰግድበት ፡ የምትሰግድበት ፡ ስለ ፡ አምላክ ፡ ከሆን ፡ ሁሉም ፡ እንደያይነቱ ፡ ስሙ ፡ ነውና ፡ ስገድበት ፡ (ማዕመ ፡ ጸሎት ፡ ም ፡ ፬ ፡ ፳) ፡ እይ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፬ ።

ስው ፡ ያናዎሩን ፡ እሳብ ፡ ለፈጣሪው ፡ የሚሰጥበት ፡ መንገድ ።

## ጥያቄ ።

፫፻፯ ፡ ለሰው ፡ ምን ፡ ኑሮ ፡ ይሻለዋል ፤ ተፈጥሮውም ፡ መኖሪያውም ፡ ከንቱ ፡ የሚሠራውም ፡ ሁሉ ፡ የሚመሳለስ ፡ እንጂ ፡ የማይጨረስ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እሳቡን ፡ ከምን ፡ ላይ ፡ ሊያቆመው ፡ ሥራውንስ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ አድርጎ ፡ ሊሠራው ፡ ይገባል ።

## ምላሽ ።

፫፻፰ ፡ ለሁሉ ፡ ነገር ፡ ሠራተኛው ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በውቀህ ፡ በማግኘት ፡ በማጣት ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በሚሆነው ፡ በሁሉ ፡ ነገር ፡ የሚያስከፋ



ህም ፡ የሚያስደስትህም ፡ የሚያስጨንቅህም ፡ ነገር ፡ አይኑር ። ይልቁንም ፡ ሰው ፡ የእግዚአብሔር ፡ መጣሪያ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ የሚሠራው ፡ ነገር ፡ የለምና ፡ ሰው ፡ በሠራብህ ፡ ሁሉ ፡ አትበሳጭ ፡ ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሠራ ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ መከፋትና ፡ መደሰት ፡ አይገባም ።

## ጥያቄ ።

፫፻፱ ፡ እንግዲያውስ ፡ ሰው ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ክፉና ፡ በጎ ፡ ካልሠራ ፡ ለምን ፡ ይኰንናል ።

## ምላሽ ።

፫፻፲ ፡ የሰው ፡ ሥራው ፡ ያሳብ ፡ መጣሪያ ፡ ነውና ፡ ሰው ፡ ባሳቡ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በሥራው ፡ አይፈረድበትም ። ይህን ፡ ልትረዳ ፡ ብትሻ ፡ የዮፍታሔና ፡ ጲላጦስ ፡ አባ ፡ መቃሪና ፡ አባ ፡ ግሉሲ ፡ የሚታየው ፡ ሥራቸው ፡ የማይገባ ፡ ሲሆን ፡ በማይታየው ፡ እሳባቸው ፡ እንደ ፡ ተጠቀሙ ፡ ሄሮድስ ፡ የታየው ፡ የተሰማው ፡ መሐላ ፡ ማክበሩ ፡ የሚገባ ፡ ሲሆን ፡ ባልታየው ፡ እሳቡ ፡ መሐላ ፡ ያከበረበት ፡ በምክንያቱ ፡ ለተድላ ፡ ሥጋው ፡ ሲል ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ባሳቡ ፡ መጐዳቱንና ፡ መጐዳቱን ፡ የዮፍታሔም ፡ ሰው ፡ መሠዋቱንና ፡ ያባ ፡ መቃሪና ፡ ያባ ፡ ግሉሲም ፡ በጾም ፡ ሥጋትን ፡ መብላት ፡ የታየው ፡ ሥራቸው ፡ የማይገባ ፡ ሲሆን ፡ የማይታየው ፡ እሳባቸው ፡ የተሠራበት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በመሆኑ ፡ መጠቀማቸው ። የእግዚአብሔ

ር ፡ ቸርንትና ፡ ፍርድ ፡ የሰውን ፡ ቍርጥ ፡ አሳቡን ፡ እንጂ ፡ የሚታይ ፡ ሥራውን ፡ ብቻ ፡ እለመከተሉን ፡ አስተውል ። ስለዚህ ፡ አቅረብኩ ፡ ለከ ፡ እሳተ ፡ ወማየ ፡ ደይ ፡ እዴከ ፡ ኀበ ፡ ዘፈቀድከ ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሰው ፡ አሳብ ፡ ፈቃድ ፡ ስጥቶታልና ፡ ሰው ፡ የሚፈርድበት ፡ ከመልካም ፡ ክፋውን ፡ መርጦ ፡ ለመሥራት ፡ ሲፈቅድ ፡ አሳቡንና ፡ ምኞቱን ፡ እግዚአብሔር ፡ ያውቀውና ፡ በባለክፋው ፡ አሳብ ፡ የጠሳውን ፡ ይቀጣበታል ። የሚያጸድቀውን ፡ መከራ ፡ ያስቀብልበታል ። በባለመልካሙ ፡ አሳብ ፡ የወደደውን ፡ ይጠቅምበታል ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ ሰውን ፡ ወዶ ፡ ለመጥቀም ፡ ጠልቶ ፡ ለመጉዳት ፡ ሠርቶ ፡ ለማስደሰት ፡ አይችልም ። ስለዚህ ፡ በሰው ፡ በደለኝ ፡ ብሎ ፡ መከፋትን ፡ ወደደኝ ፡ ብሎም ፡ መደሰትን ፡ ስትተወው ፡ በጤና ፡ ነዋሪ ፡ ባሕሪህም ፡ ያማረ ፡ ይሆናል ።

ይህ ፡ ሊታወቅ ፡ ኢትክሉ ፡ ገቢረ ፡ ወኢምንተኒ ፡ ዘእንበሌየ ፡ ብሎ ፡ የሰውን ፡ መሣሪያነት ፡ አስረድቶናል ፡ (ጣዕመ ፡ ጸሎት ፡ ም ፡ ፲) ።

ጥያቄ ።

፻፺፯ ፡ እባዲያ ፡ መሣሪያስ ፡ ቢሆን ፡ ግዕዛን ፡ የሌለው ፡ መሣሪያ ፡ እንኳ ፡ እስኪሠራበት ፡ ድረስ ፡ ወይ ፡ ከምድር ፡ ወይ ፡ ከሣጥን ፡ ማረፍ ፡ ያስፈልገዋል ፡ እንጂ ፡ እንዲያው ፡ ከጎዋጉው ፡ ላይ ፡ መቀመጥ ፡ አይቻለውም ። ሰው ፡ እግዚአብሔር ፡ እስኪሠራለትም ፡ እስኪሠራበትም ፡ ቢሆን ፡ አሳቡን ፡ ከምን ፡ ላይ ፡ ሊያደርሰው ፡ ይገባል ።



ምላሽ ።

፻፺፯ ፡ ጌታ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ፍርድና ፡ እውነትን ፡ ከነዘዴያቸው ፡ ይፈልግ ፡ እንጂ ፡ ሌላው ፡ የጌትነት ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ከነቱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይወቅና ፡ አሳቡንና ፡ ምኞቱን ፡ ከዳኘነት ፡ ላይ ፡ ያድርገው ።

ሎሎቹንም ፡ ለጌትነት ፡ የሚሻቸውን ፡ ከንቱዎችን ፡ የንብረት ፡ ሥራዎች ፡ እንዳያስጨንቁት ፡ ለበታቾቹ ፡ ሰዎች ፡ አካፍሎ ፡ ያሠራቸው ።

እሱም ፡ ለቀን ፡ ሥራ ፡ ዕረፍቱ ፡ ሌሊት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለቱም ፡ ነገሩም ፡ ዳኘነት ፡ ከንቱውን ፡ ንብረት ፡ እያሰቡና ፡ እያዩ ፡ መደሰት ፡ ዕረፍቱ ፡ ነውና ፡ ዳኘነቱንም ፡ ስልችተህ ፡ እንዳትዘነጋ ፡ የንብረትህን ፡ ሥራ ፡ ለዕረፍት ፡ ብለህ ፡ ሥራው ፡ እንጂ ፡ ለመደበኛ ፡ ሥራህ ፡ ዳኘነትን ፡ አድርግ ። የምትኖርበት ፡ ሌላ ፡ ኑሮ ፡ ሲሆን ፡ የተከፈልከውን ፡ ስትሠራ ፡ ምክንያቱ ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይሁን ።

ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

፻፺፰ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የምትሠራው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በመ ነባበሩ ፡ እንዳያስቸግርህ ፡ ለዓትህን ፡ ለሥራህ ፡

የምታካፍልበት ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሥራ ፡ የሰጠህ ፡ ሰዓት ፡ በከንቱ ፡ እንዳያልቅብህ ፡ ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ አድርገህ ፡ ከፈለው ። በ፳፬ ፡ ቀን ፡ የሚገኙትን ፡ ፲፱፻፵ቱን ፡ ሰዓት ፡ መዓልት ፡ ከሁለት ፡ ከፍሎ ፡ ባርባ ፡ ሁለቱ ፡ ለነባቢት ፡ ነፍስህ ፡ ጥቅም ፡ ለደመ ፡ ነፍስህ ፡ ዕረፍት ፡ እንዲሆንህ ፡ ዳኛ ፡ ስትሆን ፡ በቃልህ ፡ እውነትን ፡ ባዋቂ ፡ ነፍስህ ፡ ዳኝነትን ፡ ሠራተኛ ፡ ስትሆን ፡ ሥራህን ፡ እየመዘንህ ፡ የተከፈለውን ፡ ሥራበት ።

ባ፸፪ቱ ፡ ሰዓት ፡ ለባዊት ፡ ነፍስህን ፡ አሳርፈህ ፡ የደመ ፡ ነፍስህን ፡ ጥቅም ፡ በሥጋህ ፡ አሳብ ፡ እየመዘንክ ፡ በነፍስህ ፡ አሳብ ፡ ስለ ፡ ሥጋዊነትህ ፡ እያዘንህ ፡ የደመ ፡ ነፍስህን ፡ ሥራ ፡ ሥራበት ።

እንደዚህም ፡ አካፍሎ ፡ ለመሥራት ፡ ዳኛ ፡ ስትሆን ፡ ሰኞ ፡ ረቡዕ ፡ ዐርብ ፡ ፰ ፡ ፰ ፡ ሰዓት ፡ ድምር ፡ ፳፬ ፡ ሰዓት ፡ የሰውን ፡ ግፍ ፡ ጠብቀህ ፡ ከፈጣሪህ ፡ ለመጠቀም ፡ ስትል ፡ ችሎት ፡ አድርግበት ።

፻፹፱ ፡ ማክሰኞ ፡ ኀሙስ ፡ ቅዳሜ ፡ ፫ ፡ ፫ ፡ ሰዓት ፡ እሑድ ፡ አንዳንድ ፡ ሰዓት ፡ ድምር ፡ ፲ ፡ ሰዓት ፡ የሰውን ፡ ችግር ፡ ለማቅለል ፡ ስትል ፡ ቀላጤ ፡ ስጥበት ።

፻፺ ፡ እሑድ ፡ ማክሰኞና ፡ ኀሙስ ፡ ቅዳሜ ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ የምትፈርዳቸው ፡ ቃሎች ፡ መሠረታቸውን ፡ ከሕግ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላለማስለቀቅ ፡



ከፉና ፡ በጎን ፡ ለማወቅ ፡ ስትል ፡ የፍርድና ፡ ያናምር ፡ ደንብ ፡ መቃኞ ፡ የሆኑትን ፡ መጻሕፍትንና ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥትን ፡ መመርመሪያ ፡ ስለዚሁም ፡ ነገር ፡ ከሊቃውንት ፡ መጠየቂያ ፡ ይሁን ፡ ድምር ፡ ፰ ፡ ሰዓት ።

ጥቅል ፡ ፵፪ ፡ ሰዓት ፡ ይህ ፡ ስለ ፡ ዐዋቂዋ ፡ ነፍስህ ፡ ጥቅም ፡ የመዓልት ፡ ሥራህ ፡ ይሁን ።

፻፺፩ ፡ ከሰኞ ፡ ከረቡዕ ፡ ከዐርብ ፡ አራት ፡ አራቱ ፡ ሰዓት ፡ ድምር ፡ ፲፪ ፡ ሰዓት ። ከማክሰኞ ፡ ከኀሙስ ፡ ከቅዳሜ ፡ ሰባት ፡ ሰባት ፡ ኀያ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ከእሑድ ፡ ፱ኙን ፡ ድምር ፡ ፵፪ቱን ፡ ለምግብህ ፡ ለንብረትህ ፡ አድርገው ።

፻፺፪ ፡ በዚህም ፡ ሰዓት ፡ የሥጋህ ፡ አሳብና ፡ የሥጋህ ፡ ምግብ ፡ ወሰን ፡ እንዲያገኙ ።

ከእሑድ ፡ እምስቱን ፡ ሰዓት ፡ ከቀሩት ፡ ቀን ፡ ፪ ፡ ፪ቱን ፡ ሰዓት ፡ ስለ ፡ ሥጋህ ፡ እናምር ፡ ስትል ፡ ለምግብ ፡ ዕረፍት ፡ አድርገው ። ከእሑድ ፡ አራቱን ፡ ማክሰኞ ፡ ኀሙስ ፡ ቅዳሜ ፡ ፭ ፡ ፭ቱን ፡ ሰዓት ፡ ባንተ ፡ አሳብ ፡ የሚያድሩት ፡ ቤተ ፡ ሰቦችህ ፡ እንዳይጐዱብህ ፡ ቅድመ ፡ እሁኒ ፡ ለሰብእ ፡ ቤትከ ፡ ስለ ፡ ተባለው ፡ ትእዛዝ ፡ ስትል ፡ ለንብረትህ ፡ ጕዳይ ፡ ማሰናጃ ፡ አድርገው ።

፻፺፫ ፡ በዚህ ፡ ባ፸፪ ፡ ሰዓት ፡ ስለ ፡ ደመ ፡ ነፍስህ ፡ ጥቅም ፡ የመዓልት ፡ ሥራህ ፡ ይሁን ።

ይህም ፡ የሰባቱን ፡ ቀን ፡ ሰማንያ ፡ አራቱን ፡ ሰዓት፡ መዓልት ፡ እንዲህ ፡ አድርገህ ፡ እየከፈልክ ፡ ስትሠራው ፡ የደመ ፡ ነፍስህና ፡ የነባቢት ፡ ነፍስህ ፡ ጠባይና ፡ ፈቃድ ፡ ተካክለው ፡ ይፈጸማሉ ።

፻፺፬ ፡ ዳግመኛ ፡ ለዕረፍት ፡ ከተሰጠነው ፡ ከ፸፬ቱ ፡ ሰዓት ፡ ሌሊት ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ቀኑም ፡ ስለ ፡ ሌሊቱም ፡ ስለ ፡ ፻፷፰ቱ ፡ ሰዓት ፡ ዐሥራት ፡ አውጥተህ ፡ ዐሥራ ፡ ስድስት ፡ ሰዓት ፡ ካርባ ፡ ስምንት ፡ ደቂቃ ፡ ስለ ፡ ዐዋቂዋ ፡ ነፍስህ ፡ ጥቅም ፡ የታዘዝከውን ፡ የጸሎት ፡ ግብርህን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አቅርብበት ።

፻፺፭ ፡ ዐሥራንዱን ፡ ሰዓት ፡ ካሥራ ፡ ሁለት ፡ ደቂቃ ፡ ቀን ፡ የምትሠራውን ፡ አስብበት ፡ እያሰብህም ፡ ምረጥበት ።

፻፺፮ ፡ ፵፯ቱን ፡ ሰዓት ፡ ከ፳ ፡ ደቂቃ ፡ በእንቅልፍ ፡ አእምሮህን ፡ አሳርፍበት ፡ በዚህ ፡ በ፳፫ቱ ፡ ለደመ፡ ነፍስህ ፡ ጥቅም ፡ አድርግበት ።

እንዲህም ፡ በማድረግህ ፡ ካንዱ ፡ ሌሊት ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ከኻያ ፡ አራት ፡ ደቂቃ ፡ ስታመሰግንና ፡ ስትጸልይበት ፡ ለሰዓቱም ፡ ዐሥራት ፡ አውጥተህ ፡ ለመገበርህም፡ ልክ፡ ይሆናል፤የነፍስህም፡ጥቅም፡ይገኛል።

፻፺፯ ፡ ቀን ፡ የምትሠራውንም ፡ በአእምሮህ ፡ የምታመዛዝንበት ፡ በእጅህ ፡ ያሰብከውን ፡ እንዳትረሳው ፡ ማስታወሻ ፡ የምትጽፍበት ፡ ካንድ ፡ ሌሊት ፡



አንድ ፡ ሰዓት ፡ ከ፴፮ ፡ ደቂቃ ፡ ቀን ፡ ለምትሠራው፡ ለንብረትህና ፡ ለቤት፡ ሰብህ፡ ጕዳይ፡ ስታስብበት፡ ለሥጋህ ፡ አናዎር ፡ ጥቅም ፡ ይሆናል ።

፻፺፰ ፡ የመዓልቱ ፡ ጸሎት ፡ ግን ፡ በዝቶም ፡ ሥራህን ፡ እንዳያስፈታህ ፡ ቀርቶም ፡ ፈጣሪህን ፡ እንዳያስረሳህ ፡ እንተን ፡ የሚሻ ፡ ጨኸና ፡ እንግዳ ፡ ያልመጣበት ፡ የበላይ ፡ ዳኛ ፡ ያዘዘው ፡ የማይጕድልበት ፡ የምትረዳው ፡ ወይም ፡ የምታሠራው ፡ ሰው ፡ አንተን ፡ በማጣቱ ፡ የሚያዝንበት ፡ እግዚአብሔር ፡ ከፍሎህ ፡ የምትሠራውን ፡ ሥራ ፡ የማያጕድልብህ ፡ በስውር ፡ ለመጸለይ ፡ የሚመችህ ፡ ከሥራህ ፡ የሚተርፍ ፡ ሰዓት ፡ ስታገኝ ፡ ግን ፡ እንደሌሊቱ ፡ ካንዱ ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ከ፲፪ ፡ ደቂቃ ፡ ለዐሥራት ፡ አውጥተህ ፡ ሰዓቱ ፡ አለቀ ፡ ድረስ ፡ ከዳዊትም ፡ ከወንጌልም ፡ የታዘዘውን ፡ ጸሎት ፡ ጸልይበት ።

ልትሠራው ፡ ያካፈልከው ፡ ሥራ ፡ ሲበዛብህ ፡ ከመዓልቱ ፡ የሰዓት ፡ ዐሥራት ፡ ከሌሊቱ ፡ ሰዓት ፡ ላይ ፡ እያነሣህ ፡ የንባቡን ፡ ጸሎት ፡ ሁሉ ፡ ሌሊት ፡ ጸልየው ፡ ለመዓልትም ፡ የታዘዘውን ፡ ሰዓት ፡ እየጠበቅህ ፡ እንዳንዱን ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ አድርገህ ፡ ከያዝ ግብር ፡ ፍትና ፡ እንዳትታጐል ፡ እያገባህ ፡ አድርከው ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ ጣልቃ ፡ እያገባህ ፡ አድርሳት ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ ቢቸግርህ ፡ ይህችን ፡ አጭሯን ፡ አንዷን ፡ የአቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ ጸሎት ፡ አታስታጕል ።

፻፺፱ ፡ የምትኖርበት ፡ ሥራ ፡ የተግባረ ፡ እድ ፡ ሥራም ፡ ሲሆን ፡ ለነባቢት ፡ ነፍስህ ፡ የተከፈለውን ፡ ለተከፈልክበት ፡ ሥራ ፡ አድርገው ፡ እንጂ ፡ ለደመ ፡ ነፍስህ ፡ የተከፈለው ፡ አይለወጥ ።

በተግባረ ፡ ነፍስህ ፡ የምትኖር ፡ ስትሆን ፡ ግን ፡ ለደመ ፡ ነፍስ ፡ ከተከፈለው ፡ ሰዓት ፡ ላይ ፡ የሚቻልህን ፡ ያኸል ፡ ከፍለህ ፡ ወደ ፡ ነባቢት ፡ ነፍስህ ፡ ጨምርላትና ፡ ለተግባረ ፡ እድ ፡ የተከፈለውን ፡ ሥራ ፡ ጨርሰህ ፡ ለጸሎት ፡ ለቁመት ፡ ለስግደት ፡ ለእርድና ፡ አካፍለህ ፡ ሥራበት ።

፪፻ ፡ በዚህ ፡ ዓለምም ፡ ሆነህ ፡ የምትሠራው ፡ ሥራህም ፡ እከፋፈል ፡ አጥቶ ፡ ተንባብሮ ፡ እንዳያስቸግርህ ፡ የሚፈጥን ፡ የሚከተል ፡ የሚሰንብት ፡ የሚቈይ ፡ የሚል ፡ ያጻጻፍ ፡ ደንብ ፡ ያለው ፡ ማስታወሻ ፡ አበጅተህ ፡ ያንን ፡ እያየህ ፡ ሥራ ። የማስታወሻውንም ፡ አጻጻፍ ፡ ፀይነት ፡ የሚፈጥን ፡ ከሚለው ፡ አርእስት ፡ ውስጥ ፡ ከዕለት ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ የሚሠራን ፡ ከሦስት ፡ ቀን ፡ የማያልፈውን ፡ የሚያፋጥነውን ፡ ጉዳይ ፡ ጻፍበትና ፡ ግድ ፡ የሆን ፡ ድንገተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ካልመጣብህ ፡ እሱን ፡ አይተህ ፡ እሱ ፡ ላይ ፡ የተጻፈውን ፡ ሳትሠራ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አትለፍ ።

የሚፈጥን ፡ ከሚለው ፡ እስከ ፡ ሳምንት ፡ የምትሠራውን ፡ የሚከተል ፡ ከሚለው ፡ እስከ ፡ ወር ፡ የምትሠራውን ፡ የሚሰንብት ፡ ከሚለው ፡ ከወር ፡ ወዲህ ፡ የምትሠራውን ፡ የሚቈይ ፡ ከሚለው ፡ እስከ ፡ ዓመት ፡ የምትሠራውን ፡ እየጻፍክ ፡ ሥራበት ።



ይህንም ፡ አሠራር ፡ እምመክርህ ፡ አሳብ ፡ እሳት ፡ ነውና ፡ እሳቱ ፡ አሳብህ ፡ ዕንጨት ፡ ፀጥንትህን ፡ እንዳያቃጥልብህ ፡ ደም ፡ ውሃህን ፡ እንዳያፈላብህ ፡ ማንኛውንም ፡ አሳብህን ፡ በጽሕፈት ፡ መጫሪያህ ፡ ከአእምሮህ ፡ ላይ ፡ እያነሣህ ፡ ከወረቀት ፡ ምድጃህ ፡ ላይ ፡ እያደረግህ ፡ እንድትሠራበት ፡ ነው ። ይህንም ፡ ጥቅም ፡ ልትረዳ ፡ ብትሻ ፡ ትንሽ ፡ ትልቁን ፡ ሥራቸውን ፡ ከጽሕፈት ፡ ላይ ፡ እያደረጉ ፡ ከሚሠሩት ፡ ከአውሮፖች ፡ ላይ ፡ አሠራሩን ፡ ተመልከት ።

ምዕራፍ ፡ ፲፮ ።

## ስለ ፡ አእምሮ ፡ አሠራር ፡ ምክር ።

፪፻፩ ፡ አእምሮ ፡ ማለት ፡ በእግዚአብሔር ፡ አርአያ ፡ ከተፈጠረች ፡ ከነፍስ ፡ ባሕርይ ፡ የሚገኝ ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ ነውና ፡ አእምሮህን ፡ በማይረባው ፡ ሁሉ ፡ ቦታ ፡ እየበተንክ ፡ ለከንቱ ፡ ሥራ ፡ የጨረስ ከው ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ ጌታው ፡ አምና ፡ የሰጠውን ፡ ወርቅ ፡ ላገባማሪ ፡ ለዘዋሪ ፡ ለመሸታ ፡ ለጨዋታ ፡ እያደረገ ፡ ጨርሶ ፡ እንደሚቀጣ ፡ እባድ ፡ ተቈጥ ረህ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅጣት ፡ እንዳታልፍ ፡

አእምሮህን ፡ ለከንቱ ፡ ሥራ ፡ እንዳታባክን ፡ ተጠንቀቅ ።

ጥያቄ ።

፪፻፪ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ እንኳን ፡ ሌላው ፡ ከነሥጋችንም ፡ ከንቱ ፡ ነን ፡ ከንቱ ፡ ያልሆነ ፡ ነገር ፡ ተየት ፡ አግኝቼ ፡ እሠራለሁ ።

ምላሽ ።

፪፻፫ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ምንም ፡ የሚበዛው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ከንቱ ፡ ቢሆን ፡ ከየክፍሉ ፡ ኑሮ ፡ ውስጥ ፡ አንዳንድ ፡ ከንቱ ፡ ያልሆነ ፡ ነገር ፡ አለና ፡ ያንን ፡ ብትሠራው ፡ ከከንቱ ፡ ሥራዎች ፡ ተለይተህ ፡ ትድናለህ ።

ጥያቄ ።

፪፻፬ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሥራ ፡ ሁኖ ፡ ከንቱነት ፡ የሌለው ፡ ነገር ፡ ምን ፡ ይሆን ።

ምላሽ ።

፪፻፭ ፡ ኑሮህ ፡ ጌትነት ፡ ቢሆን ፡ የማትሞት ፡ ከንቱ ፡ ያልሆነችው ፡ ነፍስ ፡ ስለ ፡ ተዋሐደችው ፡ ሰው ፡ በነፍስ ፡ ባሕረው ፡ ነዋሪ ፡ እንጂ ፡ ከንቱ ፡ አይደለምና ፡ ለሰው ፡ የሕይወቱን ፡ እናዖር ፡ ለመጠበቅ ፡ በምትሠራው ፡ ሁሉ ፡ ሥራህ ፡ ጕቦ ፡ የማትበላበት ፡ ሰው ፡ የማታበላልጥበት ፡ ጥንቃቄ ፡ ይዘህ ፡



እውነተኛ ፡ ዳኛ ፡ ብትሆን ፡ ግፈኛውንም ፡ በፍርድ ፡ ወይም ፡ በምክር ፡ ከግፉ ፡ ብትከለክለው ፡ ግፍ ፡ የሚሠራበትንም ፡ ከግፉ ፡ ብታድነው ፡ ይቱንም ፡ በማዳንህ ፡ አንተም ፡ ትድናለህ ።

ይህን ፡ ትልቁን ፡ ሥራ ፡ በጥቂቱ ፡ አንዳንድ ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡ እየሠራህ ፡ ብዙውን ፡ አሳብህን ፡ አዩ ፡ ቤት ፡ አዩ ፡ ንብረት ፡ እየተባለ ፡ የሚመስገነውን ፡ ለመሻት ፡ ትልቁን ፡ አእምሮህን ፡ ለሚበላሸው ፡ ለቤትህ ፡ ማስጌጫ ፡ ለሚያልቀው ፡ ለገንዘብህ ፡ ማስናኛ ፡ ከጕረሮ ፡ ሲያልፍ ፡ መልሶ ፡ ለሚጠፋው ፡ ለምግብህ ፡ ማጣፈጫ ፡ ይህን ፡ እብዝቶ ፡ አሻሽሎ ፡ አሳምሮ ፡ አስናድቶ ፡ ለመመስገን ፡ ስትል ፡ አእምሮህን ፡ ብታባክን ፡ ሥራውም ፡ ምስጋናውም ፡ የሚቀር ፡ ከቱም ፡ ነገር ፡ የማይቈጠር ፡ መሆኑን ፡ ባለማወቅህም ፡ አእምሮህንም ፡ በከንቱ ፡ በማባከንህም ፡ እብድ ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍርድ ፡ ያሳልፍሃል ።

ጥያቄ ።

፪፻፮ ፡ ምነው ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ማንም ፡ ሠሪዐ ፡ ቤቱን ፡ ያላወቀ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ አይሾም ፡ ይል ፡ የለምን ።

ከፍርዱ ፡ ጋራ ፡ እያቀላቀለ ፡ ቤቱን ፡ ቢያስጌጠው ፡ ንብረቱን ፡ ቢያስናዳው ፡ ገንዘቡንም ፡ ቢያበዛው ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ኀጢአት ፡ ይሆንበታል ።

ምላሽ ።

፪፻፮ ፡ ጳውሎስ ፡ በዚህ ፡ ትእዛዝ ፡ ለተፈጥሮ ፡ ባሕ ርያችን ፡ የሚያሻንን ፡ እንድናዘጋጅ ፡ ሀኬተኞች ፡ እንዳንሆን ፡ ልክና ፡ ሥርዐት ፡ ዐውቀን ፡ እንድ ንሠራ ፡ ሲያዘን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የማየት ፡ ዘማ ፡ ባሕርያችንን ፡ ብቻ ፡ ለማስደሰት ፡ ቤታችንን ፡ ለማ ስጌጥ ፡ ገንዘባችንን ፡ ለማብዛትስ ፡ እሱም ፡ ራሱ ፡ እንዳልሠራው ፡ ኀጢአት ፡ አድርጎ ፡ እንደ ፡ ነቀ ፈው ፡ ጌታ ፡ በነቁ ፡ የመሰለው ፡ ያስረዳናል ። ራ ሱስ ፡ ጳውሎስ ፡ መቼ ፡ የተሰናዳ ፡ ቤትና ፡ ሚስት ፡ አግኝቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ ሆነ ፤ ሐ ዋርያትስ ፡ እንኳን ፡ የተሰናዳ ፡ ያልተሰናዳውስ ፡ ቤት ፡ መቼ ፡ ነበራቸውና ፡ ለዓለም ፡ ሁሉ ፡ የቤ ተ ፡ ክርስቲያን ፡ አለቃ ፡ ሆኑ ።

ጥያቄ ።

፪፻፯ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ኗሪ ፡ ስንሆን ፡ ኀጢአት ፡ የማይሆነው ፡ የቤት ፡ ጌጥና ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ፡ እስከ ምን ፡ ያኽሉ ፡ ድረስ ፡ ነው ።

ምላሽ ።

፪፻፰ ፡ ቤት ፡ በምትሠራበት ፡ ጊዜ ፡ እንዳይናድብህ ፡ አጥንተህ ፡ አቃንተህ ፡ እንዳያፈስብህ ፡ ባገኘኸው ፡ ክድነህ ፡ እንዳይሸክርህ ፡ ለስነህ ፡ እንዳይጠብህ ፡ የልክህን ፡ ያኽል ፡ አስፍተህ ፡ ብትሠራው ፡ በተመ ችህ ፡ ጉልበትና ፡ በተረፈህም ፡ ጊዜ ፡ ዐፈሩ ፡ እን ዳይረግፍብህ ፡ ሳታስጌጥ ፡ በሳንቃ ፡ በሸማ ፡ ብትለ ብጠው ፡ ብርሃኑ ፡ ገብቶ ፡ ነፋሱ ፡ እንዲቀርልህ ፡ መስኮቱን ፡ በመስተዋት ፡ ብትገጥመው ፡ እንዳይ ቃጠል ፡ ሸኽላ ፡ ኖራ ፡ ዐፈር ፡ ቁርቁር ፡ ብትከ ድነው ፡ ይህ ፡ ለባሕርይ ፡ የሚያሻ ፡ ነውና ፡ ጥቅም ፡ የሌለበት ፡ ያይን ፡ ጌጥ ፡ ለሚሆን ፡ ነገር ፡ ሳትጨ ምር ፡ እንዲህ ፡ አድርገህ ፡ ብትሠራ ፡ ኀጢአት ፡ አይሆንብህም ፡ ብልጥ ፡ እንጂ ፡ ብልኅ ፡ እንዳይደ ሉት ፡ ሰዎች ፡ ኑሮ ፡ ለማመሳሰል ፡ ብለህ ፡ ከቤቱ ፡ ዕቃ ፡ በመታጐሩ ፡ በቀለም ፡ በመኽጕርጐሩ ፡ ዐይኔንም ፡ ያስደስተኛል ፡ ማዕርጌንም ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ያስከብርልኛል ፡ እየመሰለህ ፡ ያንተ ፡ አጓባቢነት ፡ የተንቀፈ ፡ ሲሆን ፡ አእምሮህን ፡ ለቤትህ፡ማጓበቢያ፡አድርገህ፡ብታባክነው፡ትልቅ፡ የሚሠራውን ፡ አእምሮ ፡ ላይንህ ፡ ብቻ ፡ ጥቅም ፡ በማባከንህ ፡ ከእብደትና ፡ ከዝሙት ፡ ያስቈጥር ብሃልና ፤ ቤት ፡ በምትሠራበት ፡ ልብስም ፡ በምት ለብስበት ፡ ጊዜ ፡ ለተፈጥሮ ፡ ባሕርይ ፡ እንደሚሻህ ፡ አ ድርገህ ፡ ልብስህንም ፡ ልበስ ፡ ቤትህንም ፡ ሥራህንም ፡ ባገባብ ፡ ሥራ ፡ እንጂ ፡ የዝሙት ፡ ጠባይህ ፡ እንደሚሻ ው ፡ አድርገህ ፡ እኽጕርጕረህ ፡ አትሥራ ፡ አትልበስ ።

ጥያቄ ።

፪፻፱ ፡ ከቤቱ ፡ ዐይናቸውን ፡ በማስደሰት ፡ ቤታቸውን ፡ በማኽጕርጐር ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ የሚመጡብኝ ፡

ሲሆን ፡ እነሱ ፡ የሚወዱትን ፡ ባለማድረግ ፡ እንዳ ላስቀይም ፡ ምን ፡ ላድርግ ።

ምላሽ ።

፪፻፲፩ ፡ ለዘማዊ ፡ እንግዳ ፡ ደስ ፡ እንዲለው ፡ ተብሎ ፡ ዝሙት ፡ አይሠራምና ፡ ቢሆንልህ ፡ ሳታኽርኵረኵር ፡ በሚገባ ፡ ልክ ፡ ብቻ ፡ አጥርተህ ፡ ተቀበለው ፤ ዐይን ፡ ዘማ ፡ እንግዶችህ ፡ ወዳንተ ፡ የሚመጡ በት ፡ ምክንያት ፡ የኀዥነት ፡ ያለቅነት ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ ያዝክ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ አመጣጣቸው ፡ ግድ ፡ ሲሆንብህ ፡ ግን ፡ በኋራችን ፡ ክርስቶስ ፡ ለባሕርዩ ፡ የሚያሻው ፡ ሳይሆን ፡ ሥጋውያን ፡ የሚገኙበት ፡ ከሰርግ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ኃጥኣንን ፡ በመሻት ፡ አባቱን ፡ ለማስደሰት ፡ ሲል ፡ ከሰርግ፡ ቤት ፡ ሄዶ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ እንዳበረከተ ፡ ላንተ ፡ ለራስህ ፡ ባሕርይ ፡ ማሳደሻ ፡ ይሁንኝ ፡ ብለህ ፡ ሳትሻ ፡ ለነሱ ፡ ባሕርይ ፡ የሚሆን ፡ አንድ ፡ ቤት ፡ ሥራላቸውና ፡ አንተ ፡ ግን ፡ እድፍ ፡ ጕድፍ ፡ መብረቅረቅ ፡ መኽርኰርኰር ፡ ከሌለበት ፡ ቤት ፡ ኑር ፡ ለቤትህ ፡ የለበጥከው ፡ ጨርቁ ፡ የሚማማ ፡ ሳንቃው ፡ የሚንቃ ፡ ሁኖ ፡ በግድ ፡ ቀለምም ፡ የሚ ያሻህ ፡ ሲሆን ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ቀለም ፡ ቀባው ፡ እንጂ፡ ሁለት፡ ሦስት፡ ዐይነት፡ ቀለም፡ አትቀባው።

ገንዘብና ፡ የቤት ፡ ዕቃንም ፡ እንደዚሁ ፡ ለተፈጥ ሮው ፡ ባሕርይህና ፡ ለምታሳድረው ፡ ሰው ፡ ማሳደ



ሪያ ፡ ከሚሆን ፡ ዕቃ ፡ በቀር ፡ ለማጌጫና ፡ ለመታ መኛ ፡ እንዲሆንኝ ፡ ብለህ ፡ ትርፍ ፡ ለማሰናዳት ፡ ብትጥር ፡ ሥርዋ ፡ ለኀጢአት ፡ አፍቅሮ ፡ ንዋይ ፡ የተባለውን ፡ አግኝተህ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፍርድ ፡ ትቀጣለህና ፤ ለሕይወትህ ፡ መጣሪያ ፡ ከሚሆን ፡ ዕቃ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የጌጥ ፡ ዕቃ ፡ ለመሰብሰብ ፡ አትድከም ።

ጥያቄ ።

፪፻፲፪ ፡ እርሼ ፡ አዳሪስ ፡ ስሆን ፡ ምን ፡ ልሥራ ።

ምላሽ ።

፪፻፲፫ ፤ ዋናው ፡ ሥራ ፡ ጌታ ፡ በወንጌል ፡ እንዳለው ፡ እሽከሬ ፡ ዘመዴ ፡ ጌታዬ ፡ እያልክ ፡ የጕልበትህን ፡ ለሁብታም ፡ ለወዳጅ ፡ መለማመጫ ፡ ሳታደርግ ፡ ካመት ፡ ልብስ ፡ ከዕለት ፡ ጕርሥ ፡ የሚተርፍህን ፡ ለእንግዳና ፡ ለድኻ ፡ ለመስጠት ፡ የአእምሮህን ፡ ሥራ ፡ ከዚህ ፡ ላይ ፡ አሳርፈው ።

ጥያቄ ።

፪፻፲፬ ፤ ለሰው ፡ ጥቅም ፡ ያይደሉ ፡ ለኀጢአት ፡ ብቻ፡ የሆኑ ፡ ገንዘቦች ፡ ስንት ፡ ናቸው ።

ምላሽ ።

፪፻፲፭ ፡ ሦስት ፡ ናቸው ። አንደኛው ፤ እየፈረሱ ፡ ለጌጥ፡ የሚሠሩ ፡ የብርና ፡ የወርቅ ፡ ጌጦች ። ሁለተኛው ፡

እየተጠለፉና ፡ እየተሠሩ ፡ ለጌጥ ፡ የሚለበሱ ፡ ሐሮች ። ሦስተኛው ፤ ለልብስ ፡ ለምንጣፍ ፡ ለቤት ፡ የሚቀቡ ፡ የጌጥ ፡ ቀለማት ፡ ናቸው ። እንዚሁም ፡ የዓለም ፡ ነውሯ ፡ እንዳይመረመር ፡ የተሠሩ ፡ መጋረጃዎች ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ለሰው ፡ ባሕርይ ፡ የሚፈለጉ ፡ ገንዘቦች ፡ አይደሉም ።

ጥያቄ ።

፪፻፲፯ ፤ ምንው ፡ ያጌጠ ፡ ካላጌጠ ፡ በመብለጡ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፤ በሚያየው ፡ ዘንድ ፡ ያስከብረዋል ። ለፈታዊ ፡ ባሕርዩ ፡ በሚያሻው ፡ በሴቶችም ፡ ዘንድ ፡ ያስወድደዋል ፤ ለሥጋውማ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ እሊህ ፡ ጌጦች ፡ የማይጠቅሙት ፡ ነገር ፡ ይሆናሉ ።

ምላሽ ።

፪፻፲፯ ፤ ለተፈጥሮው ፡ ባዕድ ፡ በሚሆኑ ፡ ግዕዛን ፡ በሌላቸው ፡ ብርና ፡ ወርቅ ፡ በሐርና ፡ በቀለማት ፡ መልክ ፡ ምክንያት ፡ ላጌጠው ፡ የበለጥኩ ፡ የሚመስለው ፡ ሰው ፡ ባለማወቁ ፡ ያሳዝናል ፡ እንጂ ፡ አያስቀናም ፤ ፈረስና ፡ በቅሎ ፡ እንኳን ፡ ዕውቀት ፡ ሳይኖራቸው ፡ ጌጡን ፡ ጭነው ፡ ከሚነዷቸው ፡ እራግፈው ፡ ሲያቀሉላቸው ፡ ነው ፡ ደስ ፡ የሚላቸው ። ዐዋቂ ፡ ነኝ ፡ የሚል ፡ ሰውማ ፡ ወርቁን ፡ ሐሩን ፡ በራሱ ፡ ቢሸከመው ፡ በወገቡ ፡ በደረቱ ፡ በእጁ ፡ ቢይዘው ፡ ባንገቱ ፡ ቢያንጠለጥለው ፡ እሱንም ፡ የሚያኰራው ፡ ምንድነው ። ግዕዛን ፡ ቢኖረ



ውስ ፡ ከላዩ ፡ የተቀመጠበት ፡ ሐርና ፡ ወርቅ ፡ በኰራ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ለባሕርዩ ፡ የማያሻው ፡ ነገር ፡ በተሜነበት ፡ እላዩ ፡ የተቀመጠበት ፡ ሳይኰራ ፡ የተሸከሚ ፡ መኵራትና ፡ መደሰት ፡ የሚያሳዝን ፡ አለማወቅ ፡ ነው ።

የሚያዩትም ፡ ሰዎች ፡ ስለዚህ ፡ ሽክም ፡ ምክንያት ፡ ቢያከብሩት ፡ ቅዱስ ፡ ያዕቆብ ፡ የነቀፋቸው ፡ ዐላዋቂዎች ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፤ ዐዋቂዎች ፡ አይደሉምና ፡ የሚያውቅ ፡ ልቡና ፡ ይህን ፡ ክብር ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ አይቀበለውም ።

፪፻፲፰ ፤ ለሴቶች ፡ መውደድ ፡ ሲል ፡ የሚያጌጥ ፡ ወንድ ፡ ለሴት ፡ ሲል ፡ ይህን ፡ ያኸል ፡ በመዉነቁ ፡ ትልቅ ፡ ውርደት ፡ ነው ።

፱ኛ ፡ ሴቶችን ፡ በጌጥ ፡ እያታለለ ፡ በማሳቱ ፡ ሰይጣንነትን ፡ ለፍትወት ፡ በመገዛቱ ፡ ዘማዊነትን ፡ ሰብስቦ ፡ ከጥፋት ፡ ይወድቃል ፡ እንጂ ፡ ጥቅም ፡ የለውም ።

ጥያቄ ።

፪፻፲፱ ፤ ይህ ፡ ከሆነ ፡ ለሰው ፡ የሚገባው ፡ ምን ፡ ዐይነት ፡ ልብስ ፡ መሆኑ ፡ ነው ።

ምላሽ ።

፪፻፳ ፤ በቀለም ፡ ያልተዥጐረጐረ ፡ በወርቅ ፡ ያልተጥበረበረ ፡ በእድፍ ፡ ያልጠቈረ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሠራለትን ፡ የተፈጥሮ ፡ መልኩ ፡ ያለወጠ ፡

ያገሩን ፡ ልማድ ፡ ያለቀቀ ፡ ንጹሕ ፡ ልብስ ፡ ቢለ
ብስ ፡ የሚገባው ፡ ነው ።

ጥያቄ ።

፪፻፳፩ ፡ ሁሉም ፡ ልብሱ ፡ አንድ ፡ ነጭ ፡ ብቻ ፡ ከሆነ ፡ ጌታና ፡ ድኻ ፡ ዳኛና ፡ ዜጋ ፡ በምን ፡ ይለይ ።

ምላሽ ።

፪፻፳፪ ፡ ዳኛና ፡ ዜጋ ፡ በለበሱት ፡ ሥጋ ፡ የተፈጥሮ ፡ ልዩነት ፡ ሳይኖራቸው ፡ በውቀት ፡ ርቀት ፡ ብቻ ፡ ነውና ፡ እሚለያዩት ፡ በሩቅ ፡ የሚታየው ፡ የልብሱ ፡ መልክ ፡ እንዴ ፡ ሥጋቸው ፡ ልብስ ፡ የሁሉም ፡ ዐይነት ፡ አንድ ፡ ሆኖ ፡ የዳኞቹ ፡ ቀጭን ፡ ወይም ፡ ቀለም ፡ ያልገባ ፡ ነጭ ፡ ሐር ፡ ሲሆን ፡ በሩቅ ፡ ለሚያዩቸው ፡ የሰው ፡ ልክ ፡ መሆናቸውን ፡ በቅ ርብ ፡ ለሚያዩቸው ፡ ዳኛ ፡ መሆናቸው ፡ ይታወቅና ፡ የለበሱት ፡ ያገባብ ፡ ለባሾች ፡ ይሆናሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ በዚሁም ፡ ነጭ ፡ ልብስ ፡ የኀጢአት ፡ እለ ባበስ ፡ እድርጎ ፡ እንዳይለብሰው ፡ መጠንቀቅ ፡ ያሻዋል ።

ጥያቄ ።

፪፻፳፫ ፡ በነጩ ፡ ልብስ ፡ ደግሞ ፡ የሚሠራው ፡ ኀጢ አት ፡ ምን ፡ ዐይነት ፡ ነው ።

ምላሽ ።

፪፻፳፬ ፡ ወንድ ፡ የሴትን ፡ ሴት ፡ የወንድን ፡ ካህን ፡



የጨዋን ፡ ጨዋ ፡ የካህንን ፡ ሲለብስ ፡ ሐበሻ ፡ ሆኖ ፡ የፈረንጅ ፡ ፈረንጅ ፡ ሆኖ ፡ የሐበሻ ፡ ሲለ ብስ ፡ አርአያ ፡ ልብሱን ፡ መለወጡ ፡ ነውና ፡ ምንም ፡ ኀጢአት ፡ ባይሆን ፡ ወደ ፡ ኀጢአት ፡ ይቀርባል ። እንደ ፡ ልብሱ ፡ ባሕርይም ፡ በያዘው ፡ የማይጸና ፡ ባሕርዩም ፡ ተረማማጅ ፡ ይሆናል ።

ጥያቄ ።

፪፻፳፭ ፡ የቀረውስ ፡ ይሁን ፡ ሰው ፡ ለጌጥ ፡ ሳይሆን ፡ ለባሕርዩ ፡ ሕይወት ፡ ከፀሓይ ፡ ከብርድ ፡ ለመዳን ፡ ሲል ፡ ከፈረንጆች ፡ ልብስ ፡ ላይ ፡ የፈለገውን ፡ ቢለብስ ፡ ስለምን ፡ ይጐዳል ።

ምላሽ ።

፪፻፳፮ ፡ ፈረንጅ ፡ ልብስ ፡ ስለሌለው ፡ በልማዱ ፡
በጥብቆው ፡ በኩቱ ፡ ልብስ ፡ ላይ ፡ ሸማ ፡ ወይ ፡
ካባ ፡ ቢለብስ ፡ ሐበሻም ፡ ለራሱ ፡ ቆብ ፡ ለእግሩ ፡
ጫማ ፡ ስለሌለው ፡ የፈረንጅ ፡ ጫማ ፡ ቢያደርግ ፡
ሁለቱም ፡ ለጤናቸው ፡ መጠበቅ ፡ የሌላቸውን ፡
ባላቸው ፡ ላይ ፡ ጨመሩ ፡ እንጂ ፡ ያገር ፡ ልብሳ
ቸውን ፡ ለወጡ ፡ እያሰኝምና ፡ በዚሀ ፡ አይጐዱም ።
የሱሪያቸውን ፡ የልብሳቸውን ፡ ቅድ ፡ ግን ፡ እንደ ፡
ልብ ፡ አልባ ፡ እያረጉ ፡ ከሴት ፡ እጀ ፡ ጠባባ
ቸውን ፡ ተነፋነፍ ፡ እያደረጉ ፡ ከካህን ፡ እንደ ፡ ጥብ
ቆ ፡ እያደረጉ ፡ ከልጅ ፡ ከፈረንጅ ፡ ቢያመሳስሉት ፡
ግን ፡ ኢታፍልስ ፡ ይወለ ፡ አበዊከ ፡ የተባለውንና ፡

ዕደው ፡ ኢይልብሱ ፡ ልብሰ ፡ አንስት ፡ ወአንስትኒ ፡ ኢይልበሳ ፡ ልብሰ ፡ ዕደው ፡ የተባለውን ፡ ዐዋጅ ፡ በማፍረሳቸው ፡ ይጐዳሉ ።

፻፶፳፪ ፡ ያገራችን ፡ ልብስ ፡ እንዳይለወጥ ፡ ስለ ፡ አስፋፉ ፡ ምሳሌ ፡ ማስረጃ ። ምንም ፡ ብዙዎቹ ፡ ምሳሌውን ፡ ሳያውቁ ፡ በልማድ ፡ ብቻ ፡ ቢለብሱት ፡ እጃችንን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስምንዘረጋው ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ጥበበ ፡ እግዚአብሔር ፡ የየሥራችንን ፡ ምስጢር ፡ በልብሳችን ፡ እየተረጐምን ፡ እንድናሳይ ፡ አድርጎ ፡ ያለበሰን ፡ ነውና ፡ የልብሳችንን ፡ ትርጓሜ ፡ ዐውቀን ፡ እንዳንለውጠው ፡ ሆነን ፡ እናጽናው ። የመኳንንትና ፡ የወታደር ፡ ሱሪና ፡ እጀ ፡ ጠባብ ፡ ሠላጤ ፡ ሜፉ ፡ እንደ ፡ ጦር ፡ ራሱ ፡ እንደ ፡ ልብ ፡ ሆኖ ፡ መስፋቱ ፡ ለጊዜው ፡ ሲሮጡም ፡ ሲሄዱም ፡ ሲቀመጡም ፡ ሲነሡም ፡ የማያስቸግር ፡ ስፋቱና ፡ ጥበቱ ፡ መጠንኛ ፡ እንዲሆን ፡ ነው ። ምሳሌው ፡ ግን ፡ ቅዱ ፡ እንደ ፡ ጦር ፡ መሆኑ ፡ ልባችን ፡ ለድፍረት ፡ ሰውነታችን ፡ ለስለት ፡ የተመረጠ ፡ የጦር ፡ ሰዎች ፡ ነን ፡ ለማለት ፡ ነው ።

ሴቶች ፡ ሠላጤ ፡ የሌለው ፡ ሱሪና ፡ ቀሚስ ፡ መልበሳቸው ፡ ለጊዜው ፡ ሲጋለጡ ፡ ከከብት ፡ ሲወጡ ፡ ላካላቸው ፡ መከለያ ፡ እንዲሆን ፡ ነው ። ምሳሌው ፡ ግን ፡ የምንዋጋበት ፡ ዐቅም ፡ የምንደፍርበት ፡ ልብ ፡ የለንም ፡ የአካላችን ፡ ቅርጽ ፡ ከአካላችሁ ፡



ልዩ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ነው ፡ ስለዚህ ፡ የሱሪያቸው ፡ ስም ፡ ትርጕሙ ፡ ልብ ፡ አልባ ፡ ይባላል ። የካህናትና ፡ የባላገሮች ፡ ሱሪና ፡ እጀ ፡ ጠባብም ፡ ሠላጤውን ፡ እንደ ፡ ወታደር ፡ አድርገው ፡ መስፋታቸው ፡ የተፈጥሮው ፡ አካላችን ፡ ቅርጹ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ነው ፡ የእጃቸውን ፡ የእግራቸውን ፡ መግቢያ ፡ የሌላ ፡ ሰው ፡ እግርና ፡ እጅ ፡ ደርቦ ፡ የሚያስገባ ፡ ያኽል ፡ ቦላሌ ፡ እያደረጉ ፡ ማስፋታቸው ፡ ለጊዜው ፡ ሲሠሩ ፡ እንዳያልባቸው ፡ እንዲያናፍስላቸው ፡ ቶሎም ፡ እንዳያልቅባቸው ፡ ነው ። ምሳሌው ፡ ግን ፡ የሌላ ፡ እጅና ፡ እግር ፡ ደርቦ ፡ የሚያስገባ ፡ ያኽል ፡ አድርገው ፡ ማስፋታቸው ፡ እርስን ፡ የምንመግበው ፡ አስተምረን ፡ ለምነን ፡ የምናጸድቀው ፡ ለሌላውም ፡ ለተፈጥሮ ፡ ወንድማችን ፡ ስንል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የምንሠራው ፡ ድካማችንን ፡ ለራሳችን ፡ ጥቅም ፡ ብቻ ፡ የምናደርግ ፡ አይደለንም ፡ ለማለት ፡ ነው ። ሠላጤውንም ፡ እንደ ፡ ወታደር ፡ አድርገው ፡ መታየታቸው ፡ ስለ ፡ ሁላችሁ ፡ እንሥራ ፡ ብለን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በባሕርያችን ፡ እንደ ፡ ወታደርም ፡ የጦር ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ የምንችል ፡ ነን ፡ ለማለት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ለሥራውና ፡ ለተፈጥሮ ፡ የሚታይ ፡ ምሳሌ ፡ ሆኖ ፡ ከአበው ፡ የተደነገገለት ፡ እይገባበትን ፡ የልብሱን ፡ አርአያ ፡ ሊለውጥ ፡ አይገባውም ።

ጥያቄ ።

፪፻፳፰ ፡ የዚህ፡ ዓለም፡ የጌጥ፡ ልብስ፡ አሁንም፡ ከወንድሙ፡ ጋራ፡ በመቅናት፡ ኋላም፡ ከፈጣሪ፡ የሚያጣላው፡ ሆኖ፡ በሁለቱም፡ አገር፡ የሚጐዳ፡ ከሆነ፡ እግዚአብሔር፡ ከፍሎን፡ የሀብተ፡ ሥጋ፡ ኑሮ፡ ያደረገበት፡ ሰው፡ በደስታው፡ ወራት፡ ምን፡ መልበስ፡ ይገባዋል ።

ምላሽ ።

፪፻፳፱ ፡ ባልንጀሮችህ ፡ የነበሩት ፡ ልብሳቸው ፡ ቀሎ ፡ መልካቸው ፡ ጕስቍሎ ፡ ሳለ ፡ ያንተ ፡ መልክህ ፡ አወልውሎ ፡ ልብስህ ፡ ተንቀልቅሎ ፡ ሲያዩ ፡ የደስታህ ፡ ነበልባል ፡ ለወንድሞችህ ፡ ልብ ፡ ቅናት ፡ እየሆን ፡ እንዳያታጥልብህ ፡ ለተጕሳቈሉት፡ ወንድሞችህ ፡ ፊትህን ፡ ወልውለህ ፡ ልብስህን ፡ አንቀልቅለህ ፡ ቤትክን ፡ አጥበርብረህ ፡ ስታሳያቸው ፡ ቢሆን ፡ ኢትዝግቡን ፡ አስበህ ፡ ለትርፍ ፡ ጌጥ ፡ እያደረግህ ፡ የምትሚወትበትን ፡ ገንዘብ ፡ ለነሱ ፡ እየሰጠህ ፡ ከደስታህ ፡ አካፍላቸው ፤ ኀጢአት ፡ አሸንፎህ ፡ መስጠቱ ፡ አልሆንልህ ፡ ሲል ፡ ግን ፡ ኢታስተኀፍሮሙ ፡ ለነዳያን ፡ በእንተ ፡ ትፍሥሕትከ ፡ ያለውን ፡ አስበህ ፡ ባንተ ፡ ደስታ ፡ የሌለውን ፡ ባልንጀራህን ፡ ማሳፈሩን ፡ ማስቀናቱን ፡ እንኳ ፡ ተወው ።

ጥያቄ ።

፪፻፴ ፡ የሌለው ፡ ባልንጀራዬ ፡ ያፍራል ፡ ብዬ ፡ እኔ ፡ ወራዳ ፡ ብለብስ ፡ ለራሱም ፡ የማይሆን ፡ ጨቅ ፡ አባላለሁ ። በባልንጀሮቼም ፡ ዘንድ ፡ ሳይቸግረኝ ፡



እንደ ፡ ለበሱት ፡ ባለመልበሴ ፡ የነሱን ፡ የነቀፍኩባቸው ፡ ይመስላቸውና ፡ ያዝናሉ ፡ ሁለቱንም ፡ ወገን ፡ ላለማሳዘን ፡ በደስታዬ ፡ ወራት ፡ ምን ፡ ብለብስ ፡ ይሻላል ።

ምላሽ ።

፪፻፴፩ ፡ በሁብትህ ፡ ወራት ፡ ልብህን ፡ የውነተኛ ፡ ዳኛ ፡ አድርገህ ፡ የጌጥ ፡ ልብስ ፡ የለበስክበት ፡ ምክንያት ፡ ወይ ፡ ከበላይህ ፡ በግድ ፡ ታዞህ ፡ ወይ ፡ ለራስህ ፡ ማጓበቢያ ፡ ይሁንኝ ፡ ሳትል ፡ ስለ ፡ በዓል፡ ማክበር ፡ መሰል ፡ ባልንጀራህን ፡ ላለማሳፈር ፡ ሳትል ፡ በምትለብስበት ፡ ጊዜ ፡ አግረብኝም ፡ ብለህ ፡ ሳትቀናጣ ፡ ልብለጥም ፡ ብለህ ፡ የጌጥ ፡ ቍንጥ ፡ ሳታወጣለት ፡ ለትዝኀርት ፡ ለሆሩት ፡ ሲሉ ፡ የሰው ፡ ዐይን ፡ የሚያርፍበት ፡ ልዩ ፡ ልብስ ፡ እንደሚለብሱት ፡ ሁነህ ፡ ከሰው ፡ የተለየም ፡ ሳትለብስ ፡ ከጌጥህም ፡ መልክ ፡ ላይ ፡ ልብህን ፡ ሳትጥልበት ፡ ስለ ፡ ሥጋ ፡ ወይሙ ፡ ክብር ፡ ሰሞንኛ ፡ ስለ ፡ ጌታ ፡ ው ፡ ክብር ፡ ነፍጠኛ ፡ ታዞ ፡ እንደሚለብሰው ፡ እንደ ፡ ትእዛዝ ፡ ልብስ ፡ አድርገህ ፡ ልበሰው ፡ ባለባበስህም ፡ ተደስተህ ፡ አታጓብበት ፤ ግድ ፡ እሚያስጌጥህ ፡ ምክንያት ፡ በሌለብህ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ በወርቅ ፡ የተጥበረበረን ፡ በቀለምና ፡ በሐር ፡ የተኈጕረጐረውን ፡ ሳትለብስ ፡ ለበዓል ፡ ማክበር ፡ ባልንጀራን ፡ ላለማሳፈር ፡ የምትለብሰውን ፡ ያልወፈረ ፡ ያልቀጠን ፡ ያልከፋ ፡ ያላማረ ፡ ያላደፈ ፡ ያላስነወረ፡

አንድ ፡ ዐይነት ፡ የሆነ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ከለበሱት ፡ የሚታረብ ፡ ጥቂት ፡ አንባቢዎች ፡ ከሚለብሱት ፡ የሚርቅ ፡ መዝነህ ፡ ገምተህ ፡ ልበስ ። በዘወትሩ ፡ ልብስ ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ያላደፈ ፡ ልብስ ፡ ብቻ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ የጌጥ ፡ ቀለም ፡ ያለበት ፡ ቀለም ፡ የገባ ፡ ሐር ፡ የገባበት ፡ ለድኾች ፡ እጅግ ፡ የሚርቃቸውን ፡ ልብስ ፡ አንተ ፡ ካገኘሁ ፡ ብለህ ፡ አታዘውትረው ።

## ጥያቄ ።

፻፸፪ ፡ ባልንጀራ ፡ ላለማሳፈር ፡ ወይም ፡ በዓል ፡ ለማ ክበር ፡ ያለትእዛዝ ፡ በሚጌጥበት ፡ ጊዜ ፡ የጌጥ ፡ ባልንጀሮች ፡ የሚለብሱት ፡ እንደየፈቃዳቸው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ከስንቱ ፡ ፈቃድ ፡ ጋራ ፡ ለመመሳሰል ፡ የማይቻል ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ማናቸውን ፡ ዐይነት ፡ ቀለም ፡ ለጌጥ ፡ ብመርጠው ፡ ይሻላል ።

## ምላሽ ።

፻፸፫ ፡ ልብስን ፡ ቄንጠኛና ፡ ከተምኛ ፡ ይለዋወጠዋል ፡ እንጂ ፡ የያገሩ ፡ የልብስ ፡ አርአያ ፡ ከባላገሩ ፡ ላይ ፡ አይለወጥምና ፡ የማጌጫህን ፡ ቀለም ፡ መሠረቱን ፡ ባላገሮች ፡ ከሚለብሱት ፡ መልክ ፡ ሳታስለቅቅ ፡ ያንኑ ፡ አጣርተህ ፡ አቀላጥፈህ ፡ አክብረህ ፡ ልብስ ፡ አድርገው ፡ እንጂ ፡ እሱ ፡ ያፍራል ፡ ብለህ ፡ ቄንጠኛ ፡ ባልንጀራህን ፡ በቄንጠኛ ፡ ልብሱ ፡ አትመሳሰለው ። መደቡን ፡ የባላገሩን ፡ ልብስ ፡ አድርገህ ፡ ወደ ፡ ጌጡም ፡ መደቡን ፡ አትንሳው ።



የዚህንም ፡ ዐይነት ፡ እንድትረዳው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰዎች ፡ ልብስ ፡ መደቡ ፡ ነጭ ፡ ነው ፡ የምታጌጥበት ፡ ሁሉ ፡ በነጭ ፡ ልብስ ፡ ላይ ፡ ሲሆን ፡ በሩቅ ፡ ለሚያይህ ፡ ወገንህ ፡ ሐር ፡ ጨርቅ ፡ መሆኑ ፡ ወፍራምና ፡ ቀጭን ፡ መሆኑ ፡ አይታየውምና ፡ ትልቁ ፡ ሰው ፡ መስለን ፡ ልብሳችንንም ፡ አልናቀብንም ፡ ሲል ፡ ሳይቀና ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፡ የቅርቡም ፡ የሚያይህ ፡ ያጌጠው ፡ የክብር ፡ ባልንጀራህ ፡ ሐርነቱን ፡ ቅጥነቱን ፡ ካየ ፡ ጌጡን ፡ ናቅህብኝ ፡ ማለቱን ፡ እንዲያስቀርልህ ፡ ሲበዛ ፡ ልብስህንም ፡ ቀሚስህንም ፡ ነጭ ፡ ሐር ፡ አድርገህ ፡ በዚያ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ጌጥ ፡ አድርግበት ። በመጠነኛ ፡ ጌጥ ፡ ጊዜ ፡ ያንኑ ፡ ነጩን ፡ ቀጭን ፡ ልብስ ፡ አድርገው ፡ የመደረቢያው ፡ ልብስ ፡ ልማድ ፡ ጥቁር ፡ ነውና ፡ የጥቍሩን ፡ መደብ ፡ ሳታስለቅቅ ፡ የሚያስፈልግህን ፡ ጌጥ ፡ በመጠን ፡ ጨምርበት ። ይህንም ፡ የምታደርገው ፡ ነጸነት ፡ ሲኖርህ ፡ ነው ፡ በልብስህ ፡ ላይ ፡ የሚያዝ ፡ ዳኛ ፡ እንዳለብህ ፡ ግን ፡ ትእዛዙን ፡ ፈጽም ። (ስለ ፡ አባት ፡ እናት ፡ ም ፡ ፩) ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፮ ።

# ስለ ፡ ሰው ፡ ማዕርግ ።

፻፸፬ ፡ ሥጋዊ ፡ ሰውን ፡ በቍርጥ ፡ የሚያጣላው ፡ እስከ ፡ መጋደልም ፡ የሚያደርሰው ፡ ያከባበራችንና ፡ ያን

ቀወራችን ፡ ደንብ ፡ ሰው ፡ ጽሮ ፡ ሊጨርሰው ፡ ስላ ልቻለ ፡ ነው ። የሠለጠኑትም ፡ አውሮፖች ፡ እስካ ሁን ፡ ጽፈው ፡ አልጨረሱትም ፡ ስለዚህ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሲጣላ ፡ የሚኖረው ፡ ለነፍስ ፡ በማይጠቅመው ፡ በማዕርግ ፡ ሥጋ ፡ ምክንያት ፡ ነው ። ባገራችንም ፡ እንኳን ፡ ዝቅተኞች ፡ ንጉሦቹም ፡ ቢሆኑ ፡ በማዕርግ ፡ ምክንያት ፡ የሚነግሠውን ፡ ጠብ ፡ ለመታገሥ ፡ አልቻላቸው ፡ እያለ ፡ ጠባቸው ፡ ትልቅ ፡ እየሆነ ፡ ሲጣሉ ፡ የታዩት ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ ለዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ የኮሶ ፡ ምሳ ፡ መስጠታቸው ፡ ሳይቀር ፡ ለምን ፡ የመጣልኝ ፡ ሥጋ ፡ ታላቅ ፡ ሆነ ፡ ብለው ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ከድተው ፡ መንግሥቱ ፡ ከመፍረስ ፡ ሰው ፡ ከማለቅ ፡ ደረሰ ።

ዐፄ ፡ ዮሐንስም ፡ ካፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ቤት ፡ ግብሩን ፡ መብላታቸው ፡ ሳይቀር ፡ ከመቀመጫ ፡ መቀዳደም ፡ ብቻ ፡ ተጣሉ ፡ ከዚያም ፡ በፊት ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ባስጣጥና ፡ ባከባበር ፡ ምክንያት ፡ የሚጣላው ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ነውና ፡ ስለዚህ ፡ በዓለሙ ፡ የሚኖር ፡ ሰው ፡ የሚቻለውን ፡ ያኽል ፡ ያስጣጥና ፡ ያከባበር ፡ የተጸፈውን ፡ ደንቡን ፡ ያልተጸፈውን ፡ ልምዱን ፡ ከሱ ፡ ከሚቀድሙት ፡ ሽማግሌዎችና ፡ ፀዋቂዎች ፡ ላይ ፡ እየጠየቀ ፡ ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ያከባበርን ፡ ሥርዐት ፡ ጠንቅቆ ፡ ዐውቆ ፡ ሊሠራ ፡ ነው ፡ የሚገባው ። በእግዚአብሔርም ፡ ዘንድ ፡ ለሰው ፡ መሰማሚያ ፡ የሚያስፈልገ



ውን ፡ በመሥራቱ ፡ ብፁዓን ፡ ገባርያነ ፡ ሰላም ፡ የተባለውን ፡ ያገኛል ።

ጥያቄ ።

፪፻፴፭ ፡ ለሰው ፡ የሚያስከብሩት ፡ ማዕርጋት ፡ስንት ፡ ናቸው ።

ምላሽ ።

፪፻፴፮ ፡ ዐይነታቸው ፡ ሁለት ፡ ዝርዝራቸው ፡ ኻያ ፡ ነው ።

ጥያቄ ።

፪፻፴፯ ፡ የኒሁስ ፡ ማዕርጋት ፡ መገኛቸው ፡ ከማነው ።

ምላሽ ።

፪፻፴፰ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ነው ።

ጥያቄ ።

፪፻፴፱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ረቂት ፡ እኛ ፡ ግዙፍ ፡ የት ፡ ተገናኝተን ፡ ክብርን ፡ ሁሉ ፡ ከሱ ፡ እንቀበላለን ።

ምላሽ ።

፪፻፵ ፡ ስለዚህ ፡ ግዝፈታችን ፡ ረቂት ፡ ስጦታውን ፡ ማየት ፡ እማይቻለን ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ፀሥሩን ፡ በግዙፍ ፡ አካላችን ፡ አድሮ ፡ ይሰጠናል ፡ ፀሥሩን ፡ በየተፈጥሮ ፡ ባልንጀሮቻችን ፡ አድሮ ፡ እያሳየ ፡ ይሰጠናል ።

ስለዚህ ፡ ከእካላችንም ፡ በመገለጥ ፡ ከባልንጀራች
ንም ፡ በመቀበል ፡ የምናያቸው ፡ ሁሉ ፡ ከእግዚአ
ብሔር ፡ ነው ፡ የሚገኙት ።

ጥያቄ ።

፬፻፺፩ ፤ ከአካላችን ፡ የሚገኙት ፡ ዐሥሩ ፡ ከባልንጀ
ራችን ፡ የሚገኙት ፡ ዐሥሩ ፡ ክብሮች ፡ ምን ፡ ምን ፡
ናቸው ።

ምላሽ ።

፬፻፺፪ ፤ በባልንጀሮቻችን ፡ አፍ ፡ እየተናገረ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ እየሰጠን ፡ የሚታዩት ፡ ክብሮች ።
አንድ ፡ ጭቅንት ፤ ሁለት ፡ ዱግንት ፤ ሦስት ፡ ምስለ
ኔንት ፤ አራት ፡ አለቅንት ፤ አምስት ፡ እንበልኔት ፤
ስድስት ፡ ሻለቅንት ፤ ሰባት ፡ እንደራሴንት ፤ ስም
ንት ፡ ወንበርንት ፤ ዘጠኝ ፡ መኳንንትንት ፤ ዐሥር ፡
ንጉሥንት ፡ ናቸው ።

ጥያቄ ።

፬፻፺፫ ፤ የቀሩትስ ፡ ይሁን ፡ ንጉሥ ፡ ከማን ፡ ባልን
ጀራው ፡ ይቀበላል ።

ምላሽ ።

፬፻፺፬ ፤ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሳኦል ፡ ቁመት ፡ ሰ
ጥቶ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ ጉልበት ፡ ሰጥቶ ፡
ወይም ፡ እንደ ፡ ሰሎሞን ፡ ዕውቀት ፡ ሰጥቶ ፡



ለሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ የሚበልጣቸው ፡ አስመስሎ ፡ ሲያ
ሳያቸው ፡ እነሱኑ ፡ ንገሥብን ፡ ብለው ፡ እንዲናገሩ ፡
ያደርጋቸውና ፡ ሿሚው ፡ እሱ ፡ መሆኑን ፡ ለማስረ
ዳት ፡ ሕዝቡ ፡ እንደ ፡ ጌታ ፡ ሆነው ፡ ለሾሙት ፡
ንጉሥ ፡ ተመልሰው ፡ ሎሌ ፡ ሆነው ፡ እንዲገዙለት ፡
እንዲያከብሩት ፡ ያደርጋቸዋል ፡ እንጂ ፡ ንጉሥ ፡ በረ
ቂት ፡ የሚቀበለው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በጉልሕ ፡
የሚቀበለው ፡ ከሕዝቡ ፡ ነው ።

ከነዚህም ፡ ካሥሩ ፡ እየተጠጉ ፡ ክብሩ ፡ የነሱ ፡
ሳይሆን ፡ ከክብሮቹ ፡ በመጠጋታቸው ፡ ብቻ ፡ የሚ
ከብሩትም ፡ ፳ ፡ ናቸው ፡ የገኘ ፡ ልጅነት ፡ ሚስት
ነት ፡ ዘመድነት ፡ ሹምነት ፡ ባለሟልነት ፡ ያላቸ
ውን ፡ ሰዎች ፡ ፈጣሪ ፡ ያይደሉት ፡ ቅዱሳን ፡ ከእግ
ዚአብሔር ፡ ስለ ፡ መጠጋታቸው ፡ ለእግዚአብሔር ፡
ሲባል ፡ እንደሚከበሩት ፡ እነዚህም ፡ ገኘ ፡ ያልሆ
ኑት ፡ የክብር ፡ ጥገኞች ፡ ሁሉ ፡ ለገኛቸው ፡ ሲባል ፡
እነሱም ፡ ተጨምረው ፡ ይከብራሉ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡
ያሉት ፡ ክብሮች ፡ ሁሉ ፡ በሰው ፡ አቀባባይነት ፡
በእግዚአብሔር ፡ ሰጪነት ፡ ከአፍኣ ፡ የሚገኙ ፡
ክብሮች ፡ ናቸው ።

እሊህንም ፡ ዐሥሩን ፡ ተቀንዩ ፡ ለአጋዕዝቲክሙ ፡
በተባለው ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ስንል ፡
በየሚገባቸው ፡ ልክ ፡ ልናከብራቸው ፡ የሚገባቸው
ን ፡ ክብር ፡ ልኩን ፡ እየተመራመርን ፡ ልናውቅ
ላቸው ፡ ይገባል ።

ከራሳችን ፡ አካል ፡ ላይ ፡ እያሳየ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ የሚሰጠን ፡ ክብሮች ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ።

፩ኛ ፡ ቁመት ፡ ያለጅልነት ፡ ሲታይ ። ፪ኛ ፡ ውበት ፡ ያለእብደት ፡ ሲታይ ። ፫ኛ ፡ ውፍረት ፡ ያለዘረት ፡ ሲታይ ። ፬ኛ ፡ ሽበት ፡ ያለቅሌት ፡ ሲታይ ። ፭ኛ ፡ የአካል ፡ ዕውቀት ፡ በፊት ፡ መዝናት ፡ በከንፈር ፡ መርጋት ፡ ሲታይ ። ፮ኛ ፡ በልቡ ፡ ዕውቀት ፡ ከፉና ፡ በጎ ፡ ለይቶ ፡ በመምከሩ ፡ በማጸፉ ፡ ሲታይ ። ፯ኛ ፡ በቃሉ ፡ ዕውቀት ፡ በማስተማር ፡ በመፍረድ ፡ እንጋገር ፡ በማፍታታት ፡ ሲታይ ። ፰ኛ ፡ በእጁ ፡ ዕውቀት ፡ በመሥራት ፡ በመጨረስ ፡ ሲታይ ። ፱ኛ ፡ በንብረቱ ፡ ዕውቀት ፡ ትዳር ፡ በማቀናበር ፡ ሰው ፡ በማስተዳደር ፡ ሲታይ ። ፲ኛ ፡ በመንፈሳዊ ፡ ዕውቀቱ ፡ አምላኩን ፡ ወዶ ፡ በጎ ፡ ግብር ፡ ለምዶ ፡ ሲታይ ።

ለየተቈጠሩበት ፡ ክፍል ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ባለ ዕድል ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፡ ለማክበር ፡ ስንል ፡ ልናከብራቸው ፡ ይገባል ።

እግዚአብሔርም ፡ በሰው ፡ አካል ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ሠራው ፡ ሥራ ፡ ሰውን ፡ ማክበር ፡ መገባቱን ፡ አክብር ፡ ገጽ ፡ አረጋዊ ፡ ባለው ፡ አስተውል ። ከእኒህ ፡ ከጽው ፡



ፀይኑት ፡ ክብር ፡ ላይ ፡ ደራርበም ፡ ቢሰጠው ፡ ከፋፍሎም ፡ ቢሰጠው ፡ ፀዳዩ ፡ አምላካችን ፡ ነውና ፡ ሳትቀናበት ፡ ስለ ፡ ፀዳዩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ብለህ ፡ ታዳዩን ፡ ወንድምህን ፡ በታደለው ፡ ፀቅም፡ ልክ ፡ ልታከብረው ፡ ይገባል ። ላከበራቸውም ፡ ለደረጃው ፡ ከፍታና ፡ ዝቅታ ፡ አላቸውና ፡ እንደየማዕርጋቸው ፡ አክብራቸው ፡ የሚያዙትንም ፡ ስማቸው ፡ ለትልቁ ፡ የሚገባውን ፡ ክብር ፡ ለትንሹ ፡ ሰጥተህ ፡ አታሳፍረው ፡ ለትንሹ ፡ የሚገባውን ፡ ለትልቁ ፡ ሰጥተህ ፡ እንዳታዋርደው ፡ በየገኑ ፡ ያለውን ፡ ያከባበሩን ፡ ልማድ ፡ አስቀድመህ፡ ተማርና ፡ እንደያቅሙ ፡ አክብረው ። ስታከብር ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ትልቅ ፡ ቢሆኑ ፡ ሰዎች ፡ መሆናቸውን ፡ ፀውቀህ ፡ ከማምለክና ፡ ከመፍራት ፡ ርቀህ ፡ አክብራቸው ፡ ታዘዛቸው ፡ እንጂ ፡ አትፍራቸው ፡ አታምልካቸው ፡

ጥያቄ ።

፪፻፶፰ ፡ ሳይፈሩ ፡ ማክበር ፡ ሳያምኑ ፡ መታዘዝ ፡ እንዴት ፡ እድርገን ፡ ይገኛል ።

ምላሽ ።

፪፻፶፰ ፡ የዚህ ፡ ዕውቀት ፡ የፍጡርና ፡ የፈጣሪን ፡ ፀቅም ፡ ከሚያሳዩት ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ይገኛልሃል ፡ ከሱም ፡ ውስጥ ፡ እንኳን ፡ ሌሎችን ፡

ሹሞች ፡ ንጉሥንም ፡ ቢሆን ፡ እንድናከብር ፡ እን
ጂ ፡ እንድናመልከውና ፡ እንድንፈራው ፡ ለእግዚ
አብሔርስ ፡ ፍርሀዎ ፡ ወለንጉሥስ ፡ አክብርዎ ፡
ሲባል ፡ የታወጀውን ፡ ቃል ፡ ታገኘለህ ፤ ይህንም ፡
አመካኝተው ፡ ትዕቢትና ፡ ኵራት ፡ እንዳይጐዱህ ፡
በነሱም ፡ ላይ ፡ ሳትኰራ ፡ ሹምም ፡ ንጉሥም ፡
የሚያዙህን ፡ ሁሉ ፡ ሥራ ። እነሱን ፡ ማምለክ ፡ እን
ዳይሆንብህ ፡ ሹምንም ፡ ንጉሥንም ፡ ሳትፈራቸው ፡
የምታከብርበትም ፡ የምትታዘዝበትም ፡ ምክንያት ፡
ለእግዚአብሔር ፡ ብለህ ፡ ይሁን ።

ጥያቄ ።

፻፶፯ ፡ የሥጋ ፡ ባሕርይ ፡ እቀጣለሁን ፡ ሳይጨምር ፡
አጸድቃለሁ ፡ ብቻ ፡ ብሎ ፡ ለማክበር ፡ እማይቻለ
ውን ፡ መምከር ፡ ጸር ፡ ማክበድ ፡ አይሆንም ።

ምላሽ ።

፻፶፰ ፡ ዕውቀት ፡ እሚመከረው ፡ ለዐዋቂዋ ፡ ነፍስ ፡
ነው ፡ እንጂ ፡ የሥጋማ ፡ ጠባይ ፡ እንስሳ ፡ አይደለ
ምን ፤ ምን ፡ ይመከራል ። ለዐዋቂዋ ፡ ነፍስ ፡ ግን ፡
እንደ፩ ፡ ያለው ፡ ፍጡር ፡ ቢሾም ፡ ፍጥረቱ ፡ የተ
ለወጠ ፡ መስሏት ፡ ብትለማመጥ ፡ ብትፈራ ፡ እንደ
ኔው ፡ የተፈጠረም ፡ ነው ፡ ብላ ፡ ሹሙን ፡ ብትንቅ ፡
ባትታዘዝ ፡ ሁለቱ ፡ ኀጢአት ፡ ይሆናል ። ስለዚህ ፡
ላወቀ ፡ ሰው ፡ የሚገባው ፡ ሹም ፡ የእግዚአብሔር ፡
መግረያ ፡ በመሆኑ ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡



ማክበር ፡ መታዘዝ ፡ ሠሪ ፡ ቀጪ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ፡
እግዚአብሔርን ፡ ብቻ ፡ ማምለክ ፡ መፍራት ፡ የሚ
ገባ ፡ መሆኑን ፡ ዕወቅ ፡ (ጣዕመ ፡ ጸሎት ፡ ም ፡ ፰) ።

ጥያቄ ።

፻፶፱ ፡ አፍቅር ፡ ቢጸክ ፡ ኢትቁም ፡ ዕራቀክ ፡ ስለ ፡
ተባለው ፡ ገንዘቤን ፡ ለበላዩና ፡ ለባልንጀራዬ ፡
በምስጥበት ፡ ጊዜ ፡ የመለማመጥም ፡ የመናቅም ፡
እንዳይሆንብኝ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ እያደረግሁ ፡ ብሰጥ ፡
ይሻላል ።

ምላሽ ።

፻፷ ፡ ተለምነህ ፡ በምትሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ገን
ዘቡ ፡ እናወር ፡ ከልመናው ፡ እያመሳሰልክ ፡ ስጠ
ው ፤ ወዳጅና ፡ ዘመድ ፡ የበላይ ፡ ጌታ ፡ ሳይለምን ፡
ለፍቅር ፡ ሲባል ፡ ለመውደድ ፡ ለማክበር ፡ ተብሎ ፡
ዐውቆ ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ አገራ
ችን ፡ ልማድና ፡ ወግ ፡ በይኑቱ ፡ ዐሥር ፡ ነው ።

፩ ፡ ሲወልድ ፡ የግምዶ ።

፪ ፡ ሲያዝን ፡ የዝን ።

፫ ፡ ሲዘምት ፡ የሥንቅ ፤ ሲመለስ ፡ የደስታ ።

፬ ፡ ሲሻር ፡ የሹመት ፡ አይደንግጥ ።

፭ ፡ ሲሾም ፡ የምሥራች ፡

፮ ፡ ሲገድል ፡ የሽልማት ።

፯ ፡ ለሰርግ ፡ ሲጠራ ፡ ለጽም ።

፰ ፡ ሲታመም ፡ የመጠየቂያ ።

፱ ፡ ሲመጣ ፡ በመስተንግዶ ።

፲ ፡ ሲወረስ ፡ ሲከስ ፡ ሲቃጠል ፡ ሲቀማ ፡ በርጥባን ፡ በዚህ ፡ ባሥሩ ፡ ዐይነት ፡ ለወዳጅ ፡ ለዘመድ ፡ ለጌታ ፡ ስጪው ፡ ካልቸገረው ፡ በቀር ፡ ሳይለምን ፡ ዐውቆ ፡ የተቻለውን ፡ ያኽል ፡ የሚሰጥበት ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ቢቀርም ፡ የሚያጣላ ፡ ነው ።

በቀረው ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ የሚሰጠው ፡ ባለቤት ፡ እንደየችግሩ ፡ ሲለምን ፡ ነው ፤ ያለዚህ ፡ ምክንያት ፡ እንዲያው ፡ ሲሰጥ ፡ ለጌታ ፡ ለዳኛም ፡ ቢሰጥም ፡ ለልምምጥ ፡ ለድኻው ፡ ሲሰጥ ፡ የምጽዋት ፡ ለባልንጀራም ፡ ሲሰጥ ፡ የቸርነት ፡ ይባላል ።

ስለ ፡ ስጦታም ፡ ልክ ፡ ያገር ፡ ልማድ ፡ ምርምር ። ለትልቅ ፡ ሰው ፡ ለስጦታው ፡ እኩጋገር ፡ ልማድ ፡ እንደሚያዘን ፡ ብር ፡ እኽል ፡ ካ፲ ፡ በላይ ፡ እንደየወደደው ፡ ልማድ ፡ ቢሰጥ ፡ አያስነቅፈውም ፤ ካሥር ፡ በታች ፡ ግን ፡ መስጠት ፡ ሲሻው ፡ ፫ ፡ ፭ ፡ ፯ ፡ ይሰጣል ፡ እንጂ ፤ ከሦስት ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ ሁለት ፡ አንድ ፡ ከፍ ፡ ብሎም ፡ ፬ ፡ ፮ ፡ ስምንት ፡ ቢሰጥ ፡ አይመሰገንም ። ከቶውንም ፡ ሙሉ ፡ ሲሆን ፡ ይሰጥ ፡ አያውቅ ፡ አራት ፤ ይማታ ፡ አያውቅ ፡ እናት ፡ ተብሎ ፡ ይነቀፍበታል ።



ጥያቄ ።

፪፻፶፩ ፡ ቢያንስ ፡ አይሁን ፡ ቢያበዛ ፡ አስመመስገኑ ፡ ምንድነው ።

ምላሽ ።

፪፻፶፪ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ጠባያችንን ፡ በምስጢሩ ፡ እየቃኘ ፡ የምንወደው ፡ ጐዶሎውን ፡ ዓለም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሲያስተምረን ፡ ሦስት ፡ አምስት ፡ ሰባት ፡ ለምሳሳችን ፡ ልምድ ፡ ሆኖብን ፡ ነውና ፡ ልማዱ ፡ እስኪለወጥ ፡ ተቀባዩ ፡ በመንቀፉ ፡ እንዳይጐዳ ፡ በዚህ ፡ ልማድ ፡ መስጠት ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፰ ።

## ጠላትን ፡ ላለመጥላት ።

## ለወዳጅ ፡ ላለማድላት ።

ጥያቄ ።

፪፻፶፫ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ጌታ ፡ በወንጌል ፡ ጠላታችሁን ፡ ውደዱ ፡ አለን ።

ምላሽ ።

፪፻፶፬ ፡ ጠላት ፡ ሁሉ ፡ ሰውን ፡ የሚጠላው ፡ የሚገድለውም ፡ የሚመታውም ፡ የሚከሰውም ፡ የሚዋጋውም ፡ እግዚአብሔር ፡ ክፉውን ፡ በክፉ ፡ ይቀጣ

ልና ፡ ከሱ ፡ እየታዘዘ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ ብቻ ፡ አይበድለንምና ፤ የታዘዘን ፡ ሰው ፡ መጥላት ፡ እማይገባን ፡ ቢሆን ፡ ነው ፡፡

ምሳሌ ፡፡

የንጉሥ ፡ አሽከር ፡ ፩ዱ ፡ ታዞ ፡ ቢገርፍ ፡ ቢዘርፍ ፡ ቢበድል ፡ ቢገድል ፡ ልንጣላው ፡ እንደማይገባን ፤ ይህም ፡ ጠላት ፡ የምንለው ፡ ሰው ፡ እግዚአብሔር ፡ ያዘዘውን ፡ ያኽል ፡ ቢሠራብን ፡ ለምን ፡ ለፈጠረህ ፡ ጌታ ፡ ታዘዝክ ፡ ብለን ፡ ሰውን ፡ ብንጣላው ፡ ታዞ ፡ የሚመታውን ፡ አጋፋሪ ፡ መልሶ ፡ እንደሚመታ ፡ ባለጌ ፡ መሆን ፡ ነውና ፤ ስለዚህ ፡ ጠላታችን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ታዞ ፡ የሚሠራብን ፡ መሆኑን ፡ ሲያስረዳን ፡ ጌታ ፡ በወንጌል ፡ መጥላትን ፡ ከመከልከል ፡ አልፎ ፡ ለመውደድ ፡ ማዘዙ ፡ እኛ ፡ ጠላቶች ፡ የምንላቸው ፡ በፈቃዳቸው ፡ የማይሠሩ ፡ የኛ ፡ ኀጢአት ፡ የሚያሳዝዛቸው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ የሚያዛቸው ፡ ታዛዥ ፡ ሠራተኞች ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ጠላቶቻችን ፡ አይደሉምና ፤ በደለን ፡ ብለን ፡ ሰውን ፡ ልንጣላው ፡ አይገባንም ፡፡

የታዘዘ ፡ እንጂ ፡ የተጣላን ፡ ብቻ ፡ እማይጐዳን ፡ መሆኑንም ፡ ከማያውቁን ፡ ከማናውቃቸው ፡ ድንገት ፡ እየተገናኘን ፡ በመጣፋታችን ፡ አስተውል ፡፡

ጥያቄ ፡፡

፫፻፶፯ ፡ ሰውን ፡ ሰው ፡ የማይጐዳው ፡ ከሆነ ፡ ዘቀ



ተለ ፡ በመጥባሕት ፡ ይትቀተል ፡ በመጥባሕት ፡ ሲል ፡ ስለ ፡ ምን ፡ በፍትሐ ፡ እግዚአብሔር ፡ ታዘዘ ፡፡ ጻድቁ ፡ ዳዊትስ ፡ ኢትርሳዕ ፡ በቀለ ፡ ሳሚ ፡ ወኢዮአብ ፡ ብሎ ፡ ለልጁ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ተናዘዘለት ፡፡

ምላሽ ፡፡

፫፻፶፯ ፤ በዚህማ ፡ እግዚአብሔር ፡ ክፉውን ፡ በክፉ ፡ ይቀጣል ፡ ያልኩህ ፡ ጠላት ፡ ሆኖ ፡ የሚጐዳው ፡ ሰው ፡ ኀጢአተኛ ፡ መሆኑን ፡ ስንገርህ ፡ አይደለም፤ ፍትሐ ፡ እግዚአብሔር ፡ በገደለው ፡ ይሙት ፡ ማለቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ታዞ ፡ በመሥራቱ ፡ በኩል ፡ አይደለም ፤ ስለ ፡ ክፉ ፡ ፈቃዱ ፡ ነው ፡፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ጠላቴን ፡ ከእጇ ፡ ጣልልኝ ፡ ብለው ፡ ገልጠው ፡ ይለምኑታል ፤ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ ጥጋባቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ አጋጥሞኝ ፡ አንዱን ፡ ባንዱ ፡ ላይ ፡ አደራርቤ ፡ ገድዬ ፡ ቀምቼ ፡ ዘርፌ ፡ ለማጌጥ ፡ ለመከራት ፡ ባቢታኝ ፡ እያሉ ፡ እንዲህ ፡ የሚመኙትን ፡ ሰዎች ፡ መርጦ ፡ ለትጣት ፡ መሣሪያ ፡ አድርጎ ፡ ይቀጣባቸዋል ፡ እንጂ ፤ እነሱ ፡ የተመኙትን ፡ መሥራት ፡ አይችሉም ፡፡ ፍትሐ ፡ እግዚአብሔርም ፡ የሚፈርደው ፡ በሰው ፡ ቍርጥ ፡ ፈቃድ ፡ ላይ ፡ ነውና ፡ እነሱም ፡ ስለ ፡ ክፉው ፡ አሳባቸውና ፡ ስለ ፡ ክፉ ፡ መሻታቸው ፡ ወይም ፡ እንደነሱ ፡ ካሉ ፡ አገናኝቶ ፡ ወይም ፡ ካልበደሉት ፡ ዳኛ ፡ አጣልቶ ፡ ወይም ፡ ክፉ ፡ ምኞታቸውን ፡ በእሱ ፡ ትእዛዝ ፡ የዳኛውን ፡ አሳብ ፡ አንሣሥቶ ፡ የነ

ሱን ፡ ሥራ ፡ ገልጦ ፡ ካደባባይ ፡ አስፈርዶ ፡ ያጠፋቸዋልና ፡ በክፉ ፡ መሻታቸው ፡ እንዲፈርድባቸው ፡ ሲያስረዳ ፡ ዘቀተለ ፡ በመጥባሕት ፡ ይመውት ፡ በመጥባሕት ፡ አለ ።

ዳዊትም ፡ ስለ ፡ ሳሚ ፡ ወልደ ፡ ጌራ ፡ በፊት ፡ ሲሰድበው ፡ ሎላልቱ ፡ እንግደለው ፡ ቢሉ ፡ ተዉ ፡ እግዚአብሔር ፡ አዞታልና ፡ ይስደበኝ ፡ ማለቱ ፡ ጠላት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ታዛዥ ፡ መሆኑን ፡ በግልጽ ፡ ሲያስተምረን ፡ ነው ፤ በኋላም ፡ ኢትርሳዕ ፡ በቀለ ፡ ሳሚ ፡ ወኢዮአብ ፡ ማለቱ ፡ ምንም ፡ እግዚአብሔር ፡ መግሪያ ፡ አድርጎ ፡ ቢሠራባቸው ፡ እነሱም ፡ የሰውን ፡ ማጥፋትና ፡ ማዋረድ ፡ የሚሹ ፡ ባለክፉ ፡ ፈቃድ ፡ ናቸውና ፡ እሱ ፡ ተሸማግቶ ፡ ባለጋራውን ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ መቅጣት ፡ እንዳይሆንበት ፡ ዳኛም ፡ ነውና ፡ ዝም ፡ ብሎም ፡ በመተው ፡ ዳኝነት ፡ እንዳያጐድልበት ፡ ለልጁ ፡ ኢትርሳዕ ፡ ብሎ ፡ መናዘዙ ፡ ስለዚህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ጠላት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ታዛዥ ፡ መሆኑንስ፡ ራሱ፡ ዳዊት፡ ስመ ፡ ክብሩን ፡ ሲያዋርድበት ፡ ኢዮአብ ፡ ልጁን ፡ ሲገድልበት ፡ መቅጣት ፡ ሲቻለው ፡ መተው ፡ የሚያስረዳን ፡ መምህር ፡ ይሁንህ ።

የዚሁንም ፡ እውነትንነት ፡ በራስህ ፡ አሳብ ፡ መርምረህ ፡ ለመረዳት ፡ ብትሻ ፡ ሰው ፡ በተፈጥሮው ፡ የተካከለ ፡ ሲሆን ፡ አንዱ ፡ አንዱን ፡ ማጥቃቱ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ኃይል ፡ ሲያገኝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በራ



ሱ ፡ ዐቅም ፡ ብቻ ፡ ሊያጠቃ ፡ አለመቻሉን ፡ የተፈጥሮችን ፡ ትክክልነት ፡ ያስረዳሃል ።

ጥያቄ ።

፪፻፶፯ ፡ ትልቅና ፡ ትንሽ ፡ ደካማና ፡ ብርቱ ፡ ሰው ፡ አለ ፡ አይደለምን ፤ በጉልበት ፡ መጠቃቃትማ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ይቀራል ።

ምላሽ ።

፪፻፶፯ ፤ ይህስ ፡ አይምሰልህ ፡ ደንጊያ ፡ ሁሉ ፡ ግዘፉ፡ ቢበላለጥ ፡ የባሕርይ ፡ ብርታቱ ፡ እንደማይለያይ ፤ የሰውም ፡ መርዘሙና ፡ ማጠሩ ፡ መቅጠኑና ፡ መወፈሩ ፡ የተፈጥሮ ፡ ባሕርይን ፡ አለማበላለጡን ፡ አጭር ፡ ዳዊት ፡ ረዥም ፡ ጎልያድን ፡ ሴት ፡ ዲቦራ፡ ሲሳራን ፡ ሴት ፡ ዮዲት ፡ ወንድ ፡ ሆሎሆርኒስን ፤ በዘመናችንም ፡ በአውሮፓ ፡ አጭር ፡ ናፖልዮን ፡ ብዙና ፡ ረዥም ፡ መስኮብን ፡ ሴት ፡ ቢክቶርያ ፡ ወንዶች ፡ እንግሊዞችን ።

በሐበሻ ፡ ሴት ፡ ዘውዲቱ ፡ ወንድ ፡ ኢያሱን ፤ አጭር ፡ ተፈሪ ፡ ረዥም ፡ ሚካኤልን ፡ በማጥቃታቸው ፤ የነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ታሪክ ፡ የሰው ፡ ዐቅም ፡ አለመበላለጡን ፡ ሥራው ፡ ኀይለ ፡ እግዚአብሔር ፡ መሆኑን ፡ ርግጠኑን ፡ ያስረዳሃልና ፡ እንዲህ ፡ አድርገህ ፡ የታዛዥነቱን ፡ ርግጥነት ፡ ዕወቅ ፡ እንጂ ፡ ሰውን ፡ ወደደኝ ፡ ብለህ ፡ አትታመንበት ፤ ጠላኝም ፡ ብለህ፡ አትከፋበት ።

ጥያቄ ።

፻፶፱ ፤ የውጭስ ፡ ባላጋራ ፡ ሲበድል ፡ እሺ ፡ ጌታ ፡ እንደሚያዘው ፡ እንደ ፡ ባልንጀራ ፡ አይቼ ፡ ልታገሠው ፡ ተቀንዩ ፡ ለአጋዕዝቲከሙ ፡ የተባሉ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ አክብር ፡ አባከ ፡ ወእመከ ፡ የተባለ ፡ ልጅስ ፡ ቢበድል ፡ እንስትኒ ፡ ይትአዘዛ ፡ ለአምታቲሆን ፡ የተባለች ፡ ሚስት ፡ ስትበድል ፡ መካድ ፡ መጥላት ፡ መቅጣት ፡ አይገባምን ።

ምላሽ ።

፻፷ ፤ ስለ ፡ ዳኝነትህ ፡ በታዘዘው ፡ ልክ ፡ መቅጣት ፡ ይገባሃል ፤ ይልቁንም ፡ አንዱ ፡ አንዱን ፡ ሲበድለው ፡ በዳኝነትህ ፡ ቅጣ ፡ እንጂ ፡ ራስህን ፡ ብቻ ፡ ሲበድሉህ ፡ ሚስትህም ፡ ልጅህም ፡ ሎሌህም ፡ ቢሆን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ታዘው ፡ ነውና ፡ የሚቀጡህ ፡ ቂም ፡ ሳትይዝ ፡ ስለ ፡ ዳኝነቱ ፡ ሕግ ፡ ብቻ ፡ ቅጣቸው ፡ እንጂ ፡ ልጅህንም ፡ መካድ ፡ ሎሌህንም ፡ መጥላት ፡ አይገባህም ፤ የነሱንም ፡ ታዛዥነት ፡ ትረዳ ፡ ዘንድ ፡ ብትወድ ፡ በሳኦል ፡ ጋሻ ፡ ጃግሬውን ፤ በዘመናችንም ፡ በወሰን ፡ ሰገድ ፡ ባሪያቸውን ፡ ቀድሞም ፡ በሶምሶን ፡ ኋላም ፡ በዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ሚስቶቻቸውን ፡ ማዘዙን ፡ እስተውል ፤ አባትን ፡ ልጁ ፡ ለመቅጣት ፡ ዳዊትን ፡ በአቤሴሎም ፡ በዘመናችንም ፡ ስብስቴን ፡ ባብዩ ፡ ደጃች ፡ ትኩን ፡ በሦስቱም ፡ ልጆቻቸው ፡ መቅጣቱን ፡ እንደዚህ ፡



ያለ ፡ በየዘመኑ ፡ የተሠራ ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ መኖሩን ፡ ዕወቅ ። ከዚህም ፡ አልፎ ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ አካል ፡ አካልን ፡ እንዲቀጣ ፡ ያደርገዋል ።

ይህንም ፡ የሚያስረዳህ ፡ ስለ ፡ ንጉሥ ፡ አኪጦፌልና ፡ ይሁዳን ፤ በዘመናችንም ፡ ስለ ፡ ዙራት ፡ የብሩ ፡ አባ ፡ ዲራንና ፡ የዐፄ ፡ ቴዎድሮስን ፡ ስለ ፡ ጥቅም ፡ የስምዖን ፡ ሰፋፉ ፡ አማእንና ፡ የአባስ ፡ ካህን ፡ ሮሜን ፤ በዘመናችንም ፡ አባ ፡ ካህን ፡ ሥላሴ ፡ የገዛ ፡ አካላቸውን ፡ ቀጡ ። እንዲሁም ፡ መሆኑ ፡ አንዱ ፡ አካል ፡ አንዱን ፡ አካል ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ የቀጣው ፡ በልጦትም ፡ ጠልቶትም ፡ አይደለም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንኳን ፡ የሌላውን ፡ አካል ፡ የገዛ ፡ አካላችንን ፡ በራሳችን ፡ ላይ ፡ እዞ ፡ እንዲያሠራው ፡ ሲያስረዳን ፡ ነውና ፡ ያልተጣሉት ፡ አካሎች ፡ እየታዘዙ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ የሚቀጣጡ ፡ መሆናቸውን ፡ እያየን ፡ እንኳን ፡ ሌላው ፡ ባዕዱ ፡ ሰውና ፡ ሚስትም ፡ ልጅና ፡ ዘመድም ፡ ሎሌና ፡ ገረድም ፡ ቢጠሉን ፡ ልንጣላቸው ፡ አይገባንም ።

ጥያቄ ።

፻፷፩ ፤ ኖኅን ፡ ከነዓን ፡ ያዕቆብን ፡ ሮቤል ፡ ቢበድሏቸው ፡ ተከደው ፡ የለምን ፤ ሌላው ፡ ቢቀር ፡ አባት ፡ በዳይ ፡ ልጅን ፡ መካድ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አይገባ ፡ ይሆናል ፤ ይድሐፍ ፡ ላቲ ፡ ኀዳጋቲሃ ፡ በተባለውስ ፡ ሚስቱንስ ፡ ቢፈታት ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አይገባ ፡ ይሆናል ።

## ምላሽ ።

፻፫፭፪ ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ጠላትን ፡ መጥላት ፡ ባልተከለ
ከለበት ፡ እእምሮ ፡ ባልጐለመሰበት ፡ በዘመን ፡
ብሉይ ፡ የተሠራ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አፍቅሮ ፡ ጸላእት ፡
ለታዘዝነው ፡ ለኛ ፡ አብነት ፡ አይሆንንም ፡ እነሱ ፡
እንኳ ፡ ቢበድሉ ፡ ተረገሙ ፡ እንጂ ፡ ርስት ፡ አሳ
ጥተው ፡ ትውልዳቸውን ፡ ፍቀው ፡ አልካዷቸውም ፤
በዘመናችንስ ፡ ልጆቻቸውን ፡ ቢክዱ ፡ ያፍቅሮ ፡
ጸላእት ፡ ዐዋጅ ፡ በማፍረሳቸው ፡ አባቶች ፡ ተጨ
ምረው ፡ ይጉዳሉ ፡ እንጂ ፡ ልጆች ፡ ብቻ ፡ አይጐ
ዱም ። እንዳንዶቹስ ፡ የፈሩት ፡ ይደርሳል ፡ የጠ
ሉት ፡ ይወርሳል ፡ እንደሚባል ፡ በግድ ፡ ወራሽ ፡
ይሆናሉ ።

ሚስትም ፡ ብትሆን ፡ ከጠላችኝ ፡ ልጥላት ፡ ማለት ፡
እማይገባ ፡ መሆኑን ፡ ሚስቱን ፡ የፈታ ፡ ከዝሙት ፡
ምክንያት ፡ ሌላ ፡ ፈጽሞ ፡ አመነዘረ ፡ ባለው ፡ አስ
ተውል ።

የሚጠሏችሁን ፡ ከጠላችሁ ፡ የሚወዷችሁን ፡ ከወ
ደዳችሁ ፡ ምን ፡ ዋጋ ፡ አላችሁ ፡ የተባለውንም ፡ አ
ትርሳ ።

ስለዚህ ፡ ልጅም ፡ ሚስትም ፡ ዘመድም ፡ አካልም ፡
ሎሌም ፡ ጓደኛም ፡ ዳኛም ፡ በተጣላን ፡ ጊዜ ፡ ከእግ
ዚአብሔር ፡ መታዘዛቸውን ፡ እንወቅ ፡ እንጂ ፡ እነ
ሱን ፡ መጣላት ፡ አይገባንም ። ለማስረዳትም ፡ ይህ ፡



ይበቃል ፡ ጠላትስ ፡ መጉዳት ፡ ይጉዳል ።
መቅጣትን ፡ ላንተ ፡ ማን ፡ ሰጥቶህ ፡
ከአምላክህ ፡ ሥራ ፡ የገባህ ፡
በባለጋራ ፡ መፍረድ ፡
አለማወቅ ፡ ነው ፡ ማበድ ።
ከአብደትም ፡ በላይ ፡ ድፍረት ፡
ከአምላክ ፡ ዳኝነት ፡ መሻማት ።
ልብህ ፡ ሥልጣኑን ፡ ካወቀው ፡
በቀልን ፡ ለሱ ፡ ተወው ፡
መጥላትንም ፡ ጥላው ።

(ጣዕመ ፡ ጸሎት ፡ ም ፡ ፺፱ና ፡ ፩ ። ስለ ፡ አባትና ፡
እናት ፡ ም ፡ ፷፰) ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፱ ።

### በወዳጅ ፡ እጠቀማለሁ ፡ ለሚል ፡ የሚጉዳበት ንና ፡ የሚጠቀምበትን ፡ የፍቅርን ፡ ዐይነት ፡ ማወቂያ ።

፻፫፭፫ ፡ ሰው ፡ ሰውን ፡ ወዶ ፡ እማይጉዳው ፡ ነገር ፡ ነ
ውና ፡ ስለዚህ ፡ አንተ ፡ ሰው ፡ ውደድ ፡ ለሰው ፡ አትወ
ደድ ፡ የሚያስጠትምህ ፡ ፍቅር ፡ ድምሩ ፡ ይህ ፡ ነው ።

ጥያቄ ።

፬፻፷፱ ፡ ሰው ፡ ጠልቶ ፡ ካልጐዳ ፡ ወዶ ፡ ካልጠቀመ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ወእምነቱ ፡ ተፀቢ ፡ ተፋቅሮ ፡ ተባለ ።

ምላሽ ።

፬፻፸ ፡ የሚገባ ፡ ፍቅር ፡ የማይገባ ፡ ፍቅር ፡ አለና ፡ ከማይገባው ፡ ፍቅር ፡ የሚገባውን ፡ ለይቶ ፡ መያዝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የማይጠቅመውን ፡ የማይገባውንስ ፡ ፍቅር ፡ የያዘ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ አምልኮ ፡ ባዕድ ፡ ይደርስና ፡ በዚያው ፡ በወዳጁ ፡ ይጐዳበታል ፡ እንጂ ፡ አይጠቀምበትም ። እግዚአብሔር ፡ እንደዚህ ፡ ያሉትን ፡ በወዳጅ ፡ የሚታመኑትን ፡ ሰዎች ፡ ወዳጁን ፡ በወዳጁ ፡ ይጐዳዋል ።

ይህንም ፡ ልትረዳ ፡ ብትሻ ፡ የሳኦልና ፡ የዳዊት ፡ የሰሎሞንና ፡ የሮብዓምን ፡ በዘመናችንም ፡ የራስ ፡ ዐሊንና ፡ ያፄ ፡ ቴዎድሮስን ፡ ያፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስና ፡ ያፄ ፡ ዮሐንስን ፡ የልጅ ፡ ኢያሱን ፡ ስታስተውል ፡ እስከ ፡ መሾም ፡ የደረሱበትን ፡ ክብር ፡ እስከ ፡ መጋባት ፡ የደረሱበትን ፡ ፍቅር ፡ እስከ ፡ መጥፋት ፡ የደረሱበትንም ፡ ጠብ ፡ ታገኛለህ ።

እኒህም ፡ ሁሉ ፡ በሚያምኑት ፡ ወዳጅ ፡ መጐዳታቸው ፡ ርጉመ ፡ ይኩን ፡ ዘይትአመን ፡ በወልደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ የተባለውን ፡ ስለ ፡ ረሱ ፡ የሚያምኑት ፡ ወዳጅ ፡ መጐዳቱን ፡ እግዚአብሔር ፡ ለቀ



ሪዎቹ ፡ ሲያስተምረን ፡ ነው ፡ ትእዛዙም ፡ እፍቅር ፡ ቢጸክ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ተአመን ፡ በቢጽከ ፡ አላለንምና ፤ ሰውን ፡ መውደድ ፡ እንጂ ፡ ማመንም ፡ እንዲወደን ፡ መጣርም ፡ አይገባንም ።

ጥያቄ ።

፬፻፸፩ ፡ ምነው ፡ ዮሐንስ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ቍ ፡ ፳ ፡ የሚያየውን ፡ ወንድሙን ፡ የማይወድ ፡ ያላየውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እወዳለሁ ፡ ቢል ፡ ሐሰተኛ ፡ ነው፡ ብሎ ፡ የለም ፤ ባለቤቱስ ፡ አፍቅር ፡ ቢጸከ ፡ ብሎ ፡ የለም ፡ ባልንጀራን ፡ መውደድ ፡ አይቀድምምን ።

ምላሽ ።

፬፻፸፪ ፡ ዮሐንስ ፡ ያየኸውን ፡ ሥራውን ፡ ሰውን ፡ ያዘዘውን ፡ ቃሉን ፡ እየጠላህ ፡ ሠሪውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እወዳለሁ ፡ ብትል ፡ ሐሰተኛ ፡ ነህ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አልወደድከውም ፡ በማለቱ ፡ ለሚወደደው ፡ አምላክ ፡ የሚሠራለትን ፡ አስተማረ ፡ እንጂ ፡ ፍጡርን ፡ ሰው ፡ ከፈጣሪ ፡ ጋራ ፡ አስተካክለህ ፡ ወይም ፡ አስቀድመህ ፡ ወይም ፡ አከታትለህ ፡ ውደድ ፡ ማለቱ ፡ አለመሆኑን ፡ አስተውል ። አፍቅር ፡ ቢጸከ ፡ ብሎ ፡ ጌታ ፡ የተናገረው ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲፈጸም ፡ ግን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ተብሎ ፡ እንደሚሠራው ፡ እንደ ፡ ጾም ፡ እንደ ፡ ጸሎት ፡ ሁሉ ፡ ሲቻልህ ፡ ሰው ፡ ሳትለይ ፡ ሁሉን ፡ መውደድ ፡ ባይቻልህ ፡ ግን ፡ ውለታ ፡ ቢስ ፡ ሆነህ ፡ ፍዳ ፡ እን

ዳይጸናብህ ፡ የወዳጅህንም ፡ ውለታ ፡ አድርጎቱን ፡ ብቻ ፡ ባድርጎት ፡ እየመለስክ ፡ ሰው ፡ መውደድን ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ሥራ ፡ አድርገህ ፡ ሥራው ፡ እንጂ ፡ ሰውን ፡ ብወድ ፡ ይጠቅመኛል ፡ ብለህ ፡ ብታምነው ፡ ቢጠላ ፡ ይጐዳኛል ፡ ስትል ፡ ብትወደው ፡ ያባቶች ፡ ታሪክ ፡ ሁሉ ፡ እንደሚያስረዳን ፡ በሥጋህም ፡ ያው ፡ ከሰው ፡ ለይተህ ፡ የወደድከውና ፡ ያመንከው ፡ ይጐዳሃል ፡ በነፍስም ፡ እንደ ፡ ሄሮድስ ፡ በጽድቅህ ፡ ታላቅ ፡ ኀጢአት ፡ መሥራትህ ፡ ነውና ፡ ሰውን ፡ ከማመን ፡ ተከልከል ፡ ተጠበቅ ።

ጥያቄ ።

፪፻፸፰ ፡ እምነት ፡ የሌለበት ፡ ወዳጅነት ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ይገኛል ፡ ከሰው ፡ ለይቶ ፡ አምኖ ፡ ሲወደው ፡ ሲያገለግለውስ ፡ ከሰው ፡ አብልጦ ፡ አምኖ ፡ ካልወደደው ማ ፡ የወዳጁን ፡ ዋጋ ፡ በማስቀረቱ ፡ አይጐዳምን ።

ምላሽ ።

፪፻፸፱ ፡ ሰው ፡ ለወዳጁ ፡ ገንዘቡንም ፡ ጕልበቱንም ፡ እሚሰጥበት ፡ ትርጓሜ ፡ አድርጊያለሁና ፡ አድርግልኝ ፡ ሲል ፡ መገበያየትን ፡ ሽቶ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አምልከኝ ፡ ብሎ ፡ አይደለምና ፡ ዋጋው ፡ እንዳይቀር ፡ ድኻ ፡ ሲሆን ፡ ጕልበቱን ፡ ሀብታም ፡ ሲሆን ፡ ከብቱን ፡ በስጦታው ፡ ልክ ፡ መልሶ ፡ ማድረግ ፡ ነው ፡ እንዲህ ፡ ያደርግልኛል ፡ ብሎ ፡ ሲያመልክህ ፡ ፍጥረቱና ፡ ፍጥረትህ ፡ ፈራሽ ፡ ተለዋጭ ፡ መሆናችሁን ፡ አስረዳው ፡ እንጂ ፡ ከታመነብኝ ፡



ሊታመንበት ፡ አትበል ፡ ገንዘቡንም ፡ ስለ ፡ ሰጠህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የምትወደው ፡ ገንዘብ ፡ ወዳጅ ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ ወዳጅ ፡ አያሰኝም ።

ጥያቄ ።

፪፻፹ ፡ እስካሁን ፡ በልማድ ፡ የሚያጸድቅ ፡ ሲመስል ፡ የነበረው ፡ ፍቅር ፡ ሁሉ ፡ የአምልኮ ፡ ባዕድ ፡ ሥራ ፡ ከሆነ ፡ የሚገባው ፡ ፍቅር ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ያለ ፡ ነው ።

ምላሽ ።

፪፻፹፩ ፡ ፍቅር ፡ ማለት ፡ የበጎ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ መሠረት ፡ ለትሩፋት ፡ ፍቱን ፡ አብነት ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የሚገኝበት ፡ ትልቅ ፡ ዕውቀት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እንደ ፡ ጾም ፡ እንደ ፡ ጸሎት ፡ እንደ ፡ ስግደ ፡ እንደ ፡ ምጽዋት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ተብሎ ፡ የሚሠራ ፡ ነውና ፡ ሲሆን ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ አስተካክሎ ፡ መውደድ ፡ ነው ፡ ባይቻልም ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚወዱትን ፡ ሰዎች ፡ ስለሱ ፡ አስተካክሎ ፡ መውደድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሚወደውንስ ፡ የሚወድ ፡ ጌታ ፡ በወንጌል ፡ እንዳለው ፡ እንደ ፡ ፈረሳውያን ፡ ሥጋውን ፡ ወዳጅ ፡ በነፍሱ ፡ አላጋጭ ፡ መሆን ፡ ነውና ፡ የምትጸድቅበት ፡ ፍቅር ፡ ለገንዘብ ፡ ዋጋ ፡ ተቀ ሆኖ ፡ እንዳያጠፋብህ ፡ የሰውን ፡ ገንዘብ ፡ ተቀ ብለህ ፡ ስለ ፡ ገንዘቡ ፡ ስትል ፡ ከመውደድህስ ፡ የሚቻልኸን ፡ ያኽል ፡ አጥብቀህ ፡ ሽሽ ።

መቀበልን ፡ ጠልተህ ፡ መስጠትን ፡ ውደድ ፤ ገንዘብ ፡ ለመጥላት ፡ የማይቻልህ ፡ ሁኖ ፡ ዕድልህ ፡ የሰው ፡ ገንዘብ ፡ መቀበል ፡ ሲሆንብህ ፡ የሚሰጥህ ፡ ጌታህ ፡ ሲሆን ፡ ጕልበትህን ፡ ለገንዘቡ ፡ መሸጥህ ፡ ነውና ፡ ያንኑ ፡ የሸጥከውን ፡ ጕልበት ፡ ሳትለግም ፡ በቅንነት ፡ ሳትዋሽ ፡ በውነት ፡ እንደሚያዝህ ፡ አድርገህ ፡ ሥራ ። ጌታህን ፡ የምትወድበት ፡ ፍቅር ፡ ግን ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ ገንዘቡ ፡ አይሁን ፤ የሚሰጥህ ፡ ጓደኛህ ፡ ሲሆን ፡ እንደ ፡ ሌባ ፡ እንደ ፡ ወንበዴ ፡ እንዳትሆን ፡ መልሰህ ፡ ወርታህን ፡ በሰጠህ ፡ ልክ ፡ ለመክፈል ፡ ትጋ ፡ እንጂ ፡ ገንዘቡን ፡ አስቀርተህ ፡ ፍቅርህን ፡ ብቻ ፡ አትሽጥ ፤ እሚሰጥህ ፡ የበታችህ ፡ ዜጋ ፡ ሲሆን ፡ ከሰጠኸው ፡ ላይ ፡ ከፍሎ ፡ መተያያ ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ብሎ ፡ ከሚሰጥህ ፡ ወይም ፡ በግብሩ ፡ በዕዳው ፡ ምክንያት ፡ ማረኝ ፡ ስጠኝ ፡ ብሎ ፡ በትንሽ ፡ ሰጥቶ ፡ ትልቅ ፡ ሽቶ ፡ ሲሰጥህ ፡ አብልጠህ ፡ ለመስጠት ፡ የምትቀበለው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የቍልቍል ፡ ምጽዋት ፡ እንዳይሆንብህ ፡ ጭራሽ ፡ አትቀበለው ። መውደጃህና ፡ መጥሊያህም ፡ በመተያያ ፡ በማግለጃ ፡ ምክንያት ፡ አይሁን ። ከሰው ፡ ላይ ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ቢሆን ፡ ገንዘብ ፡ ለማኘ ፡ አትሁን ፤ ለምንህ ፡ ከምታጠራቅመው ፡ ንብረት ፡ ሳትለምን ፡ የምታገኘው ፡ የርጋታህ ፡ ማዕርግ ፡ መብለጡን ፡ ዕወቅ ፤ የለማኝነትንም ፡ እስጠሊነት ፡ ያለመለመንንም ፡ እስ



ወዳጅነት ፡ አትርሳው ። ልመና ፡ የልጆች ፡ የበሽተኞች ፡ የእዝማሪዎችና ፡ የቅሌተኞች ፡ ሥራ ፡ ነውና ፡ እንኳን ፡ ከወዳጅህ ፡ ግዴታ ፡ ካላገኘህ ፡ በቀር ፡ ከጌታህም ፡ ቢሆን ፡ አትለምን ፤ በልመና ፡ የሚገኝ ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ ወይ ፡ ለማኙን ፡ ወይ ፡ ተለማኙን ፡ ያስከፋል ፡ እንጂ ፡ ለማኝ ፡ የሆነ ፡ ምንም ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ እውነተኛውን ፡ ፍቅር ፡ አያገኛትምና ፡ የፍቅርህን ፡ ማስሪያ ፡ ልመና ፡ እንዳታደርገው ፡ ተጠንቀቅ ። ከወዳጁ ፡ መለመን ፡ የሚወድ ፡ ሰው ፡ መውደድ ፡ ከውስጥ ፡ ከልቡ ፡ ጋራ ፡ የማይዋሐድ ፡ ለቍርና ፡ ለሐሩር ፡ ብቻ ፡ ሲባል ፡ እንደሚለበስ ፡ ልብስ ፡ ይሆንበትና ፡ የሚለበስ ፡ ነገር ፡ ማለቅ ፡ ባሕርዩ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ያልቅበታል ፡ ሲያልቅም ፡ ፍቅር ፡ ያልቅና ፡ ሲሆን ፡ ግትቻ ፡ ንዝንዝና ፡ ጭቅጭቅ ፡ ብቻ ፡ እያሉ ፡ የደረሰባቸው ፡ እየገጠሙ ፡ የሚናገሩት ፡ ይደርስብሃልና ፤ ለሰው ፡ የምታደርገውን ፡ ፍቅር ፡ ከልብህ ፡ አዋሕደው ፡ እንጂ ፡ ለሥጋህ ፡ አታልብሰው ።

ጥያቄ ።

፪፻፹፪ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ፍቅር ፡ እንዴት ፡ አድርጌ ፡ አገኘዋለሁ ።

ምላሽ ።

፪፻፹፫ ፡ ከሁሉ ፡ አስቀድመህ ፡ ያንተን ፡ የምትሰጥበትን ፡ የሰው ፡ የማትቀበልበትን ፡ የተወሰነ ፡

ኑሮ ፡ አብጅተህ ፡ የሰው ፡ ገንዘብ ፡ እንዳይገባብ
ህ ፡ አድርገህ ፡ የተጠነቀቅህ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ ይህን ፡
የሚገባውን ፡ የወንድምህን ፡ ፍቅር ፡ ለማግኘት ፡
ትችላለህ ፤ ከመቀበል ፡ ሸሽተህ ፡ ወንድምህን ፡
ወደህ ፡ ብትከብር ፡ ይሻልሃል ።

የሰው ፡ ገንዘብ ፡ መብላት ፡ ባሪያ ፡ ያደርግሃል ።

አምላክን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ማመን ፡ ኗሪውን ።

እንዴት ፡ ታምነዋለህ ፡ ተለዋጭ፡ ባሕሪውን፡ የሚ
ፈርሰውን ።

ራሱ ፡ ካምላኩ ፡ ይለምን ፡ የለምን ።

ወዴት ፡ አለውና ፡ ሰጠህ ፡ ገንዘቡን ።

ባምላክህ ፡ ማመን ፡ ከሁሉ ፡ ይበልጣል ።

በሰውስ ፡ መታመን ፡ እጥብቆ ፡ ያቀላል ።

መታመንን ፡ ላምላክህ ፡ ለኗሪው ፡ ስጠው ።

ፍቅር ፡ መቼ ፡ አነሰው ፡ ለሚሞተውስ ፡ ሰው ።

ምዕራፍ ፡ ፺ ።

## የዳኛን ፡ ኀጢአትና ፡ ጽድቅ ፡ ማወቂያ ።

፪፻፸፬ ፡ የተሾመም ፡ ዳኛ ፡ በግድ ፡ ግፍ ፡ ይሠራል ።
በግድ ፡ ሁነኜ ፡ ይፈልጋልና ፡ ስለዚህ ፡ መጽደቅ ፡
ያቅተዋል ፤ ላስቸጋሪዎቹ ፡ ሕግ ፡ ሲሠራላቸው ፡



በግድ ፡ ፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሲያመጣበት ፡
ግን ፡ የዳኛ ፡ አኗኗር ፡ በበጎ ፡ ጎሊና ፡ ከተሠራ ፡
የሐዋርያነት ፡ የረድነት ፡ ሥራ፡ አለበትና ፤ ዕጥፍ ፡
ዋጋ ፡ የሚያገኝ ፡ ጻድቅ ፡ ይሆናል ።

ጥያቄ ።

፪፻፸፭ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ያቅተዋል ፡ ሰው ፡ ለሰው ፡ ዳኛ ፡ እን
ዲሆን ፡ እግዚአብሔር ፡ ያዘዘው ፡ ነገር ፡ አይደለምን ።

ምላሽ ።

፪፻፸፮ ፡ የሚቀጣና ፡ የማይቀጣውን ፡ ለይቶ ፡ ለማወ
ቅ ፡ ስላለመቻሉ ፡ ነው ፤ ዐይኑቱና ፡ ምሳሌውም ፡
አፈርሳታና ፡ ምስክር ፡ ፍርድ ፡ ነው ፤ ባያስወጣ ፡
ባያስመሰክር ፡ በሌባና ፡ በወንበዴ ፡ ይካማው ፡
ድኻ ፡ ይጐዳና ፡ ባለመጠበቁ ፡ ይፈረድበታል ፤
ቢያሶጣ ፡ የቀማው ፡ ቀርቶ ፡ ያልቀማውን ፡ የገደ
ለው ፡ ቀርቶ ፡ ያልገደለውን ፡ ጠላትነቱ ፡ ባልተ
ገለጠ ፡ አባይነቱ ፡ ባልታወቀ ፡ ምስክር ፡ በሚባል ፡
ቃል ፡ ብቻ ፡ ሰውን ፡ ያጠፋልና ፡ ግፍን ፡ በግድ ፡
ይሠራል ።

ጥያቄ ።

፪፻፸፯ ፡ አስመስክሮ ፡ ምስክሩንም ፡ አስወድዶ ፡
ነው ፡ የሚያወጣው ፡ ምስክሩ ፡ በዋሸ ፡ ዳኛውን ፡
እንዴት ፡ ግፈኛ ፡ ያሰኘዋል ።

ምላሽ ።

፪፻፸፫ ፡ የሰከረ ፡ ያበደ ፡ ሕፃን ፡ የሆነ ፡ እንኳን ፡ በተናገረው ፡ በገደለውም ፡ ቢሆን ፡ ዳኛ ፡ አይፍረ ድበት ፡ መባሉ ፡ የሚሠራውን ፡ ጥፋት ፡ ባለማ ወቁ ፡ ስለ ፡ ሠራው ፡ ነው ። እንደዚህም ፡ ሁሉ ፡ ባለመማር ፡ ዕውቀት ፡ አጥቶ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፈራጅነት ፡ የሐሰትን ፡ ኀጢአትነት ፡ የመሐላን ፡ ጕጅነት ፡ ልኩን ፡ ያላወቁትን ፡ ያልሠለጠኑትን ፡ ባላገሮቹን ፡ ሰብስቦ ፡ ስታወጡ ፡ አውጡ ፡ ብሎ ፡ በገንዘብ ፡ ቀጥቶ ፡ በረኀብ ፡ ጕድቶ ፡ ሲያስጨን ቃቸው ፡ ባለማወቅ ፡ ከነሱ ፡ የሚያንሱት ፡ ሕፃ ንና ፡ እረኛ ፡ ልጆች ፡ ሳይቀሩ ፡ እየጠየቁ ፡ ቢያገኙ፡ የነሱን ፡ ቃል ፡ ይዘው ፡ ያወጣሉ ፡ ቢያወጡ ፡ እንኳን ፡ መስክሮ ፡ ወጣቶ ፡ ሊያጠፋው ፡ የሚፈል ገው ፡ ጠላቱ ፡ የሚልከውን ፡ የሐሰት ፡ ምስክር ፡ ሰምተው ፡ በዚያ ፡ ቃል ፡ ኀጢአተኛ ፡ ይሆናል ። ያንን ፡ ተቀብሎ ፡ ዳኛው ፡ ሲቀጣው ፡ ምስክሩንም ፡ አ ስወድዶ ፡ አስመርጦ ፡ በማስረታቱ ፡ እንዳይድን ፡ የም ስክሩ ፡ መምረጫ ፡ ደንብ ፡ ሥጋዊ ፡ ባለመሆን ፡ መንፈ ሳዊ ፡ በመሆን ፡ ወይም ፡ ባለመማሩና ፡ ባለማወቁ ፡ አይ ደለምና ፡ ከቈጠረው ፡ ዝምድና ፡ ከተቀባዩ ፡ ጠብ ፡ ከ ሌለው ፡ ከቶውንም ፡ ሥጋዊነቱ ፡ በዝቶ ፡ ለፍትወቱ ፡ የሚያሻውን ፡ የሰበሰበ ፡ ብልጥ ፡ ባለገንዘብ ፡ ቢቈ ጥር ፡ ከገሌ ፡ የበለጠ ፡ ባለአዳር ፡ ማን ፡ ይቈጠርልኝ ፡ ብለህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ዳኛው ፡ በግድ ፡ ያስቀብለዋል ።



በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ፍትሐ ፡ እግዚአብሔር ፡ በምስክሮች ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ እንዳይፈርድ ፡ ዕውቀታቸው ፡ አለመ ሠልጠኑን ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ ከወዲያኛው ፡ ዓለም ፡ ጋራ ፡ አመዛዝነው ፡ ለማበላለጥ ፡ አለመቻላቸውን ፡ ማወቁ ፡ ይከለክለዋል ፤ ስለዚህ ፡ የሚበልጠውን ፡ ዓለም ፡ ባለማስተማሩ ፡ አላዋቂ ፡ አስመስክሮ ፡ በመቅጣቱ ፡ የጽድቅ ፡ መንገድ ፡ አጥቶ ፡ በግድ ፡ ዳኛው ፡ ግፈኛ ፡ ይሆናል ። ዳግመኛም ፡ አንዱ ፡ ጌታና ፡ አንዱ ፡ ጌታ ፡ ወይ ፡ በለጥከኝ ፡ በመባባል ፡ ተቃንተው ፡ ወይም ፡ እኔ ፡ ልግዛ ፡ እኔ ፡ ልግዛ ፡ በመባባል ፡ ተሻምተው ፡ ወይ ፡ በመናናቅ ፡ ተሳ ድበው ፡ ጦርነት ፡ በፈለጋቸው ፡ ጊዜ ፡ ለነሱ ፡ ጕዳይ ፡ ሲሉ ፡ ግማሹን ፡ ሥራ ፡ ጠልቶ ፡ የሚመ ጣላቸውን ፡ ሕዝብ ፡ ወታደር ፡ ብለው ፡ ይሰይሙ ና ፡ በወርቅ ፡ በጨርቅ ፡ አባብለው ፡ በእኽል ፡ በው ሃ ፡ አታለው ፡ አለጕዳዩ ፡ አዝምተው ፡ አለ ፡ ኀጢ አቱ ፡ ያስገድሉታል ።

ጥያቄ ።

፪፻፸፬ ፡ ምነው ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ጠብ ፡ ታግሠው ፡ ቢተዉት ፡ ይቻል ፡ የለምን ፡ ምን ፡ አለባቸው ።

ምላሽ ።

፪፻፸፭ ፡ ዳኛ ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ ተዋርጀና ፡ ተንቄ ፡ ሰው ፡ ሳላስገድል ፡ መክበርንም ፡ ሳልሻ ፡ ልኑር ፡ ቢል ፡ እንኳን ፡ ሰራዊቱ ፡ ሚስቱ ፡ አልታዘዘው ፡

ትልና ፡ ዳኛነቱን ፡ ጭምር ፡ ያስንቅበታል ፡ ስሙ
ንም ፡ አሚተኛና ፡ ዘፋኝ ፡ ይሜወቁበታልና ፤
ስለዚህ ፡ ሊታገሠው ፡ አይችልምና ፡ ሰው ፡ እ
ያስገደለ ፡ በግድ ፡ ኀጢአት ፡ ይሠራል ፤ ለወ
ታደሩ ፡ ማባበያ ፡ ገንዘብ ፡ ለመፈለግ ፡ የባላገ
ሩን ፡ ገንዘብ ፡ አታሎ ፡ ለመውሰድ ፡ ጥበብ ፡ እ
የፈለገ ፡ የድኻውን ፡ ገንዘብ ፡ ወስዶ ፡ ለድኻ ፡
ለመስጠት ፡ እየተራቀቀ ፡ ኵነኔ ፡ ይፈልጋል ፤
ለዚያም ፡ ለወታደሩ ፡ እንዲህ ፡ እያደረገ ፡ ሰብስቦ ፡
ገንዘቡን ፡ ከሰጠው ፡ በኋላ ፡ ከደመወዙ ፡ ወዙ ፡
ክፍትፍቱ ፡ ፊቱ ፡ የሚባለውን ፡ እባዜ ፡ መፈጸም ፡
በግድ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የማይሰጠውን ፡
የሚሰጥ ፡ እያስመሰለ ፡ እየማቀ ፡ እያታለለ ፡ እያበላ ፡
በግድ ፡ ይሜርዎን ፡ እግዚአብሔር ፡ ለከናፍረ ፡ ጕሕ
ሉት ፡ የተባለውን ፡ ኵነኔ ፡ ይፈልገዋልና ፡ ይህን ፡
ደንብ ፡ ሳይለውጥ ፡ ጌታ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ለመጽ
ደቅ ፡ ያቅተዋል ።

ዳግመኛም ፡ ጌቶች ፡ ሁሉ ፡ የበላያቸውን ፡ የንጉሡ
ን ፡ ጠባይ ፡ ካልመሰሉ ፡ ይሻራሉና ፡ እንደ ፡ ንጉ
ሡ ፡ ጠባይ ፡ በግድ ፡ ጽድቅና ፡ ኀጢአት ፡ ይሠራሉ ።

ጥያቄ ።

፪፻፷፩ ፤ ንጉሦቹ ፡ ገብሩን ፡ ተገዙን ፡ ይላሉ ፡ እንጂ ፡
ኀጢአት ፡ ሥሩልን ፡ አይሉ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ኀጢአት ፡
በግድ ፡ ይሠራሉ ።



ምላሽ ።

፪፻፷፪ ፤ ተገዙን ፡ ሲሉ ፡ ባሕርያቸውን ፡ መስለው ፡ እን
1 ዲገዟቸው ፡ ብለው ፡ ነውና ፡ የሚሾሟቸው ፡ ሰዎ
ች ፡ ሁሉ ፡ በግድ ፡ የንጉሡን ፡ ጠባይ ፡ ይከተላሉ ፤
2 መምህራኑም ፡ ንጉሥ ፡ የወደደውን ፡ ዘመን ፡ የወለደ
ውን ፡ ቢሠሩ ፡ አለመጕዳቱ ፡ የልማዱን ፡ ቃል ፡ ከገለባ
3 ው ፡ ሳይለዩ ፡ ይሰብኩላቸዋል ፤ ሽማግሌውም ፡ እንደ ፡
ንጉሡ ፡ አጕንብሱ ፡ እያለ ፡ ይተርትላቸዋልና ፡ በግድ ፡
እንደ ፡ ንጉሡ ፡ ጠባይ ፡ ይሠራሉ ። ይህንም ፡ ለመረዳ
ት ፡ ብትሻ ፡ እኛው ፡ በዘመናችን ፡ ያየነው ፡ ባገራችን ፡
4 አንድ ፡ ጊዜ ፡ በነገሠው ፡ ንጉሥ ፡ ዘመን ፡ የንጉሡ ፡
ጠባይ ፡ እብደት ፡ ሆኖ ፡ ሰው ፡ መግደል ፡ ቤት ፡ ማ
ቃጠል ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ግፍ ፡ እየተወደደ ፡ ከቶው
ንም ፡ ባላገሮችን ፡ መዝረፍ ፡ ጀግንነት ፡ ነው ፡
እየተባለ ፡ ኀጢአት ፡ ሳይመስል ፡ በመኳንንቱ ፡
5 እጅ ፡ ሁሉ ፡ ተሠራ ። ባንዱ ፡ ዘመን ፡ ማድላት ፡
ባሕርዩ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ዘመድን ፡ ብቻ ፡ መውደድ ፡
ኀጢአት ፡ ሳይመስል ፡ በሱም ፡ በሾማቸው ፡ ዘንድ ፡
6 አድልዎ ፡ ተሠራ ። ባንዱ ፡ ዘመን ፡ የንጉሡ ፡ ጠባ
ይ ፡ ኵራትና ፡ ሰው ፡ ማጥቃት ፡ ገንዘብ ፡ መዝረፍ ፡
ሰው ፡ መናቅ ፡ ባሕርዩ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ዘራፊው ፡ ተሠረ ፡
ትዕቢቱ ፡ ኵራት ፡ እየተባለ ፡ ኀጢአት ፡ ሳይመስ
ል ፡ በሱም ፡ በሰዎቹም ፡ እጅ ፡ ትዕቢት ፡ ተሠራ ።
7 በዚቱ ፡ ንጉሥ ፡ ዘመን ፡ የንጉሦች ፡ ጠባይ ፡ ንግድና ፡
ብልጠት ፡ ቅናትና ፡ ሰው ፡ ማታለል ፡ ባሕርያቸው ፡

ስለ ፡ ሆነ ፡ ተንኰሉ ፡ ብልኀት ፡ እየተባለ ፡ ኀጢአት ፡ ሳይመስል ፡ ተንኰል ፡ ተሠራ ። ባንዱ ፡ ዘመን ፡ የንጉሡ ፡ ጠባይ ፡ እብደት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እብደትና ፡ ጊልት ፡ ኀጢአት ፡ ሳይመስሉ ፡ እብደቱ ፡ ንቃት ፡ ጊልቱ ፡ ትሕትና ፡ እየተባለ ፡ ተሠሩ ፡ ስለዚህ ፡ የጕሮ ፡ የዐይን ፡ ምስክር ፡ ነኝ ። ስለዚህ ፡ ያገራች ን ፡ መኳንንት ፡ የሚያሳድረቻቸውን ፡ የንጉሡን ፡ ባሕርይ ፡ ይከተላሉ ፡ እንጂ ፡ ሌላውን ፡ ጽድቅ ፡ ለመሥራት ፡ ያቅታቸዋል ።

ዳግመኛም ፡ ዳኝነትና ፡ ጌትነት ፡ ይባልቁ ፡ ሲይዝ ፡ ለመጽደቅ ፡ ያቅተዋል ፡ በዳኝነትም ፡ በውነት ፡ ፈርጂ ፡ ልጽደቅ ፡ ብሎ ፡ ሲዠምር ፡ ፍርድ ፡ ማለት ፡ ብቻ ፡ ሰውና ፡ ሰው ፡ በሚጣላበት ፡ ነገር ፡ አይደለምና ፡ የሥስቱን ፡ ዐይነት ፡ ፍርድ ፡ ለማስተካከል ፡ ያቅተዋል ፡ በስጦታ ፡ እንደ ፡ አገልግሎቱ ፡ ሳይሆን ፡ እንደ ፡ መውደዱ ፡ ቢሰጥ ፡ ይልቁንም ፡ እንዲህ ፡ አድርጌ ፡ ብሰጠው ፡ በእንዲህ ፡ ያለ ፡ ጕዳይ ፡ ይረዳኛል ፡ ብሎ ፡ የልቡን ፡ እምነት ፡ ቢጥልበት ፡ ከሃይማኖቱም ፡ ይጐድላል ።

እፈኛና ፡ ዝምተኛ ፡ ማዕርጋቸው ፡ እኩል ፡ ሆኖ ፡ ስለ ፡ እፈኛው ፡ ፈርቶ ፡ ያመሰግነኛል ፡ ብሎ ፡ ቢያከብረውና ፡ ቢያስብለት ፡ ዝምተኛውን ፡ ከዚያ ፡ ባያስተካክለው ፡ በመፍራቱና ፡ በማድላቱ ፡ ኀጢአት ፡ ይሠራል ፡ ይልቁንም ፡ እፈኛው ፡ አመስግኖ ፡ ያስከብረኛል ፡ ባለሟሉ ፡ ከበላዩ ፡ ጌታ ፡ አስታውሶ ፡



ያስጠቅመኛል ፡ ብሎ ፡ ቢያምነው ፡ እንደ ፡ ዮሴፍ ፡ ሃይማኖቱ ፡ ይጐድላል ፤ እሊህ ፡ ሁለቱ ፡ ፍርዶች ፡ ለሰው ፡ ከባሕርዩ ፡ ጋራ ፡ የሚዋጉ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ትልቁ ፡ ፍርድ ፡ ከዚህ ፡ ከሁለቱ ፡ ውስጥ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ያለው ፡ ከሦስተኛው ፡ ውስጥ ፡ ሰውና ፡ ሰው ፡ በሚጣላበት ፡ ነገርስ ፡ ከሰው ፡ ለሰው ፡ ብሎ ፡ ማድላት ፡ የተበደሮ ፡ ኀጢአት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የባሕርዩ ፡ ጾር ፡ አይደለምና ፡ ሁለቱን ፡ ጨምሮ ፡ በሦስቱ ፡ ሁሉ ፡ የማያዳላ ፡ ለመሆን ፡ ይቸግረዋልና ፡ ስለዚህ ፡ ዳኛ ፡ ከፍዳ ፡ ለመዳን ፡ ያቅተዋል ።

ይህንንም ፡ ሁሉ ፡ ኀጢአት ፡ በግድ ፡ የቀረውን ፡ በውድ ፡ ይሠሩታል ።

ጥያቄ ።

፩፻፹፫ ፡ ጌቶች ፡ የንጉሡን ፡ ሎሌ ፡ የጌታውን ፡ ጠባይ ፡ በመከተል ፡ እንዳይጐዱ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ሆነው ፡ ቢገዙ ፡ ይድናሉ ።

ምላሽ ።

፩፻፹፬ ፡ ተገዥዎች ፡ ሁሉ ፡ የገዥዎቻቸውን ፡ ክፉ ፡ ጠባይ ፡ መከተላቸው ፡ ስለ ፡ ፍርሀትና ፡ ስለ ፡ መለማመጥ ፡ ሲሉ ፡ ነውና ፡ ስለዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ያዘዘን ፡ ለእግዚአብሔርኒ ፡ ፍርሀዎ ፡ ወለንጉሥኒ ፡ አክብርዎ ፡ ነውና ፡ የበላይ ፡ ገዥዎች ፡ የምንላቸው ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ጭቃ ፡ ሹም ፡ በየተራቸው ፡

አዘው ፡ የሚያልፉ ፡ ሁላችን ፡ ለመስማት ፡ የማይ
ቻለን ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ኢይትናገረን ፡ እግዚአብሔር ፡
አላ ፡ ይትናገረን ፡ ሙሴ ፡ ብለው ፡ እስራኤል ፡
በለመኑበት ፡ ምክንያት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡
በነሱ ፡ አፍ ፡ የምንሰማው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ብለን ፡ ልንታዘዛቸውና ፡ ልናከብራቸው ፡
ይገባናል ፡ እንጂ ፡ ልንፈራቸውና ፡ ልንለማመጣ
ቸው ፡ የማይገባን ፡ መሆኑን ፡ ስናስተውል ፡ በነሱ ፡
ጠባይ ፡ ከመጐዳት ፡ እንድናለን ።

ጥያቄ ።

፻፶፰ ፤ ላስቸጋሪው ፡ ደንብ ፡ ሕግ ፡ ከተሠራለት ፡
ያገራችን ፡ ዳኛ ፡ ባናዖር ፡ ዕጥፍ ፡ ጽድቅ ፡ ያገኛ
ል ፡ ያልከኝ ፡ ምን ፡ ዐይነት ፡ እርድናና ፡ ሐዋርያን
ት ፡ ስላለበት ፡ ነው ።

ምላሽ ።

፻፶፱ ፤ እስቦ ፡ ጥሮ ፡ ለሰው ፡ ማሳደሪያ ፡ የሚሆን
ውን ፡ ሁሉ ፡ በድካሙ ፡ ያመጣውን ፡ በሀብትህ ፡
ርዳን ፡ በውቀትህ ፡ ምራን ፡ ሲሉ ፡ አምነው ፡ ወደ
ሱ ፡ መጥተው ፡ የወደቁበት ፡ ቤት ፡ ሰቦች ፡ በአእ
ምሯቸው ፡ ሠልጥነው ፡ ለኔ ፡ ይጠቅሙኛል ፡ ብሎ ፡
ተስፋ ፡ ሳያደርግ ፡ ለነሱ ፡ ማሠልጠን ፡ ሲል ፡ ምክ
ሩን ፡ ትእዛዙን ፡ ሲነግራቸው ፡ በጎ ፡ ግብርንም ፡
እየሠራ ፡ ሲያሳያቸው ፡ እንደ ፡ እስጢፋኖስ ፡ ያለ ፡
ሐዋርያነት ፡ ይሆንለታል ።



ያገኘውንም ፡ ገንዘብ ፡ ለዝና ፡ ለምስጋና ፡ ለማታ
ለያ ፡ ወይ ፡ ለመለማመጫ ፡ ይሁነኝ ፡ ብሎ ፡ የመስ
ጠቱን ፡ ተስፋ ፡ ከነሱ ፡ ይመለስልኛል ፡ ብሎ ፡ ከሰ
ጣቸው ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ተስፋውን ፡ ሳይጥል ፡ ገንዘ
ቡን ፡ ለቤተ ፡ ሰቤ ፡ ዋጋዬ ፡ ከፈጣሪዬ ፡ ይሁንልኝ ፡
ብሎ ፡ ቤተ ፡ ሰቡን ፡ በገንዘቡ ፡ ከረዳ ፡ በሥጋ ፡
ይጠቀሙናል ፡ ሳይሉ ፡ አበውን ፡ እንደሚረዱት ፡
ከመናንያን ፡ እርድኣት ፡ ጋራ ፡ የተካከለ ፡ ይሆናል ፡
እየተጣሉ ፡ መጥተው ፡ ዳኝነቱን ፡ ዕውቀቱን ፡ ለሚ
ፈልጉት ፡ የበየንኩበት ፡ ጠልቶ ፡ ይጐዳኛል ፡ የበ
የንኩለት ፡ ወዶ ፡ ይጠቅመኛል ፡ ሳይል ፡ የእውነት ፡
ቃሉን ፡ ለተበደለው ፡ ሰጥቼ ፡ ዋጋዬን ፡ ከፈጣሪዬ ፡
አግኝቼ ፡ እጠቀማለሁ ፡ ሲል ፡ የልቡናውን ፡ ተስፋ ፡
ከዚህ ፡ ላይ ፡ አቁሞ ፡ በውነተኛ ፡ ዳኝነት ፡ የተቀማ
ውን ፡ እያስመለሰ ፡ የተጠቃውን ፡ እያስካሰ ፡ ተቸግሮ ፡
ለሚፈልገው ፡ ዘወትር ፡ እየተገኘ ፡ ለሱ ፡ ጥቅም ፡
ሳይሆን ፡ ለነሱ ፡ ሲል ፡ ባለው ፡ ዕውቀትና ፡ ጕል
በት ፡ ጥቁዎቹን ፡ በጕልበቱ ፡ አላዋቂዎችን ፡ በዕው
ቀቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሲል ፡ የሚረዳቸው ፡ በም
ስክርም ፡ የሚያልቀውን ፡ ነገር ፡ እውነት ፡ እንዲ
ሆን ፡ ምስክሮቹንም ፡ ሲቻለው ፡ አስቀድሞ ፡ ለሁ
ሉም ፡ መንፈሳዊ ፡ ዕውቀት ፡ እንዲደርሳቸው ፡ ወንጌ
ል ፡ እንዲሰበክላቸው ፡ መምህራኑን ፡ እያተጋ ፡ እንዲያስ
ተምሩ ፡ ቢያደርግ ፡ የቃላቸውንም ፡ እውነት ፡ ተጨንቆ ፡
ለመመርመር ፡ የሐሰትንም ፡ ጕድነት ፡ የሚያስረዳ ፡
እጭር ፡ ስብከት ፡ ከመጽሐፍ ፡ አስወጥቶ ፡ ተጽፎ ፡

ለእግዚአብሔር ፡ ፍርድ ፡ ፍርሀት ፡ ለወንድሙ ፡ ኀዳት ፡ ሲል ፡ እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ ለውኅት ፡ ቢደ ክም ፡ እንደ ፡ እኍ ፡ ቅዱስ ፡ ለወንድሞቹ ፡ ፍቅር ፡ የተለወጠ ፡ ጻድቅ ፡ ረድ ፡ ይሆናል ። በሚበደንበ ትም ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሀገሩ ፡ ልማድና ፡ ሕግ ፡ እን ማር ፡ ብለው ፡ ባደባባይ ፡ ለተሰበሰቡትም ፡ ሰዎ ች ፡ ለሚበየንባቸውም ፡ ተረቺዎች ፡ ይህ ፡ ክፉ ፡ ነው ፡ ያስቀጣል ፡ ይህ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ይገባል ፡ እያለ ፡ ለሰሚዎችም ፡ እንደሚገባቸው ፡ አድርጎ ፡ ካስረዳቸው ፡ ያንጋገሬ ፡ መሸብረቅ ፡ ያመራመሬ ፡ መደነቅ ፡ በሰው ፡ ዘንድ ፡ ጥቅም ፡ ይሁነኝ ፡ ብሎ ፡ ተሰፋውን ፡ ከፍጡር ፡ ላይ ፡ ልጣል ፡ ሳይል ፡ ለፈ ጣሪው ፡ ሲል ፡ ከሠራው ፡ ኀባኤ ፡ ሠርተው ፡ ካስ ተማሩት ፡ ከሐዋርያት ፡ ጋራ ፡ የተመሳሰለ ፡ ጻድቅ ፡ ሐዋርያ ፡ ይሆናል ።

ስለዚህ ፡ በጎ ፡ ኅሊና ፡ ያለው ፡ ዳኛ ፡ የሐዋርያት ንና ፡ የአርድእትን ፡ ዋጋ ፡ ያገኛል ። ይህንም ፡ ልትረዳ ፡ ብትሻ ፡ ስለ ፡ ውሉደ ፡ ንጋዴ ፡ በፊልክ ስዩስ ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ አንዱ ፡ በዓለም ፡ የሚሠ ራውን ፡ አንዱ ፡ በምናኔ ፡ የሚሠራውን ፡ ሠርተ ው ፡ ስለ ፡ ኅሊናቸው ፡ መተካከል ፡ ሥራቸው ፡ ሳይመሳሰል ፡ በኅሊናስ ፡ ኩኑ ፡ መዐርያነ ፡ ተብሎ ፡ ዋጋቸው ፡ መተካከሉን ፡ ከፊልክስዩስ ፡ መጽሐ ፈ ፡ ክፍል ፡ አስተውል ፡ (ጣዕመ ፡ ጸሎት ፡ ም ፡ ፳፱ ። ስለ ፡ አባት ፡ እናት ፡ ም ፡ ፱) ።



ምዕራፍ ፡ ፳፩ ።

## ስለ ፡ ምግብ ።

፪፻፹፯ ፡ ለንፍስ ፡ አለመጥፋት ፡ ለፈጣሪ ፡ ለመገዛት ፡ ስትወድ ፡ ከምግብህ ፡ በፊት ፡ ለምላስህ ፡ ዳኛ ፡ ሁነህ ፡ ከጣዕም ፡ መፈለግ ፡ ከልክለው ፡ ምግቡን ፡ ፈጣሪው ፡ ሳይኑጣው ፡ ለጣዕም ፡ ብቻ ፡ ብሎ ፡ የሚ ደክም ፡ ሰው ፡ ባለማወቁ ፡ የምግቡ ፡ ጣዕም ፡ ይጠ ቅመኛ ፡ ይመስለዋል ፡ እንጂ ፡ የምግቡ ፡ ጣዕም ፡ ስን ኳን ፡ ለንፍስ ፡ ለሥጋም ፡ እንድም ፡ ጥቅም ፡ የለበት ።

ጥያቄ ።

፪፻፹፰ ፡ ምነው ፡ ለሥጋማ ፡ ጣፋጭ ፡ ምግብ ፡ የማ ይጠቅም ፡ መሆን ፡ ስለ ፡ ምንድነው ።

ምላሽ ።

፪፻፹፱ ፡ ለሥጋው ፡ ከቤቱ ፡ እኽል ፡ እያለው ፡ ጣዕመ ፡ መብልዕ ፡ በጕደለበት ፡ ጊዜ ፡ ጣዕምን ፡ ብቻ ፡ ለመፈለግ ፡ ሲል ፡ ከጌታ ፡ ቤት ፡ ያስገባዋል ፡ ከድ ማስ ፡ ቤት ፡ ያዞረዋል ፡ ስለ ፡ ሞያዋ ፡ ሲል ፡ ለክፉ ፡ ሴት ፡ ያስገዛዋል ፡ እንዲህ ፡ ተዋርዶ ፡ የሚያገኘው ፡ ትርፍ ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ የኀጢአት ፡ ሥራና ፡ ሥጋውን ፡ እንደሚታረድ ፡ ከብት ፡ አወፍሮ ፡ እንደ ፡ ጠፍር ፡ አ ልፍቶ ፡ ለመዝለፍለፍ ፡ እንደ ፡ ዕቃ ፡ አስቀምጦ ፡ ለማ ስንፍ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ ትርፍ ፡ የለውም ።

ጥያቄ ።

፪፻፺ ፤ ምነው ፡ የጣመ ፡ ምግብ ፡ ሲያዩትም ፡ እም
ሮ ፡ ሲመገቡት ፡ ጣፍጦ ፡ እየተበላ ፡ ደስ ፡ ሲያሰኝ ፡
ይኸው ፡ ትርፍ ፡ ይሆን ፡ የለምን ።

ምላሽ ።

፪፻፺፩ ፤ የማየቱም ፡ ደስታ ፡ በእጅ ፡ተነሥቶ ፡ ከከን
ፈር ፡ እስኪደርስ ፡ ነው ፤ የጣዕሙም ፡ ደስታ ፡ ከም
ላስ ፡ እስከ ፡ ጕረሮ ፡ ድረስ ፡ ነው ፡ ከጕረሮም ፡
ዝቅ ፡ ሲል ፡ ይጠፋል ፡ ከዚያም ፡ ዝቅ ፡ ሲል ፡ እን
ዲያውም ፡ ግግት ፡ ብስና ፡ እሥር ፡ እየሆነ ፡ ከነ
ሽታው ፡ ያስቀይማል ፤ የደስታውንም ፡ ማነስ ፡
የመንገዱንም ፡ ማጠር ፡ እስኪ ፡ ልብ ፡ አድርገህ ፡
አስተውለው ፤ ጣዕም ፡ ማሻሻልስ ፡ ምላስን ፡ አታሎ ፡
ብዙ ፡ ለመብላት ፡ ብዙ ፡ በልቶም ፡ ኀጢአት ፡ ለመሥ
ራት ፡ ከሰይጣን ፡ የተፈጠረ ፡ ተንኰል ፡ ነውና ፤ ሔኖክ ፡
ም ፡ ፳ ፡ ለሥጋስ ፡ ጥቅም ፡ ለባሕርይህ ፡ የሚያሻውን ፡
ያኽል ፡ አለጠ ፡ ሖረጠ ፡ ጣፈጠ ፡ አልጣፈጠ ፡ ሳት
ል ፡ ሲሳየን ፡ ኀበነ ፡ ብለህ ፡ በምትለምነው ፡ ጸሎ
ት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የሚሰጥህ ፡ ነውና ፤ የቀረበ
ልህን ፡ ማናቸውንም ፡ ቢሆን ፡ ባንደበትህ ፡ ሳት
ነቅፍ ፡ በምላስህ ፡ ለማጣጣም ፡ ሳትጥር ፡ ዝም ፡
ብለህ ፡ ብትመገበው ፡ ነው ፡ የሚሻልህ ።

መልካም ፡ ምግብስ ፡ አለመጥቀሙን ፡ የጌቶች ፡
ድካምና ፡ ጤና ፡ ማጣት ፡ ጣዕም ፡ የሌለው ፡ ምግ



ብ ፡ አለማጕደሉን ፡ የድኆች ፡ ሕይወትና ፡ ብርታት ፡
መምህር ፡ ይሁንህ ፡ እንጂ ፡ ጣዕም ፡ በመሻት ፡
አእምሮህን ፡ አታጥፋ ።

ጥያቄ ።

፪፻፺፪ ፤ ምነው ፡ ያንኑ ፡ የጣመውን ፡ ምግብ ፡ በልክ ፡
ቢመገቡት ፡ ምን ፡ ኀጢአት ፡ ይባላል ።

ምላሽ ።

፪፻፺፫ ፤ ሴት ፡ ማለዋወጥ ፡ ዘማዊ ፡ እንደሚያሰኝ ፡
ምግብ ፡ ማለዋወጥም ፡ ሥጋዊ ፡ ፍትወት ፡ ስለ ፡
ሆነ ፡ ይህም ፡ ዕዳና ፡ ዝሙት ፡ ነው ። ጥንቱን ፡ ለም
ግብ ፡ ጣዕም ፡ ሲባል ፡ ያን ፡ ያኽል ፡ ለጣዕም ፡
የሚደከምበት ፡ ከልክ ፡ አልፎ ፡ ለመብላት ፡ ሲባል ፡
ነው ፡ እንጂ ፡ እግዚአብሔር ፡ የፈጠረው ፡ ምግብ ፡
እግዚአብሔር ፡ ለፈጠረው ፡ አካል ፡ እንሶን ፡
እንደ ፡ ገና ፡ እንዱን ፡ ካንዱ ፡ ጋራ ፡ እየቀላቀልን ፡
እየፈጠርን ፡ መብላታችን ፡ ትርፍ ፡ ሥራ ፡ ነው ፡
እንጂ ፡ በግድ ፡ ለባሕርያችን ፡ የሚያሻን ፡ ነገር ፡
አለመሆኑን ፡ ጥንትም ፡ የአዳም ፡ ምግብ ፡ ፍሬ ፡
ብቻ ፡ መሆኑን ፡ አስተውል ። በገዳም ፡ የሚኖሩ ፡
መነኰሳት ፡ በባላገር ፡ የሚኖሩ ፡ ገበሬርት ፡
ጥሬ ፡ እየበሉ ፡ ሕይወታቸው ፡ ሁሉ ፡ የተካከለ ፡
መሆኑን ፡ ያስረዳናልና ፡ ሀብታም ፡ ብትሆን ፡
ሠራተኞችህ ፡ የሚያቀርቡልህን ፡ ጣፍጪልና ፡
ጨምር ፡ ከፍቷልና ፡ ለውጥ ፡ ሳትል ፡ ያቀረቡል

ህን ፡ ዝም ፡ ብለህ ፡ ተመገብ ፤ በዘመናችንም ፡ ሀብታም ፡ ሁነው ፡ በዚህ ፡ አኗኗር ፡ የኖሩ ፡ ለሥጋቸው ፡ ሲሉ ፡ ያለምርምር ፡ በልማድና ፡ ለጤና ፡ ሥጋና ፡ ጥርትም ፡ ወጥና ፡ መጠጥን ፡ መተውን ፡ ፈ ፡ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ሲሠሩት ፡ በምርምር ፡ ያቀረቡላቸውን ፡ አንዱን ፡ ዐይነት ፡ በልክ ፡ መብላትን ፡ መምህር ፡ አካለ ፡ ወልድ ፡ ፍሬና ፡ የቅጠል ፡ ምግብ ፡ ማብዛትን ፡ አውሮፖች ፡ ሲሠሩት ፡ አይተናልና ፡ ድኻም ፡ ብትሆን ፡ ጥሬም ፡ ብስልም፡ ብታገኝ ፡ ማደባለቅን ፡ ትተህ ፡ አንዱ ፡ ዐይነት ፡ ይብቃኝ ፡ ብለህ ፡ ስትመገብ ፡ አእምሮህ ፡ የዕውቀት ፡ ሕይወትህ ፡ የጤና ፡ ይሆንልሃል ።

የአበው ፡ ማስረጃ ፤ የበጎ ፡ ሰውስ ፡ ዐመል ፡ ያስረዳሃል ፡ በውል ። በልብሱ ፡ መኰስቈል ፤ ባነጋገሩ ፡ አጭር ፡ ቃል ፤ በማእዱ ፡ መቅለል ፤ የግብዝም ፡ ሰው ፡ ዐመል ፡ ይታያልና ፡ አስተውል ። በማእዱ፡ ጣዕም ፡ ማባበል ፤ ባለባበሱ ፡ መወልወል ፤ ባነጋገሩ ፡ መሰብቀል ፡ (ጣዕመ ፡ ጸሎት ፡ ም ፡ ፫፻፱) ።

### ምዕራፍ ፡ ፳፱ ።

## ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍቅር ።

፪፻፺፬ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፍቅር ፡ ላይ ፡ የሚጨመረውን ፡ የፍጥረትን ፡ ፍቅር ፡ ያላገባብ ፡ ካደረገው ፡



ወደድኩህ ፡ በሚለው ፡ በፈጣሪው ፡ መዘበት ፡ ይሆናል ።

### ጥያቄ ።

፪፻፺፭ ፡ ምንነው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ቢወድ ፡ ዘበተ ፡ እንዴት ፡ ይባላል ።

### ምላሽ ።

፪፻፺፮ ፡ ሰው ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚወድበት ፡ ምክንያት ፡ ንብረቱ ፡ ስለ ፡ ሞላለት ፡ ወይም ፡ እንዲሞላለት ፡ ወይም ፡ ዕድሜው ፡ እንዲረዝምለት ፡ ወይም ፡ ስላረዘመለት ፡ ወይም ፡ ጤና ፡ ስላገኘ ፡ ወይም ፡ ልጅ ፡ ስላገኘ ፡ የሚወደውን ፡ ተድላ ፡ ስላደረገለት ፡ ወይም ፡ እንዲያደርግለት፡እንደ፡ሆነ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋውን ፡ ወደደ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፤ እግዚአብሔርን ፡ ወደደ ፡ አያሰኘውም ። እንዲያውም ፡ ሥጋዊ ፡ ነገር ፡ ሲያደረግለት ፡ የሚወድ ፡ ሥጋዊ ፡ ነገር ፡ ሲቀርበት ፡ የሚጠላ ፡ ነውና ፤ ስለዚህ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የታመነ ፡ ወዳጅ ፡ አይባልም ።

### ጥያቄ ።

፪፻፺፯ ፡ እግዚአብሔር ፡ መፍቀደ ፡ ሥጋን ፡ ሲያደርግ ፡ ቢወዱት ፡ እንዲያደርግ ፡ ቢለምኑት ፡ ስለምን ፡ ዘበትና ፡ የማይገባ ፡ ይሆናል ።

## ምላሽ ።

፪፻፺፰ ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ጠባይ ፡ በፊት ፡ በእስራ ኤል ፡ ዘንድ ፡ ልማድ ፡ ሆኖ ፡ የሚኖር ፡ ነበር ፡ በየጊዜው ፡ ከክሕደት ፡ እደረሳቸው ፡ እንጂ ፡ አል ረባቸውም ፡ በተደረገላቸው ፡ ወራት ፡ እየወደዱ ፡ ባልተደረገላቸው ፡ ወራት ፡ እየጠሉ ፡ መጕዳታ ቸውን ፡ አሳዩ ። የዚህ ፡ ዓለም ፡ ገንዘብ ፡ እንደ ፡ ትርፍ ፡ እንደ ፡ ጕርሻ ፡ ለበጎዎችም ፡ ለክፉዎችም ፡ የሚደረግ ፡ ነውና ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ ለም ኑኝ ፡ እንጂ ፡ ይህን ፡ ዓለምስ ፡ እንዲያውም ፡ አት ለምኑኝ ፡ ማለቱ ፡ መወደጃውና ፡ መጠያው ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ እንዳይሆን ፡ ነውና ፡ ሰው ፡ የዕለት ፡ ምግቡን ፡ እንኳ ፡ ሲለምን ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ላዘዘው ፡ ሥራ ፡ ሰውነቱ ፡ እንዳይደክም ፡ ለሥራ ፡ ምክንያት ፡ እንዲሆነው ፡ ይሆን ፡ እስቦ ፡ የዕለት ፡ ምግቡን ፡ ይለምን ፡ እንጂ ፡ ሌላውን ፡ የተድላ ፡ ሥጋን ፡ ነገር ፡ እንዲያደርግለትም ፡ ከፈ ለገ ፡ ሲያደርግለትም ፡ ከወደደ ፡ ሥጋውን ፡ ይወ ዳል ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ እንዴት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ወደደ ፡ ይባላል ። ከንቱውን ፡ ገንዘብ ፡ ሲሰጥ ፡ መውደድ ፡ ሲነሣ ፡ መጥላትስ ፡ ከንቱ ፡ ሰውና ፡ ከንቱ ፡ ሰው ፡ እንደየልማዳቸው ፡ ለየጥቅማቸው ፡ የሚሠሩት ፡ የዋጋ ፡ ሥራ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ፍቅር ፡ በፈጣሪያችን ፡ ልንሠራበት ፡ አይገባንም ።



## ጥያቄ ።

፪፻፺፱ ፡ ይህ ፡ ከሆነ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ልንወድ በት ፡ የሚገባው ፡ ምክንያት ፡ በምን ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ።

## ምላሽ ።

፫፻ ፡ ፩ኛ ፡ ስለ ፡ ፈጠረን ።

፪ኛ ፡ ዕውቀት ፡ ስለ ፡ ሰጠን ።

፫ኛ ፡ በሥጋ ፡ ባሕርያችን ፡ ከእንስሳትና ፡ ከአራ ዊት ፡ የበለጥን ፡ ሳንሆን ፡ ከእንስሳት ፡ ከአራዊት ፡ ለይቶ ፡ ስላከበረን ።

፬ኛ ፡ በበደልነው ፡ ግብር ፡ መካስ ፡ ቢያቅተን ፡ የሚካስው ፡ ጌታ ፡ ካሳ ፡ ሆኖ ፡ ሙቶ ፡ ስለ ፡ ተሠዋ ልን ፡ በዚህ ፡ ባራቱ ፡ ምክንያት ፡ መውደድ ፡ በቀረው ፡ በየቀኑ ፡ በሚሠራው ፡ ነገር ፡ ሲሠራብን፡ መለመን ፡ ሲሠራልን ፡ ማመስገን ፡ ይገባናል ፡ እንጂ ፡ የምንወደው ፡ ቀድሞ ፡ በሠራልን ፡ ብቻ ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ። ይህንም ፡ ትረዳው ፡ ዘንድ ፡ ብትወድ ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ እንዲሰጣቸው ፡ ደጅ ፡ ጠንተው ፡ ያገኙ ፡ ከሰጣቸውም ፡ በኋላ ፡ እንዳይ ሄድባቸው ፡ በጾም ፡ በጸሎት ፡ በስጊድ ፡ በምጽ ዋት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በመሥራት ፡ በመሳም ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ሥራው ፡ የሚገባና ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ሲሆን ፡ የሚሠሩበት ፡ ምክንያት ፡ ሥጋዊ ፡

ፈቃድን ፡ ለመሻት ፡ እንጂ ፡ ፍቅረ ፡ እግዚአብ ሔርን ፡ ለመሻት ፡ ስላልሠሩት ፡ ሥራቸውን ፡ እንጂ ፡ ሐሳባቸውን ፡ በማናውቀው ፡ በኛ ፡ ዘንድ ፡ ጻድቅ ፡ በምንላቸው ፡ ጌቶች ፡ ሁሉ ፡ በሞታቸው ፡ ወይም ፡ በሕይወታቸው ፡ የሚፈርድባቸው ፡ ያስ ረዳናልና ፤ ለኛ ፡ ጻድቅ ፡ የሚመስሉን ፡ እንደ ፡ ኃጥእ ፡ የሚቀጡ ፡ አሉ ፤ ለኛ ፡ ኃጥእ ፡ የሚመስ ሉን ፡ እንደ ፡ ጻድቅ ፡ የሚጠቀሙ ፡ አሉና ፤ ስለ ዚህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፍርድ ፡ የውስጥን ፡ ቅን ነትና ፡ የሚሠራበትን ፡ ምክንያት ፡ ይከተላል ፡ እንጂ ፡ በውጭ ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የልብ ፡ ቅንነት ፡ ካልተጨመረለት ፡ ትሩፋት ፡ ሥጋም ፡ ቢበዛ ፡ አለመጥቀሙን ፡ ቀና ፡ ልብ ፡ ግን ፡ ትሩ ፋት ፡ ሥጋም ፡ ቢያንሰው ፡ አለመጉዳቱን ፡ ያለ ፉትን ፡ ነጋሢዎች ፡ ሁሉ ፡ በየታሪካቸው ፡ እኳ ኋን ፡ አስተውል ፤ የቀረውማ ፡ እንደዚሁ ፡ ዐይ ነት ፡ ያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ የማይደረገው ፡ ታሪክ ፡ የለውም ፡ እንጂ ፡ ብዙ ፡ ነው ። እኛም ፡ በዘመ ናችን ፡ የእፍኢ ፡ ጽድቅ ፡ እያሳዩ ፡ ጻድቅ ፡ የሚመ ስሉን ፡ ሀብታሞች ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውስ ጣቸውን ፡ እያየ ፡ ሲፈርድባቸው ፡ እይተናል ። እንዲያውም ፡ አንዳንዶቹ ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋን ፡ ከእግ ዚአብሔር ፡ እንደሚገዛ ፡ ነገር ፡ ያስቡና ፡ መንፈ ሳዊውን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ለሥጋዊ ፡ ፈቃድ ፡ መፈ ለጊያ ፡ አድርገው ፡ እያቀረቡ ፡ የፈለጉትንም ፡



ሲያገኙ ፡ እንደ ፡ ሐናንያና ፡ ሰጲራ ፡ በድንገት ፡ ይሞታሉ ። ትሩፋታቸውንም ፡ ገሃነም ፡ ያደርጋሉ።

ጥያቄ ።

፫፻፭ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ወደን ፡ ስለ ፡ መውደዳችን ፡ ልናደርግለት ፡ የሚገባን ፡ ምንድር ፡ ነው ።

ምላሽ ።

፫፻፮ ፡ መውደድ ፡ ማለት ፡ የሚወዱትን ፡ መስ ጠት ፡ ነውና ፤ ስለዚህ ፡ የምትወደውን ፡ ነገር ፡ ማናቸውንም ፡ ዐይነት ፡ ቢሆን ፡ ለኔ ፡ ይቅርብኝ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሥዋዕት ፡ ይሁንልኝ ፡ ብለህ ፡ ቢቻልህ ፡ ጨርሰህ ፡ ባይቻልህ ፡ ከፍለህ ፡ በባሕ ርይህ ፡ ከምትወደው ፡ መስጠት ፡ ነው ። ጥቅሉ ፡ ፍቅር ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ዝርዝሩ ፡ ግን ፡ መጀመሪያ ፡ ከሁሉ ፡ አብልጦ ፡ ባሕርየ ፡ ሥጋህ ፡ የሚወደው ፡ የላመ ፡ የጣመ ፡ የበዛን ፡ ምግብ ፡ ነውና ፡ በመጾም ፡ በመመጠን ፡ ፈቃደ ፡ መብልዕህን ፡ ስትሠዋለት ፡ ሁለተኛ ፡ የምትወደው ፡ ዕረፍትን ፡ ነውና ፡ በጸሎት ፡ በስግደት ፡ ተግተህ ፡ ፈቃደ ፡ ዕረፍትህ ን ፡ ስትሠዋለት ። ፫ኛ ፡ ቀጥለህ ፡ የምትወደውን ፡ ከለም ፡ የምታገኘውን ፡ ፍቅረ ፡ ንዋይህን ፡ በው ሂብ ፡ ምጽዋት ፡ ፍቅረ ፡ ተግባርህን ፡ በአክብሮ ፡ በዓላት ፡ ስትሠዋለት ። ፬ኛ ፡ የምትወደው ፡ ሴስን ፡ ሥጋ ፡ ነው ፤ ሲቻልህ ፡ በንጹሕ ፡ ቢያቅ ትህ ፡ በዐቂብ ፡ ሕግ ፡ ፍትወተ ፡ ሥጋህን ፡ ብት

ሠዋለት ፡ እሊህን ፡ አራቱን ፡ የምትወዳቸው ፡ ገንዘቦችህን ፡ ስላንተ ፡ ጥቅም ፡ መፈለጊያ ፡ ሳታደርግ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ከሰጠኸው ፡ በውነት ፡ ወዳጁ ፡ ትሆናለህ ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ በባሕርይህ ፡ የምትወደው ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ቢኖርህ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚሻብህ ፡ ፍቅር ፡ በምትወደው ፡ ለውጠህ ፡ ስትወደው ፡ ነውና ፡ የማትወደውን ፡ ትልቅ፡ ነገር ፡ ከምታደርግለት ፡ የምትወደውን ፡ ትንሽ ፡ ብትሰጠው ፡ የሚወድህ ፡ መሆኑን ፡ ዕወቅ ። ይህንም ፡ ልትረዳ ፡ ብትሻ ፡ በብሉይ ፡ የወደዱትን ፡ ባለመተው ፡ የአዳምና ፡ የሔዋንን ፡ መጐዳት ፡ በዳዊትና ፡ በዮፍታሔ ፡ የወደዱትን ፡ በመተው ፡ መጠቀማቸውን ፤ በሐዲስ ፡ ጌታችን ፡ በፈቃደ ፡ ሥጋው ፡ ሐዋርያት ፡ በፈቃዱ ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ የሠሩትን ፡ አስተውል ።

ጥያቄ ።

፫፻፫ ፤ በምትወደው ፡ ሁሉ ፡ ለውጠህ ፡ ውደደው ፡ ያልከው ፡ በምን ፡ በምን ፡ ነው ።

ምላሽ ።

፫፻፬ ፤ ሰው ፡ የሚወደው ፡ ዐይነቱ ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ በቍጥር ፡ አያልቅም ፤ ዐይነቱ ፡ ግን ፡ ፈጽሞ ፡ መስነፍን ፡ የሚወድ ፡ በልቶ ፡ እንዲሠራ ፡ በልቶ ፡ መሥራቱን ፡ የሚወድ ፡ ጾሞ ፡ እንዳይከም ፤ ሥራ ፡ ጠልቶ ፡ ብዙ ፡ መጸለይ ፡ ብቻ ፡ የሚወድ ፤ ጥቂት ፡



እንዲጸልይ ፡ ብዙ ፡ እንዲሠራ ፤ ጥቂት ፡ መጸለይ ፡ እሚወድ ፡ ብዙ ፡ እንዲጸልይ ፡ ጥቂት ፡ እንዲሠራ ፤ መመጽወት ፡ የሚወድ ፡ ጨርሶ ፡ ሰጥቶ ፡ ደኽይቶ፡ የወደደውን ፡ ተመጽዋች ፡ እንዲሆን ፤ ለምኖ ፡ ተመጽውቶ ፡ መኖር ፡ የሚወድ ፡ ወዶ ፡ የሚለምነውን ፡ ሠርቶ ፡ እሚያጠራቅመውን ፡ እንዲመጸውት ፡ ነውና ፤ ከግብረ ፡ ኀጢአት ፡ ያመለጠ ፡ ወደ ፡ ትሩፋት ፡ የሮጠ ፡ በበጎ ፡ ግብር ፡ የተቀመጠ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ባሕርዩ ፡ ሥጋውን ፡ ጭምር ፡ ደስ ፡ ከሚያሰኘው ፡ በጎ ፡ ግብር ፡ ባሕርዩ ፡ ነፍሱን ፡ ብቻ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘውን ፡ በጎ ፡ ግብር ፡ ለአምላኩ ፡ ብቻ ፡ ሲሠራለት ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ፍጹም ፡ የአምላኩ ፡ ወዳጅ ፡ ይሆናል ፤ ይህንም ፡ ልትረዳ ፡ ብትሻ ፡ እንደ ፡ አባ ፡ ሣሉሲ ፡ እንደነአባ ፡ ባውማ ፡ ነቢር ፡ በአሐቲ ፡ ጸሎት ፡ እንደነእኑ ፡ ቅዱስ ፡ ያሉት ፡ የትሩፋት ፡ አርበኞች ፡ ወዳጆቹ ፡ የሠሩለትን ፡ አስተውል ፡ (ጣዕመ ፡ ጸሎት ፡ ም ፡ ፯) ።

ምዕራፍ ፡ ፳፫ ።

## የስንፍናን ፡ የቍጣን ፡ የዝንጋታን ፡ መነሻ ፡ ማወቂያ ።

፫፻፭ ፤ ስንፍና ፡ የነፍስንም ፡ የሥጋንም ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ አስተርቶ ፡ ይጐዳል ፤ በመጨረሻው ፡ የነፍስና ፡ የሥጋን ፡ ድኽነት ፡ ያመጣል ። የሚያደክመውም ፡

ሥራ ፡ ስላጣ ፡ በቍጣ ፡ ኀጢአትን ፡ ሁሉ ፡ ያሠራል ፤ ከሰው ፡ ሁሉ ፡ ያጣላል ። ልቡናውንም ፡ ሥራ ፡ ስላ ስፈታው ፡ መጨረሻው ፡ ዝንጋታ ፡ የሰውንም ፡ ወ ረታ ፡ መመለስ ፡ ያስቀራል ። የያዘውን ፡ ትቶ ፡ የ ላከውን ፡ ረስቶ ፡ ከጌታም ፡ ይጣላል ፤ የሰጠውን ፡ አ ልሰጠሁም ፡ የተናገረውን ፡ አልተናገርሁም ፡ በማ ለት ፡ ስለ ፡ መርሳቱ ፡ አባይ ፡ ሳይሆን ፡ አባይ ፡ ያ ደርጋል ። በበታቹ ፡ ታዘው ፡ ለሚያድሩት ፡ ፊት ፡ ያዘዘውን ፡ በመዘንጋት ፡ በላይ ፡ በላዩ ፡ እያዘዘ ፡ ሁሉም ፡ ሳይሠራ ፡ ይቀራል ። ያስቀመጠውን ፡ ዕ ቃውን ፡ ያሰናዳውን ፡ ገንዘቡን ፡ ቦታውን ፡ ል ኩን ፡ ረስቶት ፡ በቤተ ፡ ሰቡ ፡ ይዘረፋል ፤ የተጐዳ ውን ፡ ዘመድ ፡ ወዳጅ ፡ ባለመጠየቁ ፡ ሳይኰራ ፡ ዂሩ ፡ ተብሎ ፡ ይጠላል ፤ መጨረሻው ፡ ጅልነት ፡ ይሆናል ።

ጥያቄ ።

፫፻፺፮ ፡ እንዚህ ፡ ሦስቱ ፡ ክፉ ፡ ጠባዮች ፡ የሚነሡ ብን ፡ ከማንኛው ፡ ሥራ ፡ ነው ።

ምላሽ ።

፫፻፺፯ ፤ እኒህ ፡ ክፉ ፡ ጠባዮች ፡ የምኞት ፡ ድንበርን ፡ የአ ሳብ ፡ ልክን ፡ የሥራ ፡ ሚዛንን ፡ ካለማወቃችን ፡ ይነሡብናል ።

ጥያቄ ።

፫፻፺፰ ፡ ስንፍና ፡ ሲጀመር ፡ ምን ፡ ምልክት ፡ ያሳየናል ።



ምላሽ ።

፫፻፺፱ ፡ ስትተኛ ፡ እጅህን ፡ እግርህን ፡ ያዘረጋሃል ፤ ስትነሣ ፡ ያንጠራራሃል ፤ ስትሜወት ፡ ያስፋሽግሃ ል ፤ ስትቀመጥ ፡ ያንቀላፋሃል ። ለልብህ ፡ ተቀ ምጦ ፡ መሜወት ፡ እንደ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ሥራ ፡ ተ ራውጦ ፡ መሥራት ፡ እንደ ፡ እብደት ፡ ይመስል ሃል ። ለትጉ ፡ ሞት ፡ መስሎ ፡ የሚታየው ፡ የቀ ን ፡ እንቅልፍ ፡ ላንተ ፡ ባይንህ ፡ ዕረፍት ፡ መ ስሎ ፡ ይታይሃል ። ለጥርስህ ፡ ብዙ ፡ ማላመጥ ፡ ሥራ ፡ ይመስልሃል ፤ ተቀምጠህ ፡ ወግ ፡ አስረ ዛሚ ፡ ቃል ፡ አጋጣሚ ፡ ያደርግሃል ። እንደ ፡ ሽባ ፡ ተጣጥፈህ ፡ ተቀምጠህ ፡ እንድትውል ፡ አድርጎ ፡ ኑሮህንም ፡ እየተመጸወትክ ፡ ለትጉሁ ፡ ሰው ፡ መ ጸደቂያ ፡ ለሰይጣን ፡ መጫለቂያ ፡ ያደርግሃል ። ሰው ፡ ከሥራው ፡ ልክ ፡ ማጣት ፡ ከምኞቱ ፡ አለመርጋት ፡ ከአሳብ ፡ ማብዛት ፡ ሁሉን ፡ በመሻት ፡ የተነሣ ፡ አንዱ ፡ አልቆ ፡ የማያምር ፡ ሁሉም ፡ ኽምር ፡ ይሆ ንበትና ፡ የሚሠራውን ፡ አጥቶ ፡ ስንፍናን ፡ ፈጥሮ ፡ የባሕርይ ፡ ልጅ ፡ አድርጎ ፡ ሁሉንም ፡ አላሠራ ፡ ይለዋል ፤ ሰውነቱን ፡ ያዝለዋል ፤ ከሰው ፡ ፊት ፡ በቀን ፡ እስከ ፡ ማንቀላፋት ፡ ያደርሰዋል ። ላሳ ቡም ፡ ሳኒጋገሩም ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ ስለሌለበት ፡ የ ቃሉን ፡ ፈሳሽ ፡ ብቻ ፡ እያበዛ ፡ በተናገረው ፡ ጊዜ ፡ ነገሩ ፡ የሚሰለች ፡ ረኽም ፡ ይሆንበታል ። ስለ ዚህ ፡ ስለ ፡ ሥራ ፡ ፈትነቱ ፡ በግድ ፡ ተሻጋች ፡

ተራች ፡ ዘባች ፡ አቧላች ፡ ዘፋኝ ፡ ተጫዋች ፡ እስ ከመሆን ፡ ይደርሳል ። ትጋቱም ፡ ሁሉ ፡ ከምላሱ ፡ ላይ ፡ ይሆንና ፡ የቀረው ፡ አካሉ ፡ ሁሉ ፡ ይሰንፋል ፡ እንዲህ ፡ ያለውም ፡ ባሳብ ፡ ብዛት ፡ የሰነፈው ፡ ሰው ፡ አሳቡን ፡ ውሱን ፡ ልቡን ፡ ቁራጥ ፡ ሳያደር ግ ፡ የወደደውንም ፡ ሁሉ ፡ ልሥራ ፡ ብሎ ፡ ይዠ ምርና ፡ የሥራውን ፡ ልክ ፡ ካለመወሰን ፡ የተነሣ ፡ ኸምሩ ፡ በዝቶ ፡ አልጨረስ ፡ ሲል ፡ እየተናደደ ፡ ቊጣውን ፡ እብዝቶ ፡ ከእብደት ፡ ይደርሳል ፡ ሰው ነቱም ፡ ይቀላል ። ዕድሜውም ፡ ሥራውም ፡ የማይሰነብት ፡ ይሆናል ። የማይረባውንም ፡ ትን ሹንና ፡ የሚረባውንም ፡ ትልቁን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ደራርቤ ፡ ልሥራ ፡ እያለ ፡ ሲደክም ፡ መድከሙም ፡ ሳይቀር ፡ ስለ ፡ ሥራው ፡ ድንበር ፡ ማጣት ፡ ሁሉ ም ፡ ተቀላቅሎ ፡ የተበላሸ ፡ ይሆንበታል ። ወይም ፡ ኢይክል ፡ ተቀንየ ፡ ለክልኤ ፡ አጋዕዝት ፡ የተባ ለውን ፡ እየረሳ ፡ ሥጋዊውንና ፡ መንፈሳዊውን ፡ ሥራ ፡ ቀላቅዬ ፡ እሠራለሁ ፡ እያለ ፡ ሠርቶ ፡ የማይ ጨርሰውን ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ብዙ ፡ ግብር ፡ መር ምሮ ፡ የማያገኘውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ብዙ ፡ ምስጢር ፡ ሁለቱንም ፡ እሠራለሁ ፡ በማለት ፡ ለ ውሱን ፡ ሰውነቱ ፡ ያልተወሰነ ፡ ትልቅ ፡ አሳብ ፡ አሲዞ ፡ አንዱን ፡ ሳይጨርሰው ፡ የሱ ፡ ዕድሜ ፡ ይጨረሳል ። ለአካሉም ፡ ሥራ ፡ ሳያሲዘው ፡ ልቡን ፡ ብቻም ፡ ምስጢር ፡ መርማሪ ፡ ሲያደርገው ፡ የው ጭ ፡ አካሉ ፡ ጠባቂ ፡ እያጣ ፡ ለአካሉ ፡ የተሠራለትን ፡



ማዕርግ ፡ እየናቀ ፡ ወይም ፡ የገዛ ፡ ሰውነቱን ፡ እየዘ ነጋ ፡ በሚያሳፍረው ፡ ሁሉ ፡ የማያፍር ፡ ዝርክርክ ፡ ጥርክርክ ፡ ሆኖ ፡ ከጅልነቱ ፡ ይደርሳል ።

የኖረ ፡ ልማድ ፡ እንትፋለሁ ፡ ባነጋገር ፡ ማራቀቁ ፡ በምስጢር ፡ ማወቁ ፡ ብቻ ፡ እከብራለሁ ፡ እየመሰ ለው ፡ አለባበሱንም ፡ አስተማጠቁንም ፡ አጥፍቶ ፡ ዐይኑን ፡ እጁን ፡ ከንፈሩን ፡ ግንባሩን ፡ እነዚህን ፡ የሚንቀሳቀሱትን ፡ አካሎች ፡ ባለመጠበቁ ፡ ለአ ካሉ ፡ የልማድ ፡ ነውር ፡ አውጥቶ ፡ ሰውነቱን ፡ ያስ ንቃል ። በዚህም ፡ ልማድ ፡ የውጭ ፡ አካሉ ፡ ጸጥ ታ ፡ አጥቶ ፡ እጁን ፡ ወይ ፡ ካፉ ፡ ወይ ፡ ካፍንጫው ፡ እያደረገ ፡ ግንባሩንም ፡ በማፍታታት ፡ በመቋጠር ፡ ዐይኑን ፡ በማፃወር ፡ በማጨንቀር ፡ ከንፈሩንም ፡ በመንከስ ፡ በማንፈራፈር ፡ አካሎቹንም ፡ እስበሳ ቸው ፡ እያጫወተ ፡ አካሉ ፡ ሁሉ ፡ በየልማዱ ፡ ሲበ ተን ፡ ልቡም ፡ አብሮት ፡ ይበተንና ፡ ስለዚህ ፡ በግ ድ ፡ ዝንጉ ፡ ይሆናል ።

ጥያቄ ።

፻፶፩ ፡ ከነዚህ ፡ ከሦስቱ ፡ ጕዳት ፡ ለመዳን ፡ ምን ፡ ይ ሻላል ።

ምላሽ ።

፻፶፩ ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማመን ፡ ልክ ፡ ባሕ ኛው ፡ ምዕራፍ ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ አጭር ፡ ሆኖ ፡ በተወሰነው ፡ ልክ ፡ ማመን ፡ ነው ። ስለ ፡ ምግባር ፡

ሥራ ፡ ልክ ፡ በምዕራፍ ፡ ፪ ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ አድ
ርገህ ፡ ካራቱ ፡ ጐዳና ፡ አንዱን ፡ መርጠህ ፡ መሥ
ራት ፡ ነው ። ለምትሠራበትም ፡ የሰዓት ፡ ልክ ፡
ባ፲፫ ፡ ምዕራፍ ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ አድርገህ ፡ መ
ክፈል ፡ ነው ።

ጥያቄ ።

፫፻፲፱ ፤ ስንፍናም ፡ ቍጣም ፡ ዝንጋትም ፡ ሳይገሥግሩ
ስ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ አሳብ ፡ ልክ ፡
በማበጀት ፡ ይከለከላሉ ፤ ከገቡስ ፡ በኋላ ፡ የሚወ
ጡት ፡ በምን ፡ ሥራ ፡ ነው ።

ምላሽ ።

፫፻፲፱ ፤ ቍጣህ ፡ ስንፍናህ ፡ መንፈሳዊን ፡ ሥራ ፡ ሲ
ያስቀርብህ ፡ ባጭር ፡ ጸሎትና ፡ ስጊድ ፡ በረዥም ፡
መጽሐፍ ፡ መመልከት ፡ ትጋትን ፡ መሻት ፡ ነው ።
ትዕግሥትንም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ መለመን ፡ ነው ።
ኑሮህ ፡ ዓላማዊነት ፡ ሆኖ ፡ በዓለሙ ፡ አሳብ ፡
ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ስንፍናህ ፡ ዝንጋታህ ፡ ሥጋዊ ፡
ንብረትህን ፡ ሲያስቀርብህ ፡ ዝንጋታህን ፡ ማስ
ታወሻ ፡ በማጻፍ ፡ ስንፍ ፡ ሥራ ፡ ሲያስቀርብህ ፡
ለአካልህ ፡ ትባትን ፡ ለነፍስህ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማ
ያትን ፡ ታገኝ ፤ ዘንድ ፡ ወዝህን ፡ በንግህ ፡ ስጊድ ፡
እያወጣህ ፡ ሰውነትህን ፡ አትባው ፤ ሥጋዊነትም ፡
አሸንፎህ ፡ ስጊድም ፡ ሲያቅትህ ፡ የሚቻልህን ፡
ወዲያው ፡ ለንብረትህ ፡ የሚሆን ፡ በእጅና ፡ በእ



ግር ፡ የሚሠሩትን ፡ የሥራህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቤትህ
ንም ፡ ጠቅመህ ፡ ሰውነትህን ፡ ከመዘፍዘፍ ፡ እጅ
ና ፡ እግርህን ፡ ከመስነፍ ፡ አድንህ ፡ ትጠቀማለህ ፤
ለራስህም ፡ ጕዳይ ፡ ለመሥራት ፡ ጌትነት ፡ ቅምጥ
ልነት ፡ ሲከለክሉህ ፡ በጨዋታ ፡ የተለመደው ፡
ትባት ፡ እጅህን ፡ ወደ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ሥራና ፡ ብር
ታት ፡ እንዲያደርሱልህ ፡ ባይሆን ፡ እንኳ ፡ ድካ
ሙ ፡ ሳይታወቅ ፡ ወዝህ ፡ የሚወጣበትን ፡ ጨወታ ፡
ያዝ ። ወዝ ፡ እሚወጣበት ፡ ጨወታም ፡ የኳስ ፡ የገና ፡
የፈረስ ፡ ግልቢያ ፡ ሌላም ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ በእግር ፡
የሚያስኬድ ፡ ሥራ ፡ የውሃ ፡ ዋና ፡ ጨወታ ፡ ነው ።
የነዚህንም ፡ ጥቅምነት ፡ ልትረዳ ፡ ብትሻ ፡ በቅምጥ
ትልልቅ ፡ የአእምሮ ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩት ፡ ፈረን
ጆች ፡ የኛም ፡ አገር ፡ ጌቶች ፡ ሁሉ ፡ ሥጋቸው ፡
እንዳይሰንፍ ፡ እንዳይዶፈዱፍ ፡ በግድ ፡ እሚያስ
ፈልጋቸው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በጨወታ ፡ እያመካኙ ፡ ወዛ
ቸውን ፡ በማፍሰሳቸው ፡ ለትጋት ፡ ምክንያት ፡
ይሆናቸዋልና ፡ በዚህ ፡ አስተውለው ።

በዚህም ፡ ዐይነት ፡ ወዝህን ፡ ለማውጣት ፡ ሲያቅ
ትህ ፡ በየቀኑ ፡ አንዳንድ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ለእግ
ርህ ፡ የምትሄድበት ፡ ምክንያት ፡ እየፈልግህ ፡ ሂድ
በት ፤ ወፍራም ፡ ብረት ፡ አግሎ ፡ ማማሟት ፡ እግ
ሥቶ ፡ በውሃ ፡ ማትባት ፡ ለስለቱ ፡ ምክንያት ፡ እን
ደሚሆነው ፡ ለግዙፉ ፡ ሥጋችንም ፡ ወዛችንን ፡ የ
ምናወጣበት ፡ ምክንያት ፡ ሽተን ፡ ያወጣነው ፡ እ

ንደ ፡ ሆነ ፡ ለምንሠራውም ፡ ሁሉ ፡ ምክንያት ፡ ሆኖ ፡ ያተጋናል ፤ ከስንፍናም ፡ ያድነናል ።

ይህንም ፡ ስላልኩህ ፡ ጨወታህ ፡ በዝቶ ፡ ወደ ፡ እብደት ፡ እንዳይወስድህ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ እምትሠራበትን ፡ ጊዜ ፡ ዘጠኝ ፡ እጅ ፡ እምትጫወትበትን ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ እጅ ፡ ማድረግ ፡ ነው ።

ጥያቄ ።

፻፺፬ ፤ አሳብ ፡ ማብዛት ፡ ከምን ፡ ይነጣብናል ።

ምላሽ ።

፻፺፭ ፤ አሳብ ፡ ለማብዛት ፡ ሥራን ፡ ለመጥላት ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ መወጠንን ፡ ጥቂት ፡ ስንዠምርለት ፡ ይህን ፡ ጠላታችን ፡ ሰይጣን ፡ አስተውሎ ፡ ያይና ፡ ጠላት ፡ የሚዋጋው ፡ በላላበት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ጸላኢ ፡ የአሳብ ፡ ማስታወሻ ፡ ጸሓፊ ፡ ሆኖ ፡ ማስታወሻውን ፡ ሁሉ ፡ ገልጦ ፡ ለልቡና ፡ እያቀረበ ፡ አንድ ፡ ስታስብ ፡ አንድ ፡ እየቀጠለ ፡ የዛዘለ ፡ የረዘመ ፡ እማይቋረጥ ፡ አሳብ ፡ ይዘራብህና ፡ የዠመርከውንም ፡ አሳብ ፡ እንዳትጨርስ ፡ ያሰብከውንም ፡ እንዳትሠራ ፡ ያደርግህና ፡ የዓለምን ፡ ሁሉ ፡ የጥበብ ፡ ማስታወሻ ፡ ከልብህ ፡ ውስጥ ፡ ገልጦ ፡ ይህን ፡ ብታደርግ ፡ እንዲህ ፡ ይሆንብሃል ፡ እያለ ፡ አመንቲ ፡ ዋላላ ፡ ፈሪ ፡ ጠርጣሪ ፡ ያደርግሃልና ፤ የብዙ ፡ ነገር ፡ ማሳፈሪያ ፡ አድርጎህ ፡ ያሳብን ፡ ከስማዎች ፡ ሁሉ ፡ ከልብህ ፡ እየተከለ ፡ ያስጨንቅሃል ።



ጥያቄ ።

፻፺፮ ፤ እዛዲያ ፡ ላሳብ ፡ መዝጊያ ፡ የለው ፡ በምን ፡ እ ማደዋለሁ ።

ምላሽ ።

፻፺፯ ፤ ያሳብክን ፡ ብዛት ፡ ቢቻልህ ፡ በእምነት ፡ ቍረጠው ፡ ቢያቅትህ ፡ በዕጣ ፡ ቍረጠው ፡ እንጂ ፤ እንኳን ፡ ሥጋዊውን ፡ መንፈሳዊ ፡ አሳብ ፡ ቢሆን ፡ በማማረጥና ፡ በማሰብ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ አትዋለል ። ይልቁንም ፡ ስለዚህ ፡ ዓለም ፡ በምታስበው ፡ የምትኖርበት ፡ ቀንህ ፡ ቍርጥ ፡ ነውና ፡ አሳብህ ፡ ቍርጥ ፡ እይጣ ፤ መድኀኒታችንም ፡ በወንጌሉ ፡ በሚያስጨንቅ ፡ አሳብ ፡ አትዋልሉ ፡ ያለውን ፡ አትርሳ ።

ጥያቄ ።

፻፺፰ ፤ በዕጣ ፡ የወጣውን ፡ ወይም ፡ ልቤ ፡ የመረጠውን ፡ ጀንቼ ፡ ለመሥራት ፡ እማልችል ፡ ሁኜ ፡ ልቤ ፡ በብዙ ፡ አሳብ ፡ እየዋለለ ፡ የምወደውን ፡ አልሠራልኝ ፡ ሲል ፡ ምን ፡ ይሻለኛል ።

ምላሽ ።

፻፺፱ ፤ የልብ ፡ አሠራር ፡ እንደ ፡ ወተት ፡ አሠራር ፡ ነው ። የሚያስፈልገው ፡ ወተቱን ፡ አልቦ ፡ በገበታ ፡ የያዘ ፡ ሰው ፡ ከድኖ ፡ ካንድ ፡ ቦታ ፡ ካላስቀመጠው ፡ ይገርው ፡ ልሂድ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሁሉም ፡ ፈሶ ፡ እንደሚቀርበት ፡ ሲያስቀምጠው ፡ ግን ፡ ረግቶ ፡ ቅ

ቤን ፡ እንደሚያገኝበት ፡ ሐሳቡን ፡ በዋላላ ፡ ልብ ፡ ላይ ፡ የያዘ ፡ ሰውም ፡ እግሩን ፡ እፉን ፡ አሳርፎ ፡ ካንድ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ እስኪረጋለት ፡ ድረስ ፡ ከዋላላነት ፡ የሚበልጥ ፡ ደዌ ፡ የለምና ፤ ፊልክስዩስ ፡ እንዳለው ፡ መቃርስም ፡ ትሩፋትን ፡ በዓለሙ ፡ ሲገሥምር ፡ እሞኛል ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ሠራው ፡ እንደ ፡ በሽተኛ ፡ ሆኖ ፡ ከቤቱ ፡ ሳይወጣ ፡ ማየት ፡ መስማትን ፡ ትቶ ፡ አፉን ፡ ዘግቶ ፡ ቈይቶ ፡ ልቡ ፡ ሲረጋለት ፡ የረጋውም ፡ ልቡናው ፡ እየጎጉለ ፡ በስንፍና ፡ እንዳይበላሽበት ፡ በሚቻለው ፡ ልክ ፡ በጸሎቱ ፡ የመስበቂያውን ፡ ዘንግ ፡ ሥሩ ፡ አንድ ፡ ሜፉ ፡ ሦስት ፡ የሆነ ፡ ኀይለ ፡ እግዚአብሔር ፡ እየለመነ ፡ በፍቅሩ ፡ እየሰበቀ ፡ በሽክላ ፡ ሥጋው ፡ ርጎ ፡ አሳቡን ፡ እየገፋ ፡ ሲያሳግደው ፡ ወገሚት ፡ ስንፍናው ፡ አሠር ፡ ሆኖ ፡ እየቀረለት ፡ ቅቤ ፡ ጥቅሙ ፡ እየወጣለት ፡ ያን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እየተቀበለ ፡ በሚያውቀው ፡ ሽቱ ፡ እያጣፈጠ ፡ ይቀባውና ፡ በመንግሥት ፡ ሰማይ ፡ በቂ ፡ የሚሆንበት ፡ መንገድ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ (ጣዕመ ፡ ጸሎት ፡ ምዕ፳፫ ፡ ፳፬ ፡ ፳፭) ።

ምዕራፍ ፡ ፳፪ ።

## አልመከር ፡ ስለእሚል ፡ ልጅ ፡ ምርምር ።

ጥያቄ ።

፻፺፰ ፡ ልጅ ፡ አልመከር ፡ ሲል ፡ በምን ፡ መምከር ፡ ይሻላል ።



ምላሽ ።

፻፺፰ ፡ እንደ ፡ ጠባዩ ፡ ዐይነት ፡ መቅጣት ፡ ነው ። ኵራተኛ ፡ ሲሆን ፡ በድኽነት ፤ ዝሙተኛ ፡ ሲሆን ፡ በረኃብ ፤ ቍጠኛ ፡ ሲሆን ፡ በሚያደክም ፡ በንብረት ፡ ሥራ ፤ የዋህ ፡ ሲሆን ፡ ከንብረት ፡ ከልክሎ ፡ ከብልህ ፡ አስተማሪ ፡ በማቈየት ፡ የማይማር ፡ ጅል ፡ ሲሆን ፡ የቁም ፡ እስር ፡ አድርጎ ፡ ከሰው ፡ ለይቶ ፡ በማኖር ፤ ጨካኝ ፡ ሲሆን ፡ ባደረገው ፡ ዐይነት ፡ መቅጣት ፤ የሚዞር ፡ የማያርፍ ፡ ንቃት ፡ የበዛበት ፡ ሲሆን ፡ በማሰር ፡ መስረቅ ፡ ማበል ፡ መስከር ፡ የበዛበት ፡ ሲሆን ፡ የሦስቱም ፡ ዐይነት ፡ አንድ ፡ ቅጣት ፡ ነውና ፡ በመግረፍ ፡ መምከር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ኵሩን ፡ ቢገርፉት ፡ ቅጣተኛን ፡ ቢያደኸዩት ፡ ዝሙተኛን ፡ አስሮ ፡ ቢያበሉት ፡ ቍጡን ፡ ቢቀጡት ፡ ያብስበታል ፡ እንጂ ፡ አያድነውም ።

ምዕራፍ ፡ ፳፫ ።

## ስለ ፡ ዓለም ፡ እድፍነት ።

## ስለ ፡ ፈረንጆች ፡ አለመብሰጥ ።

፻፺፱ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የምትሠራውን ፡ ሁሉ ፡ ጨርሼ ፡ አጠራለሁ ፡ ብለህ ፡ የጣርክ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያ

ንተን ፡ አእምሮ ፡ ታዝጋለህ ፡ እንጂ ፡ እድፋሙን ፡ ዓለም ፡ ለማጥራት ፡ አይቻልህምና ፤ ሀኬት ፡ እን ዳይሠለጥንብህ ፡ ስለ ፡ ተግባረ ፡ ሥጋህ፡ ሳትጨነ ቅም ፡ እጅግ ፡ ሳትሟገና ፡ ሳታጣራም ፡ ላይ ፡ ላዩን ፡ አለቅልቀው ፡ እንጂ ፡ ውስጡን ፡ ሁሉ ፡ ገላልጨ ፡ አጥርቼ ፡ ላጥራው ፡ አትበል ።

ጥያቄ ።

፫፻፳፫ ፤ ምነው ፡ ሰው ፡ የያዘውን ፡ ነገር ፡ ቢያጠራ ፡ ብልኅና ፡ ብርቱ ፡ ያሰኘዋል ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አእ ምሮ ፡ ያዝጋል ።

ምላሽ ።

፫፻፳፬ ፤ የዓለም ፡ መላ ፡ አካሏ ፡ ምድር ፡ ነውና ፡ በሷ ፡ ላይ ፡ የሚሠራውን ፡ ሁሉ ፡ አጠራለሁ ፡ የሚ ል ፡ ምድርን ፡ ያጥባልና ፡ ጅል ፡ ያሰኘዋል ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ እውነቱ ፡ ብልኅ ፡ አይባልም ።

ጥያቄ ።

፫፻፳፭ ፤ ምነው ፡ ፈረንጆች ፡ ዕውቀታቸውን ፡ አጣ ርተው ፡ አራት ፡ ባሕርያትን ፡ በብረት ፡ ዘግተው ፡ ይዘው ፡ እንሱ ፡ ዐርፈው ፡ እሳትና ፡ ውሃን ፡ ሠራተ ኞች ፡ አድርገው ፡ በሞተር ፡ እየሠሩ ፡ ኑሯቸውን ፡ ሁሉ ፡ አጣርተው ፡ ይኖሩ ፡ የለምን ፤ ተጠቀሙ ፡ እንጂ ፡ መቼ ፡ ተጐዱ ።



ምላሽ ።

፫፻፳፮ ፤ የንሱም ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ላዩን ፡ የዓለምን ፡ እድፍ ፡ እያለቀለቁ ፡ ቢያሳዩህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ውስጣቸው ንስ ፡ አስተውለህ ፡ ብታየው ፡ ከኛ ፡ የሚበልጡበት ፡ ጥራት ፡ ያላቸው ፡ አይምሰልህ ፡ ልብ ፡ አድርገህ ፡ ስታ የው ፡ የንሱ ፡ ኑሮ ፡ ከታላላቁ ፡ ጐዳት ፡ ከማናቸው ፡ ነገር ፡ ሲያድናቸው ፡ አይተህ ፡ ነው ፡ ጥሩ ፡ የሚመስልህ ፡ ከመኖር ፡ ከመሞት ፡ ከማግኘት ፡ ከማጣት ፡ ከሐዘን ፡ ከ ብስጭት ፡ ከመጣላት ፡ ከመዋጋት ፡ ከመሥራት ፡ ከ መድከም ፡ ከማንኛው ፡ ድካም ፡ ሲያርፉ ፡ አየሃቸው ።

ይህንስ ፡ ትልቁን ፡ ነገር ፡ አጥርቶ ፡ ማረፍ ፡ ካል ተቻላቸው ፡ የሚያልቀውን ፡ ልብስ ፡ ቢያኽጉረ ጉሩ ፡ የሚፈርሰውን ፡ ቤት ፡ ቢወለውሉ ፡ ምን ፡ ነዋሪ ፡ ነገር ፡ አጠሩ ። የኑሮ ፡ ዐይነት ፡ ብቻ ፡ ለወ ጡ ፡ እንጂ ፡ ድካምና ፡ ብስጭትስ ፡ እንዲያውም ፡ ከኛ ፡ በንሱ ፡ ይጸናል ።

ጥያቄ ።

፫፻፳፯ ፤ ምነው ፡ እኛንማ ፡ ለመብለጥ ፡ ትልልቁ ፡ ጉዳ ት ፡ እስኪያገኛቸው ፡ ድረስ ፡ እስኪሞቱ ፡ ባለው ፡ በትንሹ ፡ ኑሮ ፡ ይበልጡን ፡ የለምን ።

ምላሽ ።

፫፻፳፰ ፤ በቀናተኛና ፡ በማያስተውል ፡ ዐይናችን ፡ ስና ያቸው ፡ የበለጡን ፡ ይመስለናል ፡ እንጂ ፡ በዕው

ቀት ፡ ዐይን ፡ እስተውለን ፡ ከተመለከትናቸው ፡
እነሱም ፡ ጸር ፡ ጋር ፡ አብዝተው ፡ እኛም ፡ ሳናበ
ዛ ፡ የምንሻው ፡ ጥቅሙም ፡ ፍሬውም ፡ አንድ ፡ ነ
ውና ፡ ሁላችንም ፡ የምንሻው ፡ ይህን ፡ ሥጋ ፡ ለማ
ልበስና ፡ ለመመገብ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ይህን ፡ ካገኘን ፡
አንበላለጥም ።

ጥያቄ ።

፻፶፱ ፡ የማያምርና ፡ የሚያምር ፡ ጥቅሙ ፡ እንዴት ፡
ይተካከላል ።

ምላሽ ።

፻፷ ፡ የነሱ ፡ ያማረ ፡ የኛ ፡ የከፋ ፡ እስመስሎ ፡ የሚ
ያሳስብህ ፡ ዘማዊ ፡ ዐይንህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የጥቅሙ ፡
መበላለጥ ፡ አይደለም ፤ ሰው ፡ ከመልክ ፡ መልካም ፡
ሴትም ፡ ቢሆን ፡ ከመልክ ፡ ከፉ ፡ ሴትም ፡ ቢሆን ፡
ፈቃደ ፡ ሥጋውን ፡ የሚፈጽምበት ፡ አንድ ፡ ዐይ
ነት ፡ ሲሆን ፡ በአፍኣ ፡ የምናየው ፡ የመልካቸው ፡
እለመቃናት ፡ ለፈቃደ ፡ ሥጋችን ፡ የሚያጕድለን ፡
ወይም ፡ የመልካቸው ፡ መቃናት ፡ የሚጠቅመን ፡
ነገር ፡ ሳይኖር ፡ እመንዝሬው ፡ ዐይናችን ፡ እንደ
ሚመርጥብን ፡ ሁሉ ፡ የነሱን ፡ ኑሮ ፡ የሚያስመኘን ፡
የኛን ፡ ኑሮ ፡ የሚያስንቅፈን ፡ የዐይናችን ፡ ሌሰን ፡
ነው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ኑሮው ፡ ልማዳችን ፡ ለሕይወ
ታችን ፡ የማይጠላ ፡ ምግብና ፡ ልብስ ፡ ካገኘን ፡ በ
ጥቅም ፡ ከነሱ ፡ የምናንስ ፡ አይደለንም ።



ይህን ፡ ለመረዳት ፡ የሊቁ ፡ የማህተማ ፡ ጋንዲ ፡
ታሪክ ፡ ያስረዳህ ።

፻፷፩ ፡ ይልቅስ ፡ ዳኝነት ፡ እንዳለህ ፡ የግፍ ፡ አረማቾ
ው ፡ የፍርድ ፡ ማጣራታቸው ፡ ሠራተኛ ፡ ብትሆን ፡
የመጠን ፡ ትጋታቸው ፡ ነጋዴ ፡ ስትሆን ፡ የሒሳባ
ቸው ፡ ዕውቀት ፡ ይመርህ ፡ እንጂ ፡ ልብስህን ፡ በል
ብሳቸው ፡ ቤትህን ፡ በቤታቸው ፡ በጎ ፡ ምግባር
ህን ፡ በምግባራቸው ፡ ሃይማኖትህን ፡ በሃይማኖ
ታቸው ፡ ምግብህን ፡ በምግባቸው ፡ መለወጥስ ፡
አይመርህ ። እግዚአብሔር ፡ በሀገራችን ፡ ውስጥ ፡
ለባሕርያችን ፡ የሚያሻንን ፡ ሰጥቶን ፡ ሳለ ፡ የሰው ፡
አገር ፡ ድግስ ፡ ከፈለግን ፡ ቅልውጥና ፡ ወረት ፡ ይሆ
ንብናል ፡ እንጂ ፡ ሕይወት ፡ መፈለግ ፡ አያሰኘንም ።

ከኛ ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ሆነን ፡ የነሱን ፡ ምግብ ፡ ብንመገብ ፡ አ
ገራችን ፡ ለየራሱ ፡ ነውና ፡ ከነጤናውም ፡ አናገኘው ።

ስለዚህ ፡ አባቶቻችን ፡ ዘርተው ፡ ያበቀሉትን ፡
ልማድ ፡ ከፉ ፡ ከፉውን ፡ እያረምን ፡ እናልማው ፡
እንጂ ፡ ዘር ፡ ለውጠን ፡ ምግባቸውን ፡ ልብስ ፡ ጥለ
ን ፡ ልብሳቸውን ፡ አንሻ ።

ጥያቄ ።

፻፷፪ ፡ ምነው ፡ የብልኆችን ፡ የፈረንጆችን ፡ ልብስ ፡
ብንለብስ ፡ ወደነሱ ፡ ትጋት ፡ ይመራናል ፡ እንጂ
ምን ፡ ያጕዳናል ።

ምላሽ ።

፫፻፴፫ ፡ ያልተማረ ፡ ቢጠመጥም ፡ የተማረውን ፡ ሞያ ፡ መች ፡ ያገኛል ።

የሰው ፡ ልብስ ፡ መሻት ፡ አገሬ ፡ ልብስ ፡ የለውም ፡ ማለት ፡ ነውና ፡ ከሀገራችን ፡ የሚገኘውን ፡ ልብስ ፡ እናከብር ።

የሰው ፡ ምግባር ፡ ሳንይዝ ፡ የኛኑ ፡ ምግባር ፡ በመጽሐፋችን ፡ እናጣራ ፤ የሰው ፡ ሃይማኖት ፡ ሳንይዝ ፡ የኛን ፡ ሃይማኖት ፡ እናጥና ።

ጥያቄ ።

፫፻፴፬ ፡ ወኰሎ ፡ አመክሩ ፡ ወዘሠናየ ፡ አጽንዑ ፡ እንዳለው ፡ ሁሉን ፡ እየመረመርን ፡ መልካም ፡ የመሰለንን ፡ ብንይዘው ፡ ምን ፡ ያጐዳናል ።

ምላሽ ፡

፫፻፴፭ ፡ ወኰሎ ፡ አመክሩ ፡ የተባሉ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ የነቢያትና ፡ የሐዋርያት ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ይገኝባቸዋልና ፡ ሳንከፍል ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ ሁሉ ፡ እንድናስተውል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሰውን ፡ ሁሉ ፡ ልማድ ፡ ለመከተል ፡ አይደለም ።

ያማረውንና ፡ የመሰለውን ፡ የሰው ፡ ልማድ ፡ ሁሉ ፡ ልከተል ፡ የሚል ፡ ባገሬ ፡ የሚያድጉን ፡ ሃይማኖት ፡ የሚያጸድቅ ፡ ምግባር ፡ የለበትም ፡ በማለቱ ፡ ይህን፡



የሠሩ ፡ አባቶች ፡ አልተጠቀሙም ፡ በማለቱ ፡ አባቱንም ፡ መንቀፍ ፡ አገሩን ፡ መዝለፍ ፡ ይሆንበታል ፡ እንጂ ፡ አይረባም ፤ የእምልኮት ፡ ነገር ፡ የሚፈጸመው ፡ በመጽናት ፡ በየውሀት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በመውጣትና ፡ በብልኀት ፡ አይፈጸምም ።

ይህንም ፡ ልትረዳ ፡ ብትሻ ፡ አበውን ፡ ሁሉ ፡ ክርክር ፡ አለያያቸው ፡ እንጂ ፡ አላስማማቸውምና ፡ የየዘመኑን ፡ ሃይማኖት ፡ ታሪክ ፡ አስተውል ።

ጥያቄ ።

፫፻፴፮ ፡ በእምልኮትስ ፡ ነገር ፡ ሳይሆን ፡ በኑሮ ፡ ዐይነት ፡ ልብስን ፡ ምግብን ፡ ቤትን ፡ እንደ ፡ ፈረንጆች ፡ እያመሳሰሉ ፡ ቢያደርጉት ፡ ምን ፡ ይጐዳል ።

ምላሽ ።

፫፻፴፯ ፡ በሦስት ፡ ነገር ፡ ይጐዳል ፤ በፈረንጅ ፡ ዐይነት ፡ ከተሠራ ፡ ከነስሙም ፡ የፈረንጅ ፡ ቤት ፡ የፈረንጅ ፡ ልብስ ፡ ይባላልና ፡ የኢትዮጵያን ፡ ስም ፡ ያጠፋል ። ሁለተኛ ፡ ሰው ፡ የወደደውን ፡ በግድ ፡ ይመስላልና ፡ ወደ ፡ ልምዳቸው ፡ ወደ ፡ ምግባራቸው ፡ በግድ ፡ ልቡ ፡ ያስብበታል ፤ ልማዱንም ፡ ምግባሩንም ፡ እየነቀፈ ፡ አገሬም ፡ የሚለው ፡ ዐፈሩን ፡ ብቻ ፡ ይሆናል ።

ስለዚህ ፡ የሚለበስውም ፡ ጨርቁም ፡ የነሱ ፡ ቢሆን ፡ የልብስ ፡ ቅዱና ፡ ስፉ ፡ እንደ ፡ ሐበሻ ፡ ይሁን ፤

የቤትህም ፡ መሥሪያው ፡ የነሱ ፡ ቢሆን ፡ አሠራሩ
ንና ፡ ልማድህን ፡ እንዳያስለቅቅህ ፡ አገርህን ፡ እን
ዳያስንቅህ ፡ ልብህም ፡ ለጌጡና ፡ ለማማሩ ፡ እንዳ
ይጠለፍብህ ፡ አድርገህ ፡ ሥራው ፡ እንጂ ፡ በሰው ፡
ልማድ ፡ መከተል ፡ ያገርህን ፡ ልማድ ፡ አታጥፋ ።

ጥያቄ ።

፻፶፮ ፡ ቤታቸውን ፡ ከሚሸልሙ ፡ ለዐይናቸው ፡ ደስ
ታ ፡ ከሚጥሩት ፡ ከፈረንጆች ፡ ከመሰላቸው ፡ ሥራ፡
ሁሉ ፡ ለጽድቅ ፡ የሚሆን ፡ ሥራ ፡ ምንም ፡ አይገ
ኝምን ።

ምላሽ ።

፻፶፮ ፡ ምናልባት ፡ ከሚሠሩት ፡ ከሕንጻው ፡ ከመ
ንገዱ ፡ ከድልድዩ ፡ መጪዎችን ፡ ትውልዶች ፡
ደስ ፡ ላሰኘበት ፡ ብሎ ፡ በዚህ ፡ አሳብ ፡ የሚሠራ ፡
ሰው ፡ እስካለሁ ፡ ለኔ ፡ ስሞት ፡ ለልጄ ፡ መከበሪያ ፡
ሲቈይ ፡ ለስሜ ፡ መጠሪያ ፡ ይሁነኝ ፡ ሲል ፡ ከየታ ፡
ሪኩ ፡ ላይ ፡ ስሙን ፡ ከየሥራው ፡ ቅርጹን ፡ ዕወቁ
ልኝ ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ብርታቴን ፡ ብልኀቴን ፡ አድ
ንቁልኝ ፡ ባይ ፡ ነውና ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡
እሚያገኘው ፡ ያንኑ ፡ የሻውን ፡ ውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ ብቻ ፡
ነው ፡ እንጂ ፡ ለነፍሱ ፡ ምንም ፡ ጥቅም ፡ የለው
ም ። እንዲያውም ፡ የእምላኩን ፡ ጥበብ ፡ የኔ ፡ ነው ፡
እያለ ፡ በመጻፉ ፡ ሐሰተኛና ፡ ቀማኛ ፡ ይመስላል ።
ለራሱ ፡ ጥቅም ፡ ለስሙ ፡ ክብር ፡ ሳይሆን ፡ ይመር



ልኝ ፡ ያገኘልኝ ፡ ሳይል ፡ እንዲኖርና ፡ እንዲበ
ረታ ፡ ብቻ ፡ አድርጎ ፡ ለቀሪ ፡ ሰዎች ፡ ጥቅም ፡
ብቻ ፡ አስቦ ፡ ስሙን ፡ ከታሪክም ፡ ላይ ፡ ከሥራ
ውም ፡ ላይ ፡ ሳያጽፍ ፡ ሲሠራም ፡ ጥበቡ ፡ የሱ ፡
መሆኑን ፡ እንዲታወቅለት ፡ ስሙን ፡ በማስጠራት ፡
ሳይጥር ፡ ቢሠራ ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ያለው
ዳሴ ፡ ከንቱ ፡ ዕውቀቱንና ፡ ትጋቱን ፡ ለመጪ ፡
ትውልድ ፡ የመጸወተ ፡ ነውና ፡ ዋጋው ፡ እጅግ ፡
ብዙ ፡ ሆኖ ፡ ነፍሱን ፡ ይጠቅማል ።

ለሥጋውም ፡ እንደ ፡ ሰሎሞን ፡ ያልፈለገውን ፡
ክብር ፡ እግዚአብሔር ፡ ይጨምርለታል ።

ጥያቄ ።

፻፶፯ ፡ ምነው ፡ የነቢያት ፡ የሐዋርያት ፡ መጻሕፍት ፡
ሁሉ ፡ ስማቸው ፡ እየተጻፈ ፡ ዛሬ ፡ ሁሉም ፡ ሲመ
ሰገኑበት ፡ ይኖር ፡ የለምን ፡ ሰው ፡ በሠራው ፡ ስሙ ፡
እንዲጠራ ፡ ቢያደርግ ፡ ምን ፡ ያጉድለዋል ።

ምላሽ ።

፻፶፯ ፡ ነቢያት ፡ ሐዋርያት ፡ ዕውቀታቸውን ፡ ጻፉ ፡
እንጂ ፡ ይህ ፡ የኔ ፡ ድርሰት ፡ እያሉ ፡ ስማቸውን ፡
አልጻፉም ፡ ይህንም ፡ አሁን ፡ ከየመጻፋቸው ፡ እር
እስት ፡ ተጽፎ ፡ የምናየውንም ፡ ስም ፡ ከሞቱ ፡ በ
ኋላ ፡ ይቱ ፡ ምእት ፡ የጻፉላቸው ፡ መሆኑን ፡ ፍትሐ
ነገሥት ፡ ያስረዳሃል ፡ እንደዚሁም ፡ እንት ፡ መመስ

ገንን ፡ ካልሻኸው፡ አንተንም፡ አጽድቆ ፡ ስምህን ፡
ፈጣሪ ፡ በፍርዱ ፡ ያስነግልሃል ።

ምዕራፍ ፡ ፳፯ ።

ለሃይማኖት ፡ ዕንቅፋት ፡ ለሚሆኑ ፡ ሥራዎች ፡

## ምርምር ።

፻፶፱ ፡ ሀብተ ፡ አሚን ፡ በተሰጠህ ፡ ጊዜ ፡ ሁለት ፡
ብርቱ ፡ ጾር ፡ ያገኝሃልና ፡ ተጠንቀቅ ።
የሚያገኝህም ፡
አንደኛ ፡ ሐኬት ፡
ሁሉን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይሥራልኝ ፡ በማለት ።
ሁለተኛ ፡ ድፍረት ፡
ኢታመክሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተባለውን ፡ በመር
ሳት ፡ እኒህ ፡ አጥብቀው ፡ ይዋጉሃል ፤ ዕወቅባቸው ።

፻፷ ፡ ዳግመኛም ፡ በሃይማኖት ፡ ከምትሠራው ፡
ከምግባር ፡ ጐዳናህም ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡ ዕንቅፋ
ቶች ፡ ያገኙሃል ፤ እየዞርክ ፡ እለፋቸው ።

አንደኛ ፡ ተገዥ ፡ በሆንክ ፡ ጊዜ ፡ ጌታህን ፡ ስታከ
ብረው ፡ ስትሠራለት ፡ ይዩኝ ፡ ይወቅልኝ ፡ ይስ
ጠኝ ፡ ይውደደኝ ፡ ብለህ ፡ ሳትሠራ ፡ ወዶ ፡ መስ
ጠትን ፡ ጠልቶ ፡ መጉዳትን ፡ ለጌታህ ፡ ካደረግኸ
ው ፡ ሃይማኖት ፡ ያጐድልብሃልና ፡ ለሥጋዊ ፡ ጌታ ፡



የምትሠራውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ለሱ ፡ መታየት ፡
ብለህ ፡ ሳትሠራ ፡ እሱን ፡ እንደምስለኔ ፡ እግዚአብ
ሔርን ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ አድርገህ ፡ እያመንክ ፡ የጌታ
ህን ፡ ማየትና ፡ አለማየት ፡ ሳትሻ ፡ ለበላይህ ፡ የም
ታደርገውን ፡ በኃኔት ፡ ለፈጣሪህ ፡ እየገለጥህ ፡
ስትሠራው ፡ ከፍጹማን ፡ ሃይማኖት ፡ ይቈጠርልሃል ።
እንደ ፡ ሴት ፡ እየተለማመጥክ ፡ እንደ ፡ ዘፋኝ ፡
እያሣሣቅህ ፡ እንደ ፡ ለማኝ ፡ እያመሰገንክ ፡
እንደ ፡ ልጅ ፡ የማባባያ ፡ ሥራ ፡ እያሳየህ ፡ ብታ
ገለግል ፡ ግን ፡ ጌታህን ፡ ማታለል ፡ ፈጣሪህን ፡
መበደል ፡ ሃይማኖትህን ፡ ማጉደል ፡ ይሆንብሃል ።
ሁለተኛም ፡ ለወዳጅና ፡ ለባልንጀራም ፡ በሚሠ
ራው ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ ካልተ
ሠራ ፡ ይውደደኝ ፡ ይጥቀመኝ ፡ ያመስግነኝ ፡
ብሎ ፡ የሚሠራ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ሃይማኖትን ፡ ያጐ
ድላልና ፡ ስለዚህ ፡ ለሰው ፡ የምታደርገው ፡ በጎ
ነት ፡ ሁሉ ፡ ምክንያቱ ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይሁን ።

ምዕራፍ ፡ ፳፰ ።

## ስላነጋገር ፡ ምክር ።

ጥያቄ ።

፻፷፩ ፡ ለሰው ፡ አፍ ፡ ከኮሶና ፡ ከነገር ፡ ማናቸው ፡
ይመራሉ ።

ምላሽ ።

፫፻፶፬ ፡ ሲገባ ፡ ኮሶ ፡ ይመራል ፤ ሲወጣ ፡ ግን ፡ ነገር ፡ ይመራል ።

ጥያቄ ።

፫፻፶፭ ፡ ከማርና ፡ ከዝምታ ፡ የማናቸው ፡ ጣዕም ፡ ይበልጣል ።

ምላሽ ።

፫፻፶፮ ፡ ማር ፡ ይከብዳል ፤ ሐሞት ፡ ይሆናል ።

ዝምታ ፡ ግን ፡ ጣዕሙም ፡ ከልብ ፡ ይደርሳል ፤ አእምሮንም ፡ ያጠራል ፤ ስለዚህ ፡ ከጣዕም ፡ ሁሉ ፡ ዝምታ ፡ ይበልጣል ።

ጥያቄ ።

፫፻፶፯ ፡ መናገርን ፡ እኔ ፡ ሳልወደው ፡ እንደበቴ ፡ በል ማዱ ፡ ብቻ ፡ እየተናገረ ፡ ሲያስቸግረኝ ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ ይሻለኛል ።

ምላሽ ።

፫፻፶፰ ፡ አንተ ፡ እየጠላኸው ፡ ሳታስበው ፡ እምትና ገረው ፡ ነገር ፡ የኔ ፡ ቃል ፡ ነው ፡ ብለህ ፡ አትድን ግጥ ፤ ሳታስበው ፡ ሳታውቅ ፡ እምትናገረው ፡ ሁሉ ፡ አፍህን ፡ እንደ ፡ ዋሻ ፡ አድርጎ ፡ ባንተ ፡ አፍ ፡ ሰይጣን ፡ መናገሩ ፡ ነውና ፡ ርጉም ፡ ሰይጣን ፡ እግዚአብሔር ፡ ከኔ ፡ ያርቅህ ፡ ያሳፍርህ ፡ ብለህ ፡



እማትበህ ፡ ተጻጽተህ ፡ ረድኤት ፡ ከእግዚአብ ሔር ፡ ለምን ።

ጥያቄ ።

፫፻፶፱ ፡ ሥጋ ፡ ያለነባቢት ፡ ነፍስ ፡ በሰይጣን ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ መናገር ፡ እንደ ፡ ምን ፡ አድርጎ ፡ ይቻለዋል ፤ ነፍስ ፡ ሳታውቅስ ፡ አፍ ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ መና ገር ፡ ይቻለዋል ።

ምላሽ ።

፫፻፷ ፡ የነፍሳችን ፡ ዕውቀት ፡ ሳይጨመርበት ፡ አፋችን ፡ ብቻውን ፡ ለመናገሩ ፡ ተኝተን ፡ በምን ቃዠው ፡ ሰክረን ፡ በምንናገረው ፡ ወዲያው ፡ ተና ግረን ፡ ወዲያው ፡ ረስተን ፡ በምንክደው ፡ አፋችን ፡ ብቻውን ፡ ተናጋሪ ፡ መሆኑን ፡ በዚህ ፡ እስተውል ። ሰይጣንም ፡ በሰው ፡ አፍ ፡ ለመናገሩ ፡ አንዳንዶ ቹን ፡ ሰዎች ፡ እነሱ ፡ ምንም ፡ ሳያውቁ ፡ ታመዋል ፡ አብደዋል ፡ እየተባለ ፡ ለዘወትር ፡ ባፋቸው ፡ ሰይ ጣን ፡ ብቻ ፡ ሰው ፡ ሲሰድብበት ፡ በመዋሉ ፡ እስ ተውል ። በብዙዎችም ፡ ሰዎች ፡ በዘንጉበት ፡ በዘ ኑበት ፡ በተቸሙበት ፡ በጠገቡበት ፡ ጊዜ ፡ ጠብቆ ፡ ዕውቀታቸው ፡ ያልመዘነውን ፡ ልባቸው ፡ ያላሰ በውን ፡ በድንገት ፡ አደጋ ፡ ሰይጣን ፡ ባፋቸው ፡ ተገብቶ ፡ እየተናገረ ፡ በንዴት ፡ በጸጸት ፡ እየጐዳ ፡ ያጠፋቸዋል ።

ይህን ፡ ልትረዳ ፡ ብትሻ ፡ እንኳን ፡ ከኀንዘቦቹ ፡ ከሰብአ ፡ ዓለም ፡ ከመናንያንም ፡ ቢሆን ፡ በዘንጉበት ፡ ጊዜ ፡ እያደባ ፡ ባፋቸው ፡ እያደረ ፡ ሰውን ፡ እስከ ፡ መዝለፍ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እስከ ፡ መንቀፍ ፡ መናገሩን ፡ ልብህ ፡ ሳያውቀው ፡ ሰይጣን ፡ በተናገረው ፡ እሱን ፡ መርገም ፡ አንተ ፡ ቃልህ ፡ ላለመሆኑ ፡ መመስከር ፡ የሚገባህ ፡ ለመሆኑ ፡ አረጋዊ ፡ መንፈሳዊ ፡ ተመልከት ፡ (መልእክት ፡ ፳፰) ።

ጥያቄ ።

፫፻፶፱ ፡ በመናገር ፡ ከሚሠራው ፡ ጽድቅና ፡ በዝምታ ፡ ከሚሠራው ፡ ጽድቅሳ ፡ ማናቸው ፡ ይበልጣል ።

ምላሽ ።

፫፻፶፱ ፡ ኀጢአት ፡ ሁሉ ፡ ይሰረያል ፡ ስድብ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ስርየት ፡ የለውም ፡ በማለቱ ፡ በመናገር ፡ የሚሠራ ፡ ኀጢአት ፡ መብለጡን ፡ ጌታ ፡ በወንጌል ፡ እንዳስረዳን ፡ ከልቡ ፡ አውጥቶ ፡ ከተናገረ ፡ የመናገር ፡ ኀጢአት ፡ ይበልጣል ።

በሌላው ፡ አካል ፡ የምንሠራው ፡ ለሥጋችን ፡ ደላን ፡ ነው ፡ ባፋችን ፡ የምንሠራው ፡ ኀጢአት ፡ ግን ፡ ለሥጋችን ፡ እንኳን ፡ የሚሆን ፡ አንድ ፡ ጥቅም ፡ ሳይኖርበት ፡ የሰይጣንን ፡ ፈቃድ ፡ ብቻ ፡ ለመፈጸም ፡ ብለን ፡ ሳይቸግረን ፡ የምንሠራው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ከኀጢአት ፡ ሁሉ ፡ በስድብ ፡ በሐሜት ፡ የምንሠራው ፡ እግዚአብሔርን ፡ አጥብቆ ፡ ያሳዝነዋል ።



ስለዚህ ፡ ባንደበት ፡ የሚሠራው ፡ ኀጢአት ፡ ሁለት ፡ እጅ ፡ ጽድቁ ፡ አንድ ፡ እጅ ፡ ይሆናል ።

ጥያቄ ።

፫፻፷ ፡ ምነው ፡ ነቢያት ፡ ሐዋርያት ፡ በትምርት ፡ መኳንንት ፡ ነገሥታት ፡ በፍርድ ፡ መዘምራን ፡ ካህናት ፡ በምስጋና ፡ የጸደቁበት ፡ በመናገራቸው ፡ አይደለምን ።

ምላሽ ።

፫፻፷ ፡ እነዚህ ፡ ባንደበታቸው ፡ አምላካቸው ፡ ይናገርበት ፡ ነበርና ፡ የነሱ ፡ አንደበት ፡ ስላልሆነ ፡ ነው ፡ የተጠቀሙበት ።

ባንደበት ፡ በጎነት ፡ ሢሶ ፡ የሚሆን ፡ አለው ፡ ያልኩህ ፡ እንደዚህ ፡ ያሉት ፡ የተናገሩትን ፡ ገምቼ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሢሶ ፡ አለው ፡ ያልኩህ ፡ ሌላማ ፡ ባፍ ፡ የሚሠራ ፡ ምንም ፡ ጥቅም ፡ የለ ።

ጥያቄ ።

፫፻፷፩ ፡ የሚያጸድቀው ፡ ሢሶው ፡ ያንደበት ፡ ጽድቅ ፡ ምን ፡ ምን ፡ ነው ።

ምላሽ ።

፻፶፯ ፡ ፍርድ ፡ ያውም ፡ እውነት ፡ ቢሆን ፡ ምክር ፡ ያውም ፡ ተንኰል ፡ ባይኖርበት ።

ትምርት ፡ ያውም ፡ ጸብና ፡ ክርክር ፡ ባይኖርበት ። የዘማና ፡ የጸሎት ፡ አገልግሎት ፡ ያውም ፡ ልቡ ናው ፡ መሰብሰብ ፡ ቢኖርበት ።

በጎ ፡ ጠባይ ፡ ሲኖረን ፡ ባንደበታችን ፡ እምንሠ ራው ፡ ይህ ፡ አራቱን ፡ ፀይነት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ሁለት ፡ እጅ ፡ የሚሆነው ፡ ያንደበታችን ፡ ኀጢ አት ፡ ግን ፡ ሐሰት ፡ ሐሜት ፡ ዕርፈት ፡ ሙግት ፡ ቧልት ፡ የዘፈን ፡ ጨዋታ ፡ የስንፍና ፡ ተረት ፡ የክ ርክር ፡ ድፍረት ፡ ይኸን ፡ ስምንቱን ፡ ኀጢአት ፡ እንሠራበታለንና ፡ ስለዚህ ፡ መጻሕፍተ ፡ ጥበብ ፡ ዝምታ ፡ ወርቅ ፡ ነው ፡ መናገር ፡ ብር ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ የጥቅማቸውን ፡ መበላለጥ ፡ ነግረውናልና ፡ ፈርዶ ፡ አስተምሮ ፡ ሰው ፡ ከመጥቀም ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ራስን ፡ መጥቀምም ፡ መብለጡን ፡ ማር ፡ ይሥሐቅ ፡ አስ ረድቶናልና ፤ በግድ ፡ የሚያናግርህ ፡ የዳኘነት ፡ በውድ ፡ የሚያናግርህ ፡ ተቸጋሪው ፡ የሚጠይቅህ ፡ ሆኖ ፡ ባትመልስለት ፡ በነፍሱ ፡ የሚጐዳብህ ፡ የበጎ ፡ ምክር ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ እንኳን ፡ ሰው ፡ ከሚያስከፋ ፡ ቃልና ፡ ከሚያምር ፡ ከሚያሥቅም ፡ ቃል ፡ ዝም ፡ እንበል ።



ጥያቄ ።

፻፶፰ ፡ ዝምታ ፡ ለመናንያን ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖር ፡ ሰው ፡ ዝም ፡ ቢል ፡ ያስጠቃው ፡ ያስጐዳው ፡ የለምን ፤ ከንተረቱም ፤

ገልጠው ፡ ካልነገሩት ፡ የሆድን ፡ ብልኀት ፡ ያለም ፡ ሙት ፡ ያደርጋል ፡ ዝምታ ፡ ማብዛት ፡ ይባላል ፤ ዓለማዊ ፡ ዝምታ ፡ ሲያበዛ ፡ ጉዳት ፡ ይበዛበት ፡ የለምን ።

ምላሽ ።

፻፶፱ ፡ ለጊዜው ፡ ተናጋሪ ፡ የተጠቀመ ፡ ዝምተኛ ፡ የተጠቃ ፡ ይመስላል ፡ እንጂ ፡ በማስከበሩ ፡ በማስ ወደዱ ፡ ለሥራ ፡ በማትጋቱ ፡ ለንብረት ፡ በመጥ ቀሙ ፡ አጥብቆ ፡ በልጦ ፡ ለዚህ ፡ ዓለምም ፡ ኑሮ ፡ ቢሆን ፡ የሚጠቅመው ፡ ዝምታ ፡ ነው ።

ጥያቄ ።

፻፷ ፡ ካልተናገረ ፡ አይታይ ፡ ብልኀቱ ፡ ካልታረደ ፡ አይታይ ፡ ሥባቱ ፡

እንደሚባለው ፡ ሁሉ ፡ ዝም ፡ ካለ ፡ ምን ፡ ታውቆ ፡ መውደድስ ፡ ማክበርስ ፡ መጠቀምስ ፡ ይገኛልን ።

ተመስግኖ ፡ ተደንቆ ፡ እንዲያገኝ ፡ አነጋገሩን ፡ አሳምሮ ፡ እንዳይጠቃ ፡ ተከራክሮ ፡ ካላጠራቀመ ፡ ንብረቱስ ፡ እንዴት ፡ ይሞላለታል ።

## ምላሽ ።

፫፻፳፩ ፡ ለመታወቁም ፡ በገዛ ፡ አፉ ፡ እያወራ ፡ የው
ስጡን ፡ ጥበብ ፡ ባፉ ፡ ብቻ ፡ እያወጣ ፡ ከማፍሰስ ፡
ባፉ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ በሚሠራው ፡ አካሉ ፡ እየሠራ ፡
በሚመዝነው ፡ አእምሮው ፡ እየመረጠ ፡ ሥራውን፡
ሲያሳይ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሚወደደውና ፡ የሚከበ
ረው ፡ የሚጠቀመው ፤ ባፍ ፡ ብቻ ፡ ነገር ፡ እየመ
ረጡስ ፡ መናገር ፡ አዋራጅ ፡ እንጂ ፡ አስከባሪ ፡
አለመሆኑን ፡ የሚቀኙትን ፡ ደብተሮች ፡ የሚገጥ
ሙትን ፡ አዝማሪዎች ፡ የሚከራከሩትን ፡ ተሟጋ
ቾች ፡ ማዕርጋቸው ፡ አስከባሪ ፡ ንብረታቸው ፡ አ
ግሪ ፡ አለመሆኑን ፡ ተናጋሪም ፡ ሰው ፡ ንግግሩን ፡
ብቻ ፡ ያቃናል ፡ እንጂ ፡ ንብረቱን ፡ ማቃናት ፡
እማይችል ፡ ለመሆኑ ፡ ልበ ፡ አምላክም ፡ ዳዊት ፡
ብእሲ ፡ ነባቢ ፡ ኢያረትዕ ፡ በዲበ ፡ ምድር ፡ ያለውን ፡
አስተውል ። ለንብረትም ፡ መጠራቀም ፡ ንግግር ፡
ዐውቆ ፡ ከሚራቀቅ ፡ መምህር ፡ ደንብ ፡ ዐውቆ ፡
ከሚበይን ፡ ወንበር ፡ የትዳራቸውን ፡ ሥራ ፡ ብቻ ፡
ዐውቀው ፡ አፍ ፡ ሳያበዙ ፡ የሚሠሩት ፡ የነጋዴና ፡
የባላገር ፡ ትዳር ፡ እንዲበልጣቸው ፡ አስተውል ።

፫፻፳፪ ፡ ምሳሌ ፤ ብልኆች ፡ ሠራተኞች ፡ ረቂቆች ፡
ውሃን ፡ እሳትን ፡ ነፋስን ፡ እንዳይወጡ ፡ በብረት ፡
ዘግተው ፡ ሲይዟቸው፡ ባቡር፡ ተብለው ፡ ይበራሉ ፡
መርከብ ፡ ሁነው ፡ ይዋኛሉ ።



መኪና ፡ ተብለው ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ይሠራሉ ።
ከሰውም ፡ በልጠው ፡ በሰማይ ፡ ይሄዳሉ ።
እንዲህ ፡ ሁነው ፡ መሥራታቸው ፡ እራቱን ፡ ባሕር
ያት ፡ ዘግተው ፡ ቢይዟቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ቢከ
ፈቱ ፡ ግን ፡ በድምፃቸው ፡ ብቻ ፡ እየጮኹ ፡
ይቆማሉ ። እንደዚሁም ፡ ሁሉ ፡ የኛም ፡ ተፈጥሮ ፡
ከነፋስ ፡ ከውሃ ፡ ከእሳት ፡ ከመሬት ፡ ነውና ፡
በግዙፉ ፡ በመሬት ፡ ከንፈራችን ፡ ሦስቱን ፡ ረቂ
ቃን ፡ ባሕርዮቻችንን ፡ ዘግተን ፡ የያዝናቸው ፡
እንደ ፡ ሆን ፡ ወደ ፡ ሰማያዊ ፡ ዕውቀት ፡ ያበሩናል ።
ከስንፍናም ፡ ባሕር ፡ አስዋኝተው ፡ ያወጡናል ።
ለሥራም ፡ ያተጉናል ።

ከፍተን ፡ አለልክ ፡ የለቀቅናቸው ፡ እንደ ፡ ሆን ፡
ግን ፡ ካፋችን ፡ ብቻ ፡ ላይ ፡ ፈሰው ፡ ከንቱ ፡ ሁነው፡
ይቀሩብናልና ፤ ስለዚህ ፡ በዚህ ፡ ዓለምም ፡ ኑሮ ፡
ቢሆን ፡ የነገር ፡ አራቃቂዎች ፡ ይደኸዩበታል ። የ
ሥራ፡ አራቃቂዎች፡ ይከብሩበታልና፤ ዝም፡ እንበል።

ይህንም ፡ በሰዎች ፡ አኗኗር ፡ መርምረህ ፡ ልትረዳ ፡
ብትሻ ፡ የእንግሊዞችን ፡ የሌሎችንም ፡ የሳክሶን ፡
ዘሮች ፡ የቃላቸውን ፡ ማጠር ፡ የንብረታቸውን ፡
መርዘም ፡ የጣሊያኖችንና ፡ የባልካኖችን ፡ የቃላ
ቸውን ፡ መርዘም ፡ የንብረታቸውን ፡ ማጠር ።
የቀሩትንም ፡ አውሮፖች ፡ ሁሉ ፡ እንደያገራቸው ፡
ከፍታ ፡ አፋቸው ፡ እየጠበበ ፡ አእምሯቸው ፡
እየሰፋ ፡ ይታያልና ፡ እየሄድክ ፡ ስትመረምረው ፡

ያስረዳሃል ። ከኛው ፡ አገር ፡ ብቻ ፡ ብትመረምር ፡ የደገኞችን ፡ መርጋት ፡ ከብረት ፡ የቄለኞችን ፡ አፍ ፡ ማብዛት ፡ መጊሕፍት ፡ ታያለህ ።

ባሕርያችን ፡ እንደዚህ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እንደ ፡ መና ገሩ ፡ ብዛት ፡ የውስጡ ፡ ጉልበታችን ፡ ከፋችን ፡ ላይ ፡ እየፈሰሰ ፡ ከሥራ ፡ ያሰንፈናልና ፡ ዝም ፡ እንበል ፤ ከማደኽየቱና ፡ ከማስንፋም ፡ አልፎ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ኑሮ ፡ በመናገራችን ፡ ከመሳደብ ፡ ከመሸማገት ፡ አድርሶ ፡ ከካሳ ፡ ከቅጣት ፡ እያደረሰ ፡ አካላችንን ፡ ከመገረፍ ፡ ገንዘባችንን ፡ ከመዘረፍ ፡ ያደርሰናልና ፤ ዝም ፡ እንበል ።

በጨዋታም ፡ ጊዜ ፡ መናገራችን ፡ ከመተፋፈር ፡ ከመቃለድ ፡ ከመቃለል ፡ ከማበድ ፡ ከመዝፈን ፡ ያደርሰናልና ፡ ዝም ፡ እንበል ።

በክርክር ፡ ጊዜ ፡ ከመተፋፈር ፡ ከመማረር ፡ ከመ ኳረፍ ፡ ያደርሰናልና ፤ ዝም ፡ እንበል ።

ጥያቄ ።

፻፺፫ ፤ ሰው ፡ የታደለው ፡ ጣዕመ ፡ ቃል ፡ መናገር ፡ ይሆንና ፡ ግድ ፡ የሚያናግረው ፡ ሲሆን ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ ይሻለዋል ።

ምላሽ ።

፻፺፬ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንጋገር ፡ በዋቂንት ፡ በሰ ጠህ ፡ ጊዜ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወይም ፡ ለሰው ፡ ጥ



ቅም ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ያኸል ፡ በጥቂቱ ፡ ተና ገር ፡ እንጂ ፡ ካማረብኝ ፡ ብለህ ፡ እንጋገርህን ፡ ከረርኸው ፡ ያስረዘምኸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መጥፊያ ፡ ይሆንሃል ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ እንጋገሩ ፡ ቢያምር ፡ አክሮ ፡ አስረዝሞ ፡ የሚናገር ፡ ሳይጕዳ ፡ ወይም ፡ ሳይቀሠፍ ፡ ወይም ፡ ሳይዋረድ ፡ አይቀርምና ፡ እን ኳን ፡ ክፋውን ፡ መልካምም ፡ ቢሆን ፡ ትልቅ ፡ ነገር ፡ መናገር ፡ አትውደድ ።

መጽሐፍ ።

ወኢይፃእ ፡ ዐቢይ ፡ ነገር ፡ እምአፋክሙ ።

የአበው ፡ ቃል ።

ፈትል ፡ ቢያከሩት ፡ ይበጠሳል ፤ ነገር ፡ ቢያከሩት ፡ ይበጥሳል ።

ካንጋገር ፡ ይፈረዳል ፡ ካያያዝ ፡ ይቀደዳል ፡ ይባላል ።

፻፺፭ ፤ ለጥቅም ፡ የሚሆን ፡ ነገር ፡ በምትናገረው ፡ ጊዜ ፡ ፍሬ ፡ ያላት ፡ አጭር ፡ ቃል ፡ ተናገር ፡ እንጂ ፡ ፍሬ ፡ ከሆን ፡ ብለህ ፡ ዘሩን ፡ አታብዛው ።

፻፺፮ ፤ እኽል ፡ የሚዘራ ፡ አብዝቶ ፡ የዘራው ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ በፍሬ ፡ ላይ ፡ ፍሬ ፡ እየጨመረ ፡ ስላንባበረ በት ፡ ፍሬው ፡ የሚበቅልበት ፡ ምድር ፡ ያጣና ፡ ተረኽቶ ፡ ፍሬው ፡ ሁሉም ፡ ገለባ ፡ ብቻ ፡ ይሆናል። እንደዚሁ ፡ ብዙ ፡ የሚናገርም ፡ ሰው ፡ መልካም ፡

ቃል ፡ ቢሆን ፡ መልስ ፡ መልሶ ፡ በመናገር ፡ ካስረዘመው ፡ የሚዘራው ፡ ቃል ፡ በመነባበሩ ፡ ይጠፋል ። የአበው ፡ ምክር ። ብዙ ፡ ቢተቹ ፡ ይስለቹ ፤ ብዙ ፡ ቢያወጉ ፡ ይዘነጉ ።

መጽሐፍ ።

ግብር ፡ ዘአልቦ ፡ ምጣኔ ፡ ገዓር ፡ ውእቱ ፤ ወለገዓርኒ ፡ ይትልዎ ፡ ዝንጋዔ ።

፫፻፳፯ ፤ ከሰውም ፡ ጋራ ፡ በሸንጎም ፡ በማእድም ፡ በሌላም ፡ ቦታ ፡ ሁሉ ፡ ተቀምጠህ ፡ በምትጫወትበት ፡ ጊዜ ፡ እንጋገሩን ፡ እያስረገጥህ ፡ ያለጩኸት ፡ ቀስ ፡ ብለህ ፡ ለጠየቁህ ፡ አጭር ፡ ቃል ፡ እየመለስህ ፡ የምትጠይቀውንም ፡ እያለዘብህ ፡ ተጫወት ፡ እንጂ ፤ እንደ ፡ ተሓጋች ፡ እያደመቅህ ፡ እንደ ፡ ወንበር ፡ በተራ ፡ እየደረደርህ ፡ እንደ ፡ አዝማሪ ፡ እየገጠምክ ፡ እንደ ፡ ደብተራ ፡ እየተረብህ ፡ እንደ ፡ ነፍጠኛ ፡ እየቀለድህ ፡ ያምራል ፡ ብለህ ፡ በነዚህ ፡ እንጋገር ፡ አትናገር ።

የአበው ፡ ምክር ።

እንጋገር ፡ ቢያምር ፡ አሓሓት ፡ ይከፋል ።

መጽሐፍ ።

አቤ ፡ አፀቅብ ፡ አፉየ ፡ ከመ ፡ ኢይስሐት ፡ በልሳንየ ፡ ይላል ።



፫፻፳፰ ፤ ውሌ ፡ ይዞልኛል ፡ ዳኛ ፡ ወዶልኛል ፡ ሾቆልኛል ፡ ብለህ ፡ ንግግርህ ፡ በተደመጠልህ ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ አፍ ፡ ሙሉ ፡ የሚያናግር ፡ የተመገር ፡ እንጂ ፡ ውል ፡ ብትይዝ ፡ አለስልሰህ ፡ አሳዝነህ ፡ ተናብለህ ፡ እውነቱንም ፡ ቃል ፡ ቢሆን ፡ በከራራና ፡ በሻካራ ፡ ንግግር ፡ አትናገር ፤ ይልቁንም ፡ በጕልምስናህ ፡ በጌትነትህ ፡ በባለሓልነትህ ፡ ወራት ፡ በውነትም ፡ እንጋገር ፡ ቢሆን ፡ ቃልህን ፡ ካላላጠርከው ፡ ካላለዘብከው ፡ ለመጕጃህ ፡ ይሆናል ። የፈላስፋው ፡ ቃል ። ነገሬን ፡ ሁሉ ፡ ከተናገርኩ ፡ በኋላ ፡ ያን ፡ ቃሌን ፡ እስተውዬ ፡ ስመረምረው ፡ ምንም ፡ ቢያምር ፡ ከውስጡ ፡ ከተናገርኩት ፡ ላይ ፡ እሚያስጠጥት ፡ ነገር ፡ አጥቼበት ፡ አላውቅም ፡ ከዝምታዬ ፡ ግን ፡ እንድም ፡ ቀን ፡ አልተጸጸትኩም ፡ እንዳለው ፡ አርሳንዮስ ፡ ስንክሳር ፡ መናገር ፡ የጦት ፡ ዝምታ ፡ የከብረት ፡ መገኛ ፡ መሆን ፡ በርግጥ ፡ የሚታመን ፡ ነውና ፡ እስከሚቻልህ ፡ ወደ ፡ ዝምታህ ፡ ጠባይ ፡ አድላ ።

፫፻፳፱ ፤ ጌታህም ፡ አሜዋች ፡ እንጋጋሪ ፡ ሲያደርግህ ፡ ለጠየቀህ ፡ እየመለስክ ፡ ያልጠየቀህን ፡ ከመናገር ፡ ዝም ፡ በል ፡ እንጂ ፡ ከግብር ፡ ካጀብ ፡ ካደባባይ ፡ በግድ ፡ እሚያናግርህ ፡ ጕዳይ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ባለሓልነቱን ፡ ሰው ፡ ይይልኝ ፡ ስትል ፡ እየፈ

ለግህ ፡ እያነጋገርከ ፡ ሌላውን ፡ ባለጕዳይ ፡ እታና ፍገው ፡ አታስቀናው ።

ባለሻል ፡ በመባልም ፡ እጠቀማለሁ ፡ ብለህ ፡ በማ መንህም ፡ ሃይማኖትህን ፡ ማጕደሉን ፡ ወንድምህ ም ፡ በትናት ፡ መጐዳቱን ፡ ያንተን ፡ ባለሻልነት ፡ ለማሳየት ፡ ስትል ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ የሚነጋገርበትን ፡ ጊዜ ፡ ስትወስድበት ፡ መረገምህን ፡ አትርሳው ።

የአበው ፡ ምክር ።

ጨማ ፡ አለኝ ፡ ብለህ ፡ እሾህ ፡ አትርገጥ ።
አፍ ፡ አለኝ ፡ ብለህ ፡ በሰው ፡ አታላግጥ ።

መጽሐፍ ።

እስመ ፡ እምቃልከ ፡ ትጸድቅ ፡ ወእምቃልከ ፡ ትት ኴነን ።

፫፻፸ ፡ ያንደበትክን ፡ መስላት ፡ የቃልህን ፡ መቃናት ፡ ሰው ፡ ይወቅልኝም ፡ ብለህ ፡ አትጣር ።

እኪሌ ፡ ንግግር ፡ ያውቃል ፡ ተብሎ ፡ መመረጥ ፡ ት ርፉ ፡ ከማይችሉት ፡ ኀጢአት ፡ ጋራ ፡ ያታግላል ፡ እንጂ ፡ በቃል ፡ ዕውቀት ፡ የተመረጠ ፡ ሰው ፡ ጥቅ ም ፡ የለውም ።

ጌታም ፡ ላማካሪነት ፡ ቢመርጠው ፡ ምክሩን ፡ እንቢ ፡ ብሎት ፡ ጌታው ፡ ባጠፋ ፡ እሱ ፡ ይረገ ማል ። ጌታው ፡ በሻረ ፡ እሱ ፡ እየተጠላ ፡ ተፈትሎ ፡



የማያልቀውን ፡ ተለብሶ ፡ የማይቈየውን ፡ የዓለም ፡ ድር ፡ ሲያጠነጥን ፡ ወይ ፡ በጥሳው ፡ ወይም ፡ በጥ ሶት ፡ ካላሰበው ፡ ቦታ ፡ ይወድቃል ። በሰጪና ፡ በተ ንዘብ ፡ አስቈንጣሪ ፡ ሲሆን ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ እው ራር ፡ አንዱን ፡ አመስግኖ ፡ አንዱን ፡ በግድ ፡ የሚነ ቅፍበት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እንደ ፡ ቤት ፡ ክዳን ፡ ለጂሚው ፡ ጌታ ፡ ልብሱ ፡ ሆኖ ፡ በሰው ፡ እንባ ፡ ይበሰብሳል ፡ ሽቅብ ፡ የሚመክር ፡ እንትቱ ፡ ይዝላል ፡ መካሪ ፡ የሌ ለው ፡ በላዩን ፡ ይመክራል ፡ የተባለው ፡ ይደርስበታል ። ለወንበርነትም ፡ ብትመረጥ ፡ ሐሰትና ፡ ቀጣ ፡ ማድ ላትና ፡ የኀጢአት ፡ ገንዘብ ፡ መብላት ፡ ይታገሉ ሃል ፤ እነሱ ፡ አራት ፡ አንተ ፡ አንድ ፡ በመሆንህ ፡ በትግላችው ፡ ጥለው ፡ ወደ ፡ ገሃነም ፡ ጕድጓድ ፡ ያገቡሃል ።

የአበው ፡ ቃል ።

ሰውን ፡ ሰው ፡ መዳኘት ፡ በሰማው ፡ ብቻ ፡ መቶች፤ ያላየውን ፡ ባፍ ፡ መሥራት ፤ ካልሰማው ፡ ጕድ ጓድ ፡ መግባት ፤ ወየው ፡ ለዚህ ፡ ሰው ፡ እሻሻት ፡ ይባላል ።

ጠበቃንትም ፡ ብትመርጥ ፡ ሽፍጥ ፡ ድፍረት ፡ ቅሌ ት ፡ እብለት ፡ ይታገሉሃልና ፡ በግድ ፡ ወደ ፡ ዘለ ዓለም ፡ መከራ ፡ ትወድቃለህ ፡ እንጂ ፡ በነገር ፡ ዐዋቂነት ፡ ከጕዳት ፡ በቀር ፡ ጥቅም ፡ አይገኝለ ትም ።

የአበው ፡ ቃል ።

ቅሌት ፡ ከሌላው ፡ ጥቂት ፡ ያንሳል ፤ ከጠበቃ ፡ ይብ ሳል ።

የሚብሰውም ፡ ቅሌት ፡ አፍ ፡ ሽጦ ፡ ለአፍ ፡ ማብ ላት ፡ ይባላል ።

ጥያቄ ።

፫፻፸፩ ፤ ሰው ፡ በሁሉ ፡ ነገር ፡ ዝም ፡ ካለ ፡ ጥቂት ፡ ሰንፎጥ ፡ ካለለ ፡ እጅግ ፡ ይናቅና ፡ ይጠቃ ፡ የለምን ።

ምላሽ ።

፫፻፸፪ ፤ በመቈጣቴ ፡ እፈራለሁ ፡ የሚመስለው ፡ ሰው ልቡ ፡ ሰነፍ ፡ ጕልበቱ ፡ ደካማ ፡ ቢሆን ፡ ነው ፤ በሚ ያስቈጣም፡ ነገር፡ ቢሆን፡ ከመቈጣት፡ዝም፡እንበል።

ጥያቄ ።

፫፻፸፫ ፤ ሰነፍ ፡ ይፈራል ፡ እንጂ ፡ መቼ ፡ ይቈጣል ። ሰው ፡ እየበደሉ ፡ እየገደሉ ፡ የሚያስቸግሩትስ፡ ቍ ጡዎች ፡ ተሳዳቢዎቹ ፡ አይደሉምን ።

ባይሆን ፡ እብዶች ፡ ይባላሉ ፡ እንጂ ፡ ቍጡ ፡ ሰዎች፡ ደካማ ፡ ለማለትማ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ይገባሉ ።

ምላሽ ።

፫፻፸፬ ፡ ሰው ፡ ሌላው ፡ አካሉ ፡ ሥራ ፡ ሲያቅተው ፡ ኃይ ሉን ፡ ከምላሱ ፡ ላይ፡ ብቻ ፡ ያደርግና፡ በዚሁ ፡ እፈራ



ለሁ ፡ ኃይለኛም ፡ እባላለሁ ፡ ይመስለዋል ፡ እንጂ ፡ መሳደብ ፡ መበሳጨት ፡ የደካማ ፡ ባሕርይ ፡ መሆ ኑን ፡ እስቀድመህ ፡ መሚሪያቸው ፡ ያልደረሰላቸው ፡ ሕፃናት ፡ ልቅሶና ፡ ብስጭት ፡ እንዲበዛባቸው ፡ አስ ተውል ።

ሁለተኛ ፤ ስድብና ፡ ቍጣ ፡ ኃይል ፡ ባነሳቸው ፡ ሴ ቶች ፡ አፍ ፡ ላይ ፡ መብዛቱን ፡ ሊመቱት ፡ በማይች ሉት ፡ ወንድ ፡ ላይ ፡ የሚናገሩትን ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ አስተውል ።

ሦስተኛ ፤ ይሠሩበት ፡ እጅና ፡ እግር ፡ ባጡት ፡ ሐ ሚናና ፡ ላሊበላ ፡ የሚባሉት ፡ ደካሞች ፡ እርስ ፡ በ ርሳቸው ፡ እሚሰዳደቡት ፡ አልጠቅማቸው ፡ እያለ ፡ በየደጁ ፡ እየቆሙ ፡ በያገሩ ፡ እየዞሩ ፡ መሳደባቸ ውን ፡ አስተውል ።

አራተኛ ፤ ከጌቶች ፡ ወታደሮች ፡ ከቄሶች ፡ ደብተ ሮች ፡ በማዕርጋቸው ፡ ያነሱ ፡ ሲሆን ፡ በቍጣና ፡ በስድብ ፡ የነሱ ፡ አፍ ፡ የበለጠ ፡ መሆኑን ፡ አስ ተውል ።

አምስተኛ ፤ ሰው ፡ ሲሠራበት ፡ የነበረው ፡ አካሉ ፡ ሲከበርበት ፡ የነበረው ፡ ንብረቱ ፡ ሲጕድል ፡ ከጤ ነኞች ፡ የበሽተኞች ፡ ከባለጸጎች ፡ የድኆች ፡ ቍ ጣ ፡ ብስጭት ፡ በመብዛቱ ፤ ስድብ ፡ ቍጣ ፡ የደ ካም ፡ ሥራ ፡ መሆኑን ፡ በዚህ ፡ አስተውል ።

## ጥያቄ ።

፫፻፸፫ ፡ እጅ ፡ ሆኖ ፡ እማይቃጣ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ የማይቈጣ ፡ አይገኝምና ፡ የእጅና ፡ የእግር ፡ ቍጣ ፡ ሲሆን ፡ የራቀም ፡ ያመልጠዋል ፤ ገላጋይም ፡ ያስቀረዋል ፡ የአፍ ፡ ቍጣ ፡ ሲሆን ፡ ግን ፡ ልብ ፡ እየጠላው ፡ ምላስ ፡ እየተናገረው ፡ ያስቸግራልና ፡ ስለዚህ ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ ይሻላል ።

## ምላሽ ።

፫፻፸፬ ፡ ልብህ ፡ እየጠላው ፡ ምላስህ ፡ የሚናገረው ፡ ስድብና ፡ ቍጣ ፡ ሲያገኝህ ፡ አንተን ፡ እንደ ፡ ጣዖት ፡ ማደሪያ ፡ አድርጎ ፡ በቃልህ ፡ የሚናገርብህ ፡ ሰይጣን ፡ መሆኑን ፡ ዕወቅና ፡ ከዚህ ፡ ደዌ ፡ እስክትድን ፡ ድረስ ፡ ባቍጣሮህ ፡ ጊዜ ፡ ሚም ፡ እግዚአ ፡ ዐቃቤ ፡ ለአፉየ ፡ እያልክ ፡ ፶፩ ፡ ፶፩ ፡ ጊዜ ፡ ከየንግሁ ፡ ቍጣሮህ ፡ ጋራ ፡ አድርስ ።

በልቡናህ ፡ ከፈጣሪህ ፡ ረድኤት ፡ ለምን ።

፪ኛ ፡ ቃልህን ፡ በከንፈርህ ፡ ለመያዝ ፡ ሲያቅትህ ፡ ምላስህን ፡ በጥርስህ ፡ ከንፈርህን ፡ በሽማህ ፡ ያዘው ፤ ይህም ፡ ቢያቅትህ ፡ እጅህን ፡ በእጅህ ፡ መያዝ ፡ አያቅትምና ፡ ምንም ፡ ቢቸግርህ ፡ ስድብና ፡ ቍጣህን ፡ መንቀፍን ፡ ነገር ፡ ማብዛትን ፡ ከወረቀት ፡ ላይ ፡ አትጻፈው ።

ቍጣውና ፡ ስድቡን ፡ እንዳይረሳለት ፡ የሚጽፍ ፡ ሰው ፡ የሰይጣን ፡ ጸሓፊ ፡ ትእዛዝ ፡ ሆኖ ፡ ራሱንና ፡



ልጁን ፡ ይጐዳል ፤ የቃል ፡ ብዛቱ ፡ ይሰለቻል ፡ እንጂ ፡ የሚጽፍለትን ፡ ጠላቱን ፡ አይጐዳውም ።

ባንደበት ፡ ብቻ ፡ ተመላልሶ ፡ ነገሩን ፡ የቀን ፡ ብዛት ፡ ያስረሳው ፡ የነበረው ፡ ቃል ፡ ተጽፎ ፡ ሲታተም ፡ ግን ፡ ራቁቱን ፡ በወረቀት ፡ ላይ ፡ ተገልብጦ ፡ ብልቱ ፡ ሁሉ ፡ የሚታይ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በሚያየው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ አነጋገሩን ፡ ሳይሰማ ፡ የጻፈውን ፡ ሰው ፡ አሳብ ፡ ሳያውቅ ፡ ያወቅሁ ፡ እየመሰለው ፡ የቃሉን ፡ መልክ ፡ ብቻ ፡ እያየ ፡ ይህን ፡ ይመስላል ፡ እያለ ፡ እንደያሳቡ ፡ እየተረጐመ ፡ ባለቤቱ ፡ ወዳላሰበው ፡ ክፉት ፡ እየዘረዘረ ፡ ሳለም ፡ ራሱን ፡ ሲሞትም ፡ ስሙን ፡ እስሮ ፡ የሚይዝ ፡ ወጥመድ ፡ የሚሆንበት ፡ የሚጽፈው ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ለሰው ፡ ወረቀት ፡ በምትጽፍበት ፡ ሰዓት ፡ ሰውነትህ ፡ ባልቸኰለበት ፡ በበረደበት ፡ ጊዜ ፡ ትልቁን ፡ ነገር ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ እያሳደርክ ፡ ትንሹን ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ሰዓት ፡ እያረምክ ፡ ጻፍ ፡ እንጂ ፡ በቍጣህ ፡ በችኰላህ ፡ ጊዜ ፡ አትጻፍ ።

ሰውም ፡ የሚያስቈጣ ፡ ቃል ፡ ልኮብህ ፡ በምትመልስበት ፡ ጊዜ ፡ ምላሹን ፡ አሳድረህ ፡ ሰውነትህን ፡ አብረድህ ፡ ተቈጥተህ ፡ ለመፈራት ፡ ይዘህ ፡ ለመቀጣት ፡ ካጠገብህ ፡ አለመኖሩን ፡ አስበህ ፡ የበላይም ፡ ቢሆን ፡ የአክብሮት ፡ የበታችህም ፡ ቢሆን ፡ አጭር ፡ የትዕግሥት ፡ ቃል ፡ ጻፍ ።

ሊታገሡት ፡ የማይቻል ፡ ክፉ ፡ ቃልም ፡ ቢመጣብህ ፡ ዐጥፎ ፡ ከኪሱ ፡ በሚያገባው ፡ ወረቀት ፡ ጠላትህን ፡ አትጐዳውምና ፡ ቅሌትና ፡ ንቀት ፡ ያልሆነ ፡ አጭር ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ መልስህ ፡ ዝም ፡ በል ።

እንኳን ፡ ለጠላትህ ፡ ለወዳጅህም ፡ ቢሆን ፡ የገንዘብ ፡ ድምሩ ፡ የቃል ፡ አጭሩ ፡ ነውና ፡ ለሰው ፡ ጉሮ ፡ እሚገባው ፡ አጭር ፡ ቃል ፡ ጻፍ ፡ እንጂ ፡ በምትጽፈው ፡ ወረቀት ፡ ሁሉ ፡ ዘር ፡ የበዛበት ፡ ፍሬው ፡ አይፋፋምና ፡ ስለዚህ ፡ ምንም ፡ ቢያምር ፡ የቃልህን ፡ ዘር ፡ አብዝተህ ፡ አክረህ ፡ ተቈጥተህ ፡ ሰው ፡ ንቅፈህ ፡ አትጻፈው ።

ጥያቄ ።

፫፻፸፯ ፡ ብዙ ፡ መናገርም ፡ ጠንቅቆ ፡ አለመጻፍም ፡ ጉዳት ፡ መሆኑን ፡ በሰማሁት ፡ ምርምር ፡ ተረዳሁት ፤ ከድንጋይ ፡ ቦታ ፡ የሚወርድ ፡ ውሃ ፡ ማንጐርጐሩ ፡ ከሰው ፡ ጋራ ፡ የሚኖርም ፡ ሰው ፡ መናገሩ ፡ በግድ ፡ ነው ፤ እሚሆንበት ፡ ከሰው ፡ ተለይቶ ፡ መኖር ፡ ያልቻለው ፡ ሰው ፡ እንደበቱን ፡ እንደ ፡ ምን ፡ አድርጎ ፡ ቢያኖረው ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ያለ ፡ አነጋገር ፡ ቢያስለምደው ፡ ይሻለው ፡ ይሆን ።

መልስ ።

፫፻፸፰ ፡ ግድ ፡ ለሆነብህ ፡ ነገር ፡ እንደበትህ ፡ መጠየቂያ ፡ እንዲሆንህ ፡ እንጂ ፡ መናገሪያ ፡ እንዳይሆንብህ፡



ድምፅህን ፡ በከንፈርህ ፡ መዝጊያ ፡ መግጠም ፡ ነው ።

ጥያቄ ።

፫፻፸፱ ፡ መናገርን ፡ በከንፈሬ ፡ ከዘጋሁት ፡ መጠየቅን ፡ በምን ፡ እናገረዋለሁ ፤ ጠይቅ ፡ እንጂ ፡ አትናገር ፡ የምትለኝ ፡ እንደምንድነው ።

መልስ ።

፫፻፹ ፡ ስትመከርም ፡ ስትሟወትም ፡ ሲጠይቁህም ፡ ስትመልስም ፡ ምንም ፡ መልካም፡ ቢመስልህ፡ ምንም ፡ የምታውቀው ፡ ነገር ፡ ቢሆን ፡ ይሆንብህ ፡ ይሆን ፡ ሆኖ ፡ ይሆን ፡ ይሆን ፡ ይሆን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እያልክ ፡ ያየኸውና ፡ የሰማኸውን ፡ ግድ ፡ ሆኖ ፡ የሚያናግርህ ፡ ጕዳይ ፡ ሲሆን ፡ አላሳሳትኩ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ እንደ ፡ መሰለኝ ፡ እያልክ ፡ እነዚህን ፡ ፬ቱን ፡ ቃሎች ፡ ለነገር ፡ መቋሚያ ፡ እንዲሆኑልህ ፡ እያደረግህ ፡ ሳትጠየቅበት ፡ እንደበትህ ፡ መናገሪያ ፡ መሆኑ ፡ እየቀረልህ ፡ መጠየቂያ ፡ ይሆንልሃል ። እንዲህ ፡ ባነጋገርህ ፡ ሁሉ ፡ ጠያቂ ፡ በመሆንህ ፡ ተጠያቂው ፡ የረባ ፡ ነገር ፡ ሲመልስልህ ፡ ዕውቀትን ፡ አግኝተህ ፡ የረባም ፡ ባይመልስልህ ፡ የትሕትናን ፡ ዋጋ ፡ አግኝተህ ፡ በሁቱም ፡ በኩል ፡ ይጠቅምሃል ። ሐሰትም ፡ የማትወድ ፡ እንኳን ፡ ብትሆን ፡ ይሆንብሃል ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ ጥንቂላ ፡ ሆኗል ፡ ማለትም ፡ ቢላት ፡ እንደ ፡ ሐሰተኛ ፡

ሆነም ፡ ነውም ፡ ማለት ፡ ሰው ፡ ደፋሪ ፡ በሰው ፡
መስካሪ ፡ ማስመሰሉን ፡ እያስቀረልህ ፡ በንግግር ፡
ሰውን ፡ ከማስቀየም ፡ በሰውም ፡ ከመቀየም ፡
ያድንሃል ።

የዚህን ፡ ጥቅም ፡ ለመረዳት ፡ የእንግሊዞችን ፡
ያነጋገር ፡ ልምድ ፡ ብታስተውል ፡ ያስረዳሃል ።

ተውኩ ፡ አትበል ፡ ያለግድ ፡ በቂም ፡ ሰው ፡ ነዶህ ፡
ተጐጂው ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ ተወዋ ፡ ሲልህ ፡
ስትነድ ፡ እፍክን ፡ ዝጋ ፡ እስኪበርድልህ ፡
ከስሎ ፡ እንዷን ፡ ልቡናህ ፡ እንዲተርፍልህ ፤

እፍም ፡ ሥራ ፡ ሲያጣ ፡ ጸሎት ፡ ሲያስታጕል ፡
ሰው ፡ ማጥፊያ ፡ ይመክራል ፡ እንደ ፡ አኪጦፌል ፤
እጅም ፡ ሥራ ፡ አጥቶ ፡ ከቤቱ ፡ ሲውል ፡
የሰው ፡ ነውር ፡ ይጽፋል ፡ እንደ ፡ ጋድራኤል ፤
ከነዚህ ፡ አጥፊዎች ፡ ማምለጥ ፡ እንድትችል ፡
ወዝክን ፡ በሥራ ፡ አውጣው ፡ ጸሎትም ፡ አክል ።

እምላክም ፡ የሚሾም ፡ ፍርድ ፡ የማያውቅን ፡
በሞኝ ፡ ሊቀጣ ፡ ነው ፡ በማይኩኑን ፤
ሞኝ ፡ መንቀፍ ፡ መጀል ፡ ነው ፡ አትንቀፍ ፡ ሞ
ኝን ፤
ይልቅ ፡ ለምንለት ፡ ዕውቀት ፡ ማግኘትን ።

፫፻፹፩ ፤ ይህንም ፡ ምስጢር ፡ ልትረዳ ፡ ብትሻ ፡ በሚ
ከተለው ፡ ሠምና ፡ ወርቅ ፡ አስተውለው ።



መናገር ፡ መጕዳቱን ፡ ከተረፈ ፡ ነገሥት ፡ በው
ል ፡ አስተውል ።
በኤልሳዕ ፡ በትር ፡ ላይ ፡ የነበረ ፡ ኃይል ፤
በግያዝ ፡ መናገር ፡ መሆኑን ፡ ቀላል ።
መለፍለፍ ፡ ሬት ፡ ነው ፡ አጥብቆ ፡ ይመራል ፤
የአምላክንም ፡ ጸጋ ፡ እንደ ፡ ግያዝ ፡ ያስቀራል ።

ወግ ፡ ተረት ፡ ቢጠቅም ፡ ለሰው ፡ ሳይሰለች ፡
መች ፡ ይጐዳ ፡ ነበር ፡ ተራች ፡ አቧላች ።

መርጦ ፡ ቃል ፡ መናገር ፡ ከሆነ ፡ አሳዳሪ ፡
አይደኸይም ፡ ነበር ፡ አሚናና ፡ አዝማሪ ።

አራቆ ፡ መናገር ፡ ንብረት ፡ ቢያሳምር ፡
እጅግ ፡ በከበሩ ፡ ሊቅና ፡ ወንበር ።

ደግሞም ፡ ወደ ፡ ወንጌል ፡ አልፈህ ፡ አስተውለው ፡
የጴጥሮስን ፡ እምነት ፡ መናገር ፡ ሲያደክመው ፤
የዮሐንስን ፡ ፀቅም ፡ ዝምታ ፡ እንደ ፡ ሠራው ።
ስለዚህም ፡ ምክር ፡ ልፍለፋን ፡ ተወው ፤
ዝምታ ፡ ቢያቅትህ ፡ ጕድህን ፡ አትጻፈው ።

ዝምታ ፡ ወርቅ ፡ ነው ፡ ራሱም ፡ ከባሪ ፡ ሰውን ፡
አስከባሪ ፤
ትዕግሥት ፡ ብር ፡ ነው ፡ ራሱም ፡ አማሪ ፤ ሰ
ውም ፡ አሳማሪ ፤
መናገር ፡ ርሳስ ፡ ነው ፡ ራሱም ፡ ጠቋሪ ፤ ሰውንም ፡
አጥቋሪ ።

ተኰሶም ፡ ሲሰዱት ፡ ሂዶ ፡ ሰው ፡ ይገድላል ፤
ልመርኰዝም ፡ ሲሉት ፡ ታጥፎ ፡ ሰው ፡ ይጥላል ፤
ልሸከምህ ፡ ሲሉት ፡ ከብዶ ፡ ሰው ፡ ይጐዳል ፤
ብትመዘምዘውም ፡ ጥፍርህን ፡ ያኸላል ፤
ብታሳጥረውም ፡ ጥፍርህን ፡ ያኸላል ፤
ስለዚህ ፡ መናገር ፡ ይህ ፡ አባይ ፡ ወላዋይ ፡ ክፉ ፡ ሰው ፡ ያሰኛል ።

ምዕራፍ ፡ ፳፫ ።

## ልዥራ ፡ ስሚል ፡ ሰው ፡ ስሰውነቱም ፡ ከንቱነት ፡ ማስረጃ ።

፲፻፺፩ ፤ ሰው ፡ እንኳን ፡ ከመሰሉ ፡ ሰው ፡ ከእንስሳ ፡ አይበልጥምና ፡ በልቡ ፡ ትዕቢትን ፡ ባለባበሱ ፡ ኵራትን ፡ ባነጋገሩ ፡ ትምክሕትን ፡ ባካሄዱ ፡ መቋፍን ፡ ባስተያየቱ ፡ ፊት ፡ ማጥቋርን ፡ ጨርሶ ፡ እንዲተው ፡ የሚያኰራ ፡ አካል ፡ እንዳልተፈጠረ ለት ፡ ማወቅ ፡ ነው ፡ እሚገባው ።

ጥያቄ ።

፲፻፺፪ ፤ ሰው ፡ ማለት ፡ ምንድነው ።

ምላሽ ።

፲፻፺፫ ፡ ሰው ፡ እሚባለው ፡ በሚታየው ፡ አካሉ ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ እንስሳ ፡ በማትታየው ፡ ነፍሱ ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ መልአክ ፡ ማለት ፡ ነው ።



የሰውንም ፡ እንስሳነት ፡ እንድትረዳው ፡ የጊታችንን ፡ መንበር ፡ ከያዙት ፡ አንዱ ፡ ገጸ ፡ ስብእ ፡ ሲሆን ፡ አርባዕቱ ፡ እንስሳ ፡ በመባሉ ፡ ዳዊትም ፡ ሰው ፡ ክቡር ፡ ሲሆን ፡ እንደ ፡ እንስሳ ፡ ሆነ ፡ በማለቱ ፡

ሰሎሞንም ፡ ሰው ፡ ከእንስሳ ፡ በምን ፡ ይበልጣል ፡ በማለቱ ፡ አስተውል ።

ጥያቄ ።

፲፻፺፬ ፡ እንዲህ ፡ የእንስሳ ፡ ዐይነት ፡ ከሆነ ፡ ሰው ፡ የመባሉን ፡ ስም ፡ ከምን ፡ አገኘነው ።

ምላሽ ።

፲፻፺፭ ፡ ሰው ፡ መባል ፡ የሥጋና ፡ የነፍስ ፡ ስም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ያንዱ ፡ አካላችን ፡ ስም ፡ አይደለም ።

አንድ ፡ ጊዜ ፡ ፈቃደ ፡ ነፍሱን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋውን ፡ እያፈራረቀ ፡ የሚሠራ ፡ አካል ፡ ለሁለት ፡ ጠባይ ፡ ተገዥ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ያማርኛችን ፡ ሊቆች ፡ በሁለት ፡ ፊደል ፡ ሰ ፡ ው ፡ በሚባል ፡ ስም ፡ ጠሩት ፡ ስለዚህ ፡ ሰው ፡ ማለት ፡ ደይ ፡ እደከ ፡ ኀበ ፡ ዘፈቀድከ ፡ ተብሎ ፡ የተፈጠረ ፡ ከሁሉም ፡ ለመሥል ፡ የሚችል ፡ ባለፈቃድ ፡ ነውና ።

እንደ ፡ እንስሳም ፡ እንደ ፡ መላክም ፡ መሆን ፡ የሚችል ፡ ማለት ፡ ነው ።

ፈቃደ ፡ ሥጋውን ፡ አሸንፎ ፡ ለፈቃደ ፡ ነፍሱ ፡ ብቻ ፡ የሚገዛ ፡ በግእዝ ፡ መልአክ ፡ ይባላል ።

ይኸውም ፡ መልአክ ፡ በምንባልበት ፡ አካል ፡ በነፍሳችን ፡ አርአያ ፡ ሥላሴ ፡ የሚያሰኘን ፡ ነውና ፡ መንፈሳዊን ፡ ሰው ፡ ባማርኛ ፡ መ ፡ ላ ፡ ክ ፡ ብለው ፡ በሦስት ፡ ፊደል ፡ ይጠሩታል ።

ፈቃደ ፡ ነፍሱን ፡ አሸንፎ ፡ ለፈቃደ ፡ ሥጋው ፡ ብቻ ፡ የሚገዛ ፡ እንስሳ ፡ ይባላል ።

እንስሳም ፡ ማለት ፡ ለአራቱ ፡ ባሕርያት ፡ የሚገዛ ፡ ነውና ፡ ስለዚህ ፡ ሥጋዊን ፡ ሰው ፡ እ ፡ ን ፡ ስ ፡ ሳ ፡ ብለው ፡ ባራት ፡ ቀለም ፡ ይጠሩታል ።

እንዲህ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ለሰው ፡ ለግብሩ ፡ እንጂ ፡ ለአካሉ ፡ ስም ፡ የለውምና ፡ ለሰው ፡ እውነተኛ ፡ የግብር ፡ ስሙ ፡ መልአክ ፡ ወይም ፡ እንስሳ ፡ መባል ፡ ነው ፤ ለፈቃደ ፡ ነፍሱ ፡ ተገዝቶ ፡ መላክ ፡ ቢባል ፡ በተፈጥሮም ፡ የሚቀድሙት ፡ በኃይልም ፡ የሚበልጡት ፡ ሌሎች ፡ መላእክት ፡ አሉና ፡ ታናሽ ፡ መላክ ፡ መሆኑን ፡ ይወቅ ።

ለፈቃደ ፡ ሥጋው ፡ ተገዝቶ ፡ እንስሳም ፡ ቢሆን ፡ እንደ ፡ እንበሳ ፡ እንደ ፡ በሬ ፡ እንደ ፡ ላም ፡ በግዘፍ ፡ የሚልቁት ፡ በኃይል ፡ የሚበልጡት ፡ ሌሎች ፡ እንስሳት ፡ አሉና ፡ ትንሽ ፡ እንስሳ ፡ መሆኑን ፡ ይወቅ ፡ እንጂ ፡ በማናቸውም ፡ ሥራ ፡ ምክንያት ፡ ቢያምርም ፡ ቢከብርም ፡ ቢሾምም ፡ ቢያይልም ፡ ቢሰፋም ፡ ቢረዝምም ፡ ለሰው ፡ ትልቅ ፡ ነኝ ፡ ማለት ፡ አይገባውምና ፤ አይቋፍ ፡ አይኵራ ፡ አይተብት ፤ አይመካ ።



ጥያቄ ።

፲፻፺፯ ፤ በባሕርየ ፡ ሥጋችን ፡ ከእንስሳ ፡ የምንመስልበት ፡ ስንት ፡ ዐይነት ፡ ነው ።

ምላሽ ።

፲፻፺፰ ፤ አራት ፡ ዐይነት ፡ ነው ።

አንደኛ ፤ በመብላት ፡ በመጠጣት ።

ሁለተኛ ፤ በመሞትና ፡ በመተኛት ።

ሦስተኛ ፤ በሩካቤ ፡ መውለድና ፡ በሩካቤ ፡ በመወለድ ።

አራተኛ ፤ በመታመምና ፡ በመጨነቅ ፡ ነው ።

ጥያቄ ።

፲፻፺፱ ፤ በዚህስ ፡ ምሳሌያችን ፡ ሁሉ ፡ ጥቂት ፡ እንኳን ፡ ከእንስሳ ፡ አንሻልምን ፤ ልክ ፡ እንስሳ ፡ ብቻ ፡ ነን ።

ምላሽ ።

፲፩፻ ፤ ፈቃደ ፡ ሥጋቸው ፡ ያሸነፋቸው ፡ ሰዎች ፡ ከተውንም ፡ ከእንስሳ ፡ ያንሳሉ ።

ከአራዊትም ፡ ግብር ፡ ጨምረው ፡ ይከፋሉ ፡ እንጂ ፡ አይሻሉም ።

ጥያቄ ።

፲፩፻፩ ፤ ደግሞ ፡ ከእንስሳም ፡ አልፈን ፡ አራዊትን ፡ መምሰል ፡ አለብን ።

ምላሽ ።

፫፻፺፪ ፡ ሰው ፡ ሦስቱን ፡ መንበር ፡ ተሸካሚ ፡ ጓደኞ
ቿን ፡ ለመምሰል ፡ ይችላል ፡ ከአራዊትም ፡ ከአዕዋ
ፍም ፡ ጠባይ ፡ ጋራ ፡ የሚመሳሰል ፡ ጠባይ ፡ አለ
ንና ፡ እንመስላለን ።

አንበሳውን ፡ ሥጋ ፡ በመብላታችን ፡ እርስ ፡ በርሳ
ችን ፡ በመጣላታችን ፡ በመዥራታችን ፡ እንመስ
ላለን ።

ንስሩን ፡ ዐቅማችን ፡ የቻለውን ፡ ያኽል ፡ በመዞራ
ችን ፡ በሁለት ፡ እግር ፡ ብቻ ፡ በመቆማችን ፡ እንመ
ስላለን ።

ላሕሙን ፡ እኽል ፡ ውሃ ፡ ሣር ፡ ቅጠል ፡ በመሻታ
ችን ፡ የሚያርደንና ፡ የማያርደንን ፡ ለይተን ፡ ባለ
ማወቃችን ፡ እንመስለዋለን ።

ጥያቄ ።

፫፻፺፫ ፡ የኒህ ፡ ሁሉ ፡ ቅርጽ ፡ ባንዳንዱ ፡ አካል ፡
ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሚመስሉን ፡ በቀረው ፡
ቅርጽ ፡ የኛ ፡ የሚያምር ፡ ይመስላል ።
ባይሆን ፡ በቅርጻችን ፡ አንበልጥምን ።

ምላሽ ።

፫፻፺፬ ፡ በቅርጽም ፡ ቢሆን ፡ አንበልጥም ፡ ባንተ ፡
አሳብ ፡ ሁነህ ፡ ብታየው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለነሱም ፡



የነሱ ፡ ቅርጽ ፡ ያምራቸው ፡ ይሆናል ፡ በፊታችን
ስ ፡ ቅርጽ ፡ ምክንያት ፡ ትልቅ ፡ የሆን ፡ እንዳይመ
ስልህ ፡ ከሁሉ ፡ የሚያንሱት ፡ የዝንጀሮና ፡ የጦጣ ፡
ቅርጽ ፡ ወደኛ ፡ የተቃረበ ፡ መሆኑን ፡ አስተውል ።

ጥያቄ ።

፫፻፺፭ ፡ ባራተኛው ፡ ምላሽ ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋው ፡ ያሸ
ነፈው ፡ ከእንስሳ ፡ ያንሳል ፡ ያልኸኝ ፡ በምን ፡ በም
ን ፡ ያንሳል ።

ምላሽ ።

፫፻፺፮ ፡ እንስሳት ፡ ከብዙ ፡ ሣር ፡ ከፍለው ፡ ከብዙ ፡
ውሃ ፡ ትተው ፡ መጥነው ፡ በልተው ፡ በደኅና ፡ ይኖ
ራሉ ፤ ሥጋዊ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ መመጠን ፡ እያቃተው ፡
በልቶ ፡ ያቁነጣል ፡ ጠጥቶ ፡ ይሰክራል ።

አዕዋፍ ፡ ከንቅልፋቸው ፡ ነቅተው ፡ ተግተው ፡
በየዘማቸው ፡ ለፈጣሪያቸው ፡ ይሰግዳሉ ።

ሥጋዊ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ይኸን ፡ መሥራት ፡ እያቃ
ተው ፡ ቀኑን ፡ በቧልት ፡ በመዝፈን ፡ ሌቱን ፡ በመ
ተኛት ፡ ይጨርሰዋል ።

አርጋብ ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ባንድ ፡ ወንድ ፡ ተወስ
ነው ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይውላሉ ።

ሥጋዊ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ እሱ ፡ አንድ ፡ ሲሆን ፡ አንዲት ፡
ሴት ፡ አልበቃው ፡ ብሎ ፡ በብዙ ፡ ሴት ፡ ፍለጋ ፡
ይባክናል ።

እንኳን ፡ ዘወትር ፡ በታዘዘም ፡ ጊዜ ፡ እቤተ ፡ ክርስ
ቲያን ፡ ለመሄድ ፡ ያቅተዋል ።

## ጕንዳን ፡ ዝንጀሮ ።

እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ያንዱን ፡ ድካም ፡ አንዱ ፡ እየ
ረዳ ፡ ይሸከመዋል ።

ሥጋዊ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ አንዱን ፡ አንዱ ፡ ለመብለጥ ፡
ሲል ፡ ከቶውንም ፡ ባልንጀራውን ፡ ይቀማዋል ፤
ያታልለዋል ፤ ይጐዳዋል ፤ ይገድለዋል ።

## እንስሳት ።

ላልፈጠራቸው ፡ ሰው ፡ እርሰው ፡ ጭነው ፡ ይገዛሉ፡
ሥጋዊ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ እንኳን ፡ ላልፈጠረው ፡ ለፈጠ
ረው ፡ አልገዛም ፡ እያለ ፡ ፀዋቂዋን ፡ ነፍሱን ፡ ለእ
ንስሳ ፡ ባሕርዩ ፡ ያስገዛል ።

## እንስሳት ።

ፍትወታቸውን ፡ እሸንፈው ፡ የፀነሰችውን ፡ እን
ስት ፡ ይተዋሉ ።

ሥጋዊ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ፍትወቱ ፡ እያሸነፈው ፡ ወደ ፡
ፀነሰችው ፡ ይሄዳል ።

ስለዚህ ፡ ለፈቃደ ፡ ሥጋው ፡ የሚገዛ ፡ ሰው ፡ ከእን
ስሳ ፡ ያንሳል ።



## ጥያቄ ።

፻፺፯ ፤ ከእንስሳውስ ፡ በሥራችን ፡ እያነስንም ፡ እየ
ተመሳሰልንም ፡ መዋረዳችን ፡ ብዙ ፡ የሚያስረዳ ፡
ነገር ፡ አገኘንለት ፤ ሰውና ፡ ሰው ፡ በፍጥረትም ፡
ረኀብ ፡ ካጭሩ ፡ ወፍራሙ ፡ ከኰሳሳው ፡ መልክ ፡
ቀናው ፡ ከመልክ ፡ ጠማማው ፡ በየብልጫቸው ፡
ሲኰሩበት ፡ ሲደሱበት ፡ ይኖራሉ ፤ ይህስ ፡ ለሰውነ
ታችን ፡ ብልጫና ፡ ደስታ ፡ አይሆነውምን ።

## ምላሽ ።

፻፺፰ ፤ በዚህም ፡ በቈጠርከው ፡ ሁሉ ፡ አንዱ ፡
ሰው ፡ ካንዱ ፡ የበለጥኩ ፡ መስሎት ፡ ሊደሳም ፡ ሊ
ኰራም ፡ አይገባውም ።

ይህንም ፡ ልትረዳ ፡ ብትሻ ፡ ሠራተኛ ፡ መግሪያ
ውን ፡ ለሥራው ፡ እንደየሚያስፈልገው ፡ አድርጎ ፡
ቢሠራው ፡ አንዱን ፡ ጕጠት ፡ አንዱን ፡ መዶሻ ፡
አንዱን ፡ መስፍ ፡ አንዱን ፡ ሞረድ ፡ እያደረገ ፡ ስለ ፡
ሥራቸው ፡ የፀይነታቸው ፡ መለየት ፡ የነሱ ፡ የብረ
ትነታቸው ፡ መልክ ፡ ሳይለወጥ ፡ ሳይበላለጥ ፡ ሁ
ሉም ፡ ለባለቤቱ ፤ የሚሠሩለት ፡ የተካከሉ ፡ ገንዘ
ቦቹ ፡ እንደሚሆኑ ፡ ሰውም ፡ ሁሉ ፡ ለእግዚአብ
ሔር ፡ ገንዘብ ፡ በመሆን ፡ ሰውም ፡ በመሆን ፡ የ
ተካከለ ፡ ነውና ፡ እግዚአብሔር ፡ ሁሉን ፡ ማድረ
ግ ፡ የሚችል ፡ ጥበቡ ፡ የማይቈጠር ፡ መሆኑን ፡ ለ
ማሳየት ፡ ቀይና ፡ ጥቍር ፡ ረኀምና ፡ አጭር ፡ ወ

ፍራ·ምና ፡ ቀጭኑን ፡ እያቀላቀለ ፡ መልክም ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ሆኖ ፡ ሰውና ፡ ሰው ፡ አልተዋወቅ ፡ እንዳ ይልበት ፡ ቅርጹን ፡ እያዘዋወረ ፡ እሱ ፡ ለየጕዳዩ ፡ እንደሚሻው ፡ እያደረገ ፡ በሠራው ፤ ራሱን ፡ የሠ ራ ፡ ይመስል ፡ የተሠሪው ፡ ሰው ፡ መኵራቱም ፡ መደሳቱም ፡ አጥብቆ ፡ ጭንነት ፡ ነውና ፤ ሰው ፡ በተፈጥሮው ፡ መበላለጥ ፡ ቢሆን ፡ ሊኰራ ፡ ሊተ ብት ፡ ሊመካም ፡ ሊደሳም ፡ አይገባውምና ።

ታናናሽ ፡ ሰዎችን ፡ በልቡናህ ፡ ስትንቅ ፡ ከልክሎሃል ፡ ወንጌል ፡ ትእዛዙን ፡ ጠይቅ ፡ የተባለውንም ፡ አስተውል ።

ጥያቄ ።

፻፶፱ ፡ ከእንስሳ ፡ እናንሳለን ፡ ያልከኝ ፡ ቃል ፡ ምን ም ፡ ባስበው ፡ አልረዳኝ ፡ አለ ።

በሥጋችን ፡ መለስለስ ፡ እንኳ ፡ የነሱ ፡ ቀርበት ፡ የኛ ፡ ሥጋ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ከእንስሳ ፡ እንበልጥም ፤ አርደን ፡ ከምንበላቸው ፡ ጭነን ፡ ከምንቀመጥባቸ ው ፡ ከእንስሳማ ፡ እንዴት ፡ እንመሳሰላለን ፤ በሌ ሉላውስ ፡ ቢመሳሰሉን ፡ በማሸነፋችን ፡ እንበልጣ ቸውምን ።

ምላሽ ።

፻፶፱ ፤ በመለስለስም ፡ የበለጥን ፡ እንዳይመስልህ ፡ እንደነሱ ፡ ያሉ ፡ ከመለስለስም ፡ አልፈው ፡ የሚ



ያሙለጨልጩ ፡ እንደ ፡ ዓሣ ፡ ያሉ ፡ ብዙ ፡ እንስ ሳት ፡ አሉ ፤ ለጠጕሩም ፡ ማብቀል ፡ የኛ ፡ አካል ፡ ጠጕር ፡ ይበቅልበታልና ፡ ራስክን ፡ እየው ።

ተገሮም ፡ ቈዳ ፡ ለመሆኑ ፡ በንቶማስ ፡ ስልቻ ፡ መ ሆን ፡ አስተውለው ።

አርደን ፡ በመብላታችንና ፡ እላያቸው ፡ በመቀመጣ ችን ፡ ትልቅ ፡ የሆን ፡ እንዳይመስለን ፡ እኛንም ፡ አ ሽንፎ ፡ አንዱ ፡ አውሬ ፡ ይበላናል ፤ በመቀመጣች ንም ፡ ከላይ ፡ የሆን ፡ እንዳይመስልህ ፡ ከኛ ፡ የሚያን ሱት ፡ ተሐዋስያን ፡ ከራሳችን ፡ ላይ ፡ ቅሟም ፡ ቅ ማል ፡ ተብለው ፡ ይቀመጡብናልና ፤ የተሐዋስያን ፡ መቀመጫ ፡ መሆንህን ፡ ራስህ ፡ አስተውለው ።

ጥያቄ ።

፻፷ ፡ የምናየው ፡ ሥጋችን ፡ እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ ቍር በት፡እንበለውን፡አካል፡እንበለው፡ስሙ፡ማነው።

ምላሽ ።

፻፷ ፡ በባሕርይ ፡ ስሙ ፡ ውስጡ ፡ ሥጋ ፡ ላዩ ፡ ቈዳ ፡ ነው ፤ በግብር ፡ ስሙ ፡ ውስጡ ፡ ዐጥንት ፡ ላዩ ፡ ዐፈር ፡ ነው ። በተዋሕዶ ፡ ስሙ ፡ ውስጡ ፡ ነፍስ ፡ ግዘፉ ፡ አካል ፡ ነው ።

ጥያቄ ።

፻፷፩ ፡ መላክ ፤ እንስሳ ፡ ያልሆን ፤ ሰው ፡ መባል ፡ የሚ ገባው ፡ ፍጡር ፡ የለምን ።

ምላሽ ።

፬፻፬ ፤ ሰው ፡ የሚባል ፡ ግብረ ፡ መላእክትን ፡ አጥብቆ ፡ የሚሻ ፡ እያቃተውም ፡ ግብረ ፡ እንስሳን ፡ ሲሠራ ፡ መልእክነት ፡ ያለው ፡ አካሉ ፡ እንደ ፡ እንስሳ ፡ በመሥራቱ ፡ እያፈረ ፡ የእንስሳነቱን ፡ አካሉንም ፡ በልብሱ ፡ መብሉንም ፡ በቤቱ ፡ የሚሰውር ፡ መጋባቱንም ፡ የሚሻበት ፡ ለወሊደ ፡ ውሉድ ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ እንበሳ ፡ ለሥጋ ፡ ፍትወት ፡ መጽገብ ፡ ብቻ ፡ ሲል ፡ ከሴት ፡ መገናኘቱንም ፡ ሁሉ ፡ የሚሠራው ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፤ የሚያሳፍረውንም ፡ የሩካቤ ፡ ጠባዩን ፡ ከሴት ፡ ጋራ ፡ በመዳራት ፡ በማቧለት ፡ የማያሳይ ፡ ከእንስሳ ፡ የሚመስለውን ፡ ሥጋውን ፡ ለመሸፈን ፡ የታዘዘውን ፡ ልብሱንም ፡ በመጋለጥ ፡ አካሉን ፡ የማያሳይ ፡ መብላቱንም ፡ በቅልውጥ ፡ ማብዛት ፡ የማያሳይ ፡ አስቀያሚውንም ፡ የጉረሮውን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ እንኳን ፡ ለሰው ፡ ለራሱም ፡ የማያሳይ ፤ በዚህ ፡ ሁሉ ፡ እንስሳነት ፡ እየፈረደበት ፡ አጥብቆ ፡ የሚሰውር ፤ ነውር ፡ የሚያውቅ ፡ አካል ፡ ነውረኛነቱን ፡ በማወቁ ፡ ከመላእክት ፤ በመሥራቱ ፡ ከእንስሳት ፡ ስለ ፡ ተመሳሰለ ፡ ሰው ፡ ይባላል ።

ሥልጣኔና ፡ ዘመት ፡ እንደ ፡ አሳበዳቸው ፡ ሰዎች ፡ በመድፈር ፡ እንደ ፡ ሻንቅሎችም ፡ በመደንቈር ፡ ይኸንንም ፡ የሚያሳፍረውን ፡ በእንስሳዊ ፡ ጠባያቸውና ፡ አካላቸው ፡ ሳያፍሩበት ፡ አካላቸውን ፡ እየገለጡ ፡ የሚያሳዩ ፡ ወይም ፡ ቀሚሳቸውን ፡ ከከንዳቸው ፡ ከወገባቸው ፡ ሱሪያቸውን ፡ ከእግራቸው ፡ እያጣበቁ ፡ በልብሳቸው ፡ መጣበቅ ፡ እንስሳዊ ፡ አካላቸው ፡ በመታየት ፡ እንዲታወቅላቸው ፡ የሚጥሩ ፡ ከላይ ፡ በተቈጠረ ፡ በግብረ ፡ እንስሳው ፡ ሥራም ፡ ሁሉ ፡ የማያፍሩ ፡ ሰውነትንም ፡ መላእክትነትንም ፡ የተዉ ፡ ጨርሰው ፡ ወደ ፡ እንስሳነት ፡ የዞሩ ፡ ይባላሉ ።



ጥያቄ ።

፬፻፭ ፤ ትክክል ፡ ሰው ፡ ለመባል ፡ የሚገባው ፡ በምን ፡ በምን ፡ ሚዛን ፡ ሲተካከል ፡ ነው ።

ምላሽ ።

፬፻፮ ፤ የመብላትና ፡ የመተኛትን ፡ የሩካቤንና ፡ የጭንቀትን ፡ እኒህን ፡ አራቶቹን ፡ የደመ ፡ ነፍስን ፡ ሥራዎች ፡ እንደ ፡ እንስሳዎችም ፡ ሳያበዛቸው ፡ እንደ ፡ መላእክትም ፡ ጨርሶ ፡ ሳይተዋቸው ፡ መብሉን ፡ እንደ ፡ ክብት ፡ ያገኘውን ፡ ሁሉ ፡ በመብላት ፡ ሳያበዛ ፡ ረኃቡ ፡ እስኪከላለት ፡ ድረስ ፡ ካንዱ ፡ ዐይነት ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ በልቶ ፡ የሚተው ፡ እንቅልፉንም ፡ እንደ ፡ እዞ ፡ እብዝቶ ፡ ሌቱን ፡ ሁሉ ፡ በመተኛት ፡ ሳይጨርስ ፡ የሌሊቱን ፡ ሢሶ ፡ ለዕውቀቱና ፡ ለጸሎቱ ፡ መሥሪያ ፡ የሚያደርግ ፡ ሩካቤውንም ፡ ካንዲ ፡ ሚስቱም ፡ ቢሆን ፡ በዓላትና ፡ አጽዋማትን ፡ ኅርስና ፡ ትክትን ፡ ለይቶ ፡ በሚገናኝበትም ፡ ጊዜ ፡ ለእብጥሉ ፡ ፍትወቱና ፡ ለወ

ሊደ ፡ ውሉድ ፡ ብቻ ፡ ሲል ፡ የሚሠራ ፡ እንደ ፡ ውሻም ፡ ለሩካቤ ፡ በመለማመጥ ፡ ሳይቀል ፡ እንደ ፡ ፍየል ፡ ሳያበዛ ፡ ፍትወቱ ፡ እስኪበርድ ፡ ድረስ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ደርሶ ፡ የሚተው ፡ በማዘውተር ፡ በመመላለስ ፡ የማያበዛ ። በመጨነቂም ፡ ጊዜ ፡ ለብቻውም ፡ ሲሆን ፡ በአካሉ ፡ ሁሉ ፡ ከሰው ፡ ፊት ፡ ሲሆን ፡ በልቡ ፡ ተጨንቆ ፡ መላልሶ ፡ እምላኩን ፡ የሚለምን ፡ እንደሱ ፡ ያለውን ፡ ፍጡር ፡ ማን ፡ ፈርቶ ፡ እንደ ፡ ቆቅ ፡ ሳይጠረጥር ፡ እንደ ፡ ከብት ፡ ሳይደነብር ፡ እንደ ፡ ታረደ ፡ ደመ ፡ ነፍስ ፡ ሥጋም ፡ ሆኖ ፡ ሳይንበደበድ ፡ የመጣበትን ፡ ቍንቅ ፡ ሁሉ ፡ ጸጥ ፡ ብሎ ፡ ሳይቀል ፡ ሳይበሳጭ ፡ በትዕግሥት ፡ የሚቀበል ፡ ትክክል ፡ ሰው ፡ ይባላል ፡ (ስለ ፡ አባት ፡ እናት ፡ ም ፡ ፲፰) ።

ምዕራፍ ፡ ፳፱ ።

## ስለ ፡ መድኀኒት ፡ ማዳንና ፡ አለማዳን ፡ ማወቂያ ።

፩፻፯ ፡ በታመምን ፡ ጊዜ ፡ ባንጋገራችን ፡ ልማድ ፡ መድኀኒትን ፡ ባማርኛ ፡ ትርጓሜ ፡ መዳኛ ፡ ስንለው ፡ ትርጓሜ ፡ እናጠፋለን ፤ መድኀኒት ፡ ስንስለ ፡ ሃይማኖት ፡ ማጕደል ፡ ፍዳ ፡ ጨምረን ፡ እንጐዳለን ፡ እንጂ ፡ የመድኀኒት ፡ ጠባይ ፡ አያድነንም ።



ጥያቄ ።

፩፻፰ ፤ የመድኀኒትስ ፡ ትርጓሜ ፡ መዳኛ ፡ ካልተባለ ፡ ምን ፡ ይባል ።

የመድኀኒትስ ፡ ጠባይ ፡ እንዳንዶቹን ፡ ሲያድን ፡ እያየን ፡ አያድንም ፡ ያልን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ያስረዳናል ።

ምላሽ ።

፩፻፱ ፡ በመድኀኒት ፡ እግዚአብሔር ፡ ማዳን ፡ በፈቀደ ፡ ጊዜ ፡ የሚሠራበት ፡ መሣሪያውና ፡ የመድኀኒት ፡ ትርጓሜ ፡ ማዳኛ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ መዳኛ ፡ አይባልም ።

መድኀኒትም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ማዳኑ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አለማዳኑ ፡ ለመድኀኒት ፡ ማዳን ፡ ባሕርዩ ፡ አለመሆኑን ፡ ሲያስረዳን ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ማዳንማ ፡ ባሕርዩ ፡ ቢሆን ፡ መድኀኒቱን ፡ ያደረገው ፡ ሁሉ ፡ ታማሚው ፡ ሳይድን ፡ አይቀርም ፡ ነበርና ፤ ስለዚህ፡ መድኀኒት ፡ ያድነናል ፡ ብለን ፡ ልናምን ፡ አይገባንም ።

ጥያቄ ።

፩፻፲ ፡ ያ ፡ መድኀኒት ፡ ያድናል ፡ ብሎ ፡ መሻትና ፡ ማመን ፡ የማይገባን ፡ ከሆነ ፡ እግዚአብሔር ፡ በፈቀደ ፡ ጊዜ ፡ እንዲያው ፡ ማዳን ፡ ሲቻለው ፡ ስለ ፡ ም

ን ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ማዳኑን ፡ በመድኀኒት ፡ ምክ
ንያት ፡ ያደርገዋል ።

## ምላሽ ።

፩፻፲፭ ፤ በባሕርያችን ፡ ታመን ፡ በባሕርያችን ፡ ብን
ድን ፡ በልማድ ፡ የምንታመም ፡ በልማድ ፡ የምን
ድን ፡ ይመስለንና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ አዳኝነት ፡
ገዳይነቱንም ፡ ሳናውቀው ፡ እንዳንቀር ፡ ግዙፍ ፡ ሰ
ውነታችንም ፡ ረቂቅ ፡ ማዳኑን ፡ አይቶ ፡ ማመን ፡
የማይቻለው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የማናየውን ፡ ማዳኑን ፡ በ
ምናየው ፡ በግዙፍ ፡ ነገር ፡ ለመስጠት ፡ ነው ፡ እን
ጂ ፡ የመድኀኒት ፡ ባሕርይ ፡ ራሱ ፡ ተንቀሳቃሽነት ፡
የሌለው ፡ ሙት ፡ ሲሆን ፡ የሚሞት ፡ ሰውነቱን ፡
ያድንልኛል ፡ ብሎ ፡ የሚያምነው ፡ ሰው ፡ እእም
ሮው ፡ የሞተበት ፡ ነው ።

## ጥያቄ ።

፩፻፲፮ ፤ የመድኀኒት ፡ ማዳን ፡ እንዲህ ፡ ከንቱ ፡ ከሆነ ፡
በታመምን ፡ ጊዜ ፡ በመድኀኒት ፡ ምክንያት ፡ እን
ዲያደረግልን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቸርነት ፡ ስንሻ ፡
እንደ ፡ ምን ፡ ልናስብ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ልናደርግ ፡
ይገባናል ።

## ምላሽ ።

፩፻፲፯ ፤ አንደኛ ፤ ዐይንና ፡ ዐፈር ፡ የተጣላ ፡ ነገር ፡
ሲሆን ፡ የዘዕውሩ ፡ ተወልደን ፡ ዐይን ፡ በዐፈር ፡
ምክንያት ፡ ማዳኑ ። የለምጽ ፡ ደዌ ፡ ከውሃ ፡ ባሕር



ይ ፡ የሚነጣ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ውሃ ፡ ያብስበታል ፡ እንጂ ፡
የማያድነው ፡ ሲሆን ፡ ንእማን ፡ በውሃ ፡ መዳኑ ፡
የመድኀኒት ፡ ባሕርይ ፡ የማያድን ፡ መሆኑን ፡ በዚ
ህ ፡ አስብና ፡ ስለዚህ ፡ መድኀኒት ፡ የፈቀደውን ፡
የሚሠራበት ፡ የእግዚአብሔር ፡ መሣሪያ ፡ መሆኑን ፡
አስብ ።

ጸሎትህን ፡ የምታደርግበት ፡ ለእግዚአብሔርም ፡
መሣሪያ ፡ የሚሆንለት ፡ አንድም ፡ ነገር ፡ ሳታቀ
ርብ ፡ እንዲያው ፡ አድነኝ ፡ ማለት ፡ ምንም ፡ ለእግዚ
አብሔር ፡ ባይሳነው ፡ ላንተ ፡ ፈተና ፡ እንዳይሆንብ
ኝ ፡ ስትል ፡ መሣሪያ ፡ አቅራቢ ፡ መሆንህን ፡ አስብ ።

፩፻፲፰ ፤ የመሣሪያነቱም ፡ ምሳሌ ፡ የእግዚአብሔር ፡
ምሳሌ ፡ የሚሆን ፡ አናጢ ፤ የሰው ፡ ምሳሌ ፡ የሚ
ሆን ፡ ዕንጨትን ፡ የአናጺው ፡ ፈቃድ ፡ ለመጥረብ ፡
ሲሆን ፡ እየጠረበ ፡ የከበደውን ፡ አቃሎ ፡ የጠመመ
ውን ፡ አቃንቶ ፡ የወደቀውን ፡ ዕንጨት ፡ መልሶ ፡
ያቆመዋል ።

ያናጢው ፡ ፈቃድ ፡ ለመፍለጥ ፡ ለመቍረጥ ፡ ሲሆ
ን ፡ ያንኑ ፡ የሚጠርብበትን ፡ መጥረቢያ ፡ ዘወር ፡
አድርጎ ፡ መቍረጫ ፡ ያደርግና ፡ እየፈለጠ ፡ እየተ
ፈተፈ ፡ ይጥለዋል ።

እንደዚህም ፡ ሁሉ ፡ ባለፈቃዱ ፡ ሠራተኛው ፡
እግዚአብሔር ፡ በመድኀኒት ፡ መሣሪያው ፡ ከባድ ፡
ደዌውን ፡ አቃሎ ፡ ያቆምበታል ።

ፈቃዱም ፡ ለማዳን ፡ ሳይሆን ፡ ያንኑ ፡ የሚያድንበትን ፡ መድኀኒት ፡ ዘወር ፡ አድርጎ ፡ እንኳን ፡ ሌላው ፡ መድኀኒት ፡ በሥጋው ፡ ወደሙም ፡ ቢሆን ፡ አንዳንዶቹ ፡ ዕለቱን ፡ ተቀብለው ፡ ይድኑበታል ፡ አንዳንዶቹ ፡ ዕለቱን ፡ ተቀብለው ፡ ይሞቱበታልና ፡ ስለዚህ ፡ መድኀኒት ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚያድንበት ፡ ወይም ፡ የሚገድልበት ፡ መሣሪያ ፡ መሆኑን ፡ ዕወቅና ፡ ሥር ፡ ምሰው ፡ ቅጠል ፡ በጥሰው ፡ መድኀኒት ፡ ለውሰው ፡ የሚያቀርቡት ፡ ባለመድኀኒቶች ፡ እንደ ፡ ጋሻ ፡ ጃግሬ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚያድንበትንና ፡ የሚገድልበትን ፡ መሣሪያ ፡ ተሸካሚዎች ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ አዳኞች ፡ አለመሆናቸውን ፡ ራሳቸው ፡ በመሞታቸው ፡ አስተውል ።

መድኀኒትም ፡ ማድረግ ፡ ስትሻ ፡ ይህን ፡ ሦስቱን ፡ ምስጢር ፡ ማወቅና ፡ ማመን ፡ ይገባሃል ።

ዳግመኛም ፡ መድኀኒት ፡ በማድረግበት ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ ምን ፡ እንዳላደርግ ፡ ይገባል ፡ ላልከኝ ።

አቤቱ ፡ ማዳን ፡ ፈቃድህ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በዚህ ፡ መድኀኒት ፡ ሰውን ፡ ስታድንበት ፡ አይቻለሁና ፤ ያላየኸው ፡ ሲሆን ፡ ማዳንህን ፡ ስምቻለሁና ፡ ለኀጢአቴ ፡ መቀጫ ፡ ሳይሆን ፡ ለማዳንህ ፡ መሣሪያ ፡ ይሁንልኝ ፡ ብለህ ፡ ምሳሌው ፡ ከሆነው ፡ ለባለሥልጣን ፡ ካህን ፡ አቅርብለትና ፡ አስባርከህ ፡ ወይም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ አንተው ፡ ጸልየህ ፡



አድርገው ፡ እንጂ ፡ በጸሎት ፡ ሳይቀደስ ፡ መድኀኒቱን ፡ ብቻ ፡ አታድርገው ።

፩፻፲፰ ፤ ሁለተኛ ፤ ባለመድኀኒቶች ፡ መድኀኒቱን ፡ ለማስመለክና ፡ ለማስከበር ፡ በእንዲህ ፡ ያለ ፡ ዕንጨት ፡ ማሰው ፡ ለተዘክርተ ፡ ሞተ ፡ ኢየሱስ ፡ ከምትይዘው ፡ መስቀል ፡ እያስተካከልህ ፡ ባንገትህ ፡ ያዘው ፡ በራስህ ፡ አዙረው ፡ እያሉ ፡ ይህን ፡ በሚመስል ፡ ለመድኀኒት ፡ ክብር ፡ ሲሉ ፡ የሚያዙት ፡ የሐሰት ፡ ትእዛዝ ፡ ሰይጣንም ፡ ኀጢአት ፡ ለማሠራት ፡ ባለመድኀኒቱም ፡ ዋጋ ፡ ለመብላት ፡ የሠሩት ፡ ተንኰል ፡ ነውና ፤ በዚህ ፡ ሥራ ፡ ሲድንበትም ፡ ብታይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሚያድንበት ፡ ሰዓት ፡ ጋራ ፡ ጊዜ ፡ አጋጥሞት ፡ ነው ፡ በል ፡ እንጂ ፤ ወደ ፡ አምልኮ ፡ ባዕድ ፡ እንዳያስብህ ፡ የዚህን ፡ ዐይነት ፡ መድኀኒት ፡ አታድርግ ።

፩፻፲፱ ፤ ሦስተኛ ፡ ስለ ፡ መድኀኒቱ ፡ ልክም ፡ ሠለስቱ ፡ ምእት ፡ እግዚአብሔር ፡ ሚስቱን ፡ የገደለበት ፡ ደግሞ ፡ ሁለተኛ ፡ አግብቶ ፡ ይፈትን ፡ ደግሞም ፡ ሁለተኛይቱ ፡ ብትሞትበት ፡ ማግባቱን ፡ ይተው ።

መተው ፡ ባይቻለው ፡ ግን ፡ ማዕርጉን ፡ ያዋርደው ፡ እንጂ ፡ ያግባ ፤ ደግሞ ፡ አራተኛይቱን ፡ ላግባ ፡ የሚል ፡ ግን ፡ ሁሉንም ፡ ያልባረከለት ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጽሕናውን ፡ ቢወድ ፡ ነውና ፡ አራተኛዋን ፡ አያግባ ፡ እንዳሉ ፤ ምሳሌም ፡ እንዲሆን ፡ ጊታም ፡ በሰውነቱ ፡ ሙታንን ፡ ሲያስነግበት ፡ በነበ

ረው ፡ በቅዱስ ፡ ጸሎቱ ፡ ለራሱ ፡ ማዳን ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ጸልዮ ፡ ባራተኛ ፡ በፈቃዱ ፡ ወደ ፡ ሞት ፡ እን ደ ፡ ሄደ ፡ መድኀኒትም ፡ በምታደርግበት ፡ ጊዜ ፡ የመጀመሪያውን ፡ የሁለተኛውንም ፡ የሦስተኛው ንም ፡ በስሙ ፡ እየለመንክ ፡ እድርገህ ፡ አላድንህ ፡ ሲል ፡ ደዌውን ፡ በእኩቴት ፡ መቀበልህን ፡ ቢሻ ፡ መዳንህን ፡ ባይሻ ፡ ነውና ፤ አራተኛውን ፡ ፀይነት ፡ መድኀኒት ፡ አታድርግ ። ይህን ፡ ሦስቱን ፡ ፀይነት ፡ ማድረግ ፡ ነው ።

፬፻፲፯ ፤ ሦስተኛ ፤ እንዴት ፡ ማመን ፡ ይገባል ፡ ላል ከኝ ፡ ለመድኀኒትም ፡ ለባለመድኀኒቱም ፡ ማዳን ፡ መግደል ፡ የማይቻለው ፡ መሆኑን ፡ ማወቅ ፤ ማዳን ፡ መ ግደል ፡ በእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ መሆኑን ፡ ማመን ፡ ነው ።

፬፻፲፰ ፤ መድኀኒት ፡ ወይም ፡ ባለመድኀኒት ፡ የሚያ ዘጋጀው ፡ ያድነኛል ፡ ማለት ፡ ግን ፡ ለሥጋ ፡ ደዌ ፡ በደረሰው ፡ ኀጢአት ፡ ላይ ፡ ነፍሱን ፡ የሚጐዳ ፡ ክፉ ፡ ደዌ ፡ ይጨምራል ፡ እንጂ ፡ አይድንም ። ም ናልባት ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በመድኀኒቱና ፡ በባለ መድኀኒቱ ፡ ብቻ ፡ አምነህ ፡ መድኀኒት ፡ ቢያድ ንህ ፡ እንደ ፡ ፈርዖን ፡ ተአምራት ፡ ያለ ፡ ሞት ፡ ነፍስና ፡ ሞት ፡ ሥጋ ፡ የሚያስከትል ፡ ፈተና ፡ እን ደ ፡ ተዘጋጀልህ ፡ አስተውል ።

የእግዚአብሔር ፡ ተአማኒና ፡ የመድኀኒት ፡ ተአ ማኒ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በማዳን ፡ መመሳሰላቸ ው ፡ በቀለሚንጦስ ፡ መጽሐፍ ፡ አቅረብኩ ፡ ለክ ፡

ፍኖተ ፡ እእምሮ ፡ (የዕውቀት ፡ ጐዳና) ። 

እሳት ፡ ወማየ ፡ ባለው ፡ ቃል ፡ ክፋና ፡ በጎን ፡ እመ ሳስሎ ፡ ማቅረቡ ፡ ከማያድነው ፡ መድኀኒት ፡ ከሚ ባለው ፡ ሥርና ፡ ቅጠል ፡ የሚያድነውን ፡ አምላክ ፡ እንድትመርጥለት ፡ መሆኑን ፡ አስተውል ።

ማዳኑ ፡ እሱን ፡ ብቻ ፡ ለሚያምኑት ፡ ሰዎች ፡ ሆኖ ፡ ቢቀር ፡ መድኀኒቱ ፡ አንዳንድ ፡ ሰው ፡ አልፎ ም ፡ እማያድን ፡ ሆኖ ፡ መምረጫ ፡ ባይኖር ፡ እሚ መረጠውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ መርጠን ፡ ወደድ ንህ ፡ አመንህ ፡ ብለን ፡ ዋጋ ፡ ለማግኘት ፡ አይቻለ ንም ፡ ነበርና ፡ ፈርዶም ፡ የሚገድለን ፡ መሆኑን ፡ እን ድናምን ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ እስማተኞች ፡ ለማዳኑ ፡ ብቻ ፡ እንዳይታመን ፡ የነሱን ፡ የራሳቸውን ፡ የመ ድኀኒታቸውን ፡ ከንቱነት ፡ ራሳቸውን ፡ እንኳ ፡ ለማዳን ፡ አለመቻላቸውን ፡ አስተውለን ፡ የእግዚ አብሔርን ፡ የማዳኑን ፡ እውነት ፡ በሰጠን ፡ አእምሮ ፡ ተመራምረን ፡ የሰው ፡ መድኀኒት ፡ አምኖ ፡ መዳን ፡ ለፈተና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መድኀኒት ፡ አምኖ ፡ መ ዳን ፡ ለጤና ፡ መሆኑን ፡ ዐውቀን ፡ መርጠን ፡ እንድ ናምነው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ማዳን ፡ ለባለመድኀኒቶች ፡ ገንዘባቸው ፡ አለመሆኑን ፡ ከአዳም ፡ ጀምሮ ፡ እስካሁን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንኳ ፡ ከሞት ፡ ያዳኑት ፡ አለመኖሩን ፡ አስተውል ፤ ይልቁንም ፡ እነሱው ፡ ራሳቸው ፡ በመሞታቸው ፡ ያስረዳሃል ።

መድኀኒታቸው ፡ አዳኝ ፡ አለመሆኑ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ በማረው ፡ ጊዜ ፡ እንዱ ፡ ድኖበት ፡ የነበረ

ውን ፡ መድኀኒት ፡ እግዚአብሔር ፡ በፈረደበት ፡ ጊዜ ፡ ቢጠጣ ፡ እለመዳኑ ፡ ያስረዳሃል ፤ ስለዚህ ፡ ሰው ፡ በታመመ ፡ ጊዜ ፡ በ፫፻፷፭ ፡ ቍጥር ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ ፫ ፡ ጊዜ ፡ እያደረግኽ ፡ የሚ ምረው ፡ መሆኑን ፡ በተቀደሰው ፡ ማዳኛ ፡ ከጠ የቀ ፡ በኋላ ፡ መዓት ፡ ከፈረደበት ፡ አምላኩ ፡ ምሕ ረት ፡ ይለምን ፡ እንጂ ፤ የሱን ፡ ፍርድ ፡ ለመገል በጥ ፡ ከማይችሉ ፡ ባለመድኀኒት ፡ ነን ፡ ከሚሉ ፡ ሰዎች ፡ መድኀኒት ፡ አይለምን ።

ሕመምህን ፡ ግን ፡ ሐኪም ፡ ወይም ፡ ወጌሻ ፡ መር ምሮ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ አትብላ ፡ ወይም ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ አትጠጣ ፡ ብሎ ፡ የከለከለህን ፡ ነገር ፡ ቢያድ ንህም ፡ ባያድንህም ፡ ተወው ፡ እንጂ ፡ ለሆድህ ፡ ተበልጠህ ፡ የተከለከለውን ፡ ነገር ፡ አትብላ ።

በልተህም ፡ ብትገኝ ፡ በበሽታ ፡ ላይ ፡ ቅሌትና ፡ ሆ ዳምነትን ፡ ትጨምራለህ ፡ እንጂ ፡ አይረባህምና ፤ ተው ፡ ያለህን ፡ ቈርጠህ ፡ ተወው ።

ይልቁንም ፡ በመብል ፡ ለሚነሣ ፡ ደዌ ፡ መብል ፡ መጨመር ፡ በጠጅ ፡ ለሰከረ ፡ ጠጅ ፡ እንደ ፡ መጨ መር ፡ ያለ ፡ ነውና ፡ ያመመህ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ዐይነት ፡ መብል ፡ በማብዛትህ ፡ ነው ፡ ተው ፡ ያለ ህን ፡ ቈርጠህ ፡ ተወው ።

የሚበላውንም ፡ ነገር ፡ ያንኑ ፡ ጥንት ፡ የለመድከ ውን ፡ መብል ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ከንዲህ ፡ ያለ



ው ፡ አቀላቅለህ ፡ ብላ ፡ ብሎም ፡ የሚያዝህን ፡ ብታደ ርግ ፡ ያንኑ ፡ ምግብህን ፡ እንደ ፡ ሰውነትህ ፡ ዐቅም ፡ ገምቶ ፡ ማሰናዳቱ ፡ ነውና ፡ እንዳዘዘህ ፡ እየተመ ገብህ ፡ ደዌህን ፡ በእኩቴት ፡ ተቀበለው ፡ እንጂ ፡ ሲያ ድንም ፡ ብታይ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ አራተኛውን ፡ መድ ኀኒት ፡ አታድርግ ፡ (ስለ ፡ አባት ፡ እናት ፡ ም ፡ ፵፱) ።

ምዕራፍ ፡ ፴ ።

## ስለ ፡ ቅዳሜ ፡ አከባበር ፡ ምርምር ።

፩፻፲፱ ፤ ግማሾች ፡ በብሉይ ፡ የተጻፈውን ፡ ይዘው ፡ ብትሠሩ ፡ ኀጢአት ፡ ይሆንባችኋል ፡ አትሥሩ ፤ ግማሾቹ ፡ በሐዲስ ፡ የተጻፈውን ፡ ይዘው ፡ ብታከ ብሩ ፡ አይሁድን ፡ በመምሰል ፡ ኀጢአት ፡ ይሆን ባችኋል ፡ እያሉ ፡ የሰውን ፡ ልብ ፡ ስለሚያስቸግሩ ።

አንደኛ ፤ ቅዳሜ ፡ ሳይሠራ ፡ ቢያልፍ ፡ ሰውን ፡ የሚጐዳ ፡ እንደ ፡ ሐዋርያት ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ ሲገኝ ፡ በሚመስለው ፡ ችግር ፡ አይከልከል ፡ የሐዋርያት ፡ እሸት ፡ መቍረጥ ፡ አብነት ፡ ነውና ።

ሁለተኛ ፤ ሰው ፡ ለበሽተኛ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ነገ ር ፡ ቢሠራለት ፡ ባይከለከል ፡ ለዚህም ፡ ጌታ ፡ ለድ ውያን ፡ የሠራው ፡ አብነት ፡ ነውና ።

ሦስተኛ ፤ ሳይቈረጥ ፡ የተቀመጠ ፡ እንሥቶ ፡ ለማ ምጣት ፡ የሸከም ፡ ነገር ፡ አይከልከል ፡ ለዚህም ፡

የመፃጉዕ ፡ አልጋ ፡ መሸከም ፡ የጌታ ፡ መንገድ ፡ መሄድ ፡ የሀገራችን ፡ ገበያ ፡ መልመድ ፡ እብነት ፡ ነውና ።

በትዳሚ ፡ የማይሠራ ፡ ከሰኞ ፡ በመቄየቱ ፡ ሰው ፡ የሚጐዳበት ፡ ካልሆነ ፡ ለሥራ ፡ ተጓጕቶ ፡ ለንብ ረት ፡ ተደልቶ ፡ አይሠራ ።

ሁለተኛ ፤ ድንጋይ ፡ አይፈለጥ ፡ ዕንጨት ፡ አይቈ ረጥ ፡ ብረት ፡ አይቀጥቀጥ ፡ እሰኞ ፡ ድረስ ፡ የሚ በላ ፡ ካልጠፋ ፡ በቀር ፡ እኽልም ፡ አይፈጭ ፡ ማገ ዶም ፡ አይሰበር ።

ሦስተኛ ፤ እርሻም ፡ አይታረስ ፤ ቦይም ፡ አይገመስ፤ ጋይም ፡ አይታፈሥ ፤ ብለህ ፡ ልብን ፡ መዛኝ ፡ አካልህን ፡ ታዛዥ ፡ አድርገህ ፡ ባገባብህ ፡ ብትወስ ነው ፡ መልካም ፡ ይመስላል ፡ (ስለ ፡ አባት ፡ እናት ፡ ም ፡ ፵) ።

ምዕራፍ ፡ ፴፩ ።

## ላስተማሪና፡ተማሪ፡ጥቅም፡የትምርት፡ምርምር።

፩፻፳ ፤ ሰው ፡ ካገሩ ፡ መምር ፡ የሚያገኘውን ፡ ያገሩን ፡ ሳይማር ፡ የፈረንጆች ፡ ትምርት ፡ የተማረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ያገሩን ፡ ማጣራ ቱን ፡ ትቶ ፡ በሰው ፡ አገር ፡ ትምርት ፡ የሚለ



ውጥ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ጠጅ ፡ ስካር ፡ በየጠባዩ ፡ ዐይ ነት ፡ ይጐዳዋል ።

ንቁውን ፡ ሰው ፡ የገዛ ፡ አገሩን ፡ ያስድበዋል ፤ ያቀለዋል ፤ ያስለፈልፈዋል ፤ ያስወሰልተዋል ።

ዝግተኛ ፡ ሰው ፡ ያገኘ ፡ እንደሆን ፡ ያዝለዋል ፤ ያስንፈዋል ፤ ያደኸየዋል ። ቅን ፡ ሰው ፡ ያገኘ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ አእምሮውን ፡ ያስበትነዋል ፤ ያዋልለ ዋል ፡ የሚይዘውን ፡ አዳር ፡ ያስጠፋዋል ።

ብርቱ ፡ ሰው ፡ ሲማረው ፡ ያኰራዋል ፤ ያስደፍረ ዋል ፤ ከሰው ፡ ያጣላዋል ።
ትጉ ፡ ሰው ፡ ሲማረው ፡ ቶሎ ፡ ይሞታል ።

ጥያቄ ።

፩፻፳፩ ፤ እንግዲህ ፡ ምን ፡ ጠባይ ፡ ያለው ፡ ቢማረው ፡ ይሻላል ።

ምላሽ ።

፩፻፳፪ ፤ ከጠባይ ፡ የዋህነት ፡ ከዕውቀት ፡ መንፈሳዊ ነት ፡ ያለው ፡ ሲማር ፡ ይጠቀማል ። ሁለቱን ፡ እንኳ ፡ የያዘ ፡ ቢታጣ ፡ የዋህነት ፡ ብቻ ፡ የያዘ ፡ ሲማር ፡ ጥቂት ፡ ይሻላል ።

ጥያቄ ።

፩፻፳፫ ፤ ፈረንጆች ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ጠባይ ፡ እያለባ ቸው ፡ ሲጠቀሙ ፡ እኛ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ተጐዳንበት ።

ምላሽ ።

፩፻፳፱ ፡ የሰው ፡ ናላ ፡ እንደ ፡ ቅቤ ፡ እንክብል ፡ ያለ ፡ ነው ፡ የቅቤ ፡ እንክብል ፡ ከቀዝቃዛ ፡ ቦታ ፡ ያኖሩት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አካሉ ፡ ሳይፈርስ ፡ ቅባቱ ፡ ሳይፈስ ፡ ይገኛልና ፡ የባለቤቱ ፡ ዐቅም ፡ የቻለውን ፡ ያኽል ፡ እየከፈለ ፡ ለመሥራት ፡ ጊዜ ፡ ያገኝና ፡ አሳቡን ፡ ሁሉ ፡ ይጨርስበታል ።

የቅቤ ፡ እንክብል ፡ ከሞቃት ፡ ቦታ ፡ የተቀመጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አካሉም ፡ ሙቀቱ ፡ እስኪያቈየው ፡ ጥቂት ፡ ብቻ ፡ ቈይቶ ፡ ቶሎ ፡ ይፈርሳል ፤ ቅባቱም ፡ ይፈሳል ።

ስለዚህ ፡ ለባለገንዘቡ ፡ ቅቤው ፡ ቶሎ ፡ ያለልክ ፡ እየፈጠነ ፡ የሚፈስበት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ቢቀባውም ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ጠልቆ ፡ ሳይገባ ፡ የላይ ፡ ቍርበቱን ፡ ብቻ ፡ እያወዛ ፡ በመፍሰስ ፡ ያልቅበትና ፡ በጊዜው ፡ ማጠር ፡ ቅባቱ ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ስላልገባለት ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ የማይጠቅመው ፡ ይሆናል ።

አቅልጠም ፡ በብዙ ፡ ቢጠጣው ፡ መራራ ፡ ሐሞት ፡ ጨምሮ ፡ ምላሽ ፡ ሆኖ ፡ ይወጣበታል ።

እንደዚሁም ፡ ሁሉ ፡ የኛ ፡ ናላ ፡ ተፈጥሮ ፡ የተቀመጠበት ፡ የፀሓይ ፡ ሙቀት ፡ በሙሉ ፡ ከሚያርፍበት ፡ ከሞቃት ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ነውና ፡ ቅቤውም ፡ አእምሯችን ፡ ቶሎ ፡ የሚቀልጥብን ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ስንማር ፡ የመዠመሪያው ፡ ዕውቀታችን ፡ ቶሎ ፡



ይገባናል ። ስለ ፡ መቅለጡ ፡ ግን ፡ ዕውቀታችን ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ጠልቆ ፡ ሳይገባ ፡ በቶሎ ፡ ይቀልጥና ፡ በምኞትና ፡ በመናገር ፡ ብቻ ፡ ላዩን ፡ ብልኀ ፡ እንመስላለን ፡ እንጂ ፡ ውስጣችን ፡ ባዶ ፡ ይሆንብናል ።

ለመሥራት ፡ ትጋታችንን ፡ የአየራችን ፡ ወሰን ፡ አላሳልፈው ፡ ይልና ፡ እንደ ፡ ፈረንጅ ፡ መሆን ፡ ያምረውና ፡ ከነሱ ፡ መድረስ ፡ ያቅተውና ፡ ልቡናውን ፡ አበሳጭቶ ፡ ጠባዩን ፡ አበላሽቶ ፡ የሚጎዳው ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።

ከቀለጠልኝ ፡ ብሎ ፡ በብዙ ፡ ቢጠጣው ፡ መራራ ፡ ሐሞት ፡ ጨምሮ ፡ እንዲያስመልሰው ፡ ከገባኝ ፡ ብሎ ፡ በተማረው ፡ እየለካ ፡ በመጠን ፡ ሳይሠራ ፡ በላይ ፡ በላዩ ፡ ቢጨምርበት ፡ ካፉም ፡ የንቀት ፡ የድፍረት ፡ የመንቀፍ ፡ መራራ ፡ ቃል ፡ ይወጣበታል ።

ለሕይወቱም ፡ መራራ ፡ ሞት ፡ ይመጣበታል ፤ ናላውም ፡ ይዞርበታል ።

ጥያቄ ።

፩፻፴፩ ፡ የአየር ፡ ኃይል ፡ የሰውን ፡ ምኞት ፡ ለመሥራት ፡ የሚከለክለው ፡ በኛ ፡ አገር ፡ ብቻ ፡ ነውን ፡ በሁሉም ፡ ይደረጋል ።

ምላሽ ።

፩፻፴፩ ፡ ሁሉም ፡ በያገሩ ፡ እንዳየሩ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሚኖረው ፡ እንደ ፡ ምኞቱ ፡ አይኖርም ። ይህንም ፡

ለመረዳት ፡ ብትሻ ፡ ፈላስፎች ፡ እንደ ፡ መዘኑት ፡ የግሎብን ፡ መሥመርና ፡ የጂዖግራፊውን ፡ ታሪክ ፡ አስተውል ። ይህ ፡ አየር ፡ የሚመራው ፡ ጠባይ ፡ አብዛኛው ፡ ሰው ፡ በየያዘው ፡ የተገመተ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ካንድ ፡ አገር ፡ ላይ ፡ በዝቶ ፡ የሚገኘው ፡ ከሌላው ፡ እያነሰ ፡ በአምላክ ፡ ዕድል ፡ ይገኛል ፤ ይህ ፡ የሚያደረገው ፡ አለባሕሪዋ ፡ የበለዓም ፡ አህያ ፡ እንደ ፡ ተናገረችው ፡ ያለ ፡ በተአምራት ፡ የሚሠራ ፡ ነው ።

ጥያቄ ።

፩፻፳፯ ፡ እማስተውለው ፡ ማናቸው ፡ ነው ።

ምላሽ ።

፩፻፳፰ ፤ በግሎቡ ፡ መሥመር ፡ ወደ ፡ በረድም ፡ ወደ ፡ ፀሓይም ፡ የሚቀርብበት ፡ ከፍታና ፡ ዝቅታ ፡ አለው ።

ስለዚህ ፡ በዓለም ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ የትምርት ፡ መሻታቸው ፡ አንድ ፡ ሲሆን ፡ የዕውቀታቸው ፡ መበላለጥ ፡ እንደ ፡ ደረጃቸው ፡ ከፍታ ፡ እንደ ፡ አየራቸው ፡ አቀዛቀዝ ፡ ዕውቀታቸው ፡ መበላለጡን ፡ አስተውል ።

አፍሪቃ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እስክንድርያ ፡ ዐረቢያ ፡ ህንድያ ፡ እነዚህ ፡ የአየር ፡ ሙቀት ፡ ከሚያርፍባቸው ፡ ከሦስት ፡ መሥመር ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ እንዳየራቸው ፡ ከፍታ ፡ እንዳቸው ፡ ካንዳቸው ፡ ጥቂት ፡ ጥቂትም ፡ ቢበላለጡ ፡ ምንም ፡ ለትም



ርት ፡ ቢተጉ ፡ በድንበርም ፡ ቢቃረቡ ፡ አበላያቸው ፡ እንዳሉት ፡ እንደ ፡ አውሮፖች ፡ መሆንን ፡ እስካሁን ፡ አላገኙትም ።

ይህ ፡ አየር ፡ ቢከለክላቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ መማር ፡ ጠፍቷቸው ፡ ቦታ ፡ ርቋቸው ፡ አይደለም ።

ከአውሮፖችም ፡ ቢሆን ፡ ትምርታቸው ፡ እኩል ፡ ሲሆን ፡ እንደ ፡ ደረጃቸው ፡ ከፍታ ፡ ዕውቀታቸው ፡ ይበላለጣል ።

ኢጣልያ ፡ ከፈረንሳዊ ፡ ፈረንሳዊ ፡ ከጀርመን ፡ ጀርመን ፡ ከእንግሊዝ ፡ ትምርታቸው ፡ አንድ ፡ ሲሆን ፡ የመጠቀም ፡ ዕውቀታቸው ፡ የባሕርይ ፡ ርጋታቸው ፡ እስካሁን ፡ አልተካከለም ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ የአየር ፡ ኃይል ፡ ነው ።

ጥያቄ ።

፩፻፳፱ ፤ በላይኛው ፡ አየር ፡ የተፈጠሩት ፡ ለምን ፡ ለምን ፡ ሥራ ፡ ነው ፡ አየራቸው ፡ የሚረዳቸው ።

ምላሽ ።

፩፻፴ ፤ ለብርታት ፡ ለትጋት ፡ ለመርጋት ፡ ለብልጠት ፡ ለምግባር ፡ ይረዳቸዋል ።

ጥያቄ ።

፩፻፴፩ ፤ የኛስ ፡ አየር ፡ ለምን ፡ ሥራ ፡ ነው ፡ የሚረዳን ።

ምላሽ ።

፩፻፴፪ ፤ ለንቃት ፡ ለፍጥነት ፡ ላንደበት ፡ ንግግር ፡ ለየውሁት ፡ ይረዳል ።

ጥያቄ ።

፩፻፴፫ ፤ እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ አውሮፖች ፡ በብርታትና ፡ በትጋት ፡ ካጠሩት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ማናቸውን ፡ ዐይነት ፡ ብንማር ፡ ይቀናን ፡ ይመስልሃል ።

ምላሽ ።

፩፻፴፬ ፤ ካንደበት ፡ ሥራ ፡ ፍርድና ፡ ሙግታቸውን ። ከእጅ ፡ ሥራ ፡ ወታደርነታቸውን ፡ ብንማር ፡ ለንቃት ፡ ላንደበት ፡ እየራችን ፡ ስለ ፡ ረዳን ፡ ከነሱም ፡ እየተሻልን ፡ ለመሥራት ፡ እንችላለን ።

ጥያቄ ።

፩፻፴፭ ፤ ካዳር ፡ ሥራቸውስ ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ምኑን ፡ ብንማር ፡ ምን ፡ ምኑን ፡ ብንተው ፡ ይሻላል ፡ ይመስልሃል ።

ምላሽ ።

፩፻፴፮ ፤ ከምርምራቸው ፡ ከብልጠታቸው ፡ ከግምት ፡ ሚዛናቸው ፡ ትዠስንታችን ፡ እየከለከለን ፡ አንደርስባቸውም ።

ለሕይወታችን ፡ በግድ ፡ ለሚያሻን ፡ በዶማ ፡ በማረሻ ፡ በመርፌ ፡ በወስፌ ፡ የሚሠራውን ፡ ጕልሕ ፡



ጕልሕ ፡ የእጅ ፡ ሥራቸውን ፡ ለመማር ፡ ንቃታችን ፡ እየረዳን ፡ ይቻለናል ፤ ግን ፡ ሥራ ፡ እሚሰፋበት ፡ በብርታት ፡ እጅ ፡ በንቃት ፡ ብቻ ፡ ስላልሆነ ፡ ለማስፋት ፡ ያቅተናል ፡ እንጂ ፡ ለመማሩ ፡ ቢሆን ፡ ይቻለናል ።

ጥያቄ ።

፩፻፴፯ ፤ ማስፋቱ ፡ ካልተቻለን ፡ ትምርቱስ ፡ ምን ፡ ይጠቅመናል ።

ምላሽ ።

፩፻፴፰ ፤ የሥራ ፡ ዕውቀት ፡ የሚሰፋው ፡ ለንብረት ፡ አንድነት ፡ ለሥራ ፡ ተጋጋዥነት ፡ እሚሆን ፡ ማኅበር ፡ አቁሞ ፡ ነው ፡ እሚሠራው ።

ያንድነት ፡ ማኅበር ፡ የሚቆመው ፡ በራድነት ፡ ካለው ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በሞቃ ፡ አየር ፡ ላይ ፡ ከሚኖር ፡ ከትኵስ ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ንቃትና ፡ እንደበት ፡ ትኵስነት ፡ ይበዛበታልና ፤ ታግሥ ፡ በርዶ ፡ ማኅበር ፡ ለማቆም ፡ አይቻለውምና ፤ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ሥራ ፡ ለማስፋት ፡ ሳይቻለው ፡ ይቀራል ።

ይህንም ፡ ለመረዳት ፡ የሚጣሉበት ፡ ንብረት ፡ ይሁንም ፡ ሳይኖራቸው ፡ በገዳም ፡ ያሉትን ፡ የመነኮሳት ፡ ማኅበር ፡ ተስማምቶ ፡ ለማቆም ፡ ዘወትር ፡ እንደሚያስቸግራቸው ፡ እስተውል ።

ለማስፋትም ፡ ባይቻለን ፡ ለመጥቀሙ ፡ ግን ፡ የእጅ ፡ ሥራን ፡ ከተማርን ፡ ባቅሙ ፡ ልክ ፡ ይጠቅመናል ።

ጥያቄ ።

፬፻፹፱ ፤ እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ የኛ ፡ ሕዝብ ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ ውን ፡ አስተማሪው ፡ እንደ ፡ ምን ፡ አድርጎ ፡ ተማ ሪው ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ሆኖ ፡ ቢማርና ፡ ቢሠራው ፡ ይሻል ፡ ይመስልሃል ።

ምላሽ ።

፬፻፺ ፤ ለጠባዩ ፡ የሚቀናውን ፡ ጠርና ፡ የቃል ፡ ንግግርን ፡ አብዝተን ፡ ስናስተምረው ፡ ሁከት ና ፡ ሙግት ፡ በዝቶ ፡ በነፍሱ ፡ ኀጢአት ፡ በሥ ጋው ፡ ድኽነት ፡ በትምርታችን ፡ እንደ ፡ አሸመ ጠው ፡ ተማሪዎችን ፡ ከሰባት ፡ ከፍሎ ፡ ሦስቱን ፡ እጅ ፡ በዶማና ፡ በማረሻ ፡ ለሚሠራው ፡ ያዝርዕትና ያትክልት ፡ ማስተማር ፤ ሁለቱን ፡ እጅ ፡ በንዝር ትና ፡ በጣት ፡ በመርፌና ፡ በወስፌ ፡ እሚሠራውን ፡ የልብስን ፡ ዐይነት ፡ ማስተማር ፤ አንዱን ፡ እጅ ፡ በጠርና ፡ በነገር ፡ ለሚሠራ ፡ አስተዳዳሪነት ፡ ማስ ተማር ፤ አንዱን ፡ እጅ ፡ በመጥረቢያና ፡ በመዶሻ ፡ የሚሠራውን ፡ ለመኖሪያና ፡ ለመሣሪያ ፡ ዐይነት ፡ ማስተማርና ፡ ይህ ፡ የተቈጠረው ፡ በንቃትና ፡ በፍጥነት ፡ ጠባይ ፡ የሚሠራ ፡ ነውና ፡ አዳር ፡ አዳሩን ፡ ለየራሱ ፡ ይዞ ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ ሥራና ፡ ሥራ ውን ፡ እየተለዋወጠ ፡ ቢኖር ፡ ይሻለው ፡ ይመስላል ።



ጥያቄ ።

፬፻፺፩ ፤ በሀገር ፡ ድኾች ፡ እንዳይበዙ ፡ የየሥራቸውን ፡ አለዋወጥ ፡ በምን ፡ ዐይነት ፡ ተካክለው ፡ ሁሉም ፡ ይጠቀማሉ ።

ምላሽ ።

፬፻፺፪ ፤ መጀመሪያ ፡ ያንዱን ፡ ሥራ ፡ አንዱ ፡ ደርቦ ፡ አለመጠን ፡ እየከበረ ፡ አንዱ ፡ የሠራውን ፡ የሚፈ ልግለት ፡ የጐልበቱን ፡ ዋጋ ፡ የሚገዛው ፡ እያጣ ፡ አለመጠን ፡ እንዳይደኸይ ፡ ሰውን ፡ ባንዳንዱ ፡ ሥራው ፡ የሚያቆም ፡ የማያስተላልፍ ፡ ደንብ ፡ መስጠት ፡ ነው ።

ሁለተኛ ፤ ሠርቶ ፡ የሚሸጠው ፡ ሁሉ ፡ ከሚፈል ገው ፡ ተርፎ ፡ የሠራተኛው ፡ ጕልበት ፡ ከንቱ ፡ እን ዳይሆን ፡ የሚያስፈልገውን ፡ በቍጥር ፡ መዝና ፡ በየልኩ ፡ የሚማርበት ፡ ደንብ ፡ መስጠት ፡ ነው ።

ሦስተኛ ፤ ሠራተኛ ፡ ከሠራው ፡ ላይ ፡ የገንዘብ ፡ ግብር ፡ እየሰጠ ፡ ከሹም ፡ ትእዛዝ ፡ የሚያርፍበት ፤ በበጎ ፡ ምግባር ፡ ለመፀመድ ፡ ግዴታ ፡ ባልሆነባ ቸው ፡ ባንዳንዶቹ ፡ ደብተሮች ፡ ላይ ፡ የደረሰባ ቸውን ፡ ጕዳት ፡ እያስተዋልን ፡ ያፍ ፡ ትምርት ፡ ብቻ ፡ የተማረውን ፡ በጕልበት ፡ የሚሠራ ፡ ወይም ፡ መንፈሳዊ ፡ ወይም ፡ ሥጋዊ ፡ እንዲሠራ ፡ ማድ ረግ ፡ ባፉ ፡ ብቻ ፡ ላውራ ፡ ግዴታ ፡ ያለበት ፡ ሥራ ፡ አልሠራም ፡ ለሚለውም ፡ ሥራ ፡ ፈት ፡

በጐልበቱ ፡ ሥራ ፡ የሚቀጣበት ፡ ደንብ ፡ መስጠት ፡ ነው ።

ጥያቄ ።

፩፻፵፫ ፡ ሰው ፡ በትምርት ፡ ማወቁ ፡ ከበጎ ፡ ባሕርይ ፡ ምን ፡ ምን ፡ ያገኛል ።

ምላሽ ።

፩፻፵፬ ፡ ከሰው ፡ ካራቱ ፡ ባሕርያቱ ፡ በሁለቱ ፡ በውሃና ፡ በመሬት ፡ ባሕርይ ፡ የሚሠሩትን ፡ የእፍአ ፡ ጠባዮች ፡ በትምርት ፡ ያገኛቸዋል ። ይኸውም ፡ ላዳሩ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ሁሉ ፡ ተግቶ ፡ ባልንጀራውንም ፡ አታሎ ፡ አሞኝቶ ፡ ተሻምቶ ፡ የሚሠራው ፡ ብልጠት ፤ ችሎ ፡ አሳልፎ ፡ ረግቶ ፡ ገምቶ ፡ የሚሠራው ፡ ትዕግሥት ፤ እኒህ ፡ ሁለቱ ፡ ጠባያት ፡ በትምርት ፡ ይገኛሉ ።

በእሳት ፡ በነፋስ ፡ ባሕርያችን ፡ የምንሠራቸው ፡ ብልኅነት ፡ መመራመር ፡ ዕውቀት ፡ የሚባለው ፡ ማመዛዘን ፡ ግን ፡ የውስጥ ፡ ባሕርያት ፡ ናቸውና ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ይገኛሉ ፡ እንጂ ፤ ከትምርት ፡ አይገኙም ።

ጥያቄ ።

፩፻፵፭ ፡ ብልኅት ፡ የሌለበትም ፡ ብልጠት ፤ ብርታት ፡ የሌለበትም ፡ ትዕግሥት ፡ የሚጠቅመው ፡ አይደለምና ፡ ባራቱ ፡ ባሕርያት ፡ የሚሠሩትን ፡ አራቱ ፡



ጠባያት ፡ ሰው ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ ቢፈልግ ፡ ያገኛቸዋል ።

ምላሽ ።

፩፻፵፮ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በመውደድ ፡ ፈቃዱን ፡ ስትሠራ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በማመን ፡ ቸርነቱን ፡ በጸሎት ፡ ስትለምን ፡ በዚህ ፡ በሁለቱ ፡ ከውስጣችን ፡ ብልኅትና ፡ ብርታትን ፡ አመጣጣቸውን ፡ ስናይ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ይገኛሉ ።

ላስተማሪ ፡ በመታዘዝ ፡ ለትምርት ፡ በመትጋት ፡ በእፍአው ፡ ላለው ፡ አካል ፡ በእጅና ፡ በእፋችን ፡ የምንሠራውን ፡ የብልጠትና ፡ የትዕግሥትን ፡ ሥራ ፡ አመጣጣቸው ፡ በግልጽ ፡ እየታየ ፡ ከመምህራን ፡ እናገኛለን ። እኒሁም ፡ ብልጠትና ፡ ትዕግሥት ፡ የሚባሉት ፡ ብልጠት ፡ የብልኅት ፡ መማሪያ ፡ ትዕግሥት ፡ የብርታት ፡ መማሪያ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ትዕግሥትና ፡ ብልጠት ፡ ሥራም ፡ ሠራም ፡ የማይባሉ ፡ ናቸውና ፤ ስለዚህ ፡ ብርታትና ፡ ብልኅትን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ሳያገኝ ፡ ልማር ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ በልማድ ፡ የሚያጠናው ፡ ትምርት ፡ ትምርቱ ፡ መጥፊያ ፡ ይሆንበታል ፡ እንጂ ፡ መልሚያው ፡ አይሆንለትምና ፡ ለጥቅሙ ፡ ጥበብ ፡ የሚማር ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በፊት ፡ ፈጣሪውን ፡ በውቆ ፡ የሚወደውን ፡ ሥርቶ ፡ ደጅ ፡ ይጥና ፤ ቀጥሎ ፡ የፈጣሪውን ፡ ቸርነት ፡ እምኖ ፡ የሚሠራበትን ፡ ብ

ልጎት ፡ የሚችልበትን ፡ ብርታት ፡ የጥበብና ፡ የኃይል ፡ ባለጸጋ ፡ የሆነ ፡ ፈጣሪውን ፡ ይለምን ።

ይህንም ፡ ልትረዳ ፡ ብትሻ ፡ የአፍኣ ፡ ጥበብ ፡ ያልቸገረው ፡ ሰሎሞን ፡ በመንግሥት ፡ ሥራው ፡ ከበረታ ፡ በኋላ ፡ በአፍኣ ፡ የሚሠራው ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ ጥበብ ፡ አለመሆኑን ፡ ዐውቆ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ የውስጥ ፡ ጥበብን ፡ ሽቶ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ መለመኑን ፡ አስተውል ፡ (ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልእ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ እስከ ፡ ፲) ።

ጥያቄ ።

፩፻፵፯ ፤ ከትምርት ፡ ሁሉ ፡ የሚበልጠው ፡ ማናቸው ፡ ትምርት ፡ ነው ፡ ለነፍስና ፡ ለሥጋ ፡ የሚጠቅመው ።

ምላሽ ።

፩፻፵፰ ፤ ከሁሉ ፡ በፊት ፡ በትምርቱ ፡ ፈጣሪውን ፡ ዐውቆ ፡ ለሚሠራው ፡ ሁሉ ፡ መሣሪያ ፡ እንዲሆነው ፡ የሕክምናን ፡ ጽሕፈት ፡ ፊት ፡ ዠምሮ ፡ ሁለተኛ ፡ ቀጥሎ ፡ ሥጋዊ ፡ ጥበብ ፡ ሲፈልገው ፡ ለሰው ፡ ዋና ፡ ገንዘቡ ፡ አካሉ ፡ ነውና ፡ የሕክምና ፡ ትምርት ፡ ከሁሉ ፡ የሚበልጥ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የአካልን ፡ ወጌሻነት ፡ የሕክምናን ፡ ሥራ ፡ ቢማር ፡ ከእግዚአብሔርም ፡ ትእዛዝ ፡ ደወይኩና ፡ ተሞቃሕኩ ፡ ይፈጸምበታል ፤ ለቅንንነት ፡ ለርኅራኄም ፡ ጠባይ ፡ ይመቻል ።



የሰው ፡ ሕይወት ፡ የሚጸናበት ፡ በምግብ ፡ ነውና ፡ የእርሻና ፡ የአትክልትን ፡ የከብትን ፡ ሕክምና ፡ የምግብን ፡ ትንተና ፡ ይማር ፡ በዚህም ፡ ርኅብኩና ፡ ጸማእኩ ፡ ይፈጸምበታል ፤ ለቸርነትና ፡ ለትሕትናም ፡ ጠባይ ፡ ይመቻል ።

አራተኛ ፡ የጥጥን ፡ አዘራሩን ፡ የልብስን ፡ የቤትን ፡ አሠራሩን ፡ ለማወቅ ፡ መሐንዲስነት ፡ ይማር ፤ በዚህም ፡ ነግደ ፡ ኮንኩና ፡ ዐረቀ ፡ ይፈጸምበታል ፤ ለትጋት ፡ ለብርታት ፡ ባሕርይ ፡ ይመቻል ።

እነዚህ ፡ አራቱ ፡ ዐይነት ፡ የእጅ ፡ ጥበብ ፡ መንገድነታቸው ፡ የጽድቅ ፡ ናቸውና ፡ ለነፍሱም ፡ ቢያደላ ፡ ለዘለዓለም ፡ ሕይወቱ ፡ ለሥጋው ፡ ቢያደላ ፡ ለጥቂት ፡ ቀን ፡ ንብረቱ ፡ አጥብቀው ፡ ይመቹታልና ፤ ከሦስቱ ፡ ዐይነት ፡ አንዳቸውን ፡ ለመማር ፡ የቀናውን ፡ መርጦ ፡ ያጥና ፤ ከትምርት ፡ ሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ትምርት ፡ ይሆንለታል ።

ፍጹም ፡ ጽድቅም ፡ ቢፈልግ ፡ በዚሁ ፡ ሥራው ፡ ያገኛታል ።

ጥያቄ ።

፩፻፵፱ ፤ ምነው ፡ ፍርድ ፡ ተምሮ ፡ ድኻ ፡ ቢጠብቅ ፡ የቃል ፡ ሥልጣኔ ፡ ዘዴ ፡ ፀለቲካ ፡ ተምሮ ፡ ቢመክር ፡ ቢመረምር ፤ ሰልፍ ፡ ተምሮ ፡ ጥቃት ፡ ቢጠብቅ ፤ ሒሳብ ፡ ዐውቆ ፡ ንግድ ፡ ቢያሰፋ ፡ ይጠቀም

የለምን ፤ ከቶውንም ፡ ጌታ ፡ ሆኖ ፡ ከሰው ፡ በላይ ፡ የሚሆነው ፡ እኒህን ፡ ሲማር ፡ አይደለምን ።

ምላሽ ።

፩፻፶፯ ፤ እውነት ፡ ነው ፤ የሥጋውን ፡ መክበር ፡ እኒህን ፡ ቢማር ፡ ያገኛል ።

የነፍስና ፡ የሥጋውን ፡ ክብር ፡ ግን ፡ እኒህን ፡ በመማር ፡ አያገኝም ፤ በነፍሱ ፡ ትዕቢት ፡ ተንኰል ፡ ጭካኔ ፡ ቅናት ፡ ሐሰት ፡ ከበው ፡ ተዋግተው ፡ ይማርኩታልና ፡ እኒህ ፡ ሦስቱ ፡ መንገድነታቸው ፡ የኀጢአት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በግድ ፡ ወደ ፡ ኀጢአት ፡ ጐትተው ፡ ያስኰንኑታል ።

እንዳንድ ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ ያለ ፡ ዳኛ ፡ ለበጎ ፡ ግብር ፡ ሥራ ፡ ይዞ ፡ የሚዋጋ ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ ቢገኝ ፡ እንደሱው ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ በግድ ፡ ጽድቅና ፡ ኀጢአት ፡ ደባልቆ ፡ የሚሠራ ፡ ይሆናል ፡ እንጂ ፡ ፍጹምነትን ፡ ቢፈልግም ፡ አያገኘውምና ።

የነፍስና ፡ የሥጋን ፡ ጥቅም ፡ የሚያስገኙ ፡ ስላል ሆኑ ፡ በእእምሮው ፡ ባፋ ፡ ፍርድና ፡ ምክርን ፡ በጕልበቱ ፡ ንግድና ፡ ጣርን ፡ የተማረ ፡ ምንም ፡ ደግ ፡ ጠባይ ፡ ቢኖረው ፡ ጥቂት ፡ ጽድቅ ፡ ብዙ ፡ ኀጢአት ፡ ለመሥራት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሚቻለው ፡ ጽድቅን ፡ ምንም ፡ ቢወዳት ፡ አብዝቶ ፡ ለመሥራት ፡ እማይቻለው ፡ መሆኑን ፡ ስለ ፡ ተረዳ ፡ ስሎ



ሞን ፡ አታክብረኝ ፡ አታደኸየኝ ፡ ያለውን ፡ መካከለኛውን ፡ አናዎር ፡ የሚያስገኙ ፡ አጥብቀው ፡ የማያከብሩ ፡ አጥብቀው ፡ የማያደኸዩ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ከሥጋዊ ፡ ትምርት ፡ ሁሉ ፡ የእካልንና ፡ የምግብን ፡ ወጌሽነት ፡ የልብስንና ፡ የቤትን ፡ ሠራተኛነት ፡ የመረጥነው ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።

ስለ ፡ መረጥን ፡ ግን ፡ ሰው ፡ የታደለውን ፡ እንጂ ፡ የመረጠውን ፡ እማያገኝ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በግድ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የታደልነውን ፡ እንማራለን ።

ጥያቄ ።

፩፻፶፰ ፤ የእጅስ ፡ ሥራ ፡ ከመምህር ፡ ይገኛል ፡ የአእምሮ ፡ ሥራሳ ፡ ያለትምርት ፡ በጸሎት ፡ ብቻ ፡ እንዴት ፡ ይገኛል ።

እግዚአብሔርንስ ፡ ያለምክንያት ፡ ስጠኝ ፡ ማለት ፡ አይሆንምን ።

ምላሽ ።

፩፻፶፱ ፤ የአፍአ ፡ መምህራን ፡ የፈደሉን ፡ ዐይነት ፡ ለማሳየት ፡ እነሱ ፡ ለራሳቸው ፡ ተማሪዎች ፡ ናቸው ፡ የሰሙትን ፡ ያኸል ፡ ግዙፍ ፡ ቃላቸውን ፡ ከግዙፍ ፡ ገሯሯችን ፡ ያፈሱልናል ፤ ግዙፉንም ፡ ሥራቸውን ፡ ለግዙፍ ፡ ዐይናችን ፡ ያሳዩልናል ፤ ወደ ፡ ውስጡ ፡ እእምሯችን ፡ አግብተው ፡ ሊገልጡልን አይቻላቸውምና ።

ስለዚህ ፡ መምህራን ፡ ንባብና ፡ ትርጓሜ ፡ ማስጠና ታቸውን ፡ እንጂ ፡ ዕውቀት ፡ መስጠታቸውን ፡ ል ናምን ፡ አይገባንም ።

ይህንም ፡ ልትረዳ ፡ ብትሻ ፡ መድኀኒታችን ፡ ሲያ ስተምር ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ ለመረጣቸው ፡ ሐዋርያት ፡ ስንኳ ፡ በሕይወተ ፡ ሥጋው ፡ ሲያስተምራቸው ፡ የኖረው ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ውስጣቸው ፡ ገብቶ ፡ ሳይ ገለጥላቸው ፡ መኖሩን ፡ ዕውቀትን ፡ ጕልበትን ፡ የተቀበሉትን ፡ ከማስተማሩ ፡ ሳይሆን ፡ ከቸርነቱ ፡ ብቻ ፡ መሆኑን ፡ ታውቅ ፡ ዘንድ ፡ ዕውቀትን ፡ ከት ንሣኤ ፡ በኋላ ፡ ጕልበትን ፡ ከዕርገት ፡ በኋላ ፡ እንደ ገና ፡ በመቀበላቸው ፡ እስተውል ።

ይህንም ፡ ማድረጉ ፡ ዕውቀት ፡ መስጠት ፡ የመ ምራን ፡ ሥራ ፡ አለመሆኑን ፡ ሲያስረዳን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ዕውቀትና ፡ ትምርት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ለመስጠት ፡ ለእሱ ፡ ተስኖት ፡ አይደለም ።

ስለዚህ ፡ መምህራን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ስልክ ፡ መግሪያ ፡ ሁነው ፡ ባስተማሪው ፡ አምላክና ፡ በተማሪው ፡ ሰው ፡ መካከል ፡ ቃል ፡ ያቀባብላሉ ፡ እንጂ ፡ ዕውቀት ፡ የባሕርያቸው ፡ ገንዘብ ፡ ስላል ሆነ ፡ የተረዱትን ፡ እንኳ ፡ አስረድተው ፡ የተማሪ ውን ፡ ልብ ፡ ለመለወጥ ፡ ምስጢር ፡ ለመግለጥ ፡ ያቅታቸዋልና ፡ ስለዚህ ፡ ተማሪዎች ፡ ሁሉ ፡ ግዙ ፍ ፡ ንባብን ፡ ከፈጣሪ ፡ ረቂቅ ፡ ዕውቀትን ፡ ካስተ



ማሪ ፡ እናገኛለን ፡ ሳይሉ ፡ ንባብን ፡ ከመጻሕፍትና ፡ ከያስተማሪያቸው ፡ ፈልገው ፡ ዕውቀትን ፡ ግን ፡ የሚያገኙት ፡ በትጋትና ፡ በልመና ፡ ከአምላካቸው ፡ ሲፈልጉ ፡ ነውና ፡ አስተማሪዎች ፡ ከማስተማራቸ ው ፡ ተማሪዎች ፡ ከትምርታቸው ፡ አስቀድመው ፡ ይህንን ፡ የትምርት ፡ ዘዴ ፡ ይወቁ ።

(አበራ ፡ ወንጌል ፡ ገጽ ፡ ፭ ፡ እስከ ፡ ፬ ። ስለ ፡ አባት ፡ እናት ፡ ም ፡ ፳፬ ፡ ፳፪) ።

ምዕራፍ ፡ ፴፪ ።

## ስለ ፡ ጠንቋይ ፡ ወይም ፡ መነሆሴ ፡ ቃል ።

ጥያቄ ።

፬፻፶፫ ፡ በልሚ ፡ በውኔ ፡ እያለ ፡ የሚናገር ፡ ቃለኛን ፡ ሰው ፡ ነገሩ ፡ በተመሳሰለለት ፡ ጊዜ ፡ ሊሰሙት ፡ ሊቀበሉት ፡ ይገባልን ።

ምላሽ ።

፬፻፶፬ ፡ ሊሰሙት ፡ ሊቀበሉት ፡ የሚገባም ፡ የማይገ ባም ፡ አለ ፡ ሊሰሙት ፡ ሊቀበሉት ፡ የሚገባው ፡ ኀጢአትህ ፡ በዝቷል ፡ ፈጣሪህንም ፡ አስቈጥቷል ፡ ስለዚህም ፡ መዓት ፡ ታዞብሃልና ፡ በንስሓ ፡ ተመ ለስ ፡ ተጠጥተህም ፡ እልቅስ ፡ ለበደልከውም ፡

ካስ ፡ መልስ ፡ የሚልን ፡ ሰው ፡ በልሚም ፡ በውኃም ፡ ብሎ ፡ ቢነግርህ ፡ መበደልህ ፡ እውነት ፡ ከሆነ ፡ መካር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ጠንቋይ ፡ አይባልምና ፡ ሕልሙን ፡ ቢያየውም ፡ ባያየውም ፡ ስለ ፡ ቃሉ ፡ እገባብነት ፡ የሚወቅሥህን ፡ ሰምተህ ፡ አድርገኸውም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብታዝንበት ፡ አላደረግኸውም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብትጠበቅበት ፡ መልካም ፡ ነው ።

ሊሰሙት ፡ የማይገባው ፡ እንዲህ ፡ ያደረግህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ እንዲህ ፡ ስላደረግህ ፡ በዕድሜ ፡ ትኖራለህ ፡ በሀብት ፡ ትከብራለህ ፡ በመላቅ ፡ ትገዛለህ ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ነፍስን ፡ በምኞት ፡ መታመኗን ፡ አጕድሎ ፡ ለማስኮነን ፡ ልብን ፡ በትዕቢት ፡ ለማባከን ፡ ሥራን ፡ በውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ ለመበተን ፡ ለሰው ፡ ጠንቅ ፡ ለመሆን ፡ በሰይጣን ፡ ተንኰል ፡ የተላከ ፡ እሳች ፡ ሰው ፡ ነውና ፤ ጨዋም ፡ ሆኖ ፡ ዐውቃለሁ ፡ ብሎ ፡ ቢነግርህ ፡ መነኵሴም ፡ ሆኖ ፡ መስቀል ፡ ይዞ ፡ ቆብ ፡ ደፍቶ ፡ ቢነግርህ ፡ ካህን ፡ ሆኖም ፡ እራቆ ፡ እመሳስሎ ፡ ቢነግርህ ፡ አትስማው ፡ አትቀበለው ። በሱ ፡ አካል ፡ ተሰውሮ ፡ የመጣብህ ፡ ሰይጣን ፡ መሆኑን ፡ ዕወቅ ።

ሰይጣንም ፡ ባለቤቱ ፡ ባላወቀው ፡ ነገር ፡ እሰው ፡ ምላስ ፡ ላይ ፡ እየተቀመጠ ፡ ለመናገር ፡ መቻሉን ፡ አረጋዊ ፡ መንፈሳዊ ፡ እስተውልና ፡ እንደ ፡ ሰይጣን ፡ ቃል ፡ ቈጠረው ።



ጥያቄ ።

፬፻፺፫ ፡ ምንው ፡ በጎ ፡ ነገር ፡ ብትሠራ ፡ ወይም ፡ በጎ ፡ ነገር ፡ ሠርተሃልና ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ጥቅም ፡ ታዞልሃል ፡ ታገኛለህ ፡ ቢል ፡ ሰሚውም ፡ ደስ ፡ እያለው ፡ ከበጎ ፡ ግብር ፡ ይጨምርበታል ፡ እንዲህ ፡ አድርገህ ፡ የጾምህ ፡ የጸለይህ ፡ የመጸወትህ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሠርተህ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ደንብ ፡ ያቆምህ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ ትገዛለህ ፡ ትኖራለህ ፡ ቢለው ፡ ይህም ፡ እነጋገር ፡ ለሰሚውና ፡ ለተናጋሪው ፡ ኀጢአት ፡ ይሆንባቸዋልን ፡ ወይስ ፡ አይሆንባቸውም ።

ምላሽ ።

፬፻፺፬ ፡ ጾም ፡ ጸሎት ፡ ሰጊድ ፡ ምጽዋት ፡ በማትረብ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በመሥራት ፡ የሚደከመውን ፡ ድካም ፡ ሰው ፡ የአካል ፡ ወዙን ፡ የገንዘብ ፡ ደመወዙን ፡ ንጹሕ ፡ መሥዋዕት ፡ አድርጎ ፡ እንዲያቀርበው ፡ ፍጡር ፡ ለፈጣሪ ፡ ለመገዛቱ ፡ ምልክት ፡ ለመታዘዙ ፡ ምስክር ፡ አድርጎ ፡ ሰው ፡ ለአምላኩ ፡ ሊሠራለት ፡ የታዘዘ ፡ ሕግ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለሥጋዊ ፡ ፍትወት ፡ መፈለጊያ ፡ አድርጎ ፡ ሊሠራው ፡ የሚገባ ፡ አይደለም ።

ይህንም ፡ ልትረዳ ፡ ብትሻ ፡ በጎ ፡ ግብርን ፡ እንኳን ፡ ዋጋ ፡ አድርጎ ፡ ለመሸጥ ፡ ሀብት ፡ ክብረትም ፡ ስጠኝ ፡ ብሎ ፡ መለመን ፡ ኀጢአት ፡ ለመሆ

ኑ ፡ ጌታ ፡ በወንጌል ፡ የዘብዴዎስን ፡ ልጆች ፡ በለ
መኑት ፡ ሀብት ፡ መቈጣቱን ፡ ኀሡ ፡ መንግሥት ፡
ወጽድቆ ፡ ብሎ ፡ መሻታችንን ፡ ሁሉ ፡ በሰማያዊ ፡
መንግሥት ፡ እንድናደርግ ፡ መታዘዛችንን ፡ አስተ
ውል ፡ እንጂ ፡ በጎ ፡ ግብርህን ፡ ለከንቱ ፡ ዓለም ፡
መፈለጊያ ፡ አድርገህ ፡ ሥራው ፡ እያለ ፡ ሰይጣን ፡
በወዳጁ ፡ ባታላይ ፡ ጠንቀኛ ፡ ሰው ፡ እያደረ ፡ መ
ምከሩ ፡ በጎ ፡ ግብርህን ፡ ለሥጋዊ ፡ ሀብት ፡ እን
ድትሸጥለት ፡ በሠራኸው ፡ ደግነት ፡ እንድትጸድ
ቅበት ፡ የተጠበብህ ፡ ተንኰል ፡ መሆኑን ፡ ዕወቀው ፡
እንጂ ፡ ማንም ፡ ቢመክርህ ፡ በጎ ፡ ግብርህን ፡ ለሥ
ጋዬ ፡ መከበሪያ ፡ ለዕድሜዬ ፡ መርዘሚያ ፡ ይሁነኝ ፡
ብለህ ፡ ሳትሠራው ፡ ለእመ ፡ ስእሎ ፡ ወልዱ ፡ ኅብ
ስተ ፡ እብንኑ ፡ ይሁብ ፡ ባለው ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ የሚ
ጠቅመንን ፡ ከኛ ፡ ይልቅ ፡ እሱ ፡ ያውቀዋልና ፡
እንዳዘዘን ፡ ፈቃድህ ፡ ይሁን ፡ ከክፉ ፡ አድነን ፡
የሚበቃንን ፡ ስጠን ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ስም ፡ ለይ
ቶ ፡ ሥጋዊ ፡ ግብር ፡ ሽቶ ፡ በበጎ ፡ ግብሬ ፡ ይህን ፡
ዓለም ፡ ሽጥልኝ ፡ ብሎ ፡ መሻትስ ፡ ፈጣሪውንም ፡
ለትርፉ ፡ ሲል ፡ እንደሚሸጥ ፡ ነጋዴ ፡ ራሱንም ፡
ተንኰለኛ ፡ ወንበዴ ፡ ማድረግ ፡ ይሆንበታል ።
ስለዚህ ፡ በጎ ፡ ግብርን ፡ እንደ ፡ መድኀኒት ፡ አድ
ርጎ ፡ ከድኽነት ፡ ለመዳኛ ፡ ሀብቱ ፡ ሥጋ ፡ ለማ
ግኛ ፡ ሲል ፡ በልሜም ፡ በውኄም ፡ እያለ ፡ የሚነግ
ረውን ፡ ሰው ፡ ምክንያት ፡ እያደረገ ፡ የሚሠራ ፡ ሰ
ውስ ፡ የጥቅሙን ፡ ዋጋ ፡ ያላወቀ ፡ ስለ ፡ ጠንቋይ ፡



ቃል ፡ ወደ ፡ ሥጋዊ ፡ ፍትወቱ ፡ የወደቀ ፡ ከእግ
ዚአብሔር ፡ መንገድ ፡ የራቀ ፡ ይሆናልና ፤ በጎ ፡
ግብርህን ፡ ሁሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ስትል ፡
ሥራው ።

ምዕራፍ ፡ ፴፫ ።

በዚህ ፡ ዓለም ፡ ስለምናየው ፡ ሁሉ ፡ ውሸትነት ።

በዚህ ፡ ዓለም ፡ የምናየውም ፡ የምንሰማውም ፡ የም
ንሠራውም ፡ መምሰል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ መሆን ፡ የለ
ውም ።

ጥያቄ ።

፩፻፺፪ ፤ መስሎ ፡ የማይሆኑ ፡ ጉዳዮች ፡ ምን ፡ ምን ፡
ናቸው ።

ምላሽ ።

፩፻፺፫ ፤ ብልጉ ፡ ሰሎሞን ፡ እንዳለው ፡ ከፀሐይ ፡ በታ
ች ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ የሆነ ፡ የማይሆን ፡ ይመስለናል ፤
እንጂ ፡ ሁሉም ፡ ከንቱ ፡ ውሸት ፡ ነው ፤ አልሆ
ነም ።

ይኸንንም ፡ ልትረዳ ፡ ብትሻ ፡ መገርመሪያ ፡ በኛ ፡
አሳብ ፡ የምናየው ፡ ሰውነታችን ፡ እየቆመ ፡ ሲሄድ ፡
እየተናገረ ፡ ሲያስምር ፡ እየሠራ ፡ ሲያሳይ ፡ ቈም ፡
ነገር ፡ ያለው ፡ ትልቅ ፡ መስሎ ፡ ይታየናል ። ከጥ
ቂት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ የቆመው ፡ ሥጋ ፡ በሞት ፡ ወድ

ቆ ፡ የሚናገረው ፡ እንደበት ፡ ተዘግቶ ፡ የሠራው ፡
ፈርስ ፡ መስሎ ፡ የነበረው ፡ ሁሉ ፡ ለዐይንም ፡ ጠ
ፍቶ ፡ ለልብም ፡ ተረስቶ ፡ ውሸት ፡ ይሆናል ።

አንዳንዱም ፡ እስኪሞትም ፡ እንኳ ፡ ሳይቈይ ፡
እሱው ፡ ራሱ ፡ ሰውነቱን ፡ እያየው ፡ በደዌ ፡ ሥጋ
ው ፡ እንደ ፡ ጨርቅ ፡ ሲቀደድ ፡ ደሙ ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡
ሲፈስ ፡ ዐጥንቱ ፡ እንደ ፡ ዕንጨት ፡ ሲሰበር ፡ ያየ
ዋል ፡ ከደዌም ፡ ቢያመልጥ ፡ ከጥቂት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡
ያ ፡ ትልቅ ፡ መስሎ ፡ የነበረው ፡ ሰውነት ፡ በእርጅና ፡
እንደ ፡ ጨው ፡ ሻግሞቶ ፡ ዐይኑ ፡ ፈዞ ፡ ጕልበቱ ፡
ደንግዞ ፡ ልቡ ፡ ደንዝዞ ፡ ግርኀቶ ፡ ከእንስሳም ፡ እን
ሶ ፡ የልጆች ፡ መጫወቻና ፡ እንደማይረባ ፡ ጕድፍ ፡
ሆኖ ፡ ይታያል ።

፪ኛ ፡ ትልቅ ፡ ጕዳይ ፡ መስሎ ፡ የሚታየን ፡ ከሰው ፡
በላይ ፡ መሆን ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥት ፡ የሚባለውን ፡ ስ
ም ፡ ማውጣት ፡ ወይም ፡ ከሱ ፡ ሹም ፡ ሆኖ ፡ ከሱ ፡
ተካፍሎ ፡ የወደደውን ፡ ሀርና ፡ ጨርቅ ፡ አልማዝ ፡
የምድርን ፡ ቀለም ፡ ሁሉ ፡ በያይነቱ ፡ ሰብስቦ ፡ በል
ብሱ ፡ በራሱ ፡ ባሽከሩም ፡ በገረዱም ፡ ላይ ፡ አድ
ርጎ ፡ በቤቱም ፡ በከብቱም ፡ እንጠልጥሎ ፡ ሰውንም ፡
ሲያስር ፡ ሲፈታ ፡ ሲሰጥ ፡ ሲነሣ ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡
የሚገዛ ፡ መስሎ ፡ መታየት ፡ ነው ። ይህም ፡ እን
ኳን ፡ በሩቅ ፡ ለሚያየው ፡ ለሌላው ፡ ሰው ፡ ለሱም ፡
ለራሱም ፡ ላልሆነው ፡ ትልቅ ፡ ነገር ፡ የሆንኩ ፡ ይመ
ስለዋል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥት ፡ ወይ



ም ፡ እንድ ፡ ዐይነት ፡ ሹም ፡ ስለ ፡ ሆንኩ ፡ ትልቅ ፡
ነገር ፡ አግኝቻለሁ ፡ የሚመስለው ፡ ሰው ፡ ስለ ፡
ተፈጥሮው ፡ ግብዝነት ፡ እውነቱን ፡ ስላላወቀ ፡ ጥ
ቅሙን ፡ ስላልመዘነ ፡ ውሸቱ ፡ እውነት ፡ መስለው ፡
እንጂ ፡ እንደ ፡ እውነቱ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ አንድም ፡ ት
ልቅ ፡ ነገር ፡ አላገኘም ።

ይኸውም ፡ እማይረባው ፡ ክብረት ፡ ቢፈጥን ፡ በ
ሞት ፡ ቢቈይም ፡ ከጥቂት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ክብሩም ፡
በውርደት ፡ ልብሱም ፡ በማለቅና ፡ በመርገፍ ፡ ታጥ
ቶው ፡ እንዳልነበረ ፡ ሆኖ ፡ ይጠፋል ።

ወይም ፡ በዚያችው ፡ በጥቂቱ ፡ ቀን ፡ ከሞቱ ፡ ውር
ደቱ ፡ ቀድሞ ፡ እንደ ፡ ሰማንውም ፡ እንደነሶም
ሶን ፡ እንደነሴዴቅያስ ፡ እንደነናቡከደነጸር ፡ እን
ደናፖልዮን ፡ እንዳየናቸውም ፡ እንደነዐፄ ፡ ተ
ክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ እንደ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ እንደ ፡
ንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትና ፡ ንጉሥ ፡ ሚካኤል ፡
እንደነአቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ በደዌ ፡ ወይም ፡ በውርደ
ት ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ በታች ፡ ሁነው ፡ ያ ፡ የመስላ
ቸው ፡ ትልቅነት ፡ ሁሉ ፡ ውሸት ፡ መሆኑን ፡ ራ
ሳቸው ፡ ያዩታል ፡ በዚያውም ፡ ከሰው ፡ በላይ ፡ የሆን ፡
የሚመስላቸው ፡ በሚያዙበትም ፡ ወሬት ፡ ቢሆን ፡
የፈቃዳቸውን ፡ የሚሠሩ ፡ ጌቶች ፡ የሆን ፡ መስላቸ
ው ፡ እንጂ ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥት ፡ ወይም ፡ በየሌላው ፡
ልዩ ፡ ልዩ ፡ ስም ፡ የሚጠሩት ፡ ገዥዎች ፡ የሚባሉት ፡
ሁሉ ፡ እስራኤል ፡ ኢይትናገረን ፡ እግዚአብሔር ፡ እላ፡

ይትናገረን ፡ ሙሴ ፡ ብለው ፡ በለመኑት ፡ ልመና ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በሕዝብ ፡ መካከል ፡ ሁነው ፡ የትእዛዝ ፡ ቃል ፡ ለማቀባበል ፡ ለጥቂት ፡ ቀን ፡ የሚናገሩ ፡ እንደ ፡ ጭቃ ፡ ሹም ፡ ያሉ ፡ መልክተኞችና ፡ የሕዝብ ፡ አገልጋዮች ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ አዛዥና ፡ ባለፈቃዱ ፡ ግን ፡ ካሳብ ፡ ከሰውም ፡ በላይ ፡ የሆነው ፡ በዐይንም ፡ ማየት ፡ የማንችለው ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ።

ለንሉስ ፡ ፈቃድም ፡ ማዘዝም ፡ የላቸውም ። የዚህንም ፡ ርግጥነት ፡ ልትረዳ ፡ ብትሻ ፡ ራሳቸውን ፡ ከሚያገኛቸው ፡ ጭንቅ ፡ ሁሉ ፡ ለመዳን ፡ ባለመቻላቸው ፡ እስተውል ። ንግሥ ፡ ያየው ፡ ጠቢቡ ፡ ሰሎሞንም ፡ የንጉሥ ፡ ልብ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ የተያዘ ፡ በገበታ ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ ውሃ ፡ ነው ። እሱ ፡ ወደ ፡ ወደደው ፡ ያፈስዋል ፡ ባለው ፡ ዕወቅ ። በዚህ ፡ ዓለም ፡ በላይ ፡ የሌለው ፡ ትልቅ ፡ ፍጥረት ፡ የለም ፤ ለያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ሹም ፡ አለበት ፤ ለሹም ፡ ንጉሥ ፡ መንግሥት ፡ አለበት ፤ ለመንግሥት ፡ ሕዝብ ፤ ለሕዝብ ፡ ሕግ ፡ ለሕግም ፡ ዕውቀት ፡ ለዐውቀትም ፡ ፈጣሪ ፡ አለበትና ፡ ይህን ፡ አስተውል ።

ጥያቄ ።

፩፻፷ ፤ ትልቅ ፡ ጉዳይ ፡ ያገኙ ፡ የሚመስሉ ፡ እንጂ ፡ ትልቅ ፡ ያላገኙ ፡ ከሆኑ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ንጉሥን ፡ አክብሩ ፡ ለገዥዎች ፡ ተገዙ ፡ ብሎ ፡ ስለምን ፡ አዘዘን ።



ምላሽ ።

፩፻፷ ፤ ገዥዎች ፡ ለኛ ፡ አገልጋዮችና ፡ መልክተኞች ፡ ከሆኑ ፡ እኛ ፡ የገዥዎች ፡ በላይ ፡ የሆን ፡ እንዳይመስለንና ፡ እንዳንንቃቸው ፡ መልክተኝነታቸውንም ፡ እንሰማም ፡ እንዳንላቸው ፡ ወንጌልም ፡ መስቀልም ፡ ለሚያሳልም ፡ ሰው ፡ ከወንጌሉ ፡ ጋራ አብሮ ፡ እንደሚሰገድለት ፡ አምላካችን ፡ ሹማምትን ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ስም ፡ እየሰየመ ፡ ለፈቀደው ፡ ጉዳይ ፡ መልክተኛና ፡ አገልጋይ ፡ ለፈጠረው ፡ ገንዘብ ፡ አካፋይ ፡ ለፈረደው ፡ ቃል ፡ አቀባባይ ፡ እንዲሆኑት ፡ ወይም ፡ በራሱ ፡ እጅ ፡ ተአምራት ፡ እየሠራ ፡ ወይም ፡ በሰው ፡ አፍ ፡ መልካም ፡ ስም ፡ እያስወራ ፡ የሚመርጣቸውን ፡ ሹማምት ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ስንል ፡ ልናከብራቸው ፡ ልንሰማቸው ፡ የሚገባን ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የነሱ ፡ ጌትነትና ፡ ትልቅ ፡ መምሰል ፡ እውነት ፡ ሆኖ ፡ አይደለም ።

ስለዚህ ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚታይበትም ፡ ክብር ፡ የሚያገኘው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ይመስለዋል ፡ እንጂ ፡ አይደለም ።

ጥያቄ ።

፩፻፷፩ ፤ እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ ሰው ፡ በውሸቱ ፡ ዓለም ፡ እስካለ ፡ ድረስ ፡ እንዴት ፡ ሆኖ ፡ ሊኖር ፡ ይገባዋል ።

## ምላሽ ።

፬፻፷፪ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሆነ ፡ መስሎ ፡ የሚታየው ን ፡ ነገር ፡ ያለመሆኑን ፡ ለይቶ ፡ የሚያውቅበት ፡ እንደ ፡ አብርሃም ፡ እንደ ፡ በረለዓምና ፡ እንደ ፡ ዮሴፍ ፡ ዕውቀትን ፡ በተሰጠው ፡ ባሕርዩ ፡ እየፈለ ገ ፡ ዕውቀት ፡ ማግኘትን ፡ ከአምላኩ ፡ ይለምንና ፡ እንደ ፡ አሕዛብ ፡ ለምስሉ ፡ ዓለም ፡ መገዛቱን ፡ ትቶ ፡ በዐይን ፡ ሥጋ ፡ የማያየውን ፡ በዐይን ፡ ነፍስ ፡ ምርምር ፡ የሚያየውን ፡ ለንዋሪነቱ ፡ እውነት ፡ የሆ ነውን ፡ የማያልፈውን ፡ ሰማያዊ ፡ አኗኗር ፡ ይሻ ።

፬፻፷፫ ፡ ሰውም ፡ ከሸክላ ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ መመሰሉ ። የኛም ፡ አካል ፡ መምሰል ፡ እንጂ ፡ መሆን ፡ የሌለው ፡ የሥራውን ፡ ምሳሌ ፡ በሸክላ ፡ ሥራ ፡ የሚመሳሰል ፡ መሆኑን ፡ አስተውለው ።

በዚህ ፡ ዓለም ፡ ለሚኖር ፡ ለሥጋዊ ፡ ሰው ፡ ላና ዎሩ ፡ ዐይነት ፡ ሁሉ ፡ ሲሠራም ፡ መሬትና ፡ ውሃ ፡ ተለውሶ ፡ በንፋስ ፡ ደርቆ ፡ በእሳት ፡ ጠንቶ ፡ በቅ ባት ፡ ተሻሽቶ ፡ ነውና ፡ ስለዚህ ፡ ኤርምያስ ፡ (ም ፡ ፲፰ ፡ ቍ ፩ ፡ እ ፡ ፯) ፡

እንደ ፡ መሰለው ፡ እውነተኛ ፡ የሥጋችን ፡ ምሳሌ ፡ ሸክላ ፡ ነውና ፡ ከአራቱ ፡ ባሕርይ ፡ በመሠራት ፡ ይ መስለናል ፡ ከተሠራም ፡ በኋላ ፡ ተሻሽቶ ፡ ከቤት ፡ ዕቃ ፡ ጋራ ፡ እንደሚቀላቀል ፡ ሰውም ፡ በመንፈስ ፡ ቅ ዱስ ፡ ተሻሽቶ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ለመሆ



ን ፡ ሥጋችንም ፡ ዐፈር ፡ በመሆን ፡ እንደ ፡ መሰበሩም ፡ ዐጥንታችንም ፡ መሰበሩ ፡ ከተሰበረም ፡ በኋላ ፡ እየተሰበሰበ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ በመሠራቱ ፡ ለትንሣኤያችንም ፡ ገሉ ፡ ተሠርቶ ፡ ጥብቅ ፡ ሥራ ፡ በመሆን ፤ ለሁሉም ፡ ፍጹም ፡ ምሳሌያችን ፡ ነው ። ሰውም ፡ ተፈጥሮው ፡ አንድ ፡ ሲሆን ፡ አኗዎሩም ፡ እንደሚለያይ ፡ የሸክላም ፡ እንደዚሁ ፡ የመለያየት ፡ ዐይነት ፡ ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

፬፻፷፬ ፡ ጋን ፡ ከፍተኛው ፡ በንጉሥ ፡ ዝቅተኛው ፡ በመኳንንት ፡ ሆኖ ፡ ለዳኛ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ምሳሌ ፡ ነው፤ በውስጡም ፡ ውሃም ፡ ጌሾም ፡ እኽልም ፡ አገናኝቶ ፡ ያሳድራቸዋል ፡ እብር ፡ መቀመጥም ፡ እስልችቶ ፡ ሲያፈላቸውና ፡ ሲያጣላቸው ፡ እስኪበርዱ ፡ ድረስ ፡ በትዕግሥት ፡ ችሎ ፡ አብርዶ ፡ በርጋታ ፡ በማቂየቱ ፡ ጥሩና ፡ አተላውን ፡ ለይቶ ፡ ከላይ ፡ አጥሎ ፡ ጥሩውን ፡ አውጥቶ ፡ ለባለቤቱ ፡ ከሰጠ ፡ የተሠራው ፡ ለዚሁ ፡ ነውና ፤ ሠሪውንም ፡ ደስ ፡ ያሰኘዋል ።

ገንዘብም ፡ አድርጎ ፡ ከዕቃዎቹ ፡ ጋራ ፡ ይቈጥረዋል ፤ ባተላውም ፡ እንዳይበላሽ ፡ በቶሎ ፡ አድፋን ፡ ሁሉ ፡ ያጥብለታል ።

እንዳያበስብሰው ፡ አመድ ፡ ነስንሶ ፡ እንዲለሰልስ ው ፡ ዐፈር ፡ ጕዝጕዞ ፡ ከተመቸ ፡ ቦታ ፡ ያኖረዋል ። ዳኞቹም ፡ ለየሚያሳድሩት ፡ ሰው ፡ የሚሠሩት ፡ ት

ዕግሥትና ፡ ዕውቀት ፡ ዕቀቡ ፡ እባግዕየ ፡ እምተ ኵላ ፡ ስለ ፡ ተባለው ፡ ትእዛዝ ፡ ለፍቅረ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ሲል ፡ የሠራው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ትልቅ ፡ ጽ ድቅ ፡ ያገኛል ።

የሚሠራበት ፡ ምክንያቱን ፡ ትዕግሥቱንም ፡ እስኪ መቸው ፡ ለማጥመድ ፡ ዕውቀቱንም ፡ ሰው ፡ ለማ ታለልና ፡ ለብልጠት ፡ ሲል ፡ ከሠራው ፡ ሥራውም ፡ ጕሹ ፡ እንደ ፡ ሠነጠቀው ፡ ጋን ፡ ሆኖ ፡ ከንቱ ፡ ይሆናል ።

ድስት ፡ ለወታደር ፡ ኑሮ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ።

፩፻፳፭ ፡ ድስት ፡ የተሠራው ፡ ለእንጀራ ፡ መብያ ፡ ወ ጥ ፡ መሥሪያ ፡ እንዲሆን ፡ ተብሎ ፡ ነው ።

ወታደር ፡ የሚሰበሰበውም ፡ ለባላገር ፡ ገንዘብ ፡ መብያ ፡ ነው ።

ድስት ፡ በሳት ፡ ስለ ፡ ተቃጠለ ፡ ለሠሪዋ ፡ ሞያ ፡ ሆኖ ፡ ያስመሰግናል ።

ወታደርም ፡ በባሩድ ፡ እሳት ፡ ስለ ፡ ተቃጠለ ፡ ሹማ ምትን ፡ ያስመሰግናል ።

ድስት ፡ እየተቃጠለ ፡ በውስጡ ፡ ያለውን ፡ ሳያቃ ጥል ፡ ለሥጋ ፡ ሲል ፡ እሱ ፡ እየተቃጠለ ፡ ያልተቃ ጠለውን ፡ ሥጋ ፡ አብስሎ ፡ ያከብረዋል ።

ወታደርም ፡ ለሥጋው ፡ ሲል ፡ ሥጋውን ፡ አቃጥሎ ፡ ገዥዎችን ፡ ያከብራል ።



ድስት ፡ ክብር ፡ መስሎት ፡ የሚኖርበት ፡ ከባልን ጀራው ፡ ከምጣድ ፡ ተለይቶ ፡ ከዶራ ፡ ከልፍኝ ፡ ከንጉሡና ፡ ከሹም ፡ ማንባር ፡ ቀርቦ ፡ መታየቱን ፡ ዐለላ ፡ መከደኑን ፡ ቀሚስ ፡ መልበሱን ።

ሠራተኞች ፡ ለራሳቸው ፡ ክብር ፡ ሲሉ ፡ የሚያደርጉ ትን ፡ ሁሉ ፡ ያደረጉለት ፡ እየመሰለው ፡ ዘወትር ፡ ለሰው ፡ ጥቅም ፡ ሲቃጠል ፡ ይኖራል ።

ወታደርም ፡ ከባላገር ፡ ለይተው ፡ አቅርበው ፡ ሲያ ዩት ፡ ሲያስጌጡት ፡ ለነሱ ፡ መከበሪያ ፡ ያደረጉትን ፡ ለሱ ፡ ያደረጉለት ፡ እየመሰለው ፡ ለነሱ ፡ ክብር ፡ እሱ ፡ በእሳት ፡ ይቃጠላል ።

ወታደር ፡ በኑሮው ፡ ተቀንቶ ፡ ለአጋዕዝቲክሙ ፡ የተባለውን ፡ አስቦ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ቢቀበል ፡ ከጌ ታው ፡ የተረፈውን ፡ ጕልበት ፡ በጎ ፡ ግብር ፡ ቢሠ ራበት ፡ በዚህ ፡ ኑሮ ፡ ውስጥ ፡ ትልቅ ፡ ጽድቅ ፡ ያገ ኛል ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ የሚደክምበት ፡ ስለ ፡ ሥጋው ፡ ጥቅም ፡ ብቻ ፡ ሲል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ ድ ካሙ ፡ ከንቱ ፡ እንደ ፡ ድስት ፡ ያለ ፡ ይሆናል ።

ምጣድ ፡ የባላገር ፡ ምሳሌ ፡ ነው ።

፩፻፳፮ ፡ የምጣድ ፡ መቃጠል ፡ ለሁሉም ፡ ጥቅም ፡ ሲል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የገበሬም ፡ ሥራ ፡ ለሁሉም ፡ ጥ ቅም ፡ ነው ።

ምጣድ ፡ የሁሉም ፡ መጋቢ ፡ ሲሆን ፡ ክብር ፡ አጥቶ ፡ ከበላተኞች ፡ ፊት ፡ አይደርስም ።

ገበሬም ፡ ሁሉን ፡ እርሶ ፡ እያበላ ፡ ክብር ፡ አጥቶ ፡
ከሹም ፡ ከንጉሥ ፡ ቤት ፡ እንዳይገባ ፡ ይከለከላል ።
ምጣድ ፡ ተቃጥሎ ፡ ያበሰለውን ፡ እንጀራ ፡ በዕን
ጨት ፡ ሰቅስቀው ፡ በግድ ፡ አለያይተው ፡ ይወስዱ
በትና ፡ በጨርቅ ፡ መሳይ ፡ ቅባት ፡ ይዘው ፡ ያባብ
ሉታል ።

የባላገርንም ፡ ገንዘብ ፡ በሹም ፡ እየሰቀሰቁ ፡ በወታ
ደር ፡ እያስፈራሩ ፡ ገዥዎች ፡ ሁሉ ፡ በየብልንታ
ቸው ፡ ላንተ ፡ መጠበቂያ ፡ እንዲሆን ፡ ለዘበኛ ፡
ቀለብ ፡ ለጠላታችን ፡ ማጥቂያ ፡ እንዲሆን ፡ ነው ፡
እያሉ ፡ የሚያውቀው ፡ እርሻ ፡ ብቻ ፡ ነውና ፡ በሱ፡
ገንዘብ ፡ ለሱ ፡ ወይም ፡ ለየራሳቸው ፡ ጥቅም ፡ መ
ሥራታቸውን ፡ ሳያውቀው ፡ በትንሽ ፡ ጥበብ ፡ እነሱ፡
ሳይሠሩ ፡ የሱን ፡ ድካም ፡ በግድ ፡ ይወስዱበታል ፤
ምጣድ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ እየተቃጠለ ፡ የሚያበ
ስለው ፡ ሳያንስ ፡ ለቁንጥና ፡ ለጌጥ ፡ ሲሉ ፡ ብዙ ፡
ሊጥ ፡ ቈልለው ፡ በላይና ፡ በታች ፡ በሳት ፡ እያቃ
ጠሉ ፡ ዳቦ ፡ አብስል ፡ ይሉታል ።

ባላገርም ፡ እርሶ ፡ ማብላቱ ፡ ሳያንሰው ፡ እምበላ
በት ፡ ቤት ፡ ሥራልኝ ፡ እምጠበቅበት ፡ አጥር ፡
አጠርልኝ ፡ ወይ ፡ ለእንዲህ ፡ ያለ ፡ ጉዳይ ፡ ከግብ
ርህ ፡ በላይ ፡ ትርፍ ፡ ስጠን ፡ እያሉ ፡ ደሞ ፡ ሁለ
ተኛ ፡ ጉልበቱን ፡ ገንዘቡን ፡ ይወስዱበታል ።

ይህንም ፡ የሚወስዱበትን ፡ ያለብስጭት ፡ ያለ ፡
ርግማን ፡ በትዕግሥት ፡ ቢሰጣቸው ፡ ከምጽዋት ፡



ተቈጥሮለት ፡ ትልቅ ፡ ጽድቅ ፡ ያገኝበታል ። እየ
ተራገመ ፡ ቢሰጥ ፡ ግን ፡ የሚረገመውንም ፡ እያ
ጠፋ ፡ እሱም ፡ በተራጋሚነቱ ፡ እየጠፋ ፡ እንደ ፡
ምጣዱ ፡ ሥራው ፡ ከንቱ ፡ ይሆንበታል ።

እንስራ ፡ ለካህን ፡ ኑሮ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ።

፬፻፳፮ ፤ እንስራ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ለሚገኝ፡
ውሃ ፡ ማምጫ ፡ ነው ፡ ካህናትም ፡ ከእግዚአብ
ሔር ፡ ለሚገኘው ፡ ሥልጣንና፡ ዕውቀት፡ መምጫ፡
ናቸው ፤ እንስራ ፡ የዘወትር ፡ መመላለስና ፡ ካለ
ት ፡ ጋራ ፡ መጋጨት ፡ ስላለበት ፡ ተጠንቅቀው ፡ ካ
ልጠበቁት ፡ መሰበርም ፡ ከሌላው ፡ ሸክላ ፡ ሁሉ ፡
በእንስራ ፡ ይጸናበታል ።

ካህናትም ፡ ከጥሩውና ፡ ከብርቱው ፡ እግዚአብሔር ፡
ዘንድ ፡ መቅረብ ፡ ስላለባቸው ፡ ካልተጠነቀቁ ፡
መቀሠፍ ፡ መቀጣት ፡ ይጸናባቸዋል ።

እንዚህም ፡ ተጠንቅቀው ፡ ለፈጣሪያቸው ፡ ብቻ ፡
አገልጋይ ፡ ቢሆኑ ፡ ባለትልቅ ፡ ጽድቅ ፡ ይሆናሉ ፤
ለፍትወታቸው ፡ ሲሉ ፡ አገልግሎታቸውን ፡ ለሥ
ጋዊ ፡ ጌቶች ፡ ቢያደርጉ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ እንስራው ፡
ከንቱ ፡ ይሆናሉ ።

ገንቦ ፡ ለነጋዴ ፡ ኑሮ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ።

፬፻፳፯ ፤ ገንቦ ፡ እንስራ ፡ ከውሃ ፡ እየጠለቀ ፡ ጋን ፡ ፍ
ላት ፡ በመሸከም ፡ እየተጨነቀ ፡ የሠሩትን ፡ እሱ ፡

የጋን ፡ ስንፍና ፡ ለገምቦ ፡ በጅቶት ፡ ጋን ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ የማይሄድ ፡ በመሆኑ ፡ የሱን ፡ ጥሩ ፡ ገምቦ ፡ እየጠለቀ ፡ ወስዶ ፡ ቀሚስ ፡ ለብሶ ፡ ከመኳንንት ፡ ፊት ፡ ገብቶ ፡ ይከበርበታል ።

ነጋዴም ፡ እሱ ፡ ሳይሠራ ፡ በመንገዱ ፡ ብቻ ፡ በሰው ፡ ሥራ ፡ ይከብራል ፤ ይህም ፡ ነጋዴ ፡ የመንገድ፡ ከሳራውን ፡ ብቻ ፡ በውነት ፡ ግምት ፡ እየመዘነ ፡ ከሸጠ ፤ ብጹዕ ፡ ዘይረድእ ፡ ለርእሱን ፡ የፈጸመ ፡ በመሆኑ ፡ ይጸድቃል ።

ብዙ ፡ ትርፍ ፡ ለማግኘት ፡ ሲል ፡ በመግዛቱ ፡ ላይ ፡ ማታለልን ፡ ከመሸጡ ፡ ላይ ፡ ማበልን ፡ ከቀላቀለ በት ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ገንቦ ፡ ሥራው ፡ ከንቱ ፡ ይሆናል ።

ገበታ ፡ ለባለሻል ፡ ኑሮ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ።

፩፻፺፱ ፤ ገበታ ፡ እንደ ፡ ምጣድና ፡ እንደ ፡ ድስትም ፡ እሳት ፡ ሳይነካው ፡ እንደ ፡ እንስራና ፡ እንደ ፡ ገንቦም ፡ የውሃ ፡ እለት ፡ ሳይነካው ፡ የሌሎቹን ፡ ሸክሎች ፡ ሥራ ፡ ለባለቤት ፡ የሱ ፡ እያስመሰለ ፡ እየቀረበ ፡ ከመሶብ ፡ ከምንጣፍ ፡ ላይ ፡ እየቀረበ ፡ የጌትየው ፡ እጅ ፡ የሚያርፍበት ፡ ባለሻል ፡ ይሆናል ። ከሰዎችም ፡ አንዳንዶቹ ፡ ብልጦች ፡ ወይ ፡ ሎሌያቸው ፡ የሠራላቸውን ፡ ጉልበት ፡ ወይ ፡ ወዳጃቸው ፡ የነገራቸውን ፡ ዕውቀት ፡ የነሱ ፡ እያስመሰሉ ፡ የሰውን ፡ ዕውቀትና ፡ ጉልበት ፡ ለጌታቸው ፡ እያቀረቡ ፡ ይከብሩበታል ።



እነዚህም ፡ ባለሻል ፡ የሚሆኑት ፡ ጌታቸው ፡ ያዘዛቸውን ፡ ብቻ ፡ በውነት ፡ በመሥራታቸው ፡ ሲያገለግሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ይጠቀሙበታል ፤ የሰው ፡ ነገር ፡ በመመለስ ፡ ሲሆን ፡ ግን ፡ ሥራቸው ፡ እንደ ፡ ገበታው ፡ ከንቱ ፡ ሆኖ ፡ ይጐዱበታል ።

፪፻ ፤ እነዚህ ፡ ሸክሎች ፡ ባለቤት ፡ የሠራቸው ፡ ለፈቃዱ ፡ መፈጸሚያ ፡ ሲል ፡ ለያይቶ ፡ ስለ ፡ ሠራቸው ፡ እንደየሥራቸው ፡ የተከፈለላቸውን ፡ ይሠራሉ ፡ እንጂ ፤ ሁላችንም ፡ ሸክላ ፡ ነንና ፡ ባሕርያችን ፡ ፩ ፡ ከሆነ ፡ ብለው ፡ ምጣድ ፡ የጋንን ፡ ጋን ፡ የምጣድን ፡ ሊሥራ ፡ ቢል ፡ እንዳይችል ።

ሰው ፡ በፀቅሙ ፡ ልክ ፡ የተከፈለለትን ፡ ንቆ ፡ ባሕርዩ ፡ ይመሳሰላልና ፡ ሁላችንም ፡ እኩል ፡ ሰው ፡ ነን ፡ ብሎ ፡ እንኳን ፡ ሥጋዊውን ፡ የመንፈሳዊውንም ፡ በጎንም ፡ ሥራ ፡ ቢሆን ፡ ትልቅ ፡ ሥራ ፡ ቢመኝ ፡ አይሆንለትምና ፡ ሰውም ፡ እግዚአብሔር ፡ ያሊያሲያዘውን ፡ ሥራ ፡ ሊሥራ ፡ ማለት ፡ አይገባውም ፤ እንደዚህም ፡ በተፈጥሮ ፡ እንመስላለን ፡ ሁላችንም ፡ ከውሃ ፡ ከመሬት ፡ ከነፋስ ፡ ከእሳት ፡ ነውና ፡ የተፈጠርነው ፡ ብሎ ፡ ያለግብሩ ፡ ያለመልኩ ፡ ያለክፍሉ ፡ ቢሠራ ፡ ያጠፋዋል ፡ እንጂ ፤ እግዚአብሔርን ፡ አይጠቅም ፤ ራሱም ፡ አይጠቀም ፤ ለሁሉም ፡ በየተከፈለበት ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ አለበት ፤ ያን ፡ ይሥራ ፡ እንጂ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያሊያሲያዘውን ፡ ሥራ ፡ አይፈልግ ።

እግዚአብሔር ፡ የሚያሲዘውም ፡ ሥራ ፡ መታወቂያው ፡ ልቡናው ፡ ለመሥራት ፡ ከሚመኘው ፡ ከብዙው ፡ ዐይነት ፡ ኑሮ ፡ አንዱን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘውን ፡ መጀመር ፡ ነው ፤ ያ ፡ የጀመረው ፡ ነገር ፡ ሲቀናለት ፡ መጀመሪያ ፡ ማሳሰቡን ፡ ፪ኛ ፡ ከብብዙ ፡ ምኞት ፡ መሻል ፡ ለይቶ ፡ ማስጀመሩን ፡ ፫ኛ ፡ ሥራውን ፡ መባረኩንና ፡ ማቃናቱን ፡ ይህን ፡ እንደ ፡ ሦስት ፡ ምክር ፡ አድርጎ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ይታወቃል ።

ግን ፡ ሰው ፡ ካባቱ ፡ ካዳም ፡ ከፋውንና ፡ በጎውን ፡ ጠባይ ፡ ስለ ፡ ወረሰ ፡ ዘወትር ፡ ምኞቱ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ጋራ ፡ የገጠመ ፡ አይደለምና ፡ መርጦ ፡ የጀመረው ፡ ኑሮ ፡ አልቀናለት ፡ ብሎ ፡ በውስጡ ፡ ያለውን ፡ ጽድቅ ፡ ለመሥራት ፡ እማይቻለው ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በውስጡ ፡ ያለውን ፡ ጽድቅ ፡ ጨምሮ ፡ ለመሥራት ፡ እስኪቻለው ፡ ድረስ፡ የኑሮውን ፡ ዐይነት ፡ እያዘዋወረ ፡ እየፈተነ ፡ በኑሮው ፡ ጽድቅን ፡ ለመሥራት ፡ የሚቻለው ፡ ከሆነ ፡ የመጽደቂያው ፡ ክፍል ፡ በዚያው ፡ ሥራ ፡ መሆኑ ፡ ነውና ፡ ያንኑ ፡ እያጽናና ፡ እያጣራ ፡ ይሥራ ፡ እንጂ ፤ ያልታደለውን ፡ ቢፈልግም ፡ አያገኘውምና ፤ እግዚአብሔር ፡ ያሲያዘውን ፡ ሥራ ፡ ለቆ ፡ ሌላውን ፡ ሥራ ፡ አይፈልግ ።

በያዙት ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ እየተዉ ፡ ባሊያዙት ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡



በጎ ፡ ሥራ ፡ የመመኘታቸውን ፡ ጥፋት ፡ ለማወቅ ፡ ወቅረስ ፡ ምሳሌ ፡ ሆኖ ፡ ያስተምረናል ። መጽሐፈ ፡ ቆሮንቶስም ፡ (ም ፡ ፯ ፡ ቍ ፡ ፳) ። የጨዋ ፡ ምክር ፤ የያዘውን ፡ የሚጥል ፡ ያሊያዘው ፡ ያምረዋል ፡ አልጠግብ ፡ ባይ ፡ ይተፋል ።

የብልኖች ፡ ምሳሌ ። ውሻ ፡ ባፉ ፡ ሥጋ ፡ ይዞ ፡ ከባሕር ፡ ዳር ፡ ቁሞ ፡ ሳለ ፡ ባፉ ፡ የያዘውን ፡ ሥጋ ፡ ከውሃው ፡ ውስጥ ፡ ሲያይ ፡ ያየውን ፡ እይዛለሁ ፡ ሲል ፡ የያዘው ፡ እንደሚወድቅበት ፡ እንደዚሁም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በየባሕርዩ ፡ ታድሎ ፡ የሚሠራውን ፡ እያየ ፡ ያየውን ፡ ሁሉ ፡ እይዛለሁ ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ እንደዚህ ፡ ውሻ ፡ ሁለቱንም ፡ እንዳያጣ ፡ የተከፈለለትን ፡ ይሥራ ፡ እንጂ ፡ ያልተከፈለለትን ፡ እሠራለሁ ፡ ብሎ ፡ አይመኝ ፤ አይሥራ ።

ምዕራፍ ፡ ፴፬ ።

## እሳቤን ፡ ጽፌ ፡ እጨርሳለሁ ፡

### ስለሚመስለው ፡ ስላለማለቱ ፡ ማስረጃ ።

ጥያቄ ።

፩፻፸፩ ፤ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ጀምሮ ፡ እስካሁን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ሕግ ፡ ከሙሴ ፡ እንዶቶ ፡ እስ

ካሁን ፡ የቤተ ፡ መንግሥትንም ፡ ሕግ ፡ ከሳእል ፡ እንሥቶ ፡ እስካሁን ፡ ለመጻፍ ፡ አላረፈም ፤ ተወስናም ፡ ሰውን ፡ ከጸብ ፡ ከርክር ፡ የማያድንበት ፡ ተጽፎም ፡ የማያልቅበት ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ነው ።

ምላሽ ።

፩፻፸፱ ፤ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ሥራውም ፡ ሐሳቡም ፡ ተለዋዋጭና ፡ የሚዞር ፡ እሱም ፡ የማይኖር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሥጋዊም ፡ መንፈሳዊም ፡ መጻሕፍት ፡ ሁሉ ፡ የአእምሮ ፡ መመለሻ ፡ መንገድ ፡ እንዲሆኑ ፡ ተብሎ ፡ የተጠረጉ ፡ መንገዶች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ማረፊያ ፡ ቤቶች ፡ ስላልሆኑ፡ መጻሕፍት ፡ ሁሉ ፡ ሰውን ፡ ሊያሳርፉት ፡ አልቻሉም ፤ ስለዚህ ፡ የሚጻፉትም ፡ አእላፍ ፡ መጻሕፍት ፡ ለማይወሰኑት ፡ የአእላፍ ፡ አሳቦች ፡ መሂጃ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ነው ።

ጥያቄ ።

፩፻፹ ፤ መጻሕፍት ፡ ሁሉ ፡ መንገድ ፡ ብቻ ፡ ከሆኑ ፡ ሰውንም ፡ ማሳረፍ ፡ ካልቻሉ ፡ እኒህ ፡ መንገዶች ፡ ወስደው ፡ ወስደው ፡ ከምን ፡ ላይ ፡ ያደርሱናል ።

ምላሽ ።

፩፻፹፩ ፤ ሥጋዊው ፡ ታሪክና ፡ ፍልስፍና ፡ ደንብና ፡ ሥርዐት ፡ የሚባሉት ፡ የብልጦቹ ፡ መጻሕፍት ፡ ትምርታችን ፡ እስከ ፡ መቃብር ፡ ድረስ ፡ ሸኝተው ፡ ተመልሰው ፡ ለጥቂት ፡ ቀን ፡ ለውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ ስም ፡ ብቻ ፡ ይሆኑናል ፤ ወደ ፡ ዕረፍት ፡ ቦታ ፡ የሚያደርሱን ፡ መንፈሳዊ ፡ መጻሕፍት ፡ ግን ፡ ሥጋችንንም ፡ ከመቃብር ፡ አድርሰው ፡ ነፍሳችንንም ፡ ዘወትር ፡ ከምታርፍበት ፡ ከሰማያዊ ፡ መንግሥት ፡ ያደርሷታል ።



ጥያቄ ።

፩፻፹፪ ፤ ከእኒህስ ፡ ፪ቱ ፡ መንገድ ፡ ባንዳቸው ፡ ለመሄድ ፡ የቈረጠ ፡ የሚሄድበት ፡ እንዳንዳቸው ፡ ስንት ፡ መንገድ ፡ ያሳዩታል ።

ምላሽ ።

፩፻፹፫ ፤ መንፈሳውያን ፡ መጻሕፍት ፡ ከምዕራፍ ፡ ፫ ፡ እንደ ፡ ተጻፉት ፡ አብርሃም ፡ ዳዊት ፡ ዮሐንስ ፡ እንጦንስ ፡ የጠረጉትን ፡ ፬ ፡ መንገድ ፡ ያሳዩታል ። ሥጋዊ ፡ ታሪክና ፡ ደንብ ፡ ግን ፡ እእላፍ ፡ ሰራዊት ፡ የሄዱበትን ፡ ተቈጥሮ ፡ የማያልቀውን ፡ መንገድ፡ ሁሉ ፡ ያሳያሉ ፡ እንጂ ፡ ደንብም ፡ ሆነው ፡ ጸንቶ ፡ ለመኖር ፡ ጥቅም ፡ ሆነው ፡ ሰውን ፡ ለማኖር ፡ አይችሉም ።

ጥያቄ ።

፩፻፹፬ ፤ ሥጋዊ ፡ መጽሐፍ ፡ ሁሉ ፡ ጸንቶም ፡ አጽንቶም ፡ የማይኖር ፡ ከሆነ ፡ የዓለም ፡ ጠቢባን ፡ ሁሉ ፡ መጻሕፍትን ፡ ለፍርድና ፡ ላናምር ፡ የደንብ ፡

ለመጪ ፡ ትውልድ ፡ የታሪክ ፡ መጻሕፍትን ፡ ስለ
ምን ፡ ይጽፏቸዋል ።

ምላሽ ።

፬፻፹፫ ፤ ሥጋዊ ፡ መጽሐፍ ፡ የሥራ ፡ ማስታወሻ ፡
ነው ፡ እንጂ ፡ ተለዋጩና ፡ ፈራሹ ፡ ሰው ፡ እንደየ
መሰለው ፡ የሚጽፈው ፡ ደንብና ፡ ታሪክ ፡ ሁሉ ፡
ነዋሪም ፡ ጽኑም ፡ ሥርዐት ፡ ሊሆን ፡ መጽሐፍ ፡
ሊባል ፡ አይገባውም ።

ይህንኑ ፡ ጽሕፈት ፡ ግን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንደየሚመ
ስለው ፡ ያቅሙን ፡ ያኸል ፡ ደክሞበታልና ፡ እንደ
ማስታወሻ ፡ ዐይነት ፡ ያኸል ፡ አድርጎ ፡ እንደ ፡
ሕግ ፡ ሳያደርግ ፡ ቢመለከተውና ፡ የሚያሻውን ፡
ያኸል ፡ ይምረጥለት ፡ እንጂ ፡ ነገርም ፡ ሁከትም ፡
አናኗርም ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ዘወትር ፡ አዲስ ፡ አዲሶ
ች ፡ እየሆኑ ፡ ይወለዳሉ ።

ያካላችንም ፡ አርአያው ፡ አንድ ፡ ሲመስል ፡ ቅርጹ ፡
ያንዱ ፡ ካንዱ ፡ እንደማይመሳሰል ፡ ነገርም ፡ ምንም ፡
ከተሠራው ፡ ደንብ ፡ ጋራ ፡ ቢመሳሰል ፡ ስልቱና ፡
ምስጢሩ ፡ ዕለት ፡ የሚፈጠረው ፡ ነገርና ፡ ያለፈው ፡
ነገር ፡ በምርምር ፡ ስልት ፡ ሲመለከቱት ፡ ምንም ፡
ቢሆን ፡ ጥቂት ፡ እንጂ ፡ ጨርሶ ፡ አይመሳሰልምና ፡
እንደ ፡ እስተዋዮቹ ፡ እንግሊዞች ፡ አናዎር ፡
ሰው ፡ የጻፈውን ፡ በበረድ ፡ አሳብ ፡ እየመረመርክ ፡
እእምሮ ፡ የደንብ ፡ በላይ ፡ ደንብ ፡ የእእምሮ ፡ አስ



ታዋሽ ፡ መሆኑን ፡ ዐውቀህ ፡ ለየተፈጠረው ፡
ላዲሱ ፡ ነገር ፡ ከያይነቱ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ እየለቀምህ ፡
በእእምሮ ፡ሚዛን ፡ እየተረጐምኽ ፡ ስላልተመሳሰ
ለልህ ፡ እንደ ፡ ተገለጠልህ ፡ እያደረግህ ፡ ሥራ ፡
እንጂ ፤ እንኳን ፡ ሌላው ፡ ለጻፈው ፡ ደንብ ፡ አን
ተም ፡ ብትጽፈው ፡ ጽኑ ፡ ደንብ ፡ ሆኖ ፡ እኔንም ፡
ያሳርፈኛል ፤ አሳቤንም ፡ ይወስንልኛል ፡ ብለህ ፡
ሳታምን ፡ ላዲሱ ፡ ነገር ፡ የማያሻውን ፡ ደንብ ፡
ለመሥራት ፡ ማድላትና ፡ ብልጠት ፡ የሌለበት ፡
ቅን ፡ ልቡና ፡ የታደልህ ፡ ስትሆን ፡ ላንተ ፡ አዲስ ፡
የሆነብህ ፡ ነገር ፡ ቀድሞ ፡ ከተጻፈው ፡ ውስጥ ፡
ተሠርቶ ፡ ያገኘኸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡
የተጻፈና ፡ የሚጻፍ ፡ ነገር ፡ የሚቻለውን ፡ ንባብ ፡
ይጽፋል ፡ እንጂ ፡ በሚጽፍበት ፡ ጊዜ ፡ ለልቡናው ፡
ሲታየው ፡ የነበረውን ፡ ትርጓሜ ፡ ለመጻፍ ፡
ወይ ፡ የሚጻፍበት ፡ ቋንቋው ፡ እያጠረ ፡ ወይም ፡
ለጸሓፊው ፡ ጊዜ ፡ አልመቸው ፡ በማለት ፡ እያፈረ ፡
እንኳን ፡ ከትርጉሙ ፡ ከንባቡም ፡ ላይ ፡ የሚቀረው ፡
ብዙ ፡ ነውና ፡ በተሰጠህ ፡ እእምሮ ፡ የተሠራውን ፡
ደንብ ፡ ያልሠራውን ፡ ሰው ፡ እንሌ ፡ ይተርጉምል
ኝና ፡ እኔ ፡ በእሱ ፡ አሳብ ፡ ልሂድ ፡ እያልክ ፡ የፍርድ ፡
ዕውቀትህን ፡ በሰው ፡ ክንድ ፡ ሳትሰፍር ፡ ፍትሐ ፡
ነገሥትም ፡ ወይም ፡ በየጊዜው ፡ የተጻፉትን ፡
የሕግ ፡ መጻሕፍት ፡ መርማሪውም ፡ ትርጓሜውን ፡
መካሪ ፡ መርማሪውን ፡ የራስክን ፡ እእምሮ ፡ አኖ
ርቶ ፡ እንዲመረምረው ፡ አትጋውና ፡ ሰው ፡ ወይም ፡

የመሰለህን ፡ እንዲያጸናልህ ፡ ወይም ፡ የመሰለህ ፡ በሚመስልህ ፡ ትርጓሜ ፡ አስረድቶ ፡ እንዲለውጥልህ ፡ ፈልገው ፡ እንጂ ፡ ያንተን ፡ አሳብ ፡ ሥራ ፡ አስፈትተህ ፡ በሱ ፡ አሳብ ፡ ብቻ ፡ ልሂድ ፡ አትበል ።

የመጣብህ ፡ አዲሱ ፡ ነገር ፡ ከሕግ ፡ ያልተጻፈ ፡ ሲሆን ፡ ልቡናህ ፡ ወደ ፡ ራስህም ፡ ጥቅም ፡ ሳይመራ ፡ ወደ ፡ ተናጋሪም ፡ ጥቅም ፡ ሳያደላ ፡ ባንደበትህ ፡ የሚሰማው ፡ ፍርድ ፡ ሁሉ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የሚገኘው ፡ ነውና ፡ እሱ ፡ እንደ ፡ ገለጸልህ ፡ ፍረድ ፡ እንጂ ፡ ለነዋሪ ፡ ደንብ ፡ ለመሥራት ፡ ከምታስብበት ፡ ጊዜ ፡ በቀር ፡ በብይን ፡ ጊዜ ፡ ዋላላ ፡ እንዳትሆን ፡ አስታውስ ፡ እንጂ ፤ አማካሪ ፡ አትሻ ፡ (ስለ ፡ አባት ፡ እናት ፡ ም ፡ ፷፩) ።

ምዕራፍ ፡ ፴፰ ።

## ስለ ፡ ውዳሴ ፡ ከንቱ ።

ጥያቄ ።

፬፻፸፱ ፤ ውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የተጠላ ፡ ነገር ፡ መሆኑ ፡ ሰው ፡ በሥራው ፡ ቢመሰገን ፡ ምን ፡ ተንኮቶበት ፡ ነው ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚጠላው ።



ምላሽ ።

፬፻፹ ፤ ምስጋና ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚገባው ፡ ግንዘቡ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሰውም ፡ ለሱ ፡ የሚገባውን ፡ ያምላኩን ፡ ገንዘብ ፡ ለመውሰድ ፡ ፈልጎ ፡ ስለ ፡ ሥራው ፡ ምስጋናን ፡ ፈላጊ ፡ ሰው ፡ ያምላኩን ፡ ገንዘብ ፡ የሚሰርቅ ፡ ሌባ ፡ ባልሠራው ፡ የሚዋሽ ፡ ሐሰተኛ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሰውን ፡ የሚያታልል ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚበድል ፡ በመሆኑ ፡ የተጠላ ፡ ይሆናል ።

ጥያቄ ።

፬፻፹፩ ፤ ምስጋናንስ ፡ በመሻት ፡ በመስረቁ ፡ ወደ ፡ ሌባው ፡ ተመሰለ ፡ በሥራው ፡ ቢመሰገን ፡ ከሐሰተኛና ፡ ከታላይ ፡ ጋራ ፡ መመስሉ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ይሆን ።

ምላሽ ።

፬፻፹፪ ፤ ሰው ፡ የሚሠራብት ፡ ጕልበት ፡ የሚሰጠው ፡ ክብት ፡ ምንም ፡ ሳይኖረው ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጥሮ ፡ ያስቀመጠውን ፡ ገንዘብ ፡ እያንሣ ፡ ቢያካፍል ፡ እመ ያልፈጠረውን ፡ ያልሰጠውን ፡ የኔ ፡ ነውና ፡ አመስግኑኝ ፡ በማለቱ ፡ ከዋሾው ፡ ከዲያብሎስ ፡ ስለ ፡ ተመሳሰለ ፡ ሐሰተኛ ፡ የሚባል ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ነው ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ኃይለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእሱ ፡ እያደረ ፡ እሱን ፡ መሣሪያ ፡ አድርጎ ፡ ሲሠራበትም ፡ ሥራው ፡ በእሱ ፡ አካል ፡ ላይ ፡ መታየቱን ፡ ምክንያት ፡ አድርጎ ፡ ኢትክሉ ፡ ገቢረ ፡ ወኢ

ምንትኢ ፡ ያለውን ፡ መማሪያነቱን ፡ ረስቶ ፡ ይህን ፡ ሥራዬን ፡ እያያችሁ ፡ አመስግኑኝ ፡ በማለቱ ፡ የሌላውን ፡ ሥራ ፡ የሱ ፡ አስመስሎ ፡ ከሚያሳይ ፡ ከምትሀተኛው ፡ ሰይጣን ፡ የሚመስል ፡ አታላይ ፡ የሚባል ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ጥያቄ ።

፬፻፸፫ ፤ ውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ መሻት ፡ ቊጥሩ ፡ ከንኢሳን ፡ ኀጣውእ ፡ ጋራ ፡ ነው ፤ ሐሰት ፡ ግን ፡ ከዐበይት ፡ ኀጣውእ ፡ ጋራ ፡ ነው ፡ ቊጥሩ ፤ እንዴት ፡ ሐሰትና ፡ ውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ ይተካከላሉ ።

ምላሽ ።

፬፻፸፬ ፤ ሐሰትና ፡ ውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ መሻት ፡ የተዝመሩበት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የሠራቸው ፡ አንድ ፡ ዲያብሎስ ፡ ነው ፤ ሁለቱም ፡ የተካከሉ ፡ የኀጢአት ፡ መሠረቶች ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ አይተናነሱም ፤ እንዲያውም ፡ ቀድሞ ፡ የተሠራው ፡ ኀጢአት ፡ ውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ ነውና ፡ ይቀድማል ፤ (ይበልጣል) ።

ይህንም ፡ ልትረዳ ፡ ብትሻ ፡ ዲያብሎስ ፡ ኀጢአትን ፡ ሲዠምር ፡ በፊት ፡ ምስጋናን ፡ ሽቶ ፡ ምስጋናውን ፡ ለማግኘት ፡ ግን ፡ ሌላ ፡ መንገድ ፡ ቢያጣ እኔ ፡ ነኝና ፡ የፈጠርኋችሁ ፡ አመስግኑኝ ፡ ብሎ ፡ በውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ መሻቱ ፡ ላይ ፡ ሐሰትን ፡ ጨመራት ፡ እንጂ ፡ ከፈጣሪው ፡ ጋራ ፡ ለመጣላት ፡ ያደ



ረሰው ፡ መዠመሪያው ፡ ኀጢአት ፡ ውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ መሻት ፡ መሆኑን ፡ አስተውለው ።

ጥያቄ ።

፬፻፸፭ ፤ እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ ብዙው ፡ በጎው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ለሰው ፡ የሚሠራ ፡ ነው ፤ ለሰው ፡ ሲሠራም ፡ ሰው ፡ ማየቱ ፡ አይቀር ፤ ሰው ፡ ካየው ፡ ማመስገኑ ፡ አይቀር ፤ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ እንዳይመስገን ፡ ብሎ ፡ በጎ ፡ ሥራውን ፡ ይተውን ፤ እንደ፡ ምን ፡ ይሁን ።

ምላሽ ።

፬፻፸፮ ፤ በጎ ፡ ግብር ፡ የሚባሉ ፡ ጾም ፡ ጸሎት ፡ ስግደት ፡ ምጽዋት ፡ ናቸው ፤ እንደ ፡ ዐቢይ ፡ ጾም ፡ ያለ ፡ የሕማን ፡ ጾም ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፡ በግልጽ ፡ በምትጾምበት ፡ ጊዜ ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ የሚጨመረውን ፡ የትሩፋት ፡ እጁጁምን ፡ ስትጨምር ፡ ሰው ፡ እንዳያውቅብህ ፡ ሥጋዊ ፡ ጓደኛ ፡ ማበጀቱን ፡ ዙረቱን ፡ ትልውጡን ትተህ ፡ የቤትህን ፡ ምግብ ፡ ብቻ ፡ የምትወድ ፡ ሁነህ ፡ በግድም ፡ ከሰው ፡ ጋራ ፡ የሚያገናኝ ፡ ምግብ ፡ ሲያገኝህ ፡ ከሰው ፡ ፊት ፡ ከሚያሰክረው ፡ መጠጥ ፡ በቀር ፡ እንደ ፡ ሰውየው ፡ በቤትህ ፡ ስትሆን ፡ ብቻ ፡ በስውር ፡ እያደረግህ ፡ የትሩፋት ፡ ጾምህን ፡ ጹመው ፤ እንደ ፡ ቅዳሴ ፡ እንደ ፡ ምሕላ ፡ ያለው ፡ ከብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ እየተቀባበሉ ፡ በዕድል ፡ እየተከፋፈሉ ፡ የሚያደርሰውን ፡ ጸሎት ፡ በግልጽ ፡

ራስህ ፡ የምታደርሰውን ፡ በስውር ፡ እያደረግህ ፡ ስገድ ፡ እንደ ፡ ሕማማት ፡ እንደ ፡ ስቅለት ፡ ያለውን ፡ የጉባኤ ፡ ስግደት ፡ በግልጽ ፡ ለራስህ ፡ ወደ ፡ ፈጣሪህ ፡ የምትሰግደውን ፡ በስውር ፡ እያደረግህ ፡ ምጽዋትም ፡ እንደ ፡ ዝክር ፡ ማኅበር ፡ እንደ ፡ ድኻ ፡ ቤት ፡ መሥራት ፡ ያለውን ፡ ያለግልጥ ፡ ሥራ ፡ የማይፈጸመውን ፡ እስጣጥ ፡ በግልጽ ፡ ቢሰጥ ፡ እንደ ፡ ገንዘብ ፡ ስጦታ ፡ ያለውን ፡ ስምና ፡ መልክ ፡ ሰውር ፡ በጨለማ ፡ ወስዶ ፡ በሸማ ፡ ሸፍኖ ፡ በስውና ፡ በመልክት ፡ አዛውሮ ፡ ወይም ፡ በሌላው ፡ ሰው ፡ ዝክር ፡ ጊዜ ፡ ከሚሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ ጋራ ፡ ሰውነቱን ፡ ሰውሮ ፡ ገንዘቡን ፡ ቀላቅሎ ፡ በስውር ፡ ለመስጠት ፡ የሚመቸውን ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ በስውር ፡ እየሰጠ ፡ ለድኾች ፡ ያደረገው ፡ ሥራ ፡ የሰጠው ፡ ስጦታ ፡ እሱ ፡ ሳይሻው ፡ በግድ ፡ ተገልጾ ፡ የሚወራበት ፡ ሲሆን ፡ ገንዘቡ ፡ የብዙ ፡ ሰዎች ፡ ገንዘብ ፡ ነው ፡ እንሱ ፡ ውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ ፈርተው ፡ እኔ ፡ እንድሠራላቸውና ፡ እንድሰጥላቸው ፡ ስለ ፡ ለመኑኝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በኔ ፡ እጅ ፡ መሠራቱ ፡ የኔ ፡ ገንዘብ ፡ አይደለም ፡ እያልክ ፡ ባንተ ፡ እንጋገር ፡ ውዳሴ ፡ ከንቱው ፡ እንዲቀርልህና ፡ እንዲጐድልልህ ፡ ካደረግህ ፡ ሥራህም ፡ ይሰወርልሃል ፡ ውዳሴ ፡ ከንቱም ፡ ይጐድልልሃል ።

ውዳሴ ፡ ከንቱን ፡ ጨርሶ ፡ ለማስቀረት ፡ ከሁሉም ፡ የሚሻለው ፡ ከሰው ፡ መለየት ፡ ነው ።



መለየትን ፡ እስክታገኘው ፡ ግን ፡ በዚሁ ፡ ዐይነት ፡ እየሠራህ ፡ ብትቈይ ፡ ይሻላል ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ጾም ፡ ጸሎትን ፡ ሰጊድ ፡ ምጽዋትን ፡ በስውር ፡ ለመሥራት ፡ መድኀኒታችን ፡ ክርስቶስ ፡ በወንጌል ፡ ያዘዘንን ፡ ማስተዋል ፡ ነው ።

ጥያቄ ።

፩፻፺፯ ፡ ሰው ፡ እየሠራ ፡ እየሰገደ ፡ ወዙን ፡ እፍሶ ፡ እየጾመ ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋውን ፡ እየሰጠ ፡ ገንዘቡን ፡ ጨርሶ ፡ ውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ ነው ፡ የሠራኸው ፡ ተብሎ ፡ ሲሞት ፡ በቁሙም ፡ ተጉድቶ ፡ በነፍሱም ፡ እንዴት ፡ ጭራሽ ፡ የድካም ፡ ዋጋው ፡ ይቀራል ፡ ለነፍሱ ፡ ጥቂት ፡ ዋጋ ፡ እንኳ ፡ እያገኝምን ።

የሱስ ፡ አለማወቅ ፡ እንዴት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቸርነት ፡ ጨርሶ ፡ ያስቀርበታል ።

ምላሽ ።

፩፻፺፯ ፡ የፈጣሪያችን ፡ ጠባይ ፡ እንዱ ፡ ጌር ፡ ዘበሀላዌሁ ፡ ዘልማዱ ፡ ጌሩት ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራ ፡ ቸር ፡ መሐሪ ፡ ነውና ፡ እንኳን ፡ የማብዝነት ፡ ኀጢአት ፡ የበደልንም ፡ ኀጢአት ፡ በቸርነቱ ፡ ማመዛዘን ፡ ልማዱ ፡ ነውና ፡ ዘር ፡ ዘርቶ ፡ ተባዩን ፡ አልጠብቅ ፡ ብሎ ፡ ሰብሉን ፡ ያስጨረሰ ፡ ሰው ፡ ጥቂት ፡ ቃርሚያ ፡ እንደማያጣ ፡ ፍዳ ፡ ያቀልለት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ያልሻውን ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትንማ ፡ ለማግኘት ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ይሆንለታል ።

ቸር ፡ ሰጭውስ ፡ የለመነውን ፡ አይደለም ፡ የሚ ሰጥ ፡ እሱ ፡ መመስገን ፡ ቢሻ ፡ ያልፈለገውን ፡ መን ግሥት ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ይስጠው ፡ ትላለህ ።

ጥያቄ ።

፩፻፹፱ ፤ ይህ ፡ የውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ ጾር ፡ የሚነግብን ፡ ማናቸው ፡ ጠባያችን ፡ ሲያሸንፈን ፡ ነው ።

የምናመልጠውስ ፡ ምን ፡ ብንሠራ ፡ ነው ።

ምላሽ ።

፩፻፺ ፤ ውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ መሻት ፡ የሚወድ ፡ ሰው ፡ በብልጠት ፡ የተሸፈነ ፡ ጅል ፡ ይባላል ።

ጅል ፡ መባሉም ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ደክሞ ፡ ሠርቶ ፡ ይለ ብሰው ፡ ጨርቅ ፡ አጥቶ ፡ እየዞረ ፡ የሚለምነውን ፡ ድኻ ፡ እጅግ ፡ የሚያምር ፡ የሐር ፡ ልብስ ፡ ማለ ፊያ ፡ ነው ፡ ግዛኝ ፡ እያለ ፡ ቢያቈላምጠው ፡ ቢያ ሳየው ፡ ዋጋ ፡ ለመስጠት ፡ የማይቻል ፡ መሆኑን ፡ ተመራምሮ ፡ ባለማወቁ ፡ ጅል ፡ እንደሚያሰኘው ፤ ይህም ፡ ብዙው ፡ ድካም ፡ የሚሠራውን ፡ ምግባር ፡ ትሩፋትን ፡ ራሱ ፡ ከሚለምን ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ላይ ዋጋ ፡ ሽቶ ፡ ሥራውን ፡ ቢያሳይ ፡ ምንም ፡ መስ ጠት ፡ የማይችል ፡ እንደሱ ፡ ያለ፡ ድኻ ፡ መሆኑን ፡ ተመራምሮ ፡ ባለማወቁ፡ማስተዋሉን፡የብልጠት ፡ መጋረጃ ፡ የሸፈነበት ፡ ጅል ፡ ይሆናል ።



መጋረጃ ፡ እየሆነ ፡ የሚያጀለውም ፡ ብልጠት ፡ የሚባለው ፡ ጠባይ ፡ ነው ፡ ይኸውም ፡ የብልጠት ፡ ጠባይ ፡ የሚያስበው ፡ በጎ ፡ ሥራዬን ፡ ሰው ፡ ሲያይ ልኝ ፡ ያውቅልኛል ፡ አመስግና ፡ ላመስጋኝ ፡ ሲያ ወራልኝ፡ እመሰገናለሁ ፡ እንደኔ፡ ከማይሠራውም ፡ በልጬ ፡ እወደዳለሁ፡ በመወደዴም፡ እከብራለሁ ፡ በመከበሬም፡ ገንዘብ፡ አገኛለሁ፡ በማግኘቴም፡ ዐይ ኔን፡ በቤቴ፡ ውበት፡ ደስ፡ አሰኛዋለሁ፡ ጆሮዬንም፡ በምስጋና ፡ እሞላዋለሁ ፡ ሆዴንም ፡ በምግብ ፡ እጠ ግበዋለሁ ፡ እየመሰለው ፡ ዐይን ፡ በማየት ፡ አለማ ግኘቱን ፡ ጆሮም፡ በመስማት ፡ አለመሙላቱን ፡ ሆ ድም ፡ በመብላት ፡ አለመጥገቡን ፡ ዘወትር ፡ ሰው ነታችንን ፡ መንገድ ፡ አድርገው ፡ የሚመላለሱ ብን ፡ እንጂ ፡ የሚጠቅሙን ፡ አለመሆናቸውን ፡ በብልኅቱ ፡ ተመራምሮ ፡ በመጻሕፍት ፡ ተምሮ ፡ ስላላወቀ ፡ ለጅሉ ፡ ሥጋችን ፡ ይኸንን ፡ ከንቱ ፡ እያሳየ ፡ ውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ ፈላጊ ፡ ያደርገዋልና ፡ ስለዚህ ፡ ሰው ፡ ከዓለም ፡ የሚገኙት ፡ ሁሉ ፡ የሚረቡ ፡ መስለው ፡ መታየት ፡ እንጂ ፡ የማ ይረቡ ፡ መሆናቸውን ፡ የሚያሳውቁትን ፡ ከወን ጌል ፡ ዠምሮ ፡ የመነኮሳትና ፡ የመንፈሳዊ ፡ ፈላስ ፎችን ፡ መጻሕፍት ፡ እየመረጠ ፡ ሲያስተውል ፡ የምስጋናን ፡ ከንቱነት ፡ በውቆ ፡ ውዳሴ ፡ ከንቱን ፡ ከመሻት ፡ ሰውን ፡ የሚያሳርፈው ፡ ይህ ፡ ነው ። የውዳሴ ፡ ከንቱን ፡ ያጥፊነቱን ፡ ባለፈው ፡ ተመ ራምረህ ፡ ለመረዳት ፡ ብትሻ ፡ ግን ፡ ትልቁ ፡ ጸድ

ቅ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ የተነጋገረው ፡ ሙሴ ፡ ነፍስ ፡ በመግደሉ ፡ ታቦት ፡ በመስበሩ ፡ ሥራው ፡ ትልቅ ፡ ኀጢአት ፡ ሲሆን ፡ ያሠራሩ ፡ ምክንያት ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ ጥቅም ፡ ሳይሆን ፡ ስለ ፡ አምላኩ ፡ ማክበር ፡ ሲል ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ኀጢአት ፡ ሳይሆንበት ፡ ከጽድቅ ፡ ተቈጠረለት ።

ውሃ ፡ ሲያፈልቅ ፡ ግን ፡ እኔ ፡ አፈለቅሁላችሁ ፡ ብሎ ፡ በቃሉ ፡ እንኳ ፡ ደፍሮ ፡ ሳይናገር ፡ በልቡ ፡ ብቻ ፡ ውዳሴ ፡ ከንቱን ፡ ፈልጎ ፡ የኔም ፡ ሥራ ፡ አይደል ፡ የአምላክ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ባለመናገሩ ፡ ብቻ ፡ ኀጢአት ፡ ትንሽ ፡ መስሎ ፡ እየታየ ፡ ትልቅ ፡ ፍርድ ፡ ማስፈረዱ ፡ እግዚአብሔር ፡ የውዳሴ ፡ ከንቱን ፡ መሻት ፡ አጥብቆ ፡ የሚጠላው ፡ ንስሓ ፡ እንኳ ፡ ቢገባ ፡ ለኋላ ፡ እንደ ፡ ሙሴ ፡ ይምረዋል ፡ እንጂ ፡ የሻውን ፡ ውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ ግን ፡ ለጊዜውም ፡ ቢያገኘው ፡ ኋላ ፡ በሞቱ ፡ ጊዜ ፡ እንዲያጣው ፡ ማድድረጉን ፡ በሙሴ ፡ አሻሻትና ፡ ምድረ ፡ ርስት ፡ ማጣት ፡ አስተውለው ።

## ምዕራፍ ፡ ፴፮ ።

### ሰው ፡ የሚገባውን ፡ ንጽሕና ፡ እንዲያውቅ ፡ ንጽሕና ፡ ስለ ፡ ሚባለው ፡ ማስረጃ ።

### ጥያቄ ።

፩፻፺፩ ፡ ሰውን ፡ እግዚአብሔር ፡ ረድቶ ፡ ከዝሙት ፡



ከሴሰን ፡ ከምንዝር ፡ መጠበቅን ፡ የሠራው ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ ንጹሕ ፡ መባልን ፡ ያገኛልን ።

ወይስ ፡ ደግሞ ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ መጨመር ፡ ያስፈልጋል ።

### ምላሽ ።

፩፻፺፪ ፡ እነዚህን ፡ ሦስቱን ፡ ብቻ ፡ ግብረ ፡ ሩካቤ ፡ የተወ ፡ ሰው ፡ ስሙ ፡ ያልመነዘረ ፡ ያልሴሰነ ፡ ያልዘሞተ ፡ ጥንቁቅ ፡ ወይም ፡ ጥቡቅ ፡ ሰው ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ ንጹሕ ፡ ሰው ፡ አይባልም ።

ንጹሕ ፡ የሚባል ፡ ጌታ ፡ በኦሪትም ፡ በወንጌልም ፡ እንዳስታወቀን ፡ በፍጹም ፡ አሳቡ ፡ በፍጹም ፡ ኃይሉ ፡ ፈጣሪውን ፡ የሚወድ ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ አሳብ ፡ በመተው ፡ ልቡን ፡ ንጹሕ ፡ ያደረገ ፡ በዓለምና ፡ በሥጋዊ ፡ አሳቡ ፡ ልቡን ፡ ያላሳደፈ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ንጹሕ ፡ የሚባል ፡ ጋብቻን ፡ ብቻ ፡ ከንጎዙ ፡ መተውስ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ እንዳመለከተን ፡ መጋባት ፡ አሳብን ፡ ወዳገባት ፡ ወዳገባችው ፡ የሚጠልፍ ፡ አለመጋባት ፡ አሳብን ፡ ወደ ፡ ፈጣሪው ፡ የሚጠልፍ ፡ የንጽሕና ፡ መግሪያ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በዚህ ፡ መግሪያ ፡ የዓለምን ፡ ፍትወትና ፡ ድሎት ፡ የገንዘብን ፡ ፍሊጋና ፡ ጭንቀት ፡ ሁሉ ፡ እየከለከለበት ። ጌታ ፡ በወንጌል ፡ በሚያስጨንቅ ፡ አሳብ ፡ አትዋለሉ ፡ ምን ፡ እንለብሳለን ፡ ምን ፡ እንበላለን ፡ አትበሉ ፡ ያለውን ፡ እየሠራበት ።

ባሳቡ ፡ ሁሉ ፡ ፈጣሪውን ፡ ቢያስብበት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ንጹሕ ፡ የሚባለው ፡ ጋብቻን ፡ ብቻ ፡ ትቶ ፡ ባሳቡ ፡ የተድላ ፡ ሥጋን ፡ መገኛ ፡ ለንብረቱ ፡ ለ ክብሩ ፡ እያሰበ ፡ ከሚኖርስ ፡ በእርአያ ፡ ሥላሴ ፡ ለተፈጠሩት ፡ ለልጆቹ ፡ ለሚስቱ ፡ እያሰበ ፡ የሚ ኖር ፡ ሰው ፡ ይበልጠዋልና ፡ ጋብቻንና ፡ ሩካቤን ፡ ብቻ ፡ ቢተው ፡ ንጹሕ ፡ እያሰኘውም ።

ከቶውንም ፡ ሰነፍ ፡ ልግመኛ ፡ ብልጥ ፡ ንፉግ ፡ የ ሚያሰኘው ፡ ይመስላል ።

ከጋብቻው ፡ መተው ፡ ጋራ ፡ ሌላውን ፡ የተድላ ፡ ሥጋ ፡ ጸሎትን ፡ የገንዘብ ፡ አፍቅሮትን ፡ ሲተው ፡ ግን ፡ እውነተኛን ፡ ንጽሕና ፡ ያገኛል ።

ጥያቄ ።

፩፻፺፫ ፡ ማስረጃ ፡ (ጳውሎስ ፡ በሮሜ ፡ ምዕ ፡ ፲፫ ፡ ቍ ፡ ፲፫ ። በ፩ ፡ ቆ ፡ ምዕ ፡ ፮ ፡ ቍ ፡ ፱ ፡ ፲) ፡ ዝሙት ፡ ምን ዝር ፡ ሴሰን ፡ የሥስቱ ፡ ሥራቸው ፡ እንደ ፡ አይደለ ምን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ለየብቻ ፡ እየጠራ ፡ ነቀፋቸው ።

ምላሽ ።

፩፻፺፬ ፡ እመንዝራ ፡ ምንዝር ፡ ማለት ፡ ገሚሥ ፡ እ ጁንዎ ፡ ርእይ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሴሰን ፡ ሩካቢውን ፡ ማ ብዛት ፡ ካንድ ፡ ጊዜ ፡ እልፎ ፡ ማመላለሱ ፡ የሚ ሠራ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እሊህን ፡ ሦስቱን ፡ ሳይዝ ፡ የፈ ቷው ፡ ንጽሕናን ፡ ይዣለሁ ፡ ማለት ፡ የማይገባ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ነው ።



ጥያቄ ።

፩፻፺፭ ፡ ባማርኛችን ፡ የእኒህ ፡ የሦስቱ ፡ ኀጢአቶች ፡ የትርጓሜ ፡ ስማቸው ፡ ማነው ።

ምላሽ ።

፩፻፺፮ ፡ እመንዝራ ፡ ማለት ፡ ለሴት ፡ ምርመራ ፡ አካ ሉን ፡ መንዛሪ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ዘማዊ ፡ ማለት ፡ ለሴት ፡ ፍቅር ፡ ልቡን ፡ አገማሚ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ሴሰኛ ፡ ማለት ፡ የሴት ፡ ሩካቢ ፡ የማይጠግብ ፡ ሥ ሥታም ፡ ማለት ፡ ነው ።

ጥያቄ ።

፩፻፺፯ ፡ እመንዝራው ፡ ሴት ፡ መርማሪ ፡ የሚባልበ ት ፡ ምን ፡ ሲመረምር ፡ ነው ።

ምላሽ ።

፩፻፺፰ ፡ ባይኑ ፡ የመልኳን ፡ ቅርጽና ፡ ልብሷን ፡ እየ ገፋ ፡ የሚታየውን ፡ ያካሏን ፡ መጠን ፡ ሲመለከታ ት ፡ እሷም ፡ አይታ ፡ እንድትወደው ፡ ባለባበሱ ፡ ባካሄዱ ፡ እያንበበ ፡ ሲያጓጓት ፡ በእጁ ፡ ወይም ፡ በ ሌላ ፡ አካሉ ፡ ሲዳስሳት ፡ ወይም ፡ እሷ ፡ እንድት ዳስሰው ፡ ሲያደርጋት ፡ የሽቱውንም ፡ መዐዛ ፡ እሱ ም ፡ እየተቀባ ፡ ለሴቷ ፡ ሲያሸታት ፡ ወይ ፡ እ ፡

የተቀባችውን ፡ እየፈለገ ፡ ሲያሽታት ፡ ማመንዘር ፡ ሁኖ ፡ አመንዝራ ፡ የሚያሰኘው ፡ ይህ ፡ ነው ።

ጥያቄ ።

፩፻፶፱ ፡ ዘማዊ ፡ የሚያሰኘው ፡ ምን ፡ ሲሠራ ፡ ነው ።

ምላሽ ።

፩፻፷ ፡ አስቀድሞ ፡ እኽል ፡ ውሃ ፡ በማብዛት ፡ ሩካቤ ፡ ማድረግን ፡ ወዶ ፡ የልቡን ፡ አሳብ ፡ ለሴሰን ፡ ሲነሣበት ፡ ጹሞም ፡ እማትቦም ፡ ሳይከለክለው ፡ በልቡ ፡ ሴሰን ፡ ፈላጊ ፡ ሁኖ ፡ አሳቡን ፡ እያረከሰ ፡ ዘሩን ፡ እያፈሰሰ ፡ ሴት ፡ ሲያስብ ፡ ወይም ፡ መውደዱን ፡ ገልጦ ፡ በስዒም ፡ በከንፈሩ ፡ ባካሉ ፡ ሴት ፡ ሲነካ ፡ ዝሙት ፡ ሆኖ ፡ ዘማዊ ፡ የሚያሰኘው ፡ ይህ ፡ ነው ።

ጥያቄ ።

፩፻፷፩ ፡ ሴሰኛ ፡ የሚባለውስ ፡ ምን ፡ ሲሠራ ፡ ነው ።

ምላሽ ።

፩፻፷፪ ፡ ሴሰን ፡ ማለት ፡ የምንዝርና ፡ የዝሙት ፡ መጨረሻው ፡ ድምሩ ፡ ነው ። ድምራቸው ፡ የሚሆንበት ፡ ሰው ፡ ለመገናኘት ፡ ከሴት ፡ ጋራ ፡ ሲተኛ ፡ ርእይን ፡ አጼንዎውንም ፡ ገሲሱንም ፡ ስዒምንም ፡ ፈቃዱን ፡ እያየ ፡ ሲሠራው ፡ የነበረውን ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የሚሠራው ፡ ስለ ፡ ሆነ ።



ይህንኑም ፡ ከምትገባው ፡ ከሚስቱም ፡ ቢሆን ፡ አጽዋማትና ፡ በዓላትን ፡ ሳይጠብቅ ፡ ወይም ፡ በሚገባው ፡ ጊዜ ፡ ለፍትወቱ ፡ የሚያሻውን ፡ መገናኘት ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ። ረኃቡ ፡ ከተከላለት ፡ በኋላ ፡ ምግብ ፡ እያለዋወጠ ፡ እስከ ፡ ቍንጣን ፡ ድረስ ፡ እንደሚበላ ፡ ሰው ፡ ሁኖ ፡ ከልክ ፡ አልፎ ፡ ከድካም ፡ እስኪደርስ ፡ ድረስ ፡ የመገናኘቱን ፡ ሥራ ፡ ሲያበዛው ፡ ሴሰን ፡ ሁኖ ፡ ሴሰኛ ፡ የሚያሰኘው ፡ ይህ ፡ ነው ።

ይህንኑም ፡ ጌታ ፡ በወንጌል ፡ ዘርእየ ፡ ለብእሲት ፡ ብሎ ፡ አለማመንዘርን ፤ ወፈተዋ ፡ ብሎ ፡ አለመሴሰንን ። ወድአ ፡ ዘመወ ፡ ባቲ ፡ ብሎ ፡ አለመዘሞትን ፡ ባንድ ፡ ንባብ ፡ ሦስቱንም ፡ አስተምሮናል ።

በልማድ ፡ እንነጋገራችንም ፡ ዝሙት ፡ ከጀላ ፡ ጕጕት ፡ ይባላል ። ምንዝር ፡ ድሪያ ፡ ንኪኪ ፡ ይባላል ። ሴሰን ፡ መገናኘት ፡ መተኛት ፡ ይባላል ፡ ለ፫ቱ ፡ ስድስት ፡ ስም ፡ አላቸው ።

ስለዚህ ፡ ሰው ፡ ባይኔ ፡ አየሁ ፡ እንጂ ፡ በከንፈሬ ፡ አልተገናኘሁም ፡ ሴሰኛ ፡ አይደለሁም ፡ አይበል ።

በሌላውም ፡ በአፍአው ፡ አካሌ ፡ ተንካካሁ ፡ እንጂ ፡ በእጄ ፡ አልጨበጥኩምና ፡ አመንዝራ ፡ አይደለሁም ፡ አይበል ።

አንድ ፡ አልጋ ፡ በመተኛት ፡ ተነካክሁ ፡ እንጂ ፡ አልተገናኘሁምና ፡ ሴሰኛ ፡ አይደለሁም ፡ አይበል፤ የሰው ፡ ከራስ ፡ ጸጕሩ ፡ እስከ ፡ እግር ፡ ጥፍሩ ፡ (እየዘሞተና) ፡ እየከጀለ ፡ በማናቸውም ፡ አካሉ ፡ ከሴት ፡ አካል ፡ ቢነካካም ፡ ንጽሕናው ፡ አይፈርስም ፡ በአባለ ፡ ዘሩ ፡ ብቻ ፡ መንካት ፡ ነው ፡ ንጽሕናውን፡ የሚያፈርስበት ፡ ማለት ፡ አይገባም ።

ነፍስ ፡ የገደለ ፡ ሰው ፡ የገደለው ፡ እጁ ፡ ይቈረጥ ፡ እንጂ ፡ እንገቱ ፡ አይቈረጥ ፡ ብሎ ፡ ካንድ ፡ ሰው ፡ አካል ፡ ላይ ፡ ኀጢአቱን ፡ ለይቶ ፡ ላንድ ፡ ብልት ፡ መስጠት ፡ እንደማይገባ ፡ በማናቸውም ፡ አካሉ ፡ ማንኛውንም ፡ አካሏን ፡ በክጀላ ፡ ከነካው ፡ ከመገናኘት ፡ እኩል ፡ ሁኖ ፡ ንጽሕናውን ፡ ያፈርስበታልና ፤ ለባለሕግም ፡ ቢሆን ፡ ለመገናኘት ፡ በማይገባው ፡ ጊዜ ፡ መገናኘቱን ፡ በመላ ፡ አካሉ ፡ ይተው ።

መናኒ ፡ ወይም ፡ ንጹሕ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ መላ ፡ አካሉንና ፡ ባስተያየቱ ፡ የሴትን ፡ አካል ፡ በመመንኘት ፡ እንዳይነካ ፡ ሲጠነቀቅ ፡ ነው ፡ ንጹሕ ፡ ሥጋን ፡ የሚያገኘው ።

ጥያቄ ።

፩፻፫ ፤ ፍትወትን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኙት ፡ ሁሉ ፡ ኀጢአት ፡ ከሆኑ ፡ ሰው ፡ መጋባት ፡ የሚፈልግበት ፡ ምክንያት ፡ ለምንድን ፡ ጥቅም ፡ ነው ።



ምላሽ ።

፩፻፬ ፤ መጋባት ፡ የሚፈለግበት ፡ ስለ ፡ ፪ ፡ ነገር ፡ ነው ። ፩ኛ ፤ ልጅ ፡ ለመውለድ ። ፪ኛ ፤ ባንዲ ፡ ለመቆምና ፡ ወደ ፡ ሌላይቱ ፡ ሴት ፡ ከሚያስከድ ፡ ኀጢአት ፡ ለመጠበቅ ። ፫ኛ ፤ ሚስቱን ፡ ልጆቹን ፡ በመርዳቱ ፡ ለመጠቀም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በቀሊል ፡ ልብ ፡ ወይም ፡ በድፍረት ፡ የሥጋን ፡ ፈቃድ ፡ ለመሻትና ፡ ለመጃገብ ፡ ብቻ ፡ እንደሚሠሩት ፡ እንደ ፡ እንስሳ ፡ ለመሆን ፡ አይደለምና ፡ የተጋባ ፡ ሰው ፡ ሳሠራሩ ፡ መመሳሰል ፡ ከእንስሳ ፡ ተቈጣሪ ፡ እንዳይሆን ፡ ምንም ፡ የመገናኘቱን ፡ ግዴታ ፡ ቢያመሳስለው ፡ የሰው ፡ ሥጋ ፡ በውስጡ ፡ የንጹሕ ፡ የእግዚአብሔር ፡ እስትንፋስ ፡ ያለበት ፡ ነውና ፡ የሩካቤው ፡ አሠራር ፡ ከእንስሳ ፡ ጋራ ፡ እንዳይመሳሰልበት ፡ መጠንቀቅ ፡ ይገባዋልና ። ከሚስቱም ፡ በጣም ፡ ማብዛትንና ፡ መሴሰኘት ፡ እንደ ፡ ተው ፡ ነው ፡ (ስለ አባት ፡ እናት ፡ ፵ ፡


ፍኖተ፡አእምሮ፡
የዕውቀት ፡ ጎዳና ።
ከልዑል፡ራስ፡ካሳ፡ኃይሉ ።